# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤቶች

## የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

## ዓመታዊ ሪፖርት

ጥራዝ 1

ሚያዝያ/ 2004

አዲስ አበባ

**የልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤቶች**

**የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት**

**ዓመታዊ ሪፖርት**

**ማውጫ**


**ገጽ**

I. መግቢያ..................................................................1

II ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ......................4

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ ኦዲት................................................4

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት........................................................4

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች....4

2. ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ...........................................................5

2.1 በየመ/ቤቶቹ የተገኘ ተሰብሳቢ ሂሣብ........................5

2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች.............7

3. የገቢ ሂሣብ.........................................................................9

3.1 ገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይበሰበብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ..............................9

3.2 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ.....................................11

3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ.12

3.4 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ...................................12

3.5 በበጀት ዓመቱ ያልተሰበሰበ የወጪ መጋራት ሂሳብ.........................13

3.6 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ስለተገኘው ሂሳብ..................14

3.7 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢአሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች...........................................................14

4. የወጪ ሂሣብ.........................................................................20

4.1 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ.........................................20

4.2 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ......................21

4.3 ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች............21

4.4 የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዢዎች.................22

4.5 በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸሙ ክፍያዎች...........................23

4.6 የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ....................24

4.7 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት.......................................24

4.8 አላግባብ በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ..............................25

4.9 በብልጫ የተከፈለ ወጪ........................................................26

4.10 የወጪ የሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች..............26

4.11 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ..................................27

4.12 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ..................................28

5. የተከፋይ ሂሣብ.........................................................................28

5.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ..........................................28

5.2 በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ላይ የታዩ ድክመቶች............................29

6. የበጀት አጠቃቀም......................................................................32

6.1 ከበጀት በላይ የወጣ.............................................................32

6.2 ያልተሠራበት በጀት..............................................................33

6.3 ስለበጀት ሌሎች ጉዳዮች.......................................................33

7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ........................................................35

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳዳር ድክመቶች...............................35

7.2 በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች....36

7.3 የተሽከርካሪ አያያዝ..........................................................40

7.4 የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም በተመለከተ................................41

8. ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ............41

9. ልዩ ልዩ.......................................................................45

9.1 የቅጥር ደንብን ተከትሎ ያልተፈጸመ የሠራተኞች ቅጥር..............45

9.2 የቅጥር መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመ የውጭ አገር ዜጐች ቅጥር...46

9.3 የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የክፍያ መመሪያ መሠረት ያልተፈጸሙ....48

9.4 በተመሳሳይ ፊርማዎች ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ............................48

III የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር ኦዲት ሪፖርት .................................49

1. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንé é é é é é é é é é é é é é ..49

2. የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . é é é é é é 89

3. የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች...........................................................131

4. የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት መ/ቤቶች. . . . . . . . . . . . . . . . é é é é é ..151

5. የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . é é é é é .185

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤቶች የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዓመታዊ ሪፖርት

## I. <u>መግቢያ</u>

**የዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 101 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡**

- *የፌዴራሉን መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣*
- *የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጡት ሕጎች፣ በአስፈጻሚው አካል በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣*
- *በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የፋይናንስ፤ የክዋኔ የአካባቢ ጥበቃ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣*
- *አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣*
- *በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣*
- *የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ /ስታንዳርድ/ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣*

ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥትና የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋልአስፈላጊውንም ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣
- ለግል ኦዲተሮችና የሂሳብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ የሂሳብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለማሰማራት የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች፤ ኦዲት የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን፣ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍን በተመለከተ በተለያዩ ክልሎች ሥር ባሉ የወረዳና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶችን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም በተከታታይ ኦዲት በማድረግ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ነው::

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተከናወነው የኦዲት ሥራ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉ ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ለእያንዳንዱ ኦዲት

ተደራጊ የፌዴራል መ/ቤትና ተቆጣጣሪ መ/ቤት እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለሥራ አመራር ሪፖርት መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው::

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ ተከታታይ ኦዲት ደግሞ ኦዲቱ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የሴክተር ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ጋር የመውጫ ውይይት የተደረገበትና የኦዲት ሪፖርቱም በየሩብ ዓመቱ ተጠቃሎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር እየተላከ ውይይት የተደረገበትና አጠቃላይ ሂሳቡም ላይ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡

ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል እንዲሁም አንዳንዴም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ ሂሳብ ኦዲት ደረጃዎች እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው::

ከመንግሥት በሚመደብላቸው በጀት በሚተዳደሩ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በተደረገው የፋይናንስ ኦዲት በኦዲት የእንጌጅሜነት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በ4 ዘርፍ በተደረጁ መ/ቤቶች፡- የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች፣ የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች፣ የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች እና የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች፣ እንዲሁምበክልል መንግስታት የተከናወነው የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲት በተሻሻለው የኢትዮጵያ መንግሥትና ዓለም ባንክ የኦዲት ሥራ ስምምነት መሠረት በህጋዊነት (Fiduciary Responsibility) ላይ ኦዲቱ በማትኮር የፕሮጀክቱ ሂሣብ ዓመታዊ ኦዲት አካል እንዲሆን ተደርጓል፡፡

መ/ቤታችን በሚከተለው የኦዲት ጊዜ አቆጣጠር ከጥር 1/2003 እስከ ታህሣሥ 30/2004 ዓ.ም የ131 በፌዴራል መ/ቤቶች የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ መደበኛ ኦዲት እና በ262 የወረዳና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶች የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲትና የተጠቃለለው የPBS ሂሣብ ኦዲት/ዝርዝሩ በአጠቃላይ ዘገባ ጥራዝ 2 ቀርቧል/ አከናውኗል፡፡ በመደበኛ ኦዲት የተከናወኑትን ኦዲቶች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች ሪፖርት የላከ ሲሆን፣ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተ ደግሞ በየሩብ ዓመቱ እና የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተልኳል::

## II ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት በርካታ የጥሬ የገንዘብና የአሠራር ጉድለቶች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ጉድለቶች በዚሁ ጥራዝ ከገጽ 44 ጀምሮ በየኦዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በዝርዝር እና በክልላዊ መንግሥት የወረዳና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶች የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ተከታታይ ኦዲት ደግሞ በተጠቃለለ መልኩ የቀረቡ ሲሆን፣ የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርበዋል::

### 1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ ኦዲት

#### 1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት አያያዝና አጠባበቅ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የውስጥ ኦዲተሮች ባደረጉት ምርመራ በ4 መ/ቤቶች ብር 1,066,524.68 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ - 6 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

#### 1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፣ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ29 መ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ-8 ተመልክቷል/

ከሚታዩት ዋናዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያየዝ ጉድለቶች፣

- የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉ /የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አድርገናል ቢሉም ማስረጃ ያላቀረቡ/ መሆኑ፣

- የዋና ገንዘብ ያዥ የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠርያ መዝገብ አለማዘጋጀት፣
- በባንክ ሂሣብ ገቢ ለሆኑ ሂሣቦች የገቢ ደረሰኝ አለማዘጋጀትና አለመመዝገብ፣
- የተሰበሰበውን ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ አለማድረግ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ መሆኑ፣
- ለልዩ ልዩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ያለማስፈቀድ እና ከተፈቀደውም በላይ በሳጥን ማስቀመጥ፣
- በግዥ ሠራተኞች እጅ በርካታ የጥሬ ገንዘብ እንዲያዝ መደረጉ፣
- በውጭ ምንዛሪ ባንክ ያለ ገንዘብ /4102/ ተብሎ ሪፖርት የተደረገውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የባንክ ሂሣብ መግለጫ ያልቀረበለት መገኘቱ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል ልዩነት በ9 መ/ቤቶች ብር 1,555,007.88 በማነስ የሚታይና /ዝርዝሩ በአባሪ-7 ተመልክቷል/ በሀገር መከላከያ ሚ/ር የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 291,928.19 ለዓመታት ያልተተካ መሆኑተረጋግጧል፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፣ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ፣ እንዲሁም በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር ከቆጠራው ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባና በማነስ የታየው ልዩነት/ጉድለትም ተጣርቶ እንዲተካ አሳስበናል፡፡

2. ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ

## 2.1 <u>በየመ/ቤቶቹ የተገኘ ተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ**59**

መ/ቤቶች ብር 1,275,970,326.90 የሰነድ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ-9 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር 71,059,514.64 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 770,261,856.19 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 207,999,800.32 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 226,649,155.75 |
| ድምር | 1,275,970,326.90 |

ውዝፍ ሠነድ /ተሰብሳቢ/ የተገኘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የትምህርት ሚኒስቴር ብር 723.77 ሚሊዮን፣ የመከላከያ ሚ/ር ብር 133.78 ሚሊዮን፣ ግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ብር 115.02 ሚሊዮን፣ጤና ጥበቃ ሚ/ር ብር 48.05፣ የግብርና ሚ/ር 38.55 ሚሊዮን፣ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 35.16 ሚሊዮን፣ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ብር 31.79 ሚሊዮን፣ ውጭ መልዕክተኞች ብር 29.97 ሚሊዮን እና የፌዴራል ፖሊስ ብር 23.99 ሚሊዮን ይገኙበታል፡፡

ስለተሰብሳቢው ሂሳብ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ከሰጡት ምላሽ፣ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ለሥራ አመራር ሪፖርት በሰጠው መልስ ብር 18,500,490.05 በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ማለት በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ብር 11,593,098.46 እና በሌሎች 8 ክፍሎች ብር 6,907,391.59 የወደመ፣ የጠፋና የተሰረቀ መሆኑን እና በፋይናንስ ሕግ መሠረት ከመዝገብ ለማስረዣ ኮሚቴ መቋቋሙን፣ ለብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽንና ለብራና ማተሚያ ቤት ከተከፋይ የሠራዊት ደመወዝ በብድር ከተሰጠው ብር 55,000,000.00 ብር 4,000,000.00 ከብራና ማተሚያ ቤት የሚፈለግ የሚቀር መሆኑንና ሌላው ብር 51,000,000.00 በዚህ ዓመት ተመላሽ መደረጉን፣ ብር 17,830,739.30 ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ በሰነድ ወጪ መደረጉን ጠቅሶ እየተወራረደ መሆኑን፣

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በላከው መልስ እስከ 2004 በጀት ዓመት አጋማሽ በርካታ ሂሣብ እንዲወራረድ መደረጉን፣ ትምህርት ሚኒስቴር

ለየዩኒቨርስቲዎች ግንባታ የተሰጠውን በርካታ ገንዘብ እንዲወራረድ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑንና ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ሰነዱን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

## 2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

- በትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 11,004,054.87 ማስረጃ የሌለው የተሰብሳቢ ሂሳብ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሔራዊ ጽ/ቤት ብር 2,482,145.92 ለቃሊቲ ማእከል ግንባታ ቅድሚያ ክፍያ ከተከፈለው ሂሳብ ማስረጃው ያልቀረበ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- የኢትዮጵያ የሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የታየው የተሰብሳቢ ሂሳብ በትክክል በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ መያዙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ብር 84,878.90 በሂሳብ ሪፖርት ያልተገለጸ መሆኑ ታውቋል፡፡

- በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በተቀጽላ የሂሳብ ሌጀሮች በድምሩ ብር 420,850.71 በክሬዲት አቅጣጫ ተመዝግቦ ተገኝቷል::

- በአንዳንድ መ/ቤቶች/ድርጅቶችና ግለሰቦች ስም ያሉ ክፍያዎች በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች የሂሳብ መደብ የተያዘ ቢሆንም ሂሳቡ ከማን እንደሚፈለግና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ የማይታወቅ መሆኑ፤

- ለእቃ ግዥ ሰራተኞችና ሌሎች ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በተደጋጋሚ የሚሰጥ በመሆኑና በእያንዳንዱ የእቃ ግዥ ሰራተኛ ተቀጽላ ሌጀር

ባለመኖሩ ማስረጃ ቀርቦለት ያልተወራረደና ከሰራተኛው የሚፈለግ ቀሪ እዳ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥና ለይቶ ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ፤

- ለበርካታ ዓመታት ሳይወራረዱ የቆዩና ያለበቂ ማስረጃ በተሰበሳብ ሂሳቦች ስለሚያዙ ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ መኖሩ፤
- የወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 1,953,500.00 በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድመ ክፍያዎች ብር 21,205.30 በልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ እና ብር 20,849.64 በአቅራቢዎች ቅድመ ክፍያ መያዝ ሲገባው፣ በጥቅሉ ብር 1,995,554.94 በግዥ ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መደብ ተይዞ መገኘቱ፤ በተጨማሪም በዚሁ ዩኒቨርስቲ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 66,145.03 በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች የሂሳብ መደብ የተያዘ ቢሆንም ሂሳቡ ከማን እንደሚፈለግና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ የማይታወቅመሆኑ፤
- በጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 448,095.38 ተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ የተያዘ ቢሆንም ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ የሠነድ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤
- በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 74,313.27 በተቋሙ ሠራተኞች ላይ የሚፈለግ ዕዳ እንደሆነ ቢገለጽም በእያንዳንዱ ባለዕዳ ስም ተቀጽላ የሂሳብ ሌጀር በመክፈት  የሚፈለግበት ሂሣብ ፤የተከፈለው ገንዘብና ቀሪ ዕዳ እየተቀናነሰ የማይመዘገብ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከሁለት የተቋሙ ሠራተኞች ደመወዝ ላይ በየወሩ 1/3 እየተቀነሰ ለጉራፈርዳ ወረዳ የገንዘብና ኢ/ል/ጽ/ቤት ገቢ እንዲደረግ የተወሰነው ገንዘብ ብር 37,814.66 አላግባብ በተቋሙ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱ፣
- በባህርዳር ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለሥራ አመራሩ በተዘጋጀው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት መሠረት ብር 20,105,034.19 ተሰብሳቢ ሂሳብመኖሩ የተገለጸ ቢሆንም በዝርዝር ለማየት ተሞክሮ ትክክለኛ ገጽታውን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፣

- በትምህርት ሚኒስቴር ከተመለከተው ተሰብሣቢ ሂሣብ ውስጥ የካፒታል ሂሳብ (የሂሳብ መደብ 4274) ብር 37,883,977.02 ከሰኔ 1994 ዓ.ም ጀምሮ ያለና በ1999 በጀት ዓመት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በቀረበው ሪፖርት ላይ የተመለከተ/ያልተወራረደ/ ሲሆን፤ የመደበኛ ሂሳብ (የሂሳብ መደብ 4201፣ 4202 እና 4253) ብር 5,478,706.92 ከ1995 ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ የተሰብሳቢ ሂሣብ ነው፣
- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሂሣብ መደብ 4203 በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት የተደረገው ሂሣብ በተቀጽላ ሌጀሮች ድምር ከታየው በብር 1,289,269.38 አንሶ መገኘቱንና ይህ ባለፉት ኦዲቶችም የታየ ልዩነት ያልተስተካከለ መሆኑ፤
- በኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ብር 141,686.45 የተሰብሳቢ ሂሣብ ከማን እንደሚፈለግ እና የየትኛው በጀት ዓመት ሂሣብ እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ለቅድሚያ ክፍያ የተሰጡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ፤ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ተጣርቶ አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግለቸው፤ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

3.1 ገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ <u>አዋጆች መሠረት ሳይበሰበብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ16 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 952,938,239.61 በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 11 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---|
| የፋይናንስናኮሙኒኬሽንመ/ቤቶች | ብር 831,660,870.20 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 395,518.64 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 76,462.08 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 120,805,388.69 |
| ድምር | 952,938,239.61 |

በአዋጁ በመሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፣ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ብር 638.14 ሚሊዮን፣ ምስራቅ አዲስ አበባ ብር 132.56 ሚሊዮን፣ ውሃና ኢናርጂ ሚ/ር ብር 120.63 ሚሊዮንና ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 10.58 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Coustom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሳበሳበ የንግድ ትርፍ ግብር እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ መቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ከዚህ ሂሳብ ውስጥ በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 125,182.90 እና በአዳማ ቅ/ጽ/ቤትብር 35,571.28 በድምሩ ብር 160,754.18 መሰብሰቡን የገለጹ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ እየታዩ ያሉ እንደሆነና ሌሎችም ገቢውን ለመሰብሰብ እንቅስቃሴ እንደጀመሩ ለስራ አመራር ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች ወሳኝ ስለሆነ፣ ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.2 <u>በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ</u>

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ ሰባት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፣ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 272,148,506.59 እና በሌሎች 4 መ/ቤቶች ብር 14,623,028.28 በድምሩ ብር 286,771,534.84 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-10 ተመልክቷል/

ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 120.44 ሚሊዮን፣ በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 94.59 ሚሊዮን፣ ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 26.12 ሚሊዮንና በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ብር 10.53 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ያልተሰበሰበውም ገቢ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋናው መ/ቤት የተወረሱና የተተው ዕቃዎችን ለሸቀጦችና ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ለመሸጥ በገባውውል መሰረት ያለጨረታ በዱቤ ከተሸጠው ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ውዝፍ ያልተሰበሰበ ገቢ ሲሆን፣ ሌሎቹም ከግብር ከፋዮች ሊሰበሰብ ከሚገበው የንግድ ግብር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስእና ከዚሁ ጋር የተያያዘ ወለድና ቅጣት እንዲሁም፣ የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ከደንበኞቹ ለ16 ዓመታት ያልሰበሰበው ውዝፍ ገቢ ይገኝበታል፡፡

ከዚህ ካልተሰበሰበው ገቢ ውስጥ የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 50,929.88 እንደሰበሰና ሌሎችም እንዲከፍሉ ደብዳቤ መጻፉን፣የአዲስ አበባ ንግድ ቃዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 238,651.95 መሰብሰቡን በድምሩ ብር 289,581.86 መሰብሰቡን፣ እንዲሁም የጅንአድ በተመለከተ በውሉ መሰረት በ45 ቀናት ውስጥ ገቢ እንዲያደርግ ክትትል እየተደረገ መሆኑናሌሎችም ውዝፍ ገቢውን

ለመሰበሰብ የተለያየ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ለስራ አመራር ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢ እርምጃ በመውሰድ የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለየመ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

### 3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉሶስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች ሶስት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 225,587,797.44 የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ ከማን እንደተሰበሰበ ሳይገለጽ በኮድ በመሰብሰቡ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ- 12 ተመልክቷል፡፡/

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙናተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 3.4 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ18መ/ቤቶች የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር 138,594,989.48 ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ-13 ተመልክቷል፡፡/ ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር 26,795,306.73 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 178,791.17 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 110,123,572.53 |
| ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 1,497,318.75 |
| ድምር | 138,594,989.48 |

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱት አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፣ በተጨማሪም በ9 መ/ቤቶች /ዝርዝራቸው በአባሪ-15 ተመልክቷል/ በአዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10/2 መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባሳተመው ወይም እንዲታተም በፈቀደው ደረሰኝ ገቢ መሰበሰብ ሲገባቸው የሚኒስቴሩን ፈቃድ ሳያገኙ የጥሬ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በስማቸው በማሳተም ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ገንዘብ የሚሰበስቡና ሪፖርትም የማያደርጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስበቸውን ገቢ ሕገዊ በሆነ መንገድ በታተሙ ደረሰኞች ብቻ በመጠቀም እንዲሰበስቡና በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 በበጀት ዓመቱ ያልተሰበሰበ የወጪ መጋራት ሂሳብ

የወጪ መጋራት አሰባሰብ መመሪያ ቁጥር 26/2001 ክፍል 5.2/ሀ መሰረት የተቀጣሪዎች የእፎይታ ጊዜ እንደተጠናቀቀ ከጥቅል የወር ደመወዝ ላይ 10% በአሰሪው እየተቀነሰ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈሰስ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የእፎይታ ጊዜያቸውን ከጨረሱ 31 ሠራተኞች ሊሰበሰብ የሚገባው ብር 37,879.20 እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 78,219.55 ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

በተጨማሪም 3 መ/ቤቶች- የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም፣ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ሂሳብ የማይሰበስቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

መሰብሰብ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ሊዘገይ ከመቻሉም በላይ ሳይሰበሰብ ሊቀር የሚችልበትም አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡

በመሆኑም የወጪ መጋራት ሂሳብ በመመሪያው በተቀመጠው መሰረት እንዲሰበሰብ ተገቢው ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና ያልተሰበሰበውም ሂሳብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.6. <u>የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ስለተገኘው ሂሳብ</u>

የተመዘገበው ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:-

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋናው መ/ቤትከ10 ቅ/ጽ/ቤቶች የተላከው የሂሳብ ሪፖርት በትክክል ባለመመዝገቡ በተለያዩ በሂሳብ መደብ በድምሩ ብር 70,321,371.23 በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-14 ተመልክቷል/

የገቢ ሂሳብ በተገቢው የሂሳብ መደብ ካልተመዘገበ የሂሣብ ሪፖርት እና የአፈጻጸም ሪፖርት ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አወቃቀር መሰረት ትክክለኛውን የሂሳብ መደብ ተከትሎ ሊመዘገብ እና የሂሳብ መግለጫውም ትክክለኛውን የገቢ አፈጻጸም በገቢው አይነቱ እንዲያሳይ ለማድረግ የግብር ከፋይ ምዝገባ ሲከናወን ግብር ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን የታክስ አይነት በመለየት ትክክለኛ ምዝገባ ሊከናወን የሚገባ ሲሆን፤ ከቅ/ጽ/ቤት የሚቀርበው ሪፖርት ከሂሳብ መግለጫ ጋር እየተገናዘበ አስቀድሞ የተመዘገበው የግብር መረጃ ሊስተካከል ይገባል፡፡

## 3.7 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢአሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

## የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

### 3.7.1 የኤክሳይዝ ታክስ በወቅቱ ስለማሣወቃቸው ማስረጃ ያልቀረበለት

በኤክሳይዝ ታክስ በአዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 2ሀ (2) መሰረት ታክስ በወቅቱ እና በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤

- በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ሶስት ግብር ከፋዮች ሂሳባቸውን በአዋጁ መሰረት ስለማሳወቃቸው የቀረበ ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም በላይ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ አማካኝነት አስፈላጊው እርምጃ አለመወሰዱ እንዲሁም በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤትስድስት የኤክሣይስ ግብር ከፋዮች በየወሩ ማሣወቃቸው ለማረጋገጥ ሲሞከር ሪፖርት ስለማድረጋቸው በፋይሎቻቸው ውስጥ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤
- በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት 21 ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በአዋጁ መሰረት ያላሳወቁ ቢሆንም፣ በነዚህ ግብር ከፋዮች ላይ በህጉ መሰረት እርምጃ ስለመወሰዱ የሚገልጽ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት አለመቅረቡ፤
- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ዘጠኝ ግብር ከፋዮች የ2002 የግብር ዘመን ገቢያቸውን በወቅቱ ያላሳወቁ መሆኑ፤
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በዲክላራሲዮን ቁጥር C-868/11 ለተሰበሰበው ብር 106,535.83 የተሟላ የዋጋ ሰነድ ሳይቀርብ ቀረጥና ታክሱ መሰብሰቡን፣ እንዲሁም በዲክላራሲዮን ቁጥር C-4977/10 ለተሰበሰበው ብር 1,626,359.74 በእቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ (packing list) ላይ ዝርዝር የእቃው አይነት የተገለጸ ቢሆንም፣ በዋጋ ሰነዱ ላይ ግን የእያንዳንዱ እቃ ዋጋ ያልተገለጸ በመሆኑ ምክንያት እያንዳንዱ እቃ በትክክለኛው የታሪፍ ምጣኔ መሰረት ቀረጡ ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር c-121/11 ለገባው እቃ በዶክመንቱ መሰረት የመኪናው ዓይነት Isuzu NPR እንደሆነ የመንገድ ትራንስፖርት ፈቃድ በሰጠበት

ደብዳቤ፣ የባንክ ፈቃድ፣ ትራክ ዌይ ቢል፣ ፓኪንግ ሊስት፣ ኮመርሽያል ኢንቮይስ፣ ዲክላሬሽን ኦፍ ፋክት እና የቶጎ ውጫሌ የፍተሻ ደብዳቤ ላይ የተገለጸ ሲሆን፤ በድሬዳዋ መቅረጫ ጣቢያ በተደረገ ፍተሻ መኪናው Isuzu NPR Chasis መሆኑን በመግለጽ እና የልዩነቱ መንስኤ እንዲጣራ ሳይደረግ ቀረጥና ታክስ በፍተሻው ውጤት መሰረት መሰላቱ፤

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የዋጋ ሰነዱ በአንዳንድ በዲክላራሲዮኖች ላይ የእቃዎቹን ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን ገላጭ ባልሆነበትና በፍተሻ እና በፍሬ ነገር መግለጫ (declaration of fact) ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ባልቀረበበት ሁኔታ አነስተኛ ዋጋን በመውሰድ ቀረጥና ታክስ የተሰበሰበ መሆኑ፤

<u>በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት</u>

- ✓ ለአንዳንድ ሰነዶች የፍሬ ነገር መግለጫ የማይሞላ ሲሆን ለአንዳንዶቹ የፍሬ ነገር መግለጫ ቢያያዝም እያንዳንዱ እቃ የተመደበበትን ታሪፍ ቁጥር የማይጠቅስ መሆኑ፣
- ✓ Brake Pads፣ አስቤስቶስ ያለው ከሆነ በታሪፍ ቁጥር 68132000 ላይ ተመድቦ የጉምሩክ ቀረጥ ምጣኔ (import tax rate በ35%) ተሰርቶ ኤክሳይስ ታክስም 20% መሰብሰብ የነበረበት ሲሆን፣ በአንዳንድ ዲክላራሲዮን ላይ የዋጋ ሰነዶቹ እቃው አስቤስቶስ የሌለው ለመሆኑ ገላጭ ሳይሆን ወይም በፍተሻ እና በፍሬ ነገር መግለጫ (declaration of fact) ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ሳይቀርብበት በታሪፍ ቁጥር 68138100 (አስቤስቶስ እንደሌለው በመቁጠር) ላይ በመመደብ በአነስተኛ የጉምሩክ ቀረጥ ምጣኔ (import tax rate 20%) ብቻ ቀረጡ የተሰበሰበ ሲሆን ኤክሳይስ ታክስም ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::
- ✓ በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በዲክላራሲዮን ቁጥር c-4923/2011 ዲክሌር ከተደረጉት

እቃዎች ውስጥ Bush (spare part) እቃው የላስቲክ እቃ (Rubber) ከሆነ የጉምሩክ ቀረጥ (import tax rate) 30% ሲሆን Rubber ካልሆነ ግን የጉምሩክ ቀረጥ (import tax rate ) 20% ይሆናል:: ነገር ግን እቃው የላስቲክ እቃ (Rubber) መሆን አለመሆኑ በዋጋ ሰነዱ፣ በፍተሻ ወይንም በፍሬ ነገር መግለጫ ላይ ሳይገለጽ አነስተኛ የታሪፍ ምጣኔውን በመውሰድ ቀረጡ የተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::

- ✓ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በአራት በዲክላራሲዮኖች ላይ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን በማስረጃ ላይ የተመለከተው ሞዴል እና ቀረጥ ለማስከፈል የተጠቀሙበት ሞዴል የሚለያይ እና የመጫን አቅማቸውም ሳይታወቅ መስተንግዶ የተሰጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ከቀረጥ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች ወደ ግለሰቦች በሽያጭ ሲዘዋወሩ በጉምሩክ አዋጁ ቁጥር 622/01 ምዕራፍ 2 አንቀጽ 94(1) እና 98 መሰረት ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በመንገድ ትራንስፖርት መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቱ ለመንግስት የተሰጡ መብቶች ማስፈጸሚያ የስራ ሂደት እና በኢንተለጀንስ ቡድን መካከል የመረጃ ልውውጥ ደካማ መሆን ምክንያት የተጭበረበረ ሰነድ በመጠቀም ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ከቀረጥ ነጻ የገቡ ተሽከርካሪዎች ወደ ህጋዊነት እየዞሩ መሆኑን የቅ/ጽ/ቤቱ የኢንተለጀንስ ቡድን በመግለጽ ወንጀሉን ለመከላከል እንዲቻል ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር እንደሚገባው ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች እና የስራ ክፍሎች የላከውን ደብዳቤ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም በዚሁ መሰረት የተስተካከለ አሰራር አለመኖሩ፤

3.7.2 የወጪ ንግድ (Export) ቀረጥና ታክስን በተመለከተ

- በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች በአዋጅ ቁጥር 543/1999 አንቀፅ 11(7) መሰረት ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ አራት ድርጅቶች ጥሬ ዕቃ ያስገቡ እና ጥሬ እቃው ስራ ላይ ውሎ ምርቱን ወደ ውጭ መላክ ያለባቸው ቢሆንም፣ ምርቱ ሳይላክ ከአንድ አመት በላይ የቆየና የፈቃድ ማራዘሚያም ያልተደረገ መሆኑ፤ ይህም በማበረታቻ መልክ ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ አገር ውስጥ የገባ ጥሬ እቃ ለተባለው ዓላማ ሳይውል በሀገር ውስጥ ገበያ ሊሸጥና መንግስት ሊያገኝ የሚገባው የውጭ ምንዛሬ ሊያሳጣ እና ሊሰበሰብ የሚገባው ቀረጥና ታክስም ላይሰበሰብ ይችላል፡፡
- ሳባ ሃር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወደ ውጪ የላካቸው እቃዎች ዋጋ ሲታይ በአንድ የዋጋ ደረሰኝ ላይ የተገለጹ አንድ አይነት የዕቃ ሞዴል ያላቸው እቃዎች በተመሳሳይ ቀን እና ዲክላራሲዎን ቁጥር አማካኝነት የተላኩ እቃዎች የተለያየ ዋጋ ተሰጥቷቸው አንዳንዶቹን በዝቅተኛ የነጠላ ዋጋ በማስላት መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን የውጭ ምንዘሬ አነስተኛ እንዲሆን መደረጉ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ መንግስት ሊያገኝ የሚገባው የውጭ ምንዛሬ በUSD 1034.00 አንሶ ተገኝቷል፡፡

3.7.3 ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

➢ በቤተ-መንግስት አስተዳደር

  - በቤተ መንግስቱ ቅርንጫፎች ከልዩ ልዩ የአትክልትና የአዝዕርት ምርት ሽያጮች ገቢ የሚሰበሰብ ቢሆንም፣ የተመረቱት ምርቶች ከማሣ ወደ ንብረት (ሽያጭ) ክፍል ገቢ ከተደረጉ በኋላ በገቢም ሆነ በወጪ የማይመዘገቡ መሆኑና የዋጋ ትመና ውሳኔ የሚያሳይ ማስረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ፤

- ከዋናው መ/ቤት የመጡ ደረሰኞች በሞዴል 19 ወይም በመዝገብ የማይመዘገቡና  በአመቱ መጨረሻ የደረሰኞች ቆጠራ ተከናውኖ የማያውቅ መሆኑ፣
- በሁለቱም ቅርንጫፎች ቀድመው የነበሩት ሠራተኞች ከቦታቸው ሲነሱ የተሰራባቸውንም ሆነ ያልተሰራባቸውን የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ርክክብ የማይደረግ መሆኑ፤

➢ የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን በስታዲዮም ዙሪያ ከሚያከራያቸው የንግድ ቤቶች የሚሰበስበው የኪራይ ገቢ ከ15 ዓመታት በፊት በተተመነ ዋጋ መሰረት መሆኑና አንዳንድ መ/ቤቶችም ምንም ባልተጠናና በሚመለከተው አካል  ባልተፈቀደ የዋጋ ታሪፍ ገቢ የሚሰበስቡ መሆኑ፤

➢ በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ብር 98,277.62 የያዙ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለተቀነሰ ገንዘብ የሚሰጥ ደረሰኝ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡

➢ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቁጥር አውግ-54/ በቀን 9 ነሐሴ 2000 በተላለፈ መመሪያ መሰረት ለቤት አበል የሚፈጸም ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት የተመለከተ ቢሆንም የጅማ ዩኒቨርስቲ ግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ፣ የጅማ ዩኒቨርስቲ፣ የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ፣ የመዳወላቡ ዩኒቨርስቲ፣ የጎንደር ዩኒቨርስቲና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ በተላለፈው መመሪያ መሰረት ለቤት አበል የተፈጸመው ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ የሥራ ግብር እንደማይቀነስ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ጎንደር ዩኒቨርስቲ ለትምህርት ወደ ወጭ አገርና ወደ ተለያዩ የትምህርት ተቋማት ለሄዱ መምህራን የመኖሪያ ቤት አበል እንደሚከፍልና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ለአስተዳደር ሰራተኞች የመኖሪያ ቤት አበል ክፍያ የሚፈፀም መሆኑ ታውቋል፡፡

➢ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ ክፍል በበጀት ዓመቱ ከንብረት ክፍል ወጪ ካደረጋቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ውስጥ 11

ጥራዝ ደረሰኞች ለሆሩ ጉድሩ የእንሰሳት ማዕከል ተሰጥተው ከነበረው 2ቱ (ከቁጥር 383051 - 383100 እና 382351 - 382400) የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡ በነዚህ ደረሰኞችም የተሰበሰበ ገቢ መኖር አለመኖሩም አልታወቀም፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፣ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፣ እንድሁም በገቢ ደረሰኝ አያያዝ ረገድ የሚደረገው ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባበሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

## 4. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

### 4.1 <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶች ብር 79,529,842.89 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-17 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር 18,887,608.49 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 34,924,581.81 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 293,746.00 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 25,423,906.59 |
| ድምር | 79,529842.89 |

ሲሆን፣

ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ለመ/ቤቱ የበላይ ሀላፊ ለውጭ ጉዞ ለመኝታና ቁርስ ለከፈለው የአሜሪካን ዶላር 3,450.00 እና ለእጅ ኳስ ፌደሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ ለመጠባበቂያ ለከፈለው ዩሮ 70.00፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለውጭ ጉዞ

ለተከፈለው የአሜሪካን ዶላር 621.39 ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንድቀርብለት አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ አሳስበናል፡፡

## 4.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣በ12 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 38,666,777.07 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ - 16 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር 6,776,282.58 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 31,890,494.49 |
| ድምር | 38,666,777.07 |

ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር መረጃ ሳይደገፍ፤ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጎላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽገልጻዋል፡፡

## 4.3 <u>ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ25 መ/ቤቶች ብር 237,164,457.41 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-19 ተመልክቷል/

ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር | 644,521.61 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | | 235,619,304.87 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | | 80,938.35 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | | 819,692.58 |
| ድምር | | 237,164,457.41 |

ሆኖ ተገኝቷል።

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ ክፍያዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ 119.53 ሚሊዮን፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ 79.29 ሚሊዮንና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ 34.52 ሚሊዮን ሲሆን፣ ምክንያቶቹም የምህንድስና ክፍል የቁጥጥርና የማማከር ፈቃድ ሳይኖረው የተከፈለ፣ ለማበረታቻና ለሽልማት በቦርድ ሳይጸድቅ የተከፈለ እና በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ዕቃዎች (materials on site) ብሎ የተከፈለና ሌሎችም የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈጸም፣ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑምአፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት መመሪያ የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተፈከለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል።

## 4.4 የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዢዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ33 መ/ቤቶች ብር 313,263,670.05 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል። /ዝርዝሩም በአባሪ -18 ተመልክቷል፡፡/ ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር | 8,691,779.18 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | | 274,878,089.91 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | | 24,215,511.30 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | | 5,478,289.66 |
| ድምር | | 313,263,670.05 |

ሆኖ ተገኝቷል።

ከደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፤ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 224.22 ሚሊዮን፤ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 41.38 ሚሊዮን የኢንፎረሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 7.56 ሚሊዮንና የመቀሌ ጤና ሳይንስና አይደር ሪፈራል ሆስፒታል ብር 3.06 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን ግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸም እና በአቅራቢነት ካልተመዘገቡ ድርጅቶች ግዥ ማከናወን የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዠ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፤ መ/ቤቶቹም አስተያየቱን ተቀብለውታል፡፡

## 4.5 በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት በተገቢው ባለሥልጣን እየተፈቀዱ መከናወናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,623,791.53 ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ ሳይታዘዝ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -22 ተመልክቷል/

ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር 744,848.50 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 2,878,943.03 |
| ድምር | 3,623,791.53 |

ከዚህም ዋነኛው በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 2.62 ሚሊዮን በኃላፊ ሣይፀድቅ በወጪ የተመዘገበው ነው፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ወጪ በሚመለከተው ባለሥልጣን እየተፈቀደ መከፈል እንዳለበት አሳስበናል::

## 4.6 የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ

በበጀት ዓመቱ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶች በተለያየ ምክንያት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 2,032,423,012.07 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 12 ተመልክቷል/

ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | | |
|---|---|---|
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | ብር | 2,017,833,421.34 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | | 14,589,590.73 |
| በድምሩ | | 2,032,423,012.07 |

የወጪውን ትክክለኛነትማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሣብውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሠራዊት ደመወዝ፣ ወጪ ያደረገውብር 1.87 ቢሊዮን፤ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት 54.25 ሚሊዮን፤ እንዲሁም የውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ ብር 33.34 ሚሊዮን እና የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ብር 49.99 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሶስቱ የደህንነት መ/ቤቶች ለደመወዝ ለነዳጅና ለስልክ ወዘተ… ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ለማረጋገጥ በኮድ የተከፈለውን ደመወዝ የሠራተኞቹ ኮድ፤ የመኪኖች ታርጋና የስልክ ዝርዝሮች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር በላከው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰጡ የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ሚስጥራዊ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

## 4.7 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆረጠለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች በብር 83,991,211.71 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል። /ዝርዝሩም በአባሪ- 21ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር | 133,347.12 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | | 83,191,926.53 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | | 465,532.92 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | | 200,405.14 |
| ድምር | | 83,991,211.71 |

ከዚህም ውስጥትምህርት ሚ/ር ብር 75.26 ሚሊዮን ፤ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 4.02 ሚሊዮን እና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ብር 3.9 ሚሊዮን ለተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር ለንብረት ብክነት ስለሚያጋልጥ አሠራሩ ተገቢ ሆኖ ባለመገኘቱ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊደረግና የንብረትገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ንብረቶች ለየመ/ቤቶቹ አገልግሎት ለመዋላቸው በማስረጃ እንዲረጋገጥ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 4.8 አላግባብ በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 981,864,470.70 በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---|
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ብር | 776,286,855.25 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 205,577,615.45 |
| ድምር | 981,864,470.70 |

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ትምህርት ሚ/ር ብር 539.69 ሚሊዮን፤ ጂማ ዩንቨርሲቲ ብር 168.43 ሚሊዮን፤ ውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 155.84 ሚሊዮንእናአርባ ምንጭ ዩንቨርሲቲ ብር 68.16 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርተችን አሳስበናል፡፡

## 4.9 <u>በብልጫ የተከፈለ ወጪ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡ በ 7 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግዢዎች ብር 423,674.61 እና ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በ 12 መ/ቤቶች ብር 1,204,408.33 በጠቅላላው ብር 1,628,082.94 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 24 ተመላክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ዕደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤በድግሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገበው ውል ውጭ በመክፈልና ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል፤ እንዲሁም በውጭ ጉዞ በዕለቱ ከነበረው የሚንዛሪ መጠን በላይ በመክፈል የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የግዢ ስርዓቱን ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 4.10 <u>የወጪ የሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች</u>

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ21መ/ቤቶች ብር 20,200,592.08 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -26 ተመልክቷል/ ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስናኮሙኒኬሽንመ/ቤቶች | ብር | 12,947,623.52 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | | 6,636,263.97 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | | 616,704.59 |
| ድምር | | 20,200,592.08 |

የወጪ ሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከልትምህርት ሚ/ር ብር 3.77 ሚሊዮን እና ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ብር 1.75 ሚሊዮን እና በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 1.15ሚሊዮን ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

## 4.11 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

በወጭ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ12 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 20,970,915.91 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2003 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -25 ተመልክቷል/ ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | | |
|---|---|---|
| የፋይናንስናኮሙኒኬሽንመ/ቤቶች | ብር | 8,923,256.37 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | | 2,143,069.23 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | | 9,904,590.31 |
| ድምር | | 20,970,915.91 |

ሲሆን ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.12 <u>በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ</u>

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ8 መ/ቤቶች ብር 55,270,058.06 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ የወጪ ሂሳብሪፖርት ያላደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-23 ተመልክተል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---|
| የፋይናንስናኮሙኒኬሽንመ/ቤቶች | ብር 10,901,490.92 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 32,336,992.79 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 12,031,574.35 |
| ድምር | 55,270,058.06 |

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢምሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

5.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ36 መ/ቤቶች ብር 247,976,021.92 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -27 ተመልክቷል/ ሂሣቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | |
|---|---|
| የፋይናንስናኮሙኒኬሽንመ/ቤቶች | ብር 54,066,972.56 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 19,594,526.53 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 164,620,205.87 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 9,694,316.96 |
| ድምር | 247,976,021.92 |

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 144.43 ሚሊዮን ፤ውጭ መልዕክተኞች ብር 19.33 ሚሊዮን ፤ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 49.58 ሚሊዮን፤አዲስ አበባ ንግድ ስራ ት/ቤትብር 9.68 ሚሉዮን፤ በወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 5.03 ሚሊዮን፤ አርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ብር 3.85 እና ጤና ጥበቃ ሚ/ር ብር 3.15 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ በሌሎች መ/ቤቶችም የተከፋይ ሂሳቡ የሠራተኞች የጡረታ መዋጮንም ይጨምራል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2003 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 144.43 ሚሊዮን የሠራዊቱ አባላት ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና ሂሣቡም በወጪ የተመዘገበ መሆኑን በመጥቀስ አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር እየተጠየቀ እንዲከፈልና ሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

## 5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ላይ የታዩ ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የመ/ቤቱ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- <u>ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን የማያሳዩ ሂሳቦችን በተመለከተ</u>

  ከቅ/ጽ/ቤት የተላኩ ሂሳቦች በትክክለኛ የሂሳብ ሚዛናቸውን ጠብቀው ሪፖርት መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በቅ/ጽ/ቤቶችና የሂሳብ መደቦች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን የማያሳዩ በዋናው መ/ቤት እና በአምስት ቅርንጫፎች የተከፋይ ሂሳብ ብር 1,883,172.42 በዴቢት፣ ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 122.53 በክሬዲት እንዲሁም በአንድ ቅርንጫፍ የወጪ ሂሳብ ብር 13,123.80 በክሬዲት የሚታይ መሆኑ እና ይህም ተገቢው ማጣራት እና ማስተካከያ ሳይደረግ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫ ላይ ተካቶ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ - 32 ቀርቧል/

- በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅትብር 7,150.81፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሔራዊ ጽ/ቤት ብር 4,403.65 (ሁለት የተለያዩ ሂሳቦች) መነሻ ሰነድ የሌላቸው መሆኑ፤ ኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን ብር 4,693.33፤ እንዲሁም በማዕከላዊ ስታስቲክስ ብር 700,860.51፤ በድምሩ ብር 717,108.30 ማስረጃው ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማጣራት አልተቻለም፡፡

- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ: የጡረታ መዋጮ ብር 125,146.77; የደመወዝ የተጣራ ተከፋይ ሂሣብ ብር 23,000,357.47 ሰኔ 30/2003 በተከፋይ ሂሣብ መግለጫ ውስጥ ተካተው ሪፖርት ለተደረገው ሂሣብ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- የውጭ መልዕክተኞች በተለያዩ የተከፋይ የሂሣብ መደቦች ባልተለመደ የሂሣብ መደብ (Abnormal Balance) የዴቢት ሚዛን ብር 112,770.06 የሚያሳይ፤

- በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 79,416.94 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን /Abnormal Debit balance/ በመያዙ የ2003 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሣብ ሚዛን በብር 79,416.94 አላግባብ ዝቅ ተደርጎ የተያዘ መሆኑ፤

- በሃዋሳ ዩኒቨርስቲ-የወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ የተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች በድምሩ ብር 55,713.75 ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን /Abnormal Debit balance/ የሚያሣዩ በመሆኑ የ2003 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሣብ ሚዛን በብር 55,713.75 ዝቅ እንዲል አድርጓል፡፡

- የጅማ ዩኒቨርስቲ ግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ ብር 4,648.52 ተከፋይ ዕዳ መኖሩ የተመለከተ ቢሆንም ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ ባለመኖሩ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፤

- በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ የ2003 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሳብ መግለጫ መሰረት ለዩኒቨርስቲው ሠራተኞች ያልተከፈለ ደመወዝ ብር 342,021.17 መኖሩ የተመለከተ ቢሆንም ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ ሂሣብ ውስጥ ብር 191,810.66 ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ ሂሣብ እንደሆነና በጉዳዩ ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በተደጋጋሚ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፤

- በባህርዳር ዩኒቨርስቲ ብር 5,758,577.00 እና በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ብር 7,546,129.63 በድምሩ ብር 13,304,706.63 ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ የተገለጸ ቢሆንም በዝርዝር ለማየት ተሞክሮ ትክክለኛ ገጽታውን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፤

- በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ተከላ እና ሽያጭ የተሰበሰበው ብር 1,403,036.37 በገቢ መያዝ ሲገባው በተከፋይ ሒሳብ ተይዞ ተገኝቷል::

- በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 283,295.29 ተከፋይ ሂሳብ በዴቢት አቅጣጫ ተመዝግቦ ተገኝቷል በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በሌሎች የመያዣ ሂሳቦች (5054) የሂሳብ መደብ በመነሻነት (Opening Balance) የተመዘገበው በDአካውንት ባንክ ስቴትመንት ላይ ከታየው በብር 748,767.88 አንሶ ተገኝቷል፡፡

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል፡፡

## 6. አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 6.1 ከበጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ29 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 288,580,617.52 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-28 ተመልክቷል/

ሂሣቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር 3,493,939.48 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 206,646,896.66 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 7,663,228.96 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 776,552.42 |
| ድምር | 288,580,617.52 |

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 102.40 ሚሊዮን፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 67.40 ሚሊዮን፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 47.44 ሚሊዮን፣ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 24.07 ሚሊዮን እና ጥቁር አንበሳ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 20.82 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ

ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱም መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙም የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 6.2 ያልተሠራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት በጀታቸውን በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ92 መ/ቤቶች ብር 3,054,108,751.58 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-28 ተመልክቷል፡፡

ሂሣቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | ብር 188,221,179.96 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 73,007,404.39 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 1,018,356,356.15 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 1,774,523,811.08 |
| ድምር | 3,054,108,751.58 |

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት የተገኘ ሲሆን፣ በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም ሌሎች መ/ቤቶች በመንግስት ተፈቅዶላቸው ሊጠቀሙበት የሚችሉትን በጀት እንዳይጠቀሙ ከማድረጉም በላይ የብቃት ማነስን (inefficiency) የሚያመለክት በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 6.3 ስለበጀት ሌሎች ጉዳዮች

- ከውስጥ ገቢ ወጪ ለማድረግ ከተፈቀደው በጀት በላይ ጥቅም ላይ የዋለ፣
    - ጎንደር ዩኒቨርስቲ - ብር 2,419,084.20
    - ባህርዳር ዩኒቨርስቲ - ብር 66,247,352.36 መገኘቱ፣

- በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ሆኖም በድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,942,149.92፣ በደብራማርቆስ ዩኒቨርስቲ ብር 8,959,340.44 በድምሩ ብር 10,901,490.36 የውስጥ ገቢያቸውን በደንቡ መሰረት ሳያስፈቅዱ ስራ ላይ አውለው ተገኝቷል፡፡

- የደቡብ ኢትዮጵያ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሄራዊ ጽ/ቤት በመንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ ሀ-መ መሰረት በ2003 በጀት ዓመት የተፈቀደለትን በጀት አጠቃቀም በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችል የበጀት መቆጣጠሪያ ቋት (ሌጀር) ያላዘጋጀ መሆኑ፤

- ከሁለት የተለያዩ የሂሳብ መደቦች ማለትም ከሂሳብ መደብ 6212 ብር 25,000.00 እና ከሂሳብ መደብ 6313 ብር10,000.00 ወደ ሂሳብ መደብ 6259 ዝውውር የተከናወነ ስለመሆኑ በዘገባ መዝገብ ላይ ማየት የተቻለ ቢሆንም፣ በድምሩ ብር 35,000.00 የበጀት ዝውውሩ የተፈቀደበት ቅጽ በማ/1 ለኦዲት ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648 አንቀፅ 10(3) መሰረት የተሰበሰበው የመንግስት ገንዘብ ወደ ተጠቃለለው ፈንድ ገቢ ማድረጉንና ሂሳቡንም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በየወሩ ሪፖርት ማድረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ከሰበሰበው ከውስጥ ገቢ ብር 9,803,084.23 ውስጥ ብር 3,017,000.00 እንዲጠቀም የተፈቀደለት ሲሆን ቀሪው ብር 6,786,084.23 እና ቀደም ካሉት አመታት የዞረው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ በአዋጁ መሰረት ፈሰስ ያለመደረጉ፤ አሰራሩ በአዋጁ መሰረት እንዲስተካከል በ2002 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት ላይ የተገለፀ ቢሆንም ምንም አይነት እርምጃ አልተወሰደም፡፡

  ይህም ያልተጠየቀና ያልተፈቀ የበጀት ዝውውር ሊመዘገብና ሥራ ላይ ሊውል ይችላል፡፡ ከተፈቀደው በጀት በላይ ስራ ላይ ቢውል በወቅቱ ላይደረስበት ይችላል፡፡ የውሰጥ ገቢን በጀት ሳያስፈቅዱ ስራ ላይ ማዋል የህግ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁን መሰረት አድርገው እንዲሰሩ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. <u>የንብረት አያያዝና አጠባበቅ</u>

7.1 <u>የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳዳር ድክመቶች</u>

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች ተገኝቷል፡፡

- ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ 26 መ/ቤቶች
- ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ 15 መ/ቤቶች
- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ 22 መ/ቤቶች
- ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ 22 መ/ቤቶች
- አገልግሎት ላይ ያልዋሉ ንብረቶች የተገኙባቸው 8 መ/ቤቶች
- አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶችን በመንግስት መመሪያ መሰረት ሳያስወገዱ የተገኘባቸው 33 መ/ቤቶች
- ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው 7 መ/ቤቶች

እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-29 ተመልክቷል/ መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም። በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፣አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንም በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 7.2 <u>በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች</u>

<u>የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች</u>

- በመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት፤
  - በተደራራቢ ግዥ በመፈፀሙ ምክንያት በመጋዘን ውስጥ ዕቃዎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
  - በመጋዘን ውስጥ ያለአገልግሎት ለብዙ አመታት የተቀመጡ የተለያዩ ዕቃዎች መገኘታቸው፤
- በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የቋሚ ዕቃ መጋዘን ውስጥ ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት ከ1999 ጀምሮ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ 10 ፕሮጀክተሮች ወደፊት ሊጠቅሙ ይችላሉ በሚል ለረዥም ጊዜ ያለስራ እንዲቀመጡ መደረጉ፤ ለብልሽት እንዲዳረጉ የሚዳርግ በመሆኑ በሽያጭ ወይም በስጦታ ሊወገዱ የሚችሉበት መንገድ መፈለግ እንደሚኖርበት፣
- በማእከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2003 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት መሰረት ከአየርላንድ ኢምባሲ በእርዳታ ከተሰጡት እቃዎች ውስጥ ብዛታቸው 15 የሆኑ ያገለገሉ ቋሚ ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ አለመደረጋቸው እና እቃዎቹንም የተረከበው ግለሰብ ስራው የማይመለከተው መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች</u>

- በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ፤
  - ከግብርና ሚኒስቴር የመጡ የተለክዩ አሮጌ ንብረቶችን የንብረት ክፍል ሰራተኛው ያልተረከባቸው መሆኑ፣
  - የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ ከመከናወኑም በላይ ሥራው የሚከናወነው በኤጀንሲው የመልዕክት ሰራተኛ በተደራቢነት መሆኑ፤
- በብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል፤
- በአብዛኛው በእንስሳት እና በአንዳንድ ቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ሪፖርት ላይ የንብረቶቹ ዋጋ ያልተጠቀሰ መሆኑ፤
- በምግብ ክምችት አስተዳደር፤

- በዋናው መሥሪያ ቤት፣ በናዝሬትና በሽንሌ መጋዘን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በእቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ በማዘጋጀት እቃዎችን የመረከብና የመጠበቅ እንዲሁም የንብረት ወጪ ደረሰኝ በማዘጋጀት እቃዎችን ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰው የሚሰራ መሆኑ፣
- በናዝሬት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በእቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ እቃዎች ከሚወገዱ እቃዎች ጋር ተቀላቅለው ተቀምጠው የሚገኙና የተለያዩ ኬሚካሎች በወለል ላይ ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ የተቀምጡ መሆኑ፣
- በናዝሬት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወደ መጋዘን የሚገቡ እህሎች በከፊል እንጂ በሙሉ የማይመዘኑ ሲሆን፤ በሽንሌ መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ደግሞ በጊቢው ውስጥ የሚገኙ የምድር ውስጥ ሚዛንና ሌሎች ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች የተበላሹና ጥቅም የማይሰጡ በመሆኑ ወደ መጋዘኖቹ የሚገቡና የሚወጡ እህሎች የማይመዘኑ መሆኑ፤
- የሽንሌ መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የእሳት አደጋ መከላከያየሌለው፤ እንዲሁም በውስጡ ያለው የተለያዩ እህሎች የታሸጉበት ማዳበሪያ በመቀደዱ በመጋዘኖቹ ወለል ላይ ስንዴ በብዛት ፈሶ የተገኘ መሆኑ፤

➢ በብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል፤

- ለምርምር የተገዙት የቀንድ ከብቶች ማለትም ፍየሎችና በጎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጣቸዉ መሆኑ፣

➢ በብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ንብረቶች እንዲሁም በስፖርት ኮሚሽን በዕርዳታ የሚገቡ የስፖርት ትጥቆች፣ ቱታዎች፣ ማልያዎች በመዝገብ ተመዝግበው ያልተያዙ መሆኑ፤

➢ በቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል አንድ የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ የተረከቡትን የቡና መቁያ ማሽኖች፣ የቡና ሳንፕል ሚዛን፣ የኤሌክትሪክ ምድጃዎች ኮምፒዩተር ከነፕሪንተሩ እና የተለያዩ ቋሚ አቃዎች ያላስረከቡ መሆኑ፣

- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ 173 ሰራተኞች ብር 1,594,818.71 የሚገመት ንብረት እና የገንዘብ ዕዳ እያለባቸው መ/ቤቱን የለቀቁ መሆኑ፣

- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ መካኒሳ በሚገኘው መጋዘን ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸው በርካታ ኬሚካሎች ሳይወገዱ በሰራተኞቹ ላይ የጤና ጉዳት እያደረሱ መሆኑ፣

- በግብርና ሚኒስቴር፤

  - ለረጅም ዓመታት ግምጃ ቤት ገቢ የተደረጉ፣ እና በተለይም በ1996 የተለያዩ መ/ቤቶች ሲዋሐዱ ተመላሽ የተደረጉ ንብረቶች በዓይነትና አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡት ሳይለዩ ለቁጥጥር በሚያስቸግር ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
  - መሥሪያ ቤቱ ለተመላሽ ንብረቶች ማከማቻ እንዲሆን የሚጠቀምበት 9 መጋዘኖች ሲኖረው ንብረቱን የሚረከበው እና ወጪ የሚያደርገው አንድ የግምጃ ቤት ሰራተኛ ብቻ ከመሆኑም በተጨማሪ ንብረቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል ቢን ካርድ ወይም ሌላ የመቆጣጠሪያ ስልት የሌለው፤የተሟላ መረጃ ያልያዘና ለቁጥጥር የማያመች መሆኑ፤
  - በመሥሪያ ቤቱ ለረጅም ጊዜ የንብረት ማስወገድ ስራ ባለመስራቱ ምክንያት ብዛት ያለው ንብረት፤ የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸው ከሚካሎች፣ የእንስሳት መድሃኒቶች እና ሰብሎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
  - የተመላሽ ንብረት ቆጠራ እናየመዝገብ ማስታረቂያ ወይም ኦዲት ተደረጎ ለመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣
  - በቃሊቲ በሚገኘው የመሥሪያ ቤቱ መጋዘን በክልሎች ስም የመጡ የተለያዩ ብዛት ያላቸው የግብርና መሳሪያዎች፤ እንዲሁም በዕርዳታ የተገኙ ዘመናዊ ለግብርና ሥራ የሚያገለግሉ፣ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፣

- በአላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ፤

  - በበጀት አመቱ የንብረት ቆጠራ ቢከናወንም በቆጠራ ሪፖርት ላይ በአብዛኛው የንብረቶች ዋጋ የማይጠቀ ስመሆኑ፣

- በቆጠራ ሪፖርት መሰረት 10934 ሊትር ነዳጅ ጉድለት የሚያሳይ መሆኑ፣

➢ በአጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ፤

- በንብረት ቆጠራ ሪፖርት ውስጥ የዕቃዎች ዋጋ የማይሞላ (የማይገለፅ) መሆኑ፣
- የተገዛው የነዳጅ መጠን መቆጣጠሪያ (Dip stick) በትክክል ለመሰራቱ በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን ያልተረጋገጠመሆኑ፣

➢ በአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ፤

- የመንግሥትን ንብረት ሳያስረክቡ ከኮሌጁ የለቀቁ ሰራተኞች እንዳነበሩና፣
- የመንግሥትን ንብረት አጥፍተው በስራ ላይ በሚገኙ ሰራተኞች ላይም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- በአሳሳና አርዳይታ ኮሌጅ ግቢ ውስጥ የሚገኙት የነዳጅ ማደያ ቆጣሪዎች የተበላሹ ሲሆን፤ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

<u>የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች</u>

➢ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ በብር 123,280.00 ከተገዙት 400 /Flash Disk 4 GB/ ውስጥ ብር 121,122.00 ዋጋ ያላቸው በቁጥር 393 ፍላሾች የተበላሹና አገልግሎት ላይ ሊውሉ የማይችሉ ሲሆን፣ በአቅራቢው ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

➢ በጅማ ዩኒቨርስቲ *ለሣትኮን ኮንስትራክሽን ድርጅት በብድር የተሰጠ ብዛት 100 እና ለኮሚኒቲ ት/ቤት ብዛት 200 ኩንታል ሲሚንቶ እንዲሁም ለጅማ ግብርናና እንስሳትህ ክምና ኮሌጅ በብድር የተሠጠ ቴራዞ የመሬት ምንጣፍ በቁጥር 1550 ተመላሽ አልተደረገም፡፡ በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው ለሚከናወኑ ጅምር ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚሆን ብዛት 64,400 ኩንታል ሲሚንቶ በተቋሙ መገዛቱንና ለስራ ተቋራጮች በዱቤ የተከፋፈለ መሆኑን ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ሥራ*

*ተቋራጭ የወሰደው ሲሚንቶ ብዛትና ዋጋ እንዲሁም ተቋራጩ ተመላሽ ያደረገው ወይም የከፈለው ገንዘብና የሲሚንቶው ብዛት መከታተያና መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርድ/መዝገብ በማቋቋም ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡*

<u>የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች</u>

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት መጋዘን ኬሚካሎች የጐማ የውስጥ ላስቲኮች /ከመነዳሪያ/ ሌሎችም ለረጅም ዓመታት እንውገዱ እርምጃ ሳይወሰድ መገኘቱን፣
- በብረታ ብረት ልማት ኢንስቲተዩት የወርክ ሾፑ የንብረት ክፍል ኃላፊ እና የንብረት አስተዳደር ሠራተኛ በሆኑት አንድ ሰረተኛ የንበረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ የማዘጋጀት፤ ንብረት የመመዝገብ እና የዕቃ ግምጃ ቤት ጠበቂ በመሆን ሁሉንም ሥራዎች ስለሚያከናውኑ ቁጥጥሩ የላላ ከመሆኑም በላይ የሥራ ክፍፍል ባለመኖሩ የንብረት መባከን ሊያስከትል እንደሚችል፣

*የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል እና እንዲፈፀም መሥሪያ ቤቶቹ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡*

## 7.3 <u>የተሽከርካሪ አያያዝ</u>

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል::

- ሊብሬ /የባለቤትነት መታወቂያ/ ያልቀረበላቸው በ15 መ/ቤቶች 221 ተሽከርካሪዎች፤
- በብልሽት ምክንያት የቆሙበ19 መ/ቤቶች 219 ተሽከርካሪዎች፤
- በሊብሬው ላይ የተገለጸው ቁጥር በሞተር ላይ ካለው የተለያየ በ1 መ/ቤት 1 ተሽከርካሪ

መኖራቸው ታውቋል:: /ዝርዝሩም በአባሪ-30 ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች

ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፤ ሊብሬ ያሌላቸው እንዲወጣለቸውና በሊብሬው ላይ የተገለጸው ቁጥር በሞተር ላይ ካለው የተለያየው ጉዳዩ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

በተጨማሪም የተሽከርካሪዎች የነዳጅ እና የኪሎ ሜትር ቁጥጥር ሁኔታ ሲጣራ በማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ተሽከርካሪዎች ጋራዥ ከገቡ በኋላ ተጠግነው ሲወጡ ለፍተሻ በሚል ምክንያት ከ100 ኪ.ሜ በላይ የሚነዱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም ውስጥ አምስት ተሽከርካሪዎች ከ300 እስከ 584 ኪሎ ሜትር የተነዱ መሆኑ፤

በማዕከላዊ ስታስቲክስ የሰሌዳ ቁጥር 4-03084 ቶዮታ ኮሮላ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-00637 ሱዙኪ መኪናዎች በብልሽት ምክንያት በእርሻ መሣሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት ጋራዥ ጥገና ሳይደረግላቸው ከሁለት ዓመት በላይ መቆየቱ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

### 7.4 <u>የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም በተመለከተ</u>

- በኢትዮጵያ የምግብ፤ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን፤ ለተሽከርካሪዎች ነዳጅ ለመቅዳት የሚጠቀሙበት አቢሲንያ ካርድ በሾፌሮች እጅ የሚቀመጥና የሚደረግ ቁጥጥር አናሳ መሆኑ፤
- በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ
    - ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ነዳጅ መሙለት ኩፖኖችን ወደ ፋክቱር መቀየር ቀሪ ኩፖኖችንና ነዳጅ የተቀዳባቸውን ፋክቱሮች የመጠበቅ ስራ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፣
    - ለወጪና ለገቢ ኩኖች መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑና ከወጪ ቀሪው የማይገናዘብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ለነዳጅና ቅባቶች ግዥ ተገቢው ምዝገባ እንዲከናወንና ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 8. <u>ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ</u>

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፦

## በፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች

በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

- በዋናው መ/ቤት የችሮታ ጊዜ ተከፋይ ሂሳብ ብር 3,864,313.29 ሁኔታው ተጣርቶ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ሂሳብ በጀት በሂሳብ መደብ 6412 መጠየቅ እንደሌለበት የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠ ቢሆንም በማሻሻያ ሀሳቡ መሰረት ተፈጽሞ አልተገኘም፡፡
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ለአላቂና ቋሚ እቃ የንብረት መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑና የቆጠራ ውጤት ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር የሚገናዘብበት ስርአት የሌለ በመሆኑ እንዲስተካከል የማሻሻያ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም አለመስተካከሉ፣ ለበከልቻ ትራንስፖርት አ/ማህበር በነጻ የተላለፈው የቅ/ጽ/ቤቱ ፎርክሊፍት እንዲመለስ ወይም በሽያጭ እንዲተላለፍ የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አልተወሰደም፣ የጉምሩክ ስነስርአት ሳይፈጸምባቸው ከተከፈቱ ከአመት በላይ የሆናቸው 15 ዲክላራሲዎኖች ቀጣይ የጉምሩክ ስነስርአት ያልተፈጸመባቸው በመሆኑ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ የማሻሻያ ሀሳብ ቢሰጥም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት ከአንድ ድርጅት ብር 255,617.74 ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ በመሆኑ ቅ/ጽ/ቤቱ ከሚመለከተው ድርጅት ቀሪ ሂሳቡን እንዲሰበስብ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ቀሪ ሂሳቡን ለመሰብሰብ የተወሰደ ምንም አይነት እርምጃ አለመኖሩ፤
- በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት 27 የቫውቸር ተጠቃሚዎች በወቅቱ ሂሳባቸውን ያላወራረዱ በመሆኑ፣ የተወሰነላቸውን የጊዜ ገደብ ጠብቀው ባለመጓጓዛቸው ከተቀጡ 5 ድርጅቶች እና ወኪሎቻቸው ሊሰበሰብ የሚገባው ቅጣት ባለመሰብሰቡ፣ ለመንግሥት ገቢ ሳይደረግ የተገኘ የዋስትና ጊዜያቸው ያለፈበት የ457 ዲክላራሲዎን የቦንድ ሂሳብ የተገኘ በመሆኑ በአዋጁ መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ እና ለኦዲት ሥራ ያልቀረቡ 15 ድክላራሲዮኖች ተፈልገው በነዚህ ዲክላራሲዮኖች የተሰበሰበው ገቢ ትክክለኛነት እንዲጣራ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የእርምት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

በልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች

- በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሁለት ሠራተኞች ወደ ውጪ ሀገር ሲሄዱ ያለ አግባብ በብልጫ 320 የአሜሪካን ዶላር የተከፈላቸው ላይ ምንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በአንድ ትልቅ መጋዘን፣ ጊዜ ያለፈባቸው ብዛት ያላቸው ፀረ ተባይ ኬሚካልና ዲዲቲ በመኖራቸው፤ በዕቃ ግምጃ ቤት ባለበት አካባቢ መጥፎ ሽታ የፈጠረ ከመሆኑም በተጨማሪ ግምጃ ቤቱ በእርጅና ምክንያት በመፍረስ ላይ የሚገኝ መሆኑ፣
- በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር:
  - በግንባታ የሥራ ክፍያ ወቅት ብር 23,440,193.83 የተጨማሪ እሴት ታክስ አሁንም ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
  - የቅድመ ክፍያንና የመያዣ ሂሣብ ሳይቀነስ ለተቋራጩ ብር 132,710,589.58 የተከፈለ መሆኑ፣
  - በወጪ ተመዝግቦ ለተገኘው የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ ብር 113,692,327.25 ማስተካከያ ሳይሠራለት የተገኘ መሆኑ፣
- በምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ለብር 310,240.46 የተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች የተሰሩበት ምክንያት አይታወቅም፡፡ በተጨማሪም ማስተካከያ ሊሰራላቸው ለሚገቡ ሂሳቦችም የተሰራው ማስተካከያም ቢሆን በትክክለኛው የገንዘብ መጠን ካለመሆኑም በላይ ሂሳቡ እንዲገጥም ለማድረግ ብቻ የተሰራ መሆኑ፣

የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር

በ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ውጤት ብር 1,275,750.00 ለአሰልጣኝ፣ ለቱቶር እና ለወታደራዊ አሠልጣኞች ከውል ውጭ በብልጫ የተከፈለው ያልተተካ መሆኑን፤

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት

በ1994 ዓ.ም ለትምህርት መሣሪያዎች አቅራቢ ድርጅት ለተከፈለው ብር 279,101.07 ንብረቱ ለጽ/ቤቱ ገቢ ለመሆን የንብረት ገቢ ደረሰኝ /ሞዴል/19/ ያልቀረበለት መሆኑ፣

- በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት እና በተቀጽላ ሌጀር ልዩነት መኖሩ፣

- ከጽ/ቤቱ ሠራተኞች ለረጅም ዓመት ያልተወራረደ ብር 183,482.74 መኖሩ፣
- በጽ/ቤቱ ኦዲት መምሪያ በሰኔ 2 ቀን 2002 በተጻፈ ደብዳቤ ብር 1,574,134.88 በሁለት ክፍሎች ጉድለት መገኘቱን እንደተገለጸ በመጥቀስ አስፈላጊው ማጣራት ተደርጐ እርምጃ እንዲወሰድ በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ያሳሰብን ቢሆንም፤ ተገቢ እርምጃ አለመወሰዱ፤

<u>ሥራው ለመጠናቀቁ በባለሙያ ሳይረጋገጥ እና ተገቢው ርክክብ ሣይፈጸም የተፈጸመ ክፍያ</u>

የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በ2002 በጀት ዓመት በናዝሬት መልካሳ ላይ ባለ 2 ክፍል ቢሮና ባለ 3 ክፍል ማሰልጠኛ የፋይበር ተንቀሳቃሽ ቤት ለማሰራት ከደጀን አቬሽን ኢንጅነሪንግ ኮምፕሌክስ ጋር በብር 1,109,380.00 ውል ገብቶ የውሉን 50% ክፍያ ብር 554,690.22 በመፈጸሙ፤ የግንባታውን ቀጣይ ሂደት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ ይኸውም፡-

- ኤጀንሲው ሚያዚያ 8,2002 ዓ.ም ግንባታውን ከሚያከናውነው ከደጀን አቬሽን ኢንጅነሪንግ ኮምፕሌክስ ጋር በፈጸመው ውል ላይ ቀሪው 50% ብር 554,690.22 ርክክቡ እንደተፈጸመ በሶስት ቀናት ውስጥ የሚከፈል ለመሆኑ የተመለከተ ቢሆንም፣ ኤጀንሲው ግንባታው በተገቢው መንገድ ለመጠናቀቁ በቅድሚያ ባባለሙያ ሳያረጋገጥና ርክክቡ ሳይፈጸም የችሮታ ጊዜ ክፍያ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጠይቆ ቀሪውን ክፍያ በሙሉ ለደጀን አቬሽን ኢንጅነሪንግ ኮምፕሌክስ ፈጽሞ ተገኝቷል።
- በውሉ አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 6.1 መሰረት ዉሉ በተፈረመ በስድስት ሳምንት ግዜ ዉስጥ ድርጅቱ ስራውን አጠናቆ እንደሚያስረክብ ሥምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም ስራዉ ከተጀመረ ከአስራ ሰባት ወራት በላይ በኋላም ርክክብ ያልተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ሐምሌ 1997 በወጣው የግዥ መመሪያ አንቀጽ 11 ተራ ቁጥር 11.14 መሰረት ደጀን አቬሽን ኢንጂነሪንግ 10%የውል ማስከበሪያ ብር 110,938.00 እንዲያሲዝ ያልተደረገ መሆኑ ተገልጾ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በ2002 በጀት አመት ሂሳብ ሪፖርት ላይ የተገለጸ ቢሆንም ይህ ሳይፈጸም ሙሉ ክፍያው እንዲፈጸም ተደርጓል፡፡ አሰራሩ የመንግሥትን

የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ኤጀንሲው በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም ግዥ□ች የግዥ አዋጁና መመሪክው በሚ□ቅ□ዉ መሰረት እንዲ□ጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ከላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች በ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም የማስተካከያ እርምጃ ሣይወሰድባቸው ተገኝተዋል፡፡

- ይሁን እንጂ በተሰጠው የኦዲት የማሻሻያ ሃሳብ መሠረት እርምጃ አለመውሰድ አግባብ አለመሆኑን ገልፀን የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት አስተያየቶች መሠረት እርምጃ መወሰዱን በቅርብ ክትትል እንዲያደርጉ አስገንዝበናል፡፡

9. <u>ልዩ ልዩ</u>

9.1 <u>የቅጥር ደንብን ተከትሎ ያልተፈጸመ የሠራተኞች ቅጥር</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሰራተኛ ቅጥር የሚፈፅመው በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የሰራተኛ ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :

- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ፤

  በሕግ ጉዳዩች ላይ የሙያ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት እንዲሰጡ የቀጠራቸው የሕግ ባለሙያ የኮንትራትቅጥርአፈጻጸም ሁኔታ ሲገመገም፤

  - የኮንትራት ቅጥር የተፈጸመው በሙያው ብቃት ያላቸው ሌሎች ተወዳዳሪዎች እንዲወዳደሩ ሳይደረግ መሆኑን፣
  - ግለሰቡ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀጥረው የሚሰሩ መሆኑን ካቀረቡት የሥራ ልምድ ማስረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በታክስ አዋጁና ደንቡ መሰረት የሥራ ግብሩ ተቀናሽ መደረግ ያለበት በሌላ መንግሥት መሥሪያ ቤት ከሚያገኙት ደመወዝ ጋር ተዳምሮ በትርፍ ጊዜያቸው ካገኙት ገቢ ላይ መክፈል ያለባቸው ሥራ ግብር እንዲሰላ መደረግ ሲገባው ግብሩ የተቀነሰው በኤጀንሲው ከሚከፈላቸው ደመወዝ ላይ ብቻ መሆኑን፣

- የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ነሐሴ 4 ቀን 2003 ዓ.ም እና ጥቅምት 28 ቀን 2003 ዓ.ም የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ከፍተኛ ኦፊሰር I በቋሚነት ለመቅጠር ባወጣው ማስታወቂያ መሰረት ክፍት የሥራ መደቡ በፕሣ 6 ደረጃ ሰባት ዓመት የሥራ ልምድ ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጂ ለወጣው ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ አግባብነት ያለው አንድ ዓመት የሥራ ልምድ ብቻ ያላቸው ግለሰብ እንዲመዘገቡ ተደረጎ በዜሮ የሰራ ልምድ በሚጠይቅ ቦታ ላይ ማስታወቂያ ሳይወጣ እንዲቀጠሩየተደረገመሆኑን፣
- በአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጁ አንድ የህግ ባለሙያ በኮንትራት የተቀጠረ ሲሆን፣ ቅጥሩ ማስታወቂያ ሳይወጣ እና ያለውድድር የተፈጸመ መሆኑን፣

ለመገንዘብተችሏል፡፡

ከላይ በየመሥሪያ ቤቶቹ የተፈጸሙት የቅጥር አፈጻጸሞች ለጥፋት መንገድ የሚከፍቱ ከመሆኑም በላይ የሌሎች ዜጎችን ተወዳድሮ የመቀጠር መብት የሚገድቡ በመሆኑ መሥሪያ ቤቶቹ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር (የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ) ያወጣውን የቅጥር አፈጻጸም መመሪያ ተከትለው ቅጥር መፈጸም እንዳለባቸው ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 9.2 <u>የቅጥር መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመ የውጭ አገር ዜጎች ቅጥር</u>

በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 22/2/ መሰረትአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከፍተኛ ባለሙያ ለሚጠይቅ ማናቸውም ክፍት የሥራ መደብ በደረጃ፣ በዕድገት፣ በዝውውር ወይም በቅጥር ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ለማግኘት አለመቻሉን በማረጋገጥ፣ የውጭ አገር ዜጎችን በአገር ውስጥ በኮንትራት መቅጠር አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ፣

- በመንግሥት የተፈቀደ በጀት መኖሩ፣
- ተቀጣሪዎቹ በኮንትራት የሚቀጠሩበትን የሥራ መደብ የሚገልፅ የሥራ ዝርዝር መኖሩ፤

- የትምህርት ማስረጃው በሚመለከተው አካል አቻ ግምት የተሰጠው መሆኑ፣
- የሙያና የሥራ ልምድ ማስረጃው በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ መሆኑ፣
- ከሥራ ዝርዝሩና ከስምምነቱ አንጻ እንዲከፈላቸው የታሰበው ደመወዝ ልክ የሚያሟይ መግለጫ መኖሩ፣
- የኮንትራት ውል መኖሩ፣

መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ በ2002 እና በ2003 በጀት ዓመት ለ15 የቻይና እና ለ2 የኬንያ ዜጎች ለሁሉም በጠቅላላው በየወሩ 17,900.00 የአሜሪካን ዶላር በመክፈል ቅጥሩን የፈጸመው ከላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች ከተሟሉ በኋላ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ቅጥሩ እንዲፈጸም በባለሥልጣን የተፈቀደ ለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፡፡
- ቅጥሩ የተፈጸመው ያለውድድር መሆኑ ታውቋል፡፡
- በቻይና ቋንቋ የተጻፈ የትምህርት ማስረጃ ቢቀርብም፣ የትምህርት ማስረጃው እንዲተረጎም እንዲሁም በሚመለከተው አካል አቻ ግምት እንዲሰጠው አልተደረገም፡፡
- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 ክፍል አንድ አንቀጽ 5 በነዋሪ ስር ተራ ቁጥር 1 እና 2 መሰረት ተቀጣሪዎቹ ታክስ እንዲከፍሉ አልተደረገም፡፡

በመሆኑም ቅጥሩ የቅጥር አፈጻጸም መመሪያን ተከትሎ አለመፈጸሙ እንዲሁም በግብር አዋጁ መሰረትም ተገቢው ግብር እንዲከፍሉ አለመደረጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ከደንብ ውጪ የሆነ አሰራር የሌሎች ዜጎችን ተወዳድሮ የመቀጠር መብት ከመገደቡም በላይ የቅጥሩን አካሄድና አፈጻጸም ተዓማኒነት ያሳጣዋል፡፡ መሥሪያ ቤቱም ከአገልግሎቱ ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ወጪ ሊያወጣ ይችላል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ቅጥር የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ያወጣውን የቅጥር መመሪያ ተከትሎ እንዲፈጸም እንዲሁም በግብር አዋጁ መሰረት ተገቢው ታክስ እንዲቀነስ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

9.3 <u>የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የክፍያ መመሪያ መሠረት ያልተፈጸሙ</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው የክፍያ መመሪያ ቁጥር 4 ከብር 50,000.00 በላይ መ/ቤቶች የሚፈጽሙት ክፍያ በቀጥታ አቅራቢው ወይም ተጠቃሚው የባንክ ሂሣብ እንዲገባ የሚያዘውን በመተላለፉ፤

| | ብር |
|---|---|
| - የውጭ መልዕክተኞች | 4129,735.31 |
| - የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር | 121,775.00 |

የውጭ መልዕክተኞ ለሰነአ የትብብር ፎረም በቼክ የሀገር መከላያ ሚ/ር የኢትዮጵያ አየር ኃይል በጥሬ ገንዘብ ከፍለው መገኘታቸውን በመግለጽ በመመሪያው መሠረት ክፍያዎች አለመፈጸሙ በርካታ ገንዘብ ግለሰቦች እጅ ሊገባና ለብክነት ሊጋለጥ እንደሚችል በመግልጽ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

መ/ቤቶቹ በላኩት መልስ ለወደፊቱ በመመሪያው መሠረት እንደሚፈጽሙ ተገልጿል፡፡

9.4 <u>በተመሳሳይ ፊርማዎች ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት በቅድሚያ ለምርጫ በሰነድ ተሰጥቶ የተወራረዱ ተሰብሳቢ ሂሣቦችኦዲት ሲደረግ ብር 183,950.00 ከ32-772 ሰዎች ክፍያ በተመሳሳይ ፊርማ ተፈጽሞ ሠነድ የወሰዱት ሰዎች አወራርደው ካቀረቡት ማስረጃ መረዳት መቻሉን በመግለጽ፣ ወጪዎች ሲወራረድ የማስረጃዎች አግባብነት መጣራት እንደሚገባ በናሙና ታይቶ ከላይ የተገለጸው ሁኔታ እንዲጣራ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

## የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የስራ አመራር ሪፖርት

### መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 መሰረት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዋናውን መ/ቤት እና ከፍተኛ ግብር እና ታክስ የሚሰበስቡ የዘጠኝ

ቅ/ጽ/ቤቶች የ2003 በጀት ዓመት የሂሳብ እንቅስቃሴ ኦዲት ተደርጓል::

የሂሳብ ሪፖርቶቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

ለዋናው መ/ቤት የተላኩ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ በሚሰጥና መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት ማድረግና በባለስልጣን መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

በኦዲቱም መሰረት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ቀጥለው ቀርበዋል::

### I የኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋና መ/ቤት የ2003 በጀት ዓመት የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

II የገቢ ሂሳብ የገቢ እቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ

በ2003 በጀት ዓመት በባለስልጣኑ እያንዳንዱ የገቢ ሂሳብ ለመሰብሰብ በታቀደው በጀት መሰረት ገቢው መሰብሰቡ ሲጣራ ከታወጀው በጀት በላይ ብር 2,082,261,660.70 መሰብሰቡ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 31 ቀርቧል/

## 1. የአገር ውስጥ ሂሳብን በተመለከተ

### 1.1 ያልተሰበሰበ ሂሳብን በተመለከተ

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 መሰረት ግብር ከፋዮች በህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ሂሳባቸውን የሚያሳውቁና የሚፈለግባቸውን ግብር በትክክል የከፈሉ እንዲሁም ተገቢው ቅጣት እና ወለድ እንዲከፍሉ የተደረገ መሆኑ ሲጣራ:-

በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት

- ሶስት ግብር ከፋዮች በተለያዩ ጊዜያት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ጊዜውን በማሳለፍ የተቀናሽ ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑና በመመሪያው መሰረት የማጣራት ስራ ሳይከናወን ብር 2,328,391.96 መቀናነሱ፣ሁለት ግብር ከፋዮች በግብዓት ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማቀናነሻ ቅፅ ሣይቀርብ ብር 14,469,511.38 የተጨማሪ እሴት ታክስ የተቀነሰ መሆኑ፣
- ከሶስት ግብር ከፋዮች ሊሰበሰብ የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ መቀጫውንና ወለድ ጨምሮ ብር 3,958,610.51 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
- ስድስት ግብር ከፋዮች ያለባቸውን ንግድ ትርፍ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ቅድመ ገቢ ግብር ብር 22,626,766.53 ዘግይተው ያሳወቁ ቢሆንም፣ በአዋጁ መሰረት ቅጣትና ወለድ እንዲከፍሉ ያልተደረጉ መሆኑ፣
- ከአንድ ግብር ከፋይ በ2002 በጀት ዓመት የንግድ ትርፍ ላይ መቀነስ የማይገባው የ1996 በጀት ዓመት ኪሳራ ብር 2,011,596.84 በመቀነሱ ገቢ መሆን የሚገባው የገቢ ግብር ብር 603,479.05 ብር ሳይሰበሰብ ቀርቷል፡፡
- ከሁለት ድርጅቶች ከቴክኒክ አገልግሎት ክፍያዎች እና የትርፍ ድርሻ ላይ ያልተሰበሰበ የገቢ ግብር ብር 1,714,022.68 ተገኝቷል፡፡
- የስጦታ ወይም እርዳታ እና የመዝናኛ ሂሳብ በወጪ በመያዙ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 103,370.64 ፣

- ከአንድ ግብር ከፋይ በገቢ ግብር ከፋይ አዋጅ 286/94 አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀፅ ከ 1- 3 መሰረት ተገቢው ማጣራት ሳይደረግ በ2002 የበጀት ዓመት የትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ብር 4,153,368.72 የማይሰበሰቡ እዳዎች ወጪ ያካተተው ሂሳብ ተቀባይነት እንዲኖረው መደረጉ፣

- አንድ ግብር ከፋይ ዲክሌር ያደረገው የምርት ዋጋ ያነሰ በመሆኑ ምክንያት ያልተሰበሰበ የኤክሳይዝ ታክስ ብር 9,000.00፣

- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረቡ ግብር ከፋዮች ላይ 30% የቅድመ ታክስ መሰብሰብ ሲገባ 2% በመሰብሰቡ ምክንያት ብር 5,575,843.37 አለመሰብሰቡ ተረጋግጧል፡፡

- ግብርከፋዮች በተጨማሪ እሴትታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በንግድ ትርፍ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው ሽያጭ የሚበልጥ በመሆኑ ብር 2,421,843.72 ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር መኖሩ ታውቋል፡፡

- ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 1,256,618.75 መኖሩ ታውቋል፡፡

- አንድ የግብር ከፋይ በመመሪያ ቁጥር 30/2001 መሰረት በገቡት የክፍያ ስምምነት መሰረት በወቅቱ ያልከፈሉት ብር 8,006,751.00 ታክስ፣ ቅጣትና ወለድ መኖሩ ታውቋል፡፡

<u>በምስራቅ አዲስ አበባ</u>

- ሶስት ግብር ከፋይዮች ውዝፍ የንግድ ትርፍ፣ የቅድመ ታክስ እና የኤክሳይዝ ታክስ በድምሩ ብር 1,279,307.00 እንዲሰበሰብ የተወሰነ ቢሆንም፣ አቤቱታው ውሳኔ ያላገኘ በመሆኑ ገንዘቡ ገቢ ያልሆነ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- አምስት ግብር ከፋዮች ያለባቸውን የንግድ ትርፍ ግብር ብር 1,509,070.94 በወቅቱ ባለማሳወቃቸው ምንም አይነት ወለድም ሆነ መቀጫ እንዲጣልባቸው አልተደረገም፣ ከዚህ ውስጥ አንድ ግብር ከፋይ ያሳወቀው የ2000 በጀት ዓመት ገቢ ግብር ቢሆንም ሲስተሙ ላይ

የተመዘገበው የ2002 ገቢ እንደሆነ ተደርጎ በመመዝገቡ ቅጣት እና ወለድ ያልተጣለበት መሆኑ፣

- ሶስት የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋዮች ወቅቱን ጠብቀው ያላሳወቁ መሆኑና ዘግይተው ሪፖርት በማድረጋቸው ምክንያት በፋይላቸው ውስጥ ቅጣትና ወለድ ስለመክፈላቸው ማስረጃ አልተገኘም መኖሩ ተረጋግጧል፡፡
- የቅጣት፣ ስጦታ ወይም እርዳታ እና መዝናኛ ሂሳብ በወጪ በመያዙ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 29,635.84፣
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረቡ ግብር ከፋዮች ላይ 30% የቅድመ ታክስ መሰብሰብ ሲገባ 2% በመሰብሰቡ ምክንያት ብር 788,125.68 አለመሰብሰቡ ተረጋግጧል፡፡
- በምስራቅ አዲስ አበባ14 ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በንግድ ትርፍ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው ሽያጭ የሚበልጥ በመሆኑ ብር 3,410,480.18 ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር መኖሩ፣
- በምስራቅ አዲስ አበባ 34 ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 128,333,794.90 መኖሩ ታውቋል፡፡

በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት

- የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍሉ የታክስ ውሣኔ ደርሷቸው ክፍያ ባልፈጸሙ ወይም በውሣኔው ላይ ቅሬታ ወይም ይግባኝ ካላቀረቡት ድርጅቶች ላይ ያልተሰበሰበ ግብር በድምሩ ብር 9,579,981.84፣
- በአዋጁ መሰረት ያልተሰበሰበ የቅድመ ግብር ክፍያ ሂሳብ በድምሩ ብር 5,972.58 ተገኝቷል፡፡

ከመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት

- ሶስት ግብር ከፋዮች የስፖርት ወጪ እና አንድ ግብር ከፋይ ደግሞ የካፍቴሪያ ወጪ በመቀነሱ ሊሰበሰብ የሚገባው ታክስ ብር 1,469,519.44 የንግድ ትርፍ ግብር አለመሰብሰቡ፣

- ሶስት ድርጅቶች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር46,004,511.73መኖሩ ታውቋል፡፡

- አንድ ድርጅት የእፎይታው ጊዜ እንዲራዘምለት የጠየቀው የተፈቀደለት የእፎይታ ጊዜ ከተጠናቀቀ ከሁለት ዓመታት በኋላ ሆኖ ሳለ የእፎይታ ጊዜ የተፈቀደው ደግሞ ወደኋላ ሁለት አመት ተመልሶ በመሆኑ ውሳኔው ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባው ግለሰቡ ጥያቄ ካቀረቡበት ቀን ጀምሮ ላሉት ሁለት ዓመታት መሆን ሲገባው በሁለቱ አመታት በተገኘው ትርፍ ላይ የገቢ ግብር እንዳይከፍሉ የተደረገ በመሆኑ ድርጊቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ድርጅቱ የገቢ ግብር እንዳይከፍል የተደረገው አለአግባብ በመሆኑ ሊሰበሰብ የሚገባው የሁለት ዓመታት የንግድ ትርፍ ገቢ ብር 7,479,841.39 መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

- ✓ ከ3 ግብር ከፋዮች ብቻ በወቅቱ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ብር 2,375,228.00 እንዲሁም ወለድ እና ቅጣት ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
- አንድ ግብር ከፋይ በተለያዩ ወራት ምርቱን (output) ሲያስታውቅ በስሌት ስህተት ምክንያት ያልተሰበሰበ ኤክሳዝ ታክስ ብር 9,364.01፣

- በግብዓት ላይ ለተፈጸመ ግዢ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ወይም ዲክላራሲዮን አባሪ በተደረገ ዝርዝር ሠንጠረዥ ላይ ተሞልቶ ከኦሪጅናል የግዥ ደረሰኝ ወይም ዲክላራሲዮን ጋር ተያይዞ የማይቀርብ መሆኑ፣

- 1 ግብር ከፋይ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በንግድ ትርፍ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት

ታክስ ላይ የተመለከተው ሽያጭ የሚበልጥ በመሆኑ ብር 109,620,687.42 ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር መኖሩ፣

- አራት ድርጅቶች  በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር528,516,247.33 መኖሩ ታውቋል፡፡

በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት

- አንድ ግብር ከፋይ ከድርጅቱ ስራ ጋር የማይገናኝና ለመዝናኛ አገልግሎት የተከፈለ ሂሳብ ተቀናሽ በመደረጉ ብር ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 53,571.28 መገኘቱ፣
- ሁለት ድርጅቶች በግብአት ላይ የከፈሉትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 1,582,258.25 በትክክለኛው ጊዜ ያላሳወቁ መሆኑ እና በወቅቱ ባለማሳወቃቸው ተገቢው ቅጣት ያልተጣለባቸው መሆኑ፣
- መሰብሰብ ያለበት ገቢ ወቅቱን ጠብቆ ካልተሰበሰበ ከቆይታ ብዛት የመንግሰት ገቢ መሰብሰብ ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል::

  በመሆኑም በገቢ.ግብርአዋጅ 286/1994፣ ደንብ ቁጥር 78/94 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/2002 መሰረት ሊሰራ የሚገባው መሆኑን እና የተጨማሪ የታክስ ውሣኔ እና የታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ የደረሰው ሰው በውሣኔው ላይ ቅሬታ ሲያቀርብ ቅሬታ በወቅቱ ውሳኔ ካልተሰጠው ገቢው በወቅቱ ሊሰበሰብ አይችልም፡፡ በሌላም በኩል ቅሬታ ባላቀረቡና ሊከፍሉ የሚገባቸውን በወቅቱ ባልከፈሉት ላይ ደግሞ በአዋጁ መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ ሊሰበሰብ የሚገባውን የመንግስት ገንዘብ መሰበስብ ይኖርበታል፡፡ ይህንኑም ለመከታተል እና አፈጻጸሙንም በየጊዜው ለመገምገም የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት የመንግስት ገቢ በአዋጁ መሰረት በወቅቱ እንዲሰበሰብ መደረግ አለበት፡፡

- ያልተሰበሰበው ወለድና መቀጫ በአዋጁ መሰረት ተሰልቶ ከሚመለከተው ግብር ከፋይ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት

እንዳይፈጸም ታክስና ግብሩ የተሰበሰበበት ጊዜ እየተጣራ ወቅቱን ጠብቀው ባልከፈሉት ላይ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

- በባለስልጣን መ/ቤቱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ማንዋል መሰረት በግብርከፋዮችየሚቀርበው የሂሳብ መግለጫ ሁሉንም መስፈርት ስለማሟላቱ ማረጋገጫ ማግኘት አስፈላጊ በመሆኑ የታክስ አሰስመንት ቡድንም የሂሳብ መግለጫውን በሚያጣራበት ወቅት ዝርዝር ማብራሪያ እንዲቀርብ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- እያንዳንዱ ግብር ከፋይ በትክክለኛው ጊዜ ሂሳቡን እያሳወቀ መሆኑን የሚረጋገጥበት ስርአት መዘርጋት ያለበት መሆኑንና ከአቅርቦት ጋር በተያያዘ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲቀናነስለት ጥያቄ ሲቀርብ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅና ደንብ ላይ በተጠቀሰው መሰረት አስፈላጊው ማስረጃ የቀረበ መሆኑ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በኩል ሊጣራ ይገባል፡፡
- ግብር ከፋዮች የትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ሲያቀርቡ ቀደም ብሎ ካሳወቁት ሽያጭ ጋር የሚገናዘብበት አሰራር ቢዘረጋ የመንግስት ገቢ በወቅቱ ሊሰበሰብ የሚችልበትን እድል ስለሚፈጥር አሰራሩ ሊሻሻል ይገባል፡፡
- ፍቃዱ መራዘም ያለበት የእፎይታ ጊዜውን እንደጨረሰ መሆን ሲገባው እንድ ድርጅት ፍቃዱ ካለቀ ከሁለት አመት በኃላ ወደ ኃላ በመመለስ ካገኘው ገቢ ላይ የንግድ ትርፍ ከመክፈል ይልቅ እንዳይከፍል ማድረጉ አግባብነት የሌለውና የተጠየቀበት ጊዜ እና የተፈቀደበት ጊዜ የማይገናኝ ስለሆነ እና ህግ እንኳን የሚሰራው ከወጣበት ጀምሮ እንጂ ወደ ኋላ ተመልሶ ባለመሆኑ ድርጅቱ የሁለት አመት የስራ እንቅስቃሴ የንግድ ግብር ሊከፈልበት ይገባል፡፡
- የተሰጠውን አስተያየት ሁሉም ጽ/ቤቶች እንደሚቀበሉት በመግለጽ፤ የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ሊቀነሱ የማይገባቸውን ወጪዎች በማጣራት ተገቢውን እርምጃ ወስዶ ብር 53,571.28 የሰበሰበ መሆኑን፣
- ዘግይተው ማስታወቂያ የሚያቀርቡ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ ለሀላፊ እየቀረበ በተፈቀደው መሰረት የዘገዪ ግብር ከፋዮች የተሰተናገዱ መሆኑ

የተገለጸ ቢሆንም፣ ለበላይ ሀላፊ ስለመቅረቡ በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ አልቀረበም፡፡

## 1.2 በስሌት ስህተት ምክንያት ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር

- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤትአንድ ግብር ከፋይ የእፎይታ ጊዜ ካለቀ በኋላ ሊከፍል የሚገባው የንግድ ትርፍ ግብር ብር 13,439,382.23 መሆን ሲገባው፣ ዲክሌር የተደረገውና የተከፈለው ብር 12,489,129.82 በመሆኑብር 950,252.41 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ አንድ ግብር ከፋይ የ2002 በጀት ዓመት የትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የተሸጡ እቃዎች ዋጋ ብር 51,435,182.68 መሆን ሲገባው ብር 55,423,057.51 ተብሎ በመያዙ ምክንያት ያልተሰበሰበ ታክስ ብር 1,196,362.45፣ አንድ ግብር ከፋይ ደግሞ መሰብሰብ ከነበረበት የንግድ ትርፍ ላይ ብር 311,819.83 ያልተሰበሰበ በድምሩ ብር 2,458,434.69 አለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡
- ምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት አንድ ግብር ከፋይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ቅፅ ላይ በተፈጠረ የሂሣብ ስሌት ስህተት ምክንያት ያልተሰበሰበታክስ በብር 6,999.00፣ የሁለት ግብር ከፋዮች የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር ስሌት በትክክል ባለመሰላቱ ምክንያት ብር 330,967.10 አለመሰብሰቡ እና አንድ ግብር ከፋይ ደግሞ የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር ላይ የቋሚ ዕቃ ሽያጭ በገቢው ላይ ተደምሮ ግብር መሰላት ሲኖርበት ተቀንሶ በመሰላቱ ምክንያት ያልተሰበሰበ ብር 39,130.20 በድምሩ ብር 377,096.30 መገኘቱ፣
- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት አምስት ግብር ከፋዮች የተሸጡ እቃዎች ዋጋ መሆን ከሚገባ በላይ ከፍ ተደርጎ በመያዙ ምክንያት ብር 6,695,990.83 ያልተሰበሰበ የገቢ ግብር መገኘቱ፣
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ሶስት ግብር ከፋዮች በሀብት እና እዳ መግለጫ ላይ የተመለከተው የቆጠራ ውጤት በማነስ ወደ ትርፍና ኪሣራ የሂሣብ መግለጫ ላይ በመተላለፉ ሊሰበሰብ የሚገባው የንግድ ትርፍ በብር 32,657,970.25 አንሷል፣ ከሁለት ግብር ከፋዮች በ2002 በጀት ዓመት የሀብት ኪሣራ መግለጫ ላይ የተመለተው ከወጪ ቀሪ ሂሣብ የቆጠራ ውጤት ባለመካተቱ በብር 59,539,341.05 የሚያንስ መሆኑ እና አንድ ግብር ከፋይ በ2002 በጀት ዓመት Ending inventory ከወጪ ቀሪ ወደ ቀጣይ

ዓመት ከፍ በማለቱ በብር 14,082.00 የንግድ ትርፍ በድምሩ 92,222,393.30 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ይህም ከግብር ከፋዩ መሰብሰብ ያለበትን ግብር እንዳይሰበሰብ ያደርጋል::

በመሆኑም የግብር ከፋዮች የሚያቀርቡት የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛነቱ የሚረጋገጥበት ስርዓት ሊጠናከር ይገባል፡፡ እንዲሁም ያልተሰበሰበው ሂሣብ ከሚመለከተው አካል እንዲሰበሰብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 1.3 <u>የተሟላ ማስረጃ ባለመገኘቱ የገቢውን ትክክለኛት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀፅ 70 እና በመንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃ መሰረት ማስረጃዎች በተገቢው ሁኔታ መጠበቃቸውን እና በገቢ የተመዘገቡ ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት የዘጠኝ የግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ የሂሳብ ማስታወቂያው (ዲክላራሲዮን) እና ግብር የተከፈለበት የገቢ ደረሰኝ ባለመገኘቱ፣
- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤትከ10 ግብር ከፋዮች የተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ብር 1,754,836.02፣ ከ9 ግብር ከፋዮች የተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 1,802,074.60፣ ከ4 ግብር ከፋዮች ከቅድመ ታክስ ገቢ ብር 1,678,967.54 እና ከ2 ግብር ከፋዮች የተሰበሰበ የኤክሣይዝ ታክስብር 120,209.01 በድምሩ ብር 5,356,087.17 በግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ የግብር ማሣወቂያ ዴክላራሲዮን እና ገንዘብ የተከፈለበት ደረሰኝ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ፣ እንዲሁም የስምንት የግብር ከፋይ ፋይሎች ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ከሶስት ግብር ከፋዮች ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የቅድሚያ ግብር ተቀናሽ ብር 3,395,473.92 ትክክል ስለመሆኑ የሚያረጋግጥበት ማስረጃ እና ጽ/ቤቱም ትክክለኛነቱን ያረጋገጠበት ማስረጃ ለኦዲት አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም የ2002 በጀት ዓመት የንግድ ትርፍ ትክክል ስለመሆኑ በሚጣራበት ወቅት ከበጀት ዓመቱ የንግድ ትርፍ ውስጥ ብር 837,658.46 የዓመቱ ዲፈርድ ታክስ ተብሎ

በሂሳብ መግለጫው ውስጥ ከታክስ ላይ ተቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም የሆነው የተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የታክስ ስርዓቱን ተከትሎ ባለመሆኑ ሲሆን የግብር አሰባሰብ የስራ ሂደትም ድርጅቱ ማብራሪያ እንዲሰጥ አላደረገም፡፡ በመሆኑም የሂሳቡን ምንነት ለማወቅና በእርግጥም ሊቀነስ ይገባው የነበረ ሂሳብ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት</u>

- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት አስራ ስድስት ግብር ከፋዮች ያቀረቡት ማስረጃ በፋይላቸው ውስጥ ባለመገኘቱ በተቀናጀ የመንግስት ታክስ አስተዳደር ስርዓት ላይ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ ብር 50,131,318.25፣ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- አንድ ግብር ከፋይ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ዲክላራሲዮን ላይ ያቀረበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳብ ብር 12,100,842.46 ሲሆን ፣ ከዲክላራሲዮኑ ጋር ተያይዞ የቀረበው ዝርዝር ሰንጠረዥ ደግሞ ሊሰበሰብ የሚገባው ብር 18,562,709.29 መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ በሁለቱ መካከል የብር 6,461,866.85 ልዩነት የሚታይ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማጣራት አለመቻሉ፣
- አንድ ግብር ከፋይ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 ክፍል 3 አንቀጽ 8(ለ) መሰረት ታክስ በሚገባ ለመሰብሰብ አስፈላጊ የሆኑ የወርሃዊ ምርቱን መጠን የሚገልጽ ማስረጃ ባለማቅረቡ ሊሰበሰብ የሚገባው ግብርናታክስ በትክክል መሰብሰቡን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- አንድ ግብር ከፋይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተፈፀመውን የግብዓት ጥቅል ዋጋ ሳይገለፅ ከተጨማሪ እሴት ታክስ የተቀነሰውን የታክስ መጠን ብቻ የሚያሳይ ዝርዝር በማቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- አብዛኛቹ ግብር ከፋዮች ሌሎች ወጪዎችን /Other deductions/ በቅጹ ላይ የማይሞሉ በመሆኑ ተቀናናሽ ሂሳቦች ትክክለኛ መሆናቸውን እና የተሰበሰበውም ገቢ ትክክለኛ መሆኑን፣ እንዲሁም መቀነስ የማይገባቸው ወጪዎችም አለመቀነሳቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በኦዲቱ ወቅቱ

ከታዩት ፋይሎች ውስጥ ከሁለት ግብር ከፋዮች 4,002,118.52 በጥቅሉ ሌሎች ወጪዎች ተብሎ ተሞልቶ ተገኝቷል::

ይህም አሰራር ግብር ከፋዩ የከፈለባቸውን ደረሰኞች በአግባቡ አለመያዛቸው የተሰበሰበው የመንግስትን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀፅ 10 (3) መሰረት ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ የሚሰበስብ ገንዘቡን የተቀበለበትን ዶክመንቶች በአግባቡ መያዝ ያለበት በመሆኑ የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ ቅፅ አስፈላጊው ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ የግብር ከፋዩ ማህደር ወደ ሚገኝበት ክፍል ሲተላለፍ የርክክብ ሂደቱን በማቀላጠፍ እና ግብር ከፋዮች የሚፈለግባቸውን ሂሳብ መክፈላቸው የሚረጋገጥበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

## 1.4 የኤክሳይዝ ታክስ በወቅቱ ስለማሣወቃቸው ማስረጃ ያልቀረበለት፣

በኤክሳይዝ ታክስ በአዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 2ሀ (2) መሰረት ታክስ በወቅቱ እና በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ሶስት ግብር ከፋዮች ሂሳባቸውን በአዋጁ መሰረት ስለማሳወቃቸው የቀረበ ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም በላይ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ አማካኝነት አስፈላጊው እርምጃ አለመወሰዱ እንዲሁም በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤትስድስት የኤክሣይስ ግብር ከፋዮች በየወሩ ማሣወቃቸው ለማረጋገጥ ሲሞከር ሪፖርት ስለማድረጋቸው በፋይሎቻቸው ውስጥ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

አሰራሩ የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያበረታታና ለህገ ወጥ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

በመሆኑም የኤክሳይስ ታክስ ግብር ከፋዮች በወቅቱ የመንግስትን ገቢ አሳውቀው እንዲከፍሉ ክትትል ማድረግ ይገባል፡፡

## 1.5 ግብራቸውን የማያሳውቁ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ /Non Filers/

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 አንቀጽ 66 (1) እና በአንቀጽ 86 መሰረት ግብር ከፋዮች በህግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢያቸውን ማሳወቃቸውንና በህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላሳወቀ ግብር ከፋይ ላይ መቀጫ እንደሚጣል መደረጉ ሲጣራ፡-

- በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት 21 ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በአዋጁ መሰረት ያላሳወቁ ቢሆንም፣ በነዚህ ግብር ከፋዮች ላይ በህጉ መሰረት እርምጃ ስለመወሰዱ የሚገልጽ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ማግኘት አልተቻለም፡፡
- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ዘጠኝ ግብር ከፋዮች የ2002 የግብር ዘመን ገቢያቸውን በወቅቱ ያላሳወቁ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በአዋጁ መሰረት ወቅቱን ጠብቆ አስፈላጊውን ማጣራት አለማድረግ በወቅቱ ሊሰበሰብ የሚገባው የገቢ ግብር መሰብሰብ ከማይችልበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል::

በመሆኑም ግብራቸውን በወቅቱ ባላሳወቁት ግብር ከፋዮች ላይ አስፈላጊውን ማጣራት እና ክትትል በማድረግ በአዋጁ መሰረት ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢም ሆነ ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለማሳወቃቸው ሊከፍሉ የሚገባቸውን መቀጫ እንዲከፍሉ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል ግብራቸውን በወቅቱ ያላሳወቁ ግብር ከፋዮች መረጃ ተቀነባብሮ መያዝ ያለበት ሲሆን፣ በዚሁም መሰረት ተገቢው ክትትል እየተደረገ የመንግስት ገቢ በወቅቱ የሚሰበሰብበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

## 1.6 <u>የገንዘብ ትልልፍ ሂደትን በተመለከተ</u>

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 52 እና 53 እንዲሁም ይህንኑ ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር 22/2001 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 (ሠ) መሰረት የምስራቅ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሰበሰበውን የክልል መንግስታትን ገቢ ወደ ባለሥልጣኑ ዋናው መ/ቤት የአደራ ሂሣብ/አካውንት ወሩ ባለቀ በሚቀጥለው 10 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ማስተላለፉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከቅድሚያ ግብር ክፍያ የተሰበሰበ ግብር መመሪያው በሚያዘው ጊዜ ውስጥ ወደ ዋና መ/ቤት የማይተላለፍ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
ይህም የክልልመንግስታትናመስተዳድሮችገንዘቡ በወቅቱ ካልተላከላቸው በእቅድ የያዙዋቸው ስራዎች ሊስተጓጎሉ ይችላሉ፡፡

በመሆኑም በምላሹ እንደተጠቀሰው አዋጁ እና መመሪያው የማይጣጣሙ ከሆነ መመሪያው ከአዋጁ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ የሚገባ ሲሆን፣ የግብር አሰባሰብ እና ክትትል የሥራ ሂደትም አሰራሩ ሊቀላጠፍ የሚችልበትን ስልት በመቀየስ

የክልሎችን ገቢ በወቅቱ መለየት እና በመመሪያ መሰረት ገንዘቡን ለዋናው መ/ቤት የአደራ ሂሳብ አካውንት ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

## 2. የገቢ እቃዎችን (Import) ቀረጥና ታክስን በተመለከተ

### 2.1 ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.Code) እና የጉምሩክ ስነስርዓት ኮድ (CPC) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2009 አንቀጽ 45(1) መሰረት ዕቃዎች፡-

ሀ) በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.Code) ባለመመደባቸው ምክንያት

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤትብር 1,674,198.18
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ብር 652,884.58 ፣
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር472,606.80
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 97,101.58፣

ለ) በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት አንድ ድርጅት በትክክለኛው የጉምሩክ ስነስርዓት ኮድ (CPC) ባለመስተናገዱ ምክንያት ያለአግባብ ሁለተኛ መደብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመደረጉ ብር 16,228.06 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ

በድምሩ ከአራቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 2,913,019.20 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

ለዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር ካልተመደቡ እና ድርጅቶችም በትክክለኛው የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ (CPC) ካልተስተናገዱ መንግሥት ሊሰበስብ የሚገባውን ገቢ እንዲያጣ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም አስመጪዎችም በእኩል ባለመስተናገዳቸው ምክንያት የገበያ ውድድሩ ሚዛናዊ ላይሆን ይችላል፡፡

በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲወሰድ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የስራ አመራር አስተያየታችንን የሰጠን ሲሆን የባለስልጣን መ/ቤቱም ይህን በተመለከተ በሚመለከተው የስራ ክፍል አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ አስተያየት</u>

- የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራር ካልተሰበሰበው ተጨማሪ ሂሳብ ውስጥ ብር 40,317.33 የሰበሰበ ሲሆን ብር 1,536,129.95 የሚመለከታቸው

አስመጪዎችና ትራንዚተሮች እንዲከፍሉ ደብዳቤ የተጻፈላቸው መሆኑንና ክትትልም እየተደረገ መሆኑን የስራ አመራሩ በሰጠው ምላሽ ገልጿል::

- የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት ከአስር ዲክላራሲዮን ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ብር 187,722.07 የሰበሰበ ሲሆን ለተቀሩት ዲክላራሲዮኖችም መጠይቅ ወጥቶላቸው ተገቢው ክትትል እየተደረገ መሆኑን በመግለጽ በዲክላራሲዮን ቁጥር C-11156/11 የተመዘገበው Carter EP ግን በታሪፍ ቁጥር 27101990 መመደብ እንዳለበት በመግለጽ የተጠየቁት ተጨማሪ ሂሳብ በድጋሚ እንዲታይላቸው የድርጅቱ ሀላፊ በደብዳቤ የገለጹ በመሆኑ ጉዳያቸው እየታየ የሚገኝ መሆኑን የስራ አመራሩ ከሰጠው ምላሽ ለማወቅ ተችሏል::
- የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ከተጠቀሰው ያልተሰበሰበ ሂሳብ ውስጥ ብር 103,370.67 ተቀባይነት ያለው በመሆኑ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ሂሳቡን የሚሰበስቡ መሆኑን፣ የባጃጅ መለዋወጫን በተመለከተ ከዋናው መ/ቤት በተላለፈልን መመሪያ መሰረት ሂሳቡ በድጋሚ ታይቶ ሊሰበሰብ የሚገባው ሂሳብ ካለ እንዲሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በታሪፍ ቁጥር (HS Code) ስህተት የተገኙት ቀሪ ሂሳቦች ትክክል እና ተገቢ መሆናቸውን በመግለጽ በተገኘው የኦዲት ግኝት መሰረት ለአስመጪዎች ቀሪ ሂሳቡን እንዲከፍሉ የቀሪ ሂሳብ መጠየቅ የወጣላቸው መሆኑን የስራ አመራሩ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል::

## 2.2 በትክክለኛው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ያልተስተናገዱ ድርጅቶችን በተመለከተ

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ምዕራፍ ሶስት አንቀፅ 39፣ ንዑስ አንቀፅ 1ሀ እና አንቀፅ 37፣ ንዑስ አንቀፅ 1(ሐ) እንዲሁም በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት፣ አዘገጃጀት፣ ስርጭት አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 10/1996 እና ይህን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር 2/1996 መሰረት ድርጅቶች መስተናገዳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

- ✓ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በድምሩ ብር 392,555.35
- ✓ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በድምሩ ብር 143,229.73

በአጠቃላይ ከሁለቱም ቅ/ጽ/ቤቶች በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ድርጅቶቹ ባለመስተናገዳቸው ምክንያት ብር 535,789.08 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

የልዩነቱ መንስኤም በአንዳንድ ሰነዶች ላይ ለቀረጥ ማስከፈያነት የተወሰደው ዋጋ ከግብይት ዋጋው ያነሰ (በዋጋ ሰነዱ ላይ ከተገለጸው ዋጋ በታች) መሆኑ፣ ዋናው መ/ቤት ዋጋ ተጠይቆ ከዋናው መ/ቤት በመጣው ዋጋ መሰረት ባለመሰራቱና ለቀረጥ ማስከፈያነት መካተት ያለባቸው ሁሉም ወጪዎች አለመካተታቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::

በመመሪያው መሰረት ካልተሰራ ወደ ሀገር ውሰጥ ከሚገቡ ዕቃዎች ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

በመሆኑም በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ድርጅቶች ባለመስተናገዳቸው ምክንያት ያልተሰበሰበ የቀረጥ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች እንዲሰበሰብና የችግሩን መንስኤም ለመቅረፍ የሚመለከተው አካል አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርግ እንደሚገባ ለስራ አመራሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

## 2.3 በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ግኝት መሰረት ሳይሰበሰብ ስለተገኘው ሂሳብ

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ወደ አገር ለገባ ወይም ከአገር ለወጣ ዕቃ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሊከፈል በሚገባው ልክ መሆኑ የሚጣራ መሆኑንና ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ ሲኖር በወቅቱ እንዲሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት መሰረት በልዩነት የሚፈለግ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ሂሳብ ብር 9,984,109.98 ለንብረት ያዥ ኮሚቴ (ለሲዠር) የተላለፈ ቢሆንም፣ እርምጃ ሳይወሰድ ከሶስት ወራት እስከ ስምንት ወራት መዘግየቱ ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት መሰብሰብ የነበረበት ብር 9,984,109.98 ቀረጥና ታክስ ሳይሰበሰብ ረዥም ጊዜ ሆኖታል፡፡

የመንግስት ገቢ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡ አሰራሩም ህገወጥነት እንዲበረታታ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን የማጣራት ውጤት መሰረት ሂሳቡ እንዲሰበሰብ ለንብረት ያዥ ኮሚቴ ተላልፎ በወቅቱ ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ

ብር 9,984,109.98 በአዋጁ መሰረት ተገቢው እርምጃ ተወስዶ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች መሰብሰብ እንዳለበት ለስራ አመራሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

2.4 ዲክሌር ሳይደርግ ወደ አገር ውስጥ በገባ እቃ ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖር

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመባቸው ዕቃዎች ወደ ጉምሩክ ክልል ከገቡ የኮትሮባንድ ወንጀል በመሆኑ በህጉ መሰረት እርምጃ መወሰዱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በዲ/ዮን ቁጥር C-430/2011 ወደ ሃገር ውስጥ በመግባት ደወሌ ኬላ እንዲራገፍ የተደረገው ውድቅዳቂ ብረት ተወርሶ ወደ መጋዘን ገቢ መደረግ ሲገባው፣ እቃው በመጣበት ወቅት የአስመጪነት ፈቃድ የሌላቸው ግለሰብ ቀረጥና ታክስ በመክፈል ማስገባት እንዲችሉ ስለተፈቀደላቸው ካለምንም ቅጣት እንደ አዲስ የጉምሩክ ስነ ስርዓትን ካሟሉ በኋላ እቃውን እንዲያወጡ መደረጉ ታውቋል::

ይህ አሰራር ህገ ወጥነት እንዲስፋፋ ሊያደርግ ስለሚችል በህገ ወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ የተገኘ እቃ በህጉ መሰረት ሊወረስ እና ድረጊቱንም ሲፈጽም የተገኘው አካል ተገቢው እርምጃ ሊወሰድበት ሲገባ እንደ ህጋዊ ነጋዴ/አስመጪ ተቆጥሮ እቃው በቀረጥ እንዲገባ መደረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አሰራሩ ህገወጥ ነጋዴዎችን ሊያበረታታ ስለሚችል መስተካከል እንዳለበት ለስራ አመራሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

2.5 የተሟላ የዋጋ ሰነድ ሳይቀርብ የተስተናገደ ድርጅት መኖሩ

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 13(1) መሰረት ለባለስልጣኑ የጉምሩክ ዲክላራሲዎን በሚቀርብበት ጊዜ የዋጋ ሰነድ ዋና ቅጂ በአባሪነት መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል:: ከዚህ አንጻር የዋጋ ሰነድ እየቀረበ በዋጋ ሰነዱ መሰረት ቀረጡ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በዲክላራሲዮን ቁጥር C-868/11 ለተሰበሰበው ብር 106,532.83 የተሟላ የዋጋ ሰነድ ሳይቀርብ ቀረጥና ታክሱ መሰብሰቡን፣ እንዲሁም በዲክላራሲዮን ቁጥር C-4977/10 ለተሰበሰበው ብር 1,626,359.74 በእቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ (packing list) ላይ ዝርዝር የእቃው አይነት የተገለጸ ቢሆንም፣ በዋጋ ሰነዱ ላይ ግን የእያንዳንዱ እቃ ዋጋ ያልተገለጸ በመሆኑ ምክንያት እያንዳንዱ እቃ በትክክለኛው የታሪፍ ምጣኔ መሰረት ቀረጡ ያልተሰበሰበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ይህም ባልተሟላ ማስረጃ ቀረጥ ማስላት ለብልሹ አሰራር የሚዳርግና ሊሰበሰብ የሚገባው የመንግስት ገንዘብም እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም የተሟላና የእያንዳንዱን እቃ ዋጋ የሚያሳይ የዋጋ ሰነድ እንዲቀርብ በማድረግ መሰብሰብ ያለበት የቀረጥ መጠን ከሚመለከተው ድርጅት መሰብሰብ እንዳለበትና ለወደፊቱም የተሟላ የዋጋ ሰነድ ሳይቀርብና የእያንዳንዱ እቃ ዋጋ ሳይታወቅ ቀረጡ እንዲሰበሰብ ማድረግ አግባብ ስላልሆነ የሚመለከታቸው ሰራተኞች ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲወስዱ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ እንደሚያስፈልግ ለስራ አመራሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

## 2.6 ዲክሌር በተደረገው እና በፍተሻ ውጤቱ መካከል ስለተገኘው የዕቃ ልዩነት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 11(2) መሰረት ዕቃዎች በጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ጀምሮ የጉምሩክ ስነስርዓት አጠናቆ እስከሚወጣ ድረስ በአይነት፣ በቅርፅ፣ በይዘትና በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ሳይለወጡ ዕቃዎች በተነሱበት ሁኔታ መድረሳቸው የሚረጋገጥ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር c-121/11 ለገባው እቃ በዶክመንቱ መሰረት የመኪናው ዓይነት Isuzu NPR እንደሆነ የመንገድ ትራንስፖርት ፈቃድ በሰጠበት ደብዳቤ፣ የባንክ ፈቃድ፣ ትራክ ዌይ ቢል፣ ፓኪንግ ሊስት፣ ኮመርሺያል ኢንቮይስ፣ ዲክላሬሽን ኦፍ ፋክት እና የቶን ውጫሌ የፍተሻ ደብዳቤ ላይ የተገለጸ ሲሆን በድሬዳዋ መቅረጫ ጣቢያ በተደረገ ፍተሻ መኪናው Isuzu NPR Chasis መሆኑን በመግለጽ እና የልዩነቱ መንስኤ እንዲጣራ ሳይደረግ ቀረጥና ታክስ በፍተሻው ውጤት መሰረት መሰላቱ ታውቋል::

ይህ አሰራር ከፍተኛ ቀረጥ የሚያስከፍል እቃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ወደ መቅረጫ ጣቢያ የሚቀርበው ደግሞ አነስተኛ ዋጋ የሚያስከፍል እቃ ሊሆን ስለሚችል አሰራሩ ህገወጥነትን ያበረታታል፡፡

በመሆኑም በልዩነት የታየውም ማስረጃ፣ የፍተሻ ውጤት እና የሌሎች ጣቢያዎች ማስረጃ ተጣርቶ የቀረጥና ታክስ ልዩነት ካለ መሰብሰብ እንዳለበት ለስራ አመራሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

## 2.7 <u>የእቃውን ዋጋና ታሪፍ በትክክል ለመወሰን የዋጋ ሰነዱ ገላጭ አለመሆኑ</u>

የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት፣ አዘገጃጀት፣ ስርጭትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 10/1996 አንቀጽ 24 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ዋጋንና ታሪፍን በትክክል ለመወሰን እንዲቻል የዋጋ ሰነዱ ገላጭ በማይሆንበት ጊዜ ስለእቃው ዝርዝር መግለጫ እየቀረበ ቀረጡ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በናሙና ከታዩት ውስጥ:-

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የዋጋ ሰነዱ በአንዳንድ በዲክላራሲዮኞች ላይ የእቃዎቹን ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን ገላጭ ባልሆነበትና በፍተሻ እና በፍሬ ነገር መግለጫ (declaration of fact) ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ባልቀረበበት ሁኔታ አነስተኛ ዋጋን በመውሰድ ቀረጥና ታክስ የተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ለአንዳንድ ሰነዶች የፍሬ ነገር መግለጫ የማይሞላ ሲሆን ለአንዳንዶቹ የፍሬ ነገር መግለጫ ቢያያዝም እያንዳንዱ እቃ የተመደበበትን ታሪፍ ቁጥር የማይጠቅስ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በዲክላራሲዮን ቁጥር c-4923/2011 ዲክሌር ከተደረጉት እቃዎች ውስጥ Bush (spare part) እቃው የላስቲክ እቃ (Rubber) ከሆነ የጉምሩክ ቀረጥ (import tax rate) 30% ሲሆን Rubber ካልሆነ ግን የጉምሩክ ቀረጥ (import tax rate ) 20% ይሆናል:: ነገር ግን እቃው የላስቲክ እቃ (Rubber) መሆን አለመሆኑ በዋጋ ሰነዱ፣ በፍተሻ ወይንም በፍሬ ነገር መግለጫ ላይ ሳይገለጽ አነስተኛ የታሪፍ ምጣኔውን በመውሰድ ቀረጡ የተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በአራት በዲክላራሲዮኖች ላይ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን በማስረጃ ላይ የተመለከተው ሞዴል እና ቀረጥ ለማስከፈል የተጠቀሙበት ሞዴል የሚለያይ እና የመጫን አቅማቸውም ሳይታወቅ መስተንግዶ የተሰጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዚህ አሰራር ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ ላይሰበሰብና የተሰበሰበውንም ገቢ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

በመሆኑም የቀረበው የዋጋ ሰነድ የእቃውን ትክክለኛ ዋጋና ታሪፍ ለመወሰን ገላጭ በማይሆንበት ጊዜ በፍተሻ እና በመረጃ መስጫ ዲክላራሲዎን

(Declaration of fact) ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ እየቀረበ ቀረጡ የሚሰበሰብበት ስርአት በሁሉም ሰነዶች ላይ ተፈጻሚ መሆን እንዳለበት ለስራ አመራሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

## 2.8 ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ ሶስተኛ ወገን ስለተላለፉት ከቀረጥ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ

ከቀረጥ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች ወደ ግለሰቦች በሽያጭ ሲዘዋወሩ በጉምሩክ አዋጁ ቁጥር 622/01 ምዕራፍ 2 አንቀጽ 94(1) እና 98 መሰረት ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በመንገድ ትራንስፖርት መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቱ ለመንግስት የተሰጡ መብቶች ማስፈጸሚያ የስራ ሂደት እና በኢንተለጀንስ ቡድን መካከል የመረጃ ልውውጥ ደካማ መሆን ምክንያት የተጭበረበረ ሰነድ በመጠቀም ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ከቀረጥ ነጻ የገቡ ተሽከርካሪዎች ወደ ህጋዊነት እየዞሩ መሆኑን የቅ/ጽ/ቤቱ የኢንተለጀንስ ቡድን በመግለጽ ወንጀሉን ለመከላከል እንዲቻል ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር እንደሚገባው ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች እና የስራ ክፍሎች የላከውን ደብዳቤ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም በዚሁ መሰረት የተስተካከለ አሰራር አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይህም ህገወጥ አሰራርን ሊያስፋፋና ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ስለዚህ ችግሩ በተመሳሳይ መልኩ እንዳይቀጥል ለማድረግ የጉምሩክ የሥራ ሂደት፣ የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት እና በመንግስት የተሰጡ መብቶች ማስፈፀሚያ የሥራ ሂደቶች በቅንጅት መስራት ያለባቸው ከመሆኑም በላይ ከባለስልጣኑ መ/ቤት ውጪ ያሉ መ/ቤቶች ጋር በመነጋገር የመረጃ ልውውጥ የሚደረግበት የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ህገወጥ የሆነውን አሰራር ማስቆም እንደሚያስፈልግ ለስራ አመራሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በቀጣይ የእርምት እርምጃ የሚወሰድ መሆኑ ተገልጿል፡፡

2.9 <u>በወቅቱ ሳይሰበሰብ የተገኘ ቀረጥና ታክስ ብር 5,578,563.62 በተመለከተ</u>

የጉምሩክ ወንጀልን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እልባት ለመስጠት በወጣው መመሪያ ቁጥር 46/02 መሰረት መሠራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የሚከተሉት ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- ከቀረጥ ነፃ በገባ ዕቃ አላግባብ ሲገለገሉ የተገኙ ግለሰቦች ከ1/12/99 ጀምሮ ቀረጥና ታክሱን በሁለት አመት ውስጥ (በአራት ጊዜ) ለመክፈል ከተስማሙት ውስጥ የዋስትና ጊዜያቸው ካለፈባቸው 64 ፋይሎች ብቻ ብር 4,442,294.89 ያልተሰበሰበ መሆኑን እና ተሰብሳቢ ሂሳቡም በገቢ አሰባሰብ ክፍል በኩል የማይታወቅ መሆኑ፣
- በህግ ማስከበር የሥራ ሂደት በወንጀል ምርመራ ቡድን የተያዙ ከቀረጥ ነጻ የገቡና ለሶስተኛ ወገን ከተላለፉ መኪኖች፣ እንዲሁም ተደብቆ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ከተያዘ የመለዋወጫ ዕቃ (Spare part) ቀረጥና ታክስ በወቅቱ መሰብሰቡ ሲጣራ በኦዲት ከታዩት 7 ፋይሎች ውስጥ አራቱ ቅጣትን ሳይጨምር ቀረጥ እና ታክስ ብቻ ብር 868,537.87፣ ቀደም ብሎ ወደ አገር ውስጥ ከገቡ ተሸከርካሪዎች ሊሰበሰብ የሚገባው ሂሳብ በሙሉ ባለመሰብሰቡ በቀሪነት የሚፈለግ ብር 267,730.86 መኖሩ ታውቋል፡፡

በመሆኑም በጉምሩክ አዋጅ እና መመሪያ መሠረት በዋስትና የተያዘ ሂሣብ የጊዜ ገደቡ ሲያልፍ ወደ ቀጥታ ገቢ እንዲተላለፍ መደረግ ያለበት ሲሆን፣ ቀረጥና ታክሱ በወቅቱ ካልተሰበሰበ በመቆየት ብዛት ሊጠየቅ የሚገባው ግለሰብ ላይኖር ይችላል፡፡ ይህም የመንግስት ገቢ ሳይሰበሰብ እንዲቀር ያደርጋል፣ በተመሳሳይ መልኩ ሌሎች ግለሰቦችም ይህንኑ መንገድ በመከተል ብልሹ አሰራር እንዲስፋፉ የሚያደርግ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቁጥጥር እና ክትትል ስርዓቱ ሊስተካከል እንደሚገባ ለስራ አመራሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

2.10 <u>የተወረሱ እና የተተው እቃዎችን ሽያጭ በተመለከተ</u>

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋናው መ/ቤት የተወረሱና የተተው ዕቃዎችን ያለ ጨረታ በዱቤ ለሸቀጦችና ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ለመሸጥ በገባው ውል መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ መሰብሰቡንና ድርጅቱ በወቅቱ ካልከፈለ

በውሉ መሰረት እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከገቢ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በተገኘው መረጃ መሰረት፡-

- የ2001 በጀት ዓመት ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሳብ ብር 7,632,832.67
- የ2002 በጀት ዓመት ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሳብ ብር 21,749,094.59
- በውሉ መሰረት ክፍያ ባለመፈጸሙ ድርጅቱ ሊከፍል የሚገባው ወለድ ብር 1,727,682.65
- የ2003 በጀት ዓመት ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሳብ ብር 89,328,565.54

በድምሩ 120,438,175.45 በውሉ መሰረት አለመሰብሰቡ እና ድርጅቱ በወቅቱ ያለበትን እዳ ባለመክፈሉ በገባው ውል መሰረት የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

በዚህ ሁኔታ ጊዜው በረዘመ ቁጥር ሊሰበሰብ የሚገባው የመንግስት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

በመሆኑም የገቢ ዳይሬክቶሬት በውሉ መሠረት የተሸጡ ዕቃዎች በ45 ቀናት ውስጥ ሂሳቡ ገቢ መደረጉን ሊያረጋግጥ እና በጊዜ ገደቡ ውስጥ ሂሳቡ ገቢ ካልተደረገ ባልተከፈለ ሂሳብ ላይ በባንክ የብድር ወለድ ምጣኔ መሰረት ወለድ በመጨመር ተገቢው እርምጃ የሚወሰድበትን ሁኔታ በማመቻቸት ድርጅቱ ያለበትን እዳ እንዲከፍል ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

## 3. <u>የወጪ ንግድ (Export) ቀረጥና ታክስን በተመለከተ</u>

ከአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር አወዕ/ቀ/በመ/6/03 በቀን 23/12/2003 በቀረበልን የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ዝርዝር መሰረት 176 የቫውቸር ተጠቃሚዎች ያሉ ሲሆን በተሻሻለው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 543/1999 መሰረት ተገቢው ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

### 3.1 <u>ከቀረጥ ነጻ ጥሬ ዕቃ ወደ ሀገር ገቢ አድርገው ምርታቸውን ወደ ውጪ ስለመላካቸው ማስረጃ ያልቀረበለት</u>

በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች በአዋጅ ቁጥር 543/1999 አንቀፅ 11(7) መሰረት ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ አራት ድርጅቶች

ማለትም (ጄኒውን ሌዘር መለያ ቁጥር 0000044866 ሼባ ፕላስቲክ መለያ ቁጥር 0002900032, ካንጋሮ ጫማ መለያ ቁጥር 0000010388 እና ኤሌክትሮ ኮሜርሽያል መለያ ቁጥር 0000008481) ጥሬ ዕቃ ያስገቡ እና ጥሬ እቃው ስራ ላይ ውሎ ምርቱን ወደ ውጭ መላክ ያለባቸው ቢሆንም፣ ምርቱ ከአንድ አመት በላይ የቆየና የፈቃድ ማራዘሚያም ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ሆኖም በማበረታቻ መልክ ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ አገር ውስጥ የገባ ጥሬ እቃ ለተባለው ዓላማ ሳይውል በሀገር ውስጥ ገበያ ሊሸጥ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባው የውጭ ምንዛሬ ሊያሳጣ እና ሊሰበሰብ የሚገባው ቀረጥና ታክስም ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚ ድርጅት በተፈቀደለት የቀረጥና ታክስ ማበረታቻ መሰረት ወደ አገር ውስጥ ባስገባው ጥሬ እቃ ያመረተው ምርት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ወደ ውጭ አገር የተላከ መሆኑን በመከታተል፤ ካልተወራረደ ወይም ጊዜው ካልተራዘመ በወቅቱ ቀረጥና ታክሱ ከነወለዱ እንዲሰበስብ ተገቢው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ ለስራ አመራሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

3.2 በተመሳሳይ ቀን ወደ ውጭ አገር የተላኩ ተመሳሳይ የዕቃ ሞዴል ያላቸው እቃዎች ዋጋ በዝቅተኛ የነጠላ ዋጋ ተሰልቶ ስለመገኘቱ

ሳባ ሃር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (የቫውቸር ሰርተፍኬት ቁጥር 00068) ወደ ውጪ የላካቸው እቃዎች ዋጋ ሲታይ በአንድ የዋጋ ደረሰኝ ላይ የተገለጹ አንድ አይነት የዕቃ ሞዴል ያላቸው እቃዎች በተመሳሳይ ቀን እና ዲክላራሲዎን ቁጥር አማካኝነት የተላኩ እቃዎች የተለያየ ዋጋ ተሰጥቷቸው አንዳንዶቹን በዝቅተኛ የነጠላ ዋጋ በማስላት መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን የውጭ ምንዘሬ አነስተኛ እንዲሆን መደረጉ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ መንግስት ሊያገኝ የሚገባው የውጭ ምንዛሬ በUSD 1034.00 አንሶ ተገኝቷል፡፡

ይህ አሰራር በአነስተኛ ዋጋ ወደ ውጭ እንዲላክ የተደረገው እቃ ትክክለኛ ዋጋ ላይሆን ይችላል፡ ከአገር ውስጥ የተላከውን እቃ የሚረከበው ድርጅት ከላኪው ጋር በሚኖረው የጥቅም ትስስር የእቃ ዋጋ ኢንቮይስ ዝቅ እንዲል በማድረግ ከውጭ ንግድ የሚገኘው ምንዛሬ እንዲያንስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለአንድ አይነት ዕቃ የተለያየ የነጠላ ዋጋ መጠቀሱ ከውጭ ንግድ ላይ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አስቸጋሪ የሚያደርገው ከመሆኑም በላይ በተለይም በዝቅተኛ የነጠላ ዋጋ የተሰላው እቃ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን የውጭ ምንዛሬ የሚያሳጣ በመሆኑ ተመሳሳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ጉዳዩን ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመነጋገር ችግሩ የሚስተካከልበት ሁኔታ መመቻቸት እንዳለበት ለስራ አመራሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

በዚሁ መሠረት የወጪ እቃዎችን የሽያጭ ዋጋና የማስጫኛ ክፍያ የሚወስነውና የሚቆጣጠረው ብሄራዊ ባንክ በመሆኑ፤ ከባንኩ በሚቀርብ ሰነድ መሰረት የሚስተናገድ በመሆኑ ለወደፊቱ ከብሄራዊ ባንክ ጋር በመነጋገር እና ለባንኩ ግብዓት በመስጠት የሚታየውን ክፍተት ለመዝጋት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ተገልጿል፡፡

## 3.3 በ2002 በጀት አመት የኦዲት ግኝቶች መሰረት የእርምት

### እርምጃ ሳይወሰድበት የተገኘ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2010 ክፍል አምስት 17(3) መሰረት ተመርማሪ መ/ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለጸ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ፣ በተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችና አስተያየቶች መሰረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው፣ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይደነግጋል:: ከዚህ አንጻር ለተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ሲጣራ

- በዋናው መ/ቤት የችሮታ ጊዜ ተከፋይ ሂሳብ ብር 3,864,313.29 ሁኔታው ተጣርቶ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ሂሳብ በጀት በሂሳብ መደብ 6412 መጠየቅ እንደሌለበት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ የነበረ መሆኑ በማሻሻያ ሀሳቡ መሰረት ተፈጽሞ አልተገኘም፡፡
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ለአላቂና ቋሚ እቃ የንብረት መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑና የቆጠራ ውጤት ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር የሚገናዘብበት ስርአት

የሌለ በመሆኑ እንዲስተካከል የማሻሻያ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም አለመስተካከሉ፣ የቅ/ጽ/ቤቱ ፎርክሊፍት ለበከልቻ ትራንስፖርት አ/ማህበር በነጻ የተላለፈ መሆኑ ፎርክ ሊፍቱ እንዲመለስ ወይም በሽያጭ እንዲተላለፍ የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አልተወሰደም፣ የጉምሩክ ስነስርአት ሳይፈጸምባቸው ከተከፈቱ ከአመት በላይ የሆናቸው 15 ዲክላራሲዎኖች ቀጣይ የጉምሩክ ስነስርአት ያልተፈጸመባቸው በመሆኑ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ የማሻሻያ ሀሳብ ቢሰጥም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል::

- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት ከአንድ ድርጅት ብር 255,617.74 ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ በመሆኑ ቅ/ጽ/ቤቱ ከሚመለከተው ድርጅት ቀሪ ሂሳቡን እንዲሰበስብ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ቀሪ ሂሳቡን ለመሰብሰብ የተወሰደ ምንም አይነት እርምጃ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል::
- በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት 27 የቫውቸር ተጠቃሚዎች በወቅቱ ሂሳባቸውን ያላወራረዱ በመሆኑ፣ የተወሰነላቸውን የጊዜ ገደብ ጠብቀው ባለመጓጓዛቸው የተቀጡ 5 ድርጅቶች እና ወኪሎቻቸው ሊሰበሰብ የሚገባው ቅጣት ባለመሰብሰቡ፣ ለመንግሥት ገቢ ሳይደረግ የተገኘ የዋስትና ጊዜያቸው ያለፈበት የ457 ዲክላራሲዎን የቦንድ ሂሳብ የተገኘ በመሆኑ በአዋጁ መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ እና ለኦዲት ሥራ ያልቀረቡ 15 ድክላራሲዮኖች ተፈልገው በነዚህ ዲክላራሲዮኖች የተሰበሰበው ገቢ ትክክለኛነት እንዲጣራ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የእርምት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ ችግሮቹ እንዲቀጥሉ በማድረግ የመንግስት ሀብትና ንብረት ለብክነት እንዲጋለጥ እና ተጠያቂነት እንዳይሰፍን ያደርጋል::

ስለዚህ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ መወሰድ ነበረበት:: አሁንም ከላይ በተሰጠው አስተያየት መሰረት አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል::

# 4. <u>የሂሳብ ምዝገባ እና መደበኛ በጀትን በተመለከተ</u>

## 4.1 <u>የጥሬ ገንዘብ እና የባንክ ሂሳብ</u>

በዋናው መ/ቤት፡-

- በየወሩ ቆጠራ የማያደርግ እና ሌጀር ከሚያሳየው ከወጪ ጋር የማይመዛዘን መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሳጥን ሌጀር እና በሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተ ከወጪ ቀሪ ብር 273,630.81 ቢሆንም፣ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተገኘው ደግሞ ብር 301.00 ብቻ በመሆኑ በቆጠራው እና በሌጀር ከወጪ ቀሪ መሀከል የብር 273,330.81 ልዩነት መኖሩ ታውቋል፡፡
- በ2003 በጀት ዓመት በተሰብሳቢ የሂሳብ ሪፖርት/4202/ ከገንዘብ ያዥ የሚፈለግ የገንዘብ ጉድለት ብር 81,611.35 መታየቱና ገንዘቡ አለመሰብሰቡ የታወቀ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 38,567.53 ጉድለቱ መቼ እንደተከሰተ እና ከማን እንደሚፈለግ ማወቅ አልተቻለም፡፡
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ከአገር ውስጥ ንግድ ተሰብስቦ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ ሳይሆን ከ10 እስከ 30 ቀናት የቆየ ብር 83,919,540.72 ተገኝቷል፡፡

በቆጠራውና በሂሳብ ሪፖርቱ መሀከል የተመለከተው ልዩነት የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ሊሆን ይችላል፡፡ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ቢያጋጥም በወቅቱ ላይደረስበት ስለሚችል በጉድለቱ ተጠያቂ የሚሆን አካልም ላይታወቅ ይችላል፡፡
በመሆኑም በመመሪያው መሰረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ/የሂሳብ ቋት/ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲገናዘብ በማድረግ ክትትል መደረግ ያለበት ከመሆኑም በላይ በልዩነት የታየውም ሂሳብ መንስኤው ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ ባሳሰብነው መሠረት ፤

- በልዩነት ከታየው ሂሳብ ውስጥ ብር 238,324.49 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሶሳ ቅርንጫፍ የሚገኝ ስለሆነ ሁኔታው ተጣርቶ ወደ ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ እንደሚያርጉ እና ቀሪው ብር 35,306.42 ምን እንደሆነ ተጣርቶ እርምጃ የሚወሰድበት መሆኑ ተገልጿል፡፡
- በጉድለት ከታየው ሂሳብ ውስጥ ብር 43,043.82 ከሚመለከታቸው ግለሰቦች በመሰብሰብ ላይ የሚገኝ መሆኑን እና ቀሪው ብር 38,567.53 ጉድለቱ መቼ

እንደተፈጸመ እና ጉድለቱን የፈፀመው አካል ተጠርቶ በጉድለት የተመለከተው ሂሳብ የሚሰበሰብ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 4.2 የባንክ የሂሳብ ማስታወቂያ እና በሂሳብ መዝገብ መሀከል ስለታየው ልዩነት

- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት የዋስትና ሒሳብን /Deposit Account/ የ2003 ዓ.ም የሂሳብ ማጠቃለያ ላይ ሚዛን ብር 6,017,155.96 የዋስትና ሂሳብ አለ ተብሎ ሪፖርት የተደረገ ሲሆን የ2003 ዓ.ም በባንክ ስቴትመንት የመጨረሻ ሚዛን ላይ የተመለከተው ብር 1,576,661.66 በመሆኑ በልዮነት የብር 4,440,494.30 ታይቷል፡፡ የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ለኦዲት ባለመቅረቡ የልዩነቱን መንስኤ ማጣራት አልተቻለም፡፡
- የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች በተስተካከለው በባንክ ስቴትመንት የሂሳብ ሚዛን እና በባንክ ሂሳብ መዝገብ የሂሳብ ሚዛን መሀከል የብር 2,469.84 ልዩነት መኖሩ ታውቋል፡፡

በዚህ አሰራር የመንግስት ገንዘብ ያላግባብ ሊወጣ ይችላል።

በመሆኑም በባንክ የሌለ የዋስትና ሂሳብ እንዳለ በማስመሰል በሂሳብ መግለጫው ላይ እንዲታይ ማድረግ እና ለባለስልጣኑ መ/ቤቱ ይህንኑ ሪፖርት ማስተላለፉ የመ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የልዩነቱ መንስኤ ተጣራቶ ተገቢው እርምጃ መወሰድ ያለበት መሆኑንና ሂሳቡም ትክክለኛውን ሁኔታ ሊያሳይ በሚችል መልኩ መስተካከል ይኖርበታል፡፡

## 4.3 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ስለተገኘው ሂሳብ

የተመዘገበው ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:-

- ከባህር ዳር ፣ ከጅጅጋ፣ ከድሬደዋ፣ ሚሌ እና ሁመራ ቅ/ጽ/ቤት የተላከው የሂሳብ ሪፖርት በዋናው መ/ቤት በትክክል ባለመመዝገቡ በሂሳብ መደብ 1485 እና 1703 መመዝገብ የሚገባው ብር 24,125,743.96 በሂሳብ መደብ 1489 ተመዝግቦ መገኘቱ፣
- ከሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት የተላከው የሂሳብ ሪፖርት በትክክል ባለመመዝገቡ በሂሳብ መደብ 1429 መመዝገብ የሚገባው ብር 10,316.90 በሂሳብ መደብ 1421 ተመዝግቦ መገኘቱ፣

- በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በትክክለኛው የገቢ ሂሳብ ያልተመዘገበ የኤክሳይዝ ታክስ ገቢ ብር 321,854.91 እና ምዝገባው ስህተት እንዳለበት በአሰስመንትና ሌሎች የስራ ክፍሎች ተደርሶበት በSIGTAS የታክሱ አይነት የተስተካከለ ቢሆንም በዚሁ መሰረት የሂሳብ ክፍል ለስህተቱ ማስተካከያ ያልተሰራለት የተለያዩ የገቢ አይነቶች ድምር ብር 432,708.5 ተገኝቷል፡፡

- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ከአንድ ግብር ከፋይ የተሰበሰበ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 40,208,091.46 በነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች የሂሳብ መደብ 1121 ሊመዘገብ ሲገባው በጨርቃጨርቅና ልብሶች የገቢ ሂሳብ መደብ 1133 ተመዝገቦ ተገኝቷል፡፡

- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ከወለድ እና ከቅጣት የተሰበሰበ ብር 3,428,038.15 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በ1104 እንደ ዋና ፍሬ ግብር ተመዝግቦ ተገኝቷል:: እንዲሁም በ2003 በጀት ዓመት ከኤክሣይስ ታክስ የተሰበሰበ ሂሳብ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ መሰረት አለመመዝገቡ ታውቋል፡፡ የሂሣብ ምዝገባው በጥቅል በታክስ አይነት የሚከናወን በመሆኑ የተሰበሰበው ገቢ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ለመመዝገቡ የሚረጋገጥበት ስርዓት የሌለ መሆኑን ያሣያል፡፡

- ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሂሳብ መደብ 6232 ሊመዘገብ የሚገባው ብር 31,200.00፣ በሂሳብ መደብ 6216 ሊመዘገብ የሚገባው ብር 54,603.00፣ በሂሳብ መደብ 6217 ሊመዘገብ የሚገባው ብር 8,416.86፣ በሂሳብ መደብ 6255 ሊመዘገብ የሚገባው ብር 46,804.00 እና በሂሳብ መደብ 6419 ሊመዘገብ የሚገባው ብር 1,879,628.11 በድምሩ ብር 2,020,652 በሂሳብ መደብ 6416 መመዝገቡ እንዲሁም በሂሳብ መደብ 6232 ሊመዘገብ የሚገባው ብር 78,176.29 በሂሳብ መደብ 6625 መመዝገቡ፣ በሂሳብ መደብ 6233 ሊመዘገብ የሚገባው ብር 17,644.00 በሂሳብ መደብ 6256 በአጠቃላይ የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ የተመዘገበ ብር 2,116,472.26 ተገኝቷል፡፡

- አዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማ/ቀ/ጽ/ቤት በተለያየ ምክንያት ከመስሪያ ቤቱ ለታገዱ ሰራተኞች ሳይከፈል የቀረ ደመወዝ ለዋናው መ/ቤት ተመላሽ ሲደረግ ትክክለኛ የማስተካከያ ምዝገባ ባለመከናወኑ ምክንያት የሂሳብ መደብ 6111 በብር 1,155.36፣ የሂሳብ መደብ 6131 በብር 1,371.24፣ የሂሳብ መደብ

4008 በብር 2,687.40 ከወጪ ቀሪ ሂሳባቸው ከፍ እንዲል የተደረገ ሲሆን፣ የተጣራ ሀብት (ሂሳብ መደብ 5601) የሂሳብ ሚዛንም በብር 5,214.00 ዝቅ እንዲል የተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይህም የሂሣብ ሪፖርት እና የአፈጻጸም ሪፖርት ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የሚዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

- የስህተቱ መንስኤ ምዝገባ ከተከናወነ በኋላ በሌላ አካል የምዝገባው ትክክለኛነት የማይረጋገጥ በመሆኑ፣ የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት በሚመዘግበት ወቅት በሌላ አካል የሚረጋገጥበትን ስርዓት መዘርጋትና ከላይ የተዘረዘሩትን ስህተቶች በተመለከተ ደግሞ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡
- ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አወቃቀር መሰረት ትክክለኛውን የሂሳብ መደብ ተከትሎ ሊመዘገብ እና የሂሳብ መግለጫውም ትክክለኛውን የገቢ አፈጻጸም በገቢው አይነቱ እንዲያሳይ ለማድረግ የግብር ከፋይ ምዝገባ ሲከናወን ግብር ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን የታክስ አይነት በመለየት ትክክለኛ ምዝገባ ሊከናወን የሚገባ ሲሆን በየጊዜውም የግብር ከፋዩ ከሚያቀርበው የሂሳብ መግለጫ ጋር እየተገናዘበ አስቀድሞ የተመዘገበው የግብር መረጃ ሊስተካከል ይገባል፡፡

## 4.4 <u>በማነስ እና በመብለጥ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ</u>

የባለስልጣን መ/ቤቱ ዋና መ/ቤት ከየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚላኩ የሂሳብ ሪፖርቶችን በትክክል የሚመዘግብ እና የሂሳብ መግለጫውም ትክክለኛውን ሁኔታ የሚያሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተላኩ የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የተመለከቱ ሁለት የሂሳብ መደቦች በማነስ እና ሶስት የሂሳብ መደቦች ደግሞ በመብለጥ የተመዘገበ በመሆኑ ብር 86,973.46 በብልጫ የተመዘገበ ሂሳብ ተገኝተዋል፡፡ የችግሩ መንስኤ ምዝገባ በአንድ ሰራተኛ ከተከናወነ በኋላ በትክክል ስለመመዝገቡ የሚረጋገጥበት ስርዓት አለመኖሩ እንደሆነ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | የቅ/ጽ/ቤቱ ስም | የሂሳብ መደብ | ከቅ/ጽ/ቤት ሪፖርት የተደረገ | በዋናው መ/ቤት የተመዘገበ | ልዩነት በመብለጥ/ (በማነስ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐዋሳ | 6116 | 0 | | |
| 2 | ሐዋሳ | 6121 | 5,735 | - | |
| 3 | ጅቡቲ | 6256 | 49,997.75 | | |
| 4 | ጅቡቲ | 5004 | 0 | | |
| 5 | ምዕራብ | 6412 | 2,165,838.9 | | |
| ድምር | | | | | 86,973.46 |

የባለስልጣን መ/ቤቱን የሂሳብ መግለጫ የተዛባ ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ የመ/ቤቱ የገቢ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት ምዝገባ ከተከናወነ በኋላ ትክክል ስለመሆኑ በሌላ ሰራተኛ የሚረጋገጥበትን ስርዓት መዘርጋት የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ከላይ ለተገለጹት ስህተቶችም የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

- ከተራ ቁጥር 1 እና 2ን በተመለከተ ማስተካከያ ምዝገባ የተከናወነ መሆኑ ቢገለጽም በድጋሚ በተደረገ ማጣራት ማስተካከያ የተደረገለት የተባለው ሂሳብ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያልተላከ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ተራ ቁጥር 3 እና 4ን በተመለከተ ደግሞ የቅ/ፅ/ቤቱ ሪፖርት በወጪ ሪፖርት ማቅረቢያ ላይ ባያካትተውም በሂሳብ ማመዛዘኛ ላይ ያካተተው በመሆኑ ልዩነት የሌለው መሆኑን ቢገልጹም ወጪው ግን በትክክለኛው ሂሳብ መደብ ያልተገለፀ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- ተራ ቁጥር 5ን በተመለከተ ደግሞ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ የተደረገ ገንዘብ በወጪ ተመዝግቦ የተላከ በመሆኑ ከቅ/ፅ/ቤቱ ጋር በመነጋገር የተስተካከለ መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም፣ የቅ/ጽ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት አልተስተካከለም፡፡

## 4.5 <u>ደጋፊ ማስረጃ ሳይኖረው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

የተመዘገቡ ሂሳቦች በቂ በሆነ ደጋፊ ማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በቅ/ጽ/ቤቶች ሪፖርት ሳይደረግ በዋናው መ/ቤት በሂሳብ መደብ 6256 በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ብር 3,892,882.15 ደጋፊ ማስረጃ ሳይኖር ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል::

ይህም የተመዘገበው ሂሳብ በትክክለኛው የሂሳብ መጠን መሆኑን ለማረጋገጥ አያስችልም::

በመሆኑም ማንኛውም ሂሳብ መመዝገብ ያለበት በቂ በሆነ የሂሳብ መረጃን በማስደገፍ መሆን ይኖርበታል::

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ቅ/ጽ/ቤቶች ከቀጥታ ገቢ ሂሳባቸው ላይ የላኩትን ገንዘብ በሙሉ በዝውውር ስለሚይዙት እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደግሞ ለኬብልና ለባንክ አገልግሎት ክፍያ ወጪ የሆነውን ሳይጨምር የተጣራውን ገቢ ብቻ ስለሚመዘገብ ወጪውን በሂሳብ መደብ 6256 የተመዘገበ መሆኑ እና ለወደፊቱ እያንዳንዱ ቅ/ጽ/ቤት ሂሳቡን የሚመዘገብበት ሁኔታ የሚመቻች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 4.6 <u>ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን የማያሳዩ ሂሳቦችን በተመለከተ</u>

- ከቅ/ጽ/ቤት የተላኩ ሂሳቦች በትክክለኛ የሂሳብ ሚዛናቸውን ጠብቀው ሪፖርት መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከታች በተዘረዘሩት ቅ/ጽ/ቤቶችና የሂሳብ መደቦች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን የማያሳዩ በዋናው መ/ቤት እና በአምስት ቅርንጫፎች የተከፋይ ሂሳብ ብር 1,883,172.42 በዴቢት፣ ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 122.53 በክሬዲት እንዲሁም በአንድ ቅርንጫፍ የወጪ ሂሳብ ብር 13,123.80 በክሬዲት የሚታይ መሆኑ እና ይህም ተገቢው ማጣራት እና ማስተካከያ ሳይደረግ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫ ላይ ተካቶ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ-32 ቀርቧል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል፡፡

## 4.7 <u>ለረጅም ጊዜ በተሰብሳቢና በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታዩ ሂሳቦች</u>

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የ2003 በጀት ዓመት የተመዘገቡ ሂሳቦችና የሂሳብ ሪፖርቶች ትክክለኛነት ሲጣራ በዋናው መ/ቤት ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

- በተከፋይነት ብር 4,628,663.27 (የሂሳብ መደብ 5058)፣ ብር 43,610,408.34 (በሂሳብ መደብ 5026) እርምጃ ሳይወሰድባቸው ለረጅም ጊዜ የቆየ እንዲሁም በተሰብሳቢ ሂሳብነት የተመዘገበ ብር 12,289,141.36 (በሂሳብ መደብ 4208) በቀድሞው የተ.እ.ታ መምሪያ እርምጃ ሳይወሰድባቸው ለረጅም ጊዜ የቆየ፣
- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በክፍል 2 አንቀጽ 53 (1 እና 3) መሰረት የተሰበሰበ የቅድመ ታክስ ሂሳብ ብር 572,636.28 በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ከከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ደንብ ቁጥር 91/95 በአንቀጽ 7 (1-ሐ) መሠረት ከሰራተኞች የተሰበሰበ ብር 78,219.55 በደንቡ መሠረት በወቅቱ ፈሰስ ሳይደረግ መገኘቱ፣
- በመ/ቤቱ የተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 47,051.44 በወቅቱ ለግብር ሰብሳቢው አካል ገቢ አለመደረጉ ታውቋል፡፡
- በተከፋይነት ከተመለከተው ሂሳብ ቀሪው ብር 549,056.37 ከቀድሞ የጉምሩክ ባለሥልጣን የተላለፈና የሞጆ ቅ/ጽቤት ኮንቴነር ተጠቃሚዎች ያስያዙት የአደራ ሂሳብ መሆኑ፣

ተሰብሳቢ ሂሳቦች በቆዩ ቁጥር ሊሰበሰብ የሚችልበትን ሁኔታ ይቀንሰዋል:: ሊከፈል የሚገባው ሂሳብ በወቅቱ አለመከፈሉ የህግ ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል፡፡ መንግስት ስራ ላይ ሊያውለው የሚገባ ገንዘብ በወቅቱ ስራ ላይ እንዳይውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ ከላይ በተገለጸው የተ.እ.ታ መምሪያ ሂሳብ ላይ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድና

- የባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት በገቢ ግብር አወጅ፣ በወጪ መጋራት ደንብ እና በተጨማሪ ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 27/2002 መሠረት የሰበሰበውን ታክስ ለሚመለከተው አካል ገቢ ማድረግ ያለበት ሲሆን፣ ሌሎች ተከፋዮች በተለይም የመያዥ ሂሳብን በተመለከተ ረዥም ጊዜ የቆየ በመሆኑ በጉምሩክ አዋጅ መሰረት ወደ ቀጥታ ገቢ እንዲዞር በማድረግ ገንዘቡን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ገቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም የባለስልጣን መ/ቤቱ በተከፋይ ሂሳብ ላይ የተመለከተውን የሂሳብ ሚዛን በዝርዝር በመፈተሽ በአዋጁ እና ደንቡ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

## 4.8 የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተ

- በ2003 በጀት ዓመት ወጪዎች በታወጀው እና በተደለደለው በጀት መሰረት ስራ ላይ መዋሉን ለማጣራት ከ10% በላይ ልዩነት ያላቸውን የሂሳብ መደቦች ብቻ በመውሰድ ኦዲት ሲደረግ ከተደለደለው በጀት በላይ በልዩ ልዩ የወጪ ርዕሶች ወጪ የሆነ 67,405,518.10 እና ለልዩ ልዩ የወጪ ርእሶች ከተደለደለው በጀት ውስጥ ስራ ላይ ያልዋለ ብር 18,874,913.53 ተገኝቷል:: ዝርዝሩን በአባሪ 1 ይመልከቱ፡፡
- ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በ2003 በጀት ዓመት ከዋናው መ/ቤት የተላከውን በጀት አፈጻጸሙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከዋናው መ/ቤት በየሂሳብ መደቡ ተደልድሎ ከተላከው በጀት በላይ ብር 1,467,562.80 ስራ ላይ ውሎ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 870,981.80 የዝውውር ጥያቄ ሳይቀርብ ለሌሎች የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ስራ ላይ የዋለ ሲሆን ቀሪው ብር 596,580.40 ደግሞ ከአደራ ወይም የዲፖዚት ሂሳብ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

በበጀት አዋጁ መሰረት ከተደለደለው በጀት በላይ ዝውውር ሳይፈጸም ስራ ላይ ሊውል ይችላል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ተቋማት ስራ ላይ ሊያውሉት የሚገባ በጀት ስራ ላይ ሳይውል ሊቀር ይችላል፡፡

በመሆኑም የበጀት ዝግጅት ጥያቄ መ/ቤቱ በተጨባጭ ሊሰራ ካቀደው ተግባር ጋር በማገናዘብ እና ያለፉትን ዓመታት አፈፃፀም በመገምገም ሊከናወን የሚገባው ሲሆን፣ ለወደፊቱ የበጀት ጥያቄ ከመ/ቤቱ እቅድ ጋር እየተገናዘበ የሚቀርብበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

በሌላም በኩል ለየሂሳብ መደቡ ከተደለደለው በጀት በላይ መጠቀም የፋይናንስ አዋጅን እና ደንብን ያልተከተለ አሰራር በመሆኑ ሊስተካከል የሚገባው ሲሆን፣ በጀቱን ስራ ላይ ማዋል ከተፈለገ ተገቢው የዝውውር ጥያቄ ሊቀርብ እና ሊፈቀድ ይገባል፡፡

ከአደራ ሂሳብ ለመደበኛ ስራ ማዋል የማይቻል በመሆኑ የዚህ አይነቱ አሰራር ሊታረም ይገባል፡፡ በሌላም በኩል ቅ/ፅ/ቤቱ ከዋናው መ/ቤት በተላከለት የበጀት ድልድል መሰረት በጀቱን ስራ ላይ ማዋል ያለበት ሲሆን፣ በአጠቃቀም ረገድ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ሲኖሩ ለዋናው መ/ቤት እያስፈቀደ ስራ ላይ ማዋል ይኖርበታል፡፡ ይህም በሚሆንበት ጊዜ የባለስልጣን መ/ቤቱ አጠቃላይ ድልድሉን በማገናዘብ በአዋጁ መሰረት የበጀት ዝውውር መጠየቅ እና ማስፈቀድ እንዲችል ያግዛል፡፡

4.9 <u>የወሮታ ክፍያን በተመለከተ</u>

የወሮታ ክፍያ በመመሪያ ቁጥር 47/2003 አንቀጽ 18 (1/ሐ) መሰረት ዕቃው በክልል ወይም በከተማ መስተዳደር አካላት ወይም በመከላከያ ሠራዊት ወይም በፌዴራል ፖሊስ ሲያዝ ለተቋሙ 50% የወሮታ ክፍያ መከፈሉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ

- በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አባላት የሆኑ ሁለት ትራፊክ ፖሊሶች በተደጋጋሚ ጊዜ ለያዙት እቃ ብር 291,569.26 መከፈሉን፣ በዋናው መ/ቤት ብር 197,492.19፣ በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 152,369.74 በድምሩ ብር 641,431.19 የተከፈለ ቢሆንም፣ ለተቋሙ ሊከፈል የሚገባው 50% አለመከፈሉንና ጠቅላላው ሂሳብ ለግለሰቦቹ መከፈሉን፣
- በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት ከተያዙት 44 ፋይሎች ውስጥ 30 ፋይሎች በተደጋጋሚ በአንድ ግለሰብ የተጠቆመ መሆኑ መረጃው በውስን ሰዎች የሚታወቅና ጥቅም ለማግኘት ሆነ ተብሎ የሚቀነባበር ይመስላል፡፡
  - መቀሌ ቅ/ቤት በመመሪያ ቁጥር 47/2003 መሰረት የወሮታ ክፍያ መፈጸም ሲገባው በቀድሞ መመሪያ ቁጥር 15/2001 መሰረት በመፈጸሙ በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 69,978.06 እና በሁመራ መቅረጫ ጣቢያ ብር 422,142.79 በድምሩ ብር 492,120.85 ለያዥ እና ለጠቋሚ በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
  - በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ለተረጋገጠ መረጃ አቅራቢ የሚሰጥ የሽልማት መጠን በቀረበው የተረጋገጠ መረጃ መሰረት የተደበቀው ግብር

ገቢ በሆነ ጊዜ ተሸላሚ እንደሚሆን የተገለጸ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት ስሌቱ ባለመከናወኑ በብልጫ የተከፈለ ብር 93,000.00 ተገኝቷል፡፡

በዚህ አሰራር የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ሊከፈል ይችላል፡፡

በመሆኑም በመመሪያ ቁጥር 47/2003 መሰረት የወሮታ ክፍያ መከፈል ያለበት የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አባላት በስራ ላይ እያሉ የሚያከናውኑት ተግባር የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ወክለው በመሆኑ የሚሰጠው ወሮታም በመመሪያው መሰረት ለተቋሙ ሊሆን የሚገባው ከመሆኑም በላይ በተደጋጋሚ ተመሳሳይ ያገሮች ብቻ እንዲሳተፉ ማድረግ አጠራጣሪ እና ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት በመሆኑ በዚህ ረገድ ቅ/ጽ/ቤቱ አሰራሩን በመመሪያው መሰረት ቢያስተካክል አብዛኛው ችግር ሊቀረፍ ይችላል፡፡

ማንኛውም ክፍያ በወጡት መመሪያዎች መሰረት መከናወን ያለበት ሲሆን፣ የበላይ ሀላፊዎችም በዚሁ መሰረት መፈጸሙን የመከታተልና መቆጣጠር ሀላፊነት ያለባቸው መሆኑንና ክፍያ ከመፈቀዱ በፊት የቀረቡ የሂሳብ ማስረጃዎች ትክክለኛና በመመሪያው መሠረት የተከናወኑ መሆኑ ሊረጋገጥ እንደሚገባው እና በብልጫ የተከፈለውም የመንግስት ገንዘብ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 4.10 <u>አለአግባብ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ክፍያ</u>

የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በቁጥር መ30/ጠ13/37/820 ጳጉሜ 5/2001 ዓ.ም ባስተላለፈው ሰርኩላር መሰረት የትርፍ ሰዓት ክፍያ መክፈል የተቋረጠ በመሆኑ እና የባለስልጣን መ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለመንግስት አቅርቦ ያስፈቀደው የትርፍ ሰዓት ሳይኖር ሳይኖር፤

- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ከመስከረም 1/2003 እስከ ሰኔ 30/2003 ባለው ጊዜ ብር 155,791.63 እና በሁመራ መቅረጫ ጣቢያ ብር 54,953.84 በድምሩ ብር 210,745.47
- የአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ቤ/ት ለአራት ሰራተኞች በ2002 በጀት ዓመት ለተካሄደው ምርጫ አስፈፃሚዎች የተከፈለ ብር12,196.79 እና ለ38 ሰራተኞች ብር 19,611.65 በድምሩ ብር 31,808.44
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከመስከረም 1/2003 እስከ መጋቢት 30/2003 ባለው ጊዜ ውስጥ የተከፈለ ብር 43,324.72

በጠቅላላ ብር 285,878.63 ያልተፈቀደ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ያልተፈቀዱ ክፍያዎችን መፈፀም መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ የሚደርግና የቅ/ጽ/ቤቱ አሰራር መመሪያዎች ሥራ ላይ እንዳይውሉ መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን ጳጉሜ 5/2001 ዓ.ም. ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተግባራዊ እንዳይሆን የተወሰነ በመሆኑ፣ እንዲሁም የባለስልጣን መ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለመንግስት አቅርቦ ባለማስፈቀዱ ከመስከረም 2003 ጀምሮ የተፈጸመው ክፍያ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አላግባብ የተፈጸመው ክፍያ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ መደረግ አለበት::

<u>የሥራ አመራሩ አስተያየት</u>

- የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤ/ት በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤትና በሁመራ መቅረጫ ጣቢያ የተፈፀመው ክፍያ ለስራው አስፈላጊ በመሆኑ እና ለወደፊቱም ቢሆን በመደበኛ የሥራ ሰዓት ለማይሸፈኑ ስራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ አስቀድሞ በታቀደ መንገድ ክፍያውን መቀጠል አለበት የሚል እምነት ያላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡
- የአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ቤ/ት የትርፍ ሰዓት ሊከፈልባቸው የሚገባ መደቦችን ለዋናው መ/ቤት አቅርቦ በማስፈቀድ የፈጸመው ክፍያ በመሆኑ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ የማይገባው መሆኑ ተገልጿል፡፡
- ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የሥራ ባህሪያቸው ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ ለሚሰሩ ሾፌሮችና ገንዘብ ተቀባዮች በሥራው አስገዳጅነት ምክንያት በገቢ አሰባሰቡ ላይ ተጽዕኖ እንዳይፈጥር በሚል ከዋናው መ/ቤታችን ተፈቅዶና በጀትም ተመድቦ ሲከፈል የቆየ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 4.11 <u>የቋሚ እና አላቂ ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ</u>

የንብረት አጠባበቅና አስተዳደር ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታ ተገኝተዋል፡፡

- በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት፣ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት እና በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት የቋሚ ንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራው ውጤት ከመዝገብ ጋር የማይታረቅ መሆኑ፣

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት የንብረት መዝገብ ያልተቋቋመ እና በውርስ መጋዘን የሚገኙ እቃዎች ቆጠራ የማይደረግ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በውርስ መጋዘን ለሚገኙ ንብረቶች መመዝገቢያ ካርድ ያልተቋቋመና ዓመታዊ ቆጠራ የማይካሄድ መሆኑ፣
- በዋናው መ/ቤት የንብረት ቆጠራ አለመደረጉ እና በቀድሞ ዋና መ/ቤት /እስታዲየም/ በሶስት ግምጃ ቤቶች የተለያዩ የመኪና መለዋወጫዎችና ጎማዎች፣ ካፖርቶች፣ ጫማዎች፣ የቴምብር መረካከቢያና ወጪ ማድረጊያ ሰነዶች፣ የቡና ላኪ ቫውቸሮች፣ ኮምፒውተሮች እና ሌሎች እቃዎች አገልግሎት ሳይሰጡ ተቀምጠው መገኘቱ፣

የቆጠራው ውጤት ከመዝገብ ጋር ካልታረቀ የጎደሉ ንብረቶች ቢኖሩ ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ አይቻልም፡፡

ተሸጠው ዋጋ ሊያወጡ የሚችሉ ንብረቶች ለረዥም ጊዜ በመቀመጣቸው ምክንያት ለብልሽት እና ለብክነት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

በመሆኑም በግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና ይህንኑ ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ መሰረት ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ቆጠራ በማድረግ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ማመሳከር እና በውጤቱ መሰረት ተገቢውን እርምጃ መውሰድና በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በደንቡ መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡

## 5. <u>ልዩ ልዩ</u>

- የግብር ከፋይ ፋይሎች ውስጥ ግብር ከፋዩ ያቀረበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ዲክላራሲዎንና (on submitted column) በተቀናጀ የመንግስት ታክስ አስተዳደር ሲስተም ላይ በተመዘገበው (on revised column) መካከል ልዩነት ያለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

  በዚህም መሰረት፡-

  - በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት
    - ✓ አምስት ግብር ከፋዮች በሲስተም ላይ ተመዝግቦ የሚገኘው ለተከታዩ ወር የሚታሰብ ተመላሽ ሂሳብ በመብለጥ በድምሩ ብር 23,484,812.23 የሚታይ መሆኑን፣ አንድ ግብር ከፋይ ደግሞ ባቀረበው የተጨማሪ እሴት

ታክስ ዲክላራሲዎን መሰረት የአገር ውስጥ ግዢዎች ግብአት ዋጋ ብር 11,612,905.6 ሲሆን፣ በተቀናጀ የመንግስት ታክስ አስተዳደር (SIGTAS) ሲስተም ላይ ተመዝግቦ የተገኘው የአገር ውስጥ ግዢዎች ግብአት ዋጋ ብር 116,129,050.6 መሆኑ፣ በዚህም ምክንያት በግብአት ግዢ ላይ የሚታሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ (input vat) ብር 1,741,935.84 መሆን ሲገባው በሲስተም ላይ ብር 17,419,357.59 ተመዘግቦ መገኘቱ፣

- ✓ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዓመታዊ የቴምብር ቆጠራ ያልተከናወነ ሲሆን፤ የቴምብር ሽያጭ እና ቴምብር የመጠበቅ (የእቃ ግምጃ ቤት) ስራ በአንድ ሰራተኛ ተደርቦ የሚሰራ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት
  - ✓ አንድ ግብር ከፋይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ዲክላራሲዎንና (on submitted column) ለተከታዩ ወር የሚታሰብ ተመላሽ ሂሳብ ያላቀረበ ሲሆን፣ በተቀናጀ የመንግስት ታክስ አስተዳደር (SIGTAS) ሲስተም ላይ ደግሞ ለተከታዩ ወር የሚታሰብ ተመላሽ (on revised column) ሂሳብ ብር 1,996,846.77 ተብሎ በመመዝገቡ፣
  - ✓ ከዋስትና ሂሳብ ወደ መደበኛ በጀት የባንክ ሂሳብ በብድር መልክ የተላለፈ ሂሳብ ብር 100,000.00 በዋስትና ሂሳብ መዝገብ ላይ በተሰብሳቢነት አለመመዝገቡ፣
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
  - ✓ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ብር 46,337,011.49 እና የቅድመ ታክስ /የገቢ ግብር/ ክፍያ ብር 15,723,327.66 በድምሩ ብር 62,060,339.15 ተመላሽ የተደረገ ሂሳብ በሲስተም ውስጥ ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡
  - ✓ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤ/ት ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ የሚያረጋግጥበትም ሆነ የጽ/ቤቱን የበጀት አጠቃቀም ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት አለመኖሩ ታውቋል፡፡
- ዋናው መ/ቤት የቀረጥ ቴምብሮች ምዝገባ የሚከናወን ቢሆንም ምዝገባው የቴምብሮችን ከወጪ ቀሪ የማያሳይ በመሆኑ በዕቃ ግምጃ ቤት ያለውን የቴምብር ቀረጥ ብዛትና ዋጋ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- በአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤ/ት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት የዋጋ ውድድር ሳደረግ በብር 4,930.91 የመኪና ጥገና የተከናወነ መሆኑ፣

- በአዲስ አበባ የገቢ እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት

  - ✓ ሊሰበሰብ የሚገባው የረዥም ጊዜ የደመወዝ ብድር መሰብሰቡ ሲጣራ ከ49 ተቀጽላ መዝገቦች ሳይሰበሰብ ከሶስት አመት በላይ የቆየ ብድር ብር 55,199.30 የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡
  - ✓ የረጅም ጊዜ የደመወዝ ብድር ወስደው ክፍያቸውን ሳያጠናቅቁ ከመስሪያ ቤቱ የለቀቁ ሰራተኞች ያለባቸውን እዳ አለመክፈላቸውን እና በመመሪያውም መሰረት እዳው ከዋሶች አለመሰብሰቡ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡
  - ✓ በሁለት ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ የተመለከተ ብር 2,882.98 ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ መሆኑ እና የረጅም ጊዜ ብድር የወሰዱ ሰራተኞች ከወሰዱት በላይ በድምሩ ብር 30,097.7 የከፈሉ ስለመሆኑ በ16 ተቀጽላ መዝገብ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህም በሂሳብ ሌጀር አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ክትትል የማይደረግ እና ለስራውም ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን መረዳት ያስችላል፡፡
  - ✓ በድሬዳዋ መቅረጫ ጣቢያ ከስራ ሰዓት ውጭ በተለይም ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ እና እሁድ በሚገቡበት ጊዜ የደረሱበትን ሰዓት የሚቆጣጠሩበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑና በዲ/ዮን ቁጥሮች c- 421/2011፣ c-705/2010፣ c-212/2011፣ እና c-215/2011 ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ከወደብ በተነሱበት ሁኔታ ወደ ድሬዳዋ መቅረጫ ጣቢያ ለመድረሳቸው በትራንዚት ቡድን ኦፊሰሮች ማረጋገጫ ያልቀረበላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::

- አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ለዋስትና ሒሳብ (Deposit Account) የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ከባለፈው አመት የኦዲት አስተያየት በመነሳት ከሁለት አመት በላይ ውዝፍ የባንክ ማስታረቂያ ያዘጋጀ ቢሆንም አሁንም ከሰኔ 2002 ዓ/ም በኋላ ላለው ጊዜ የባንክ ማስታረቂያው ያልተዘጋጀ መሆኑ፣

- በአዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ቀጥታ ገቢ ሂሳብ ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4272 የተመዘገበ ብር 1,048.68 ከማን እንደሚሰበሰብ ማስረጃ ሊቀርብ ያልቻለ ሂሳብ መኖሩ::

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ባደረገው የስራ ሂደት ጥናት መሰረት ብልሹ አሰራርን ለመቀነስ ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ የፈታሾች ምደባ በሲስተም (ASCUDA++) እንዲሆን የተደረገ ቢሆንም በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዚህ መሰረት አለመስራቱንና ምደባ የሚከናወነው በሲስተም (ASCUDA++) አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት የሚሰበሰበው የእለት ገቢ የምዝገባ ማዘዣ (JV) ሳይዘጋጅለት የጉምሩክ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኙን ቀጥታ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) ላይ የሚመዘገብ መሆኑንና በተጨማሪም ሂሳብ ክፍሉ በየቀኑ የሚሰበስበውን ገቢ ከ ASYCUDA ላይ በየሂሳብ ኮዱ የተጠቃለለውን በመውሰድ ምዝገባ የማያካሂድ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል:: በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ የእለት ገቢ በትክክለኛው ሂሳብ መደብ እየተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም::
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት 36 ዲክላራሲዮኖች፣ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት 36 ዲክላራሲዮኖች እንዲሁም በአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት 11 ዲክላራሲዮኖች በድምሩ 83 ዲክላራሲዮኖች ለኦዲት ሥራ ባለመቅረባቸው በነዚህ ዲክላራሲዮኖች የተሰበሰውን ገቢ ማጣራት አለመቻሉን፣ አሰራሩ እንዲታረም ለየቅ/ጽ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አሰራራቸውን እንደሚያስተካክሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡ በተሰብሳቢ ሂሳብ ረጅም ጊዜ ቆይታ ያደረገውን ሂሳብ ብር 1048.68 በተመለከተ በ1995 ዓ/ም ከሀራጅ ሽያጭ ተጫራቾች ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው VAT (15%) መሆኑንና በወቅቱ ከሀራጅ ሽያጭ ላይ VAT እንደሚሰበሰብ የሚታወቅ ስላልነበርና መመሪያም ባለመኖሩ ሳይሰበሰብ የቀረ መሆኑን በመግለጽ መመሪያው ሲደርስም ለመሰብሰብ ተሞክሮ ግለሰቦቹ ሊገኙ ባለመቻላቸው write off እንዲደረግ ለዋናው መስሪያ ቤት የተጻጻፉበትን ማስረጃ ያገኙ ስለሆነ በድጋሚ write off እንዲደረግ ለዋናው መስሪያ ቤት ደብዳቤ ጽፈው ምላሹን በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን በመግለጽ ምላሹ እንደመጣ ማስተካከያውን እንደሚሰሩ የስራ አመራሩ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡
- ቅ/ጽ/ቤቶች ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች የሚሰበስቡትን የቅድመ ታክስ የASYCUDA ሲስተም የሚመዘግበው በሂሳብ መደብ 1104 ስለሆነና

ትክክለኛው የሂሳብ መደብ ደግሞ 1109 በመሆኑ የዋናው መ/ቤት የሂሳብ ምዝገባው በሂሳብ መደብ 1109 እንዲመዘገብ የሚደረግ ቢሆንም ቅ/ጽ/ቤቶቹ በተስተካከለው የሂሳብ መደብ ወርሃዊ ሪፖርታቸውን አስተካክለው እንዲልኩ የማይደረግ በመሆኑ በዋናው መ/ቤት የተመዘገበው እና በቅ/ጽ/ቤቶች ተመዝግቦ የሚገኘው ሂሳብ በሂሳብ መደብ ሲጣራ ልዩነት ያለው መሆኑ፣

- ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስተካከያ የሂሳብ ሪፖርት ሳይመጣ በስልክ መልእክት ብቻ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑ፣
- ከቅ/ጽ/ቤት የተላኩ የሂሳብ ሪፖርትቶች ከተጠቃለው ሂሳብ ምዝገባ ጋር ያልተጠቃቀሰ በመሆኑ ማስረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘትም ሆነ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት ረዥም ጊዜ የሚወስድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በዋናው መ/ቤት የሂሳብ ማጠቃለል ስራ በIBEX የማይከናወን መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

# የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

## 2003/4 በጀት ዓመት የልዩ ልዩ መ/ቤቶች

## ኦዲት ሪፖርት ማጠቃለያ

የ2003 በጀት ዓመት በፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች ስር የሚገኙ ልዩ ልዩ መ/ቤቶች ኦዲት ዓመታዊ ሪፖርት ማጠቃለያ እንደሚከተለው ቀርበል፡፡

## የፋይናንሻልና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም

በፋይናንስና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በ2003 በጀት አመት 33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችን ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ አቅዶ የ33 መ/ቤቶችን ኦዲት አከናውኗል፡፡ ይህም 100% እንደተከናወነ ያሳያል፡፡ የኦዲቱ ሥራ የተከናወነው በ1 ዳይሬክቶሬትና በ3 የኦዲት ማናጀሮች ነው፡፡

ዳይሬክቶሬቱ በ2003 በጀት ዓመት በፌዴራል መ/ቤቶች ላይ በመደበኛ ኦዲት ያከናወነው የፋይናንስ ኦዲት የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብን ጨምሮ 33 የኦዲት ሪፖርቶችን ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች የላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት አንፃር ሲተነተኑ፣

- አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Clean opinion) የተሰጠባቸው መ/ቤቶች — 12
- ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion) መ/ቤቶች፣ — 16
- የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adverse opinion) የተሰጠባቸው መ/ቤቶች፣ — 3
- አስተያየት መስጠት እንደማይቻል (Disclaimer of Opinion) የተሰጠባቸው መ/ቤት — 1
- ሂሳባቸውን ባለመዝጋታቸው የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠባቸው መ/ቤት ሲሆኑ፣ ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ-1 እስከ አባሪ - 5 ቀርቧል፡፡ — 1

1. <u>የሳጥን ሂሣብ</u>

1.1 <u>በቆጠራ ውጤት እና በሂሳብ መግለጫ መካከል ስለታየው ልዩነት</u>

በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ሰኔ 30/2003 በተደረገው ቆጠራ ብር 61,676.17 በጥሬ ገንዘብና በሠነድ የተገኘ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ደግሞ ብር 271,240.44 በመሆኑ የሂሳብ መግለጫው በቆጠራ ከተገኘው በብር 208,844.19 ብልጫ የሚያሳይ መሆኑ እንዲሁም የፕሬዝዳንት ጽ/ቤት በውስጥ ኦዲት በኩል ሰኔ 30/2003 በተደረገው የጥሬ ገንዘብና የሠነድ ቆጠራ እና በጽ/ቤቱ የ2003 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫ መሀከል የብር 25,960.39 ልዩነት የሚታይ በመሆኑ፣ የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት (Financial Report) ትክክለኛውን ገጽታ ላያሳይ ይችላል፡፡ የመንግስት ገንዘብም ሊባክን ይችላል፡፡

በመሆኑም የሂሳብ መግለጫው በቆጠራው መሰረት ሊስተካከል የሚገባው ሲሆን፣ በቀጣይም የልዩነቱ ትክክለኛ መንስኤ ተጣርቶ በውጤቱ መሰረት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የሬድዮና የቴሌቪዥን የባንክ ሂሳብ ወደ አንድ አካውንት በተጠቃለለበት ወቅት ከ1992 በጀት ዓመት በፊት የተፈጠረ ችግር መሆኑንና የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ከብር 1,260,339.44 ወደ ብር 271,240.44 ዝቅ ማለቱን በመቀጠልም ሂሳቡን ለማስተካከል ጥረት እያደረጉ መሆኑን በላኩት ምላሽ የገለፁ ሲሆን፣ የፕሬዚዳንት ጽ/ቤትም ገንዘብ ያገሮች ሲቀያየሩ በተሟላ መልኩ ርክክብ ባለመፈፀሙ ምክንያት የተፈጠረና ልዩነቱ በኦዲተር እስኪረጋገጥ በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ በመብለጥ ሲታይ የቆየ መሆኑንና በአሁኑ ጊዜ ግን ልዩነቱን አጣርተው የደረሱበት መሆኑን በላኩት ምላሽ የገለፁ ቢሆንም የሂሳብ ሪፖርቱ ተስተካክሎ ያልቀረበ በመሆኑ የተገኘውን ልዮነት በማሣየት የሂሳብ ሪፖርቱ ትክክለኛውን ገጽታ እንዲያሳይ ማድረግ እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 1.2 <u>የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ ጋር የማይመዛዘን ስለመሆኑ</u>

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት ቁጥር 5.ሀ መሠረት የፋይናንስ ኃላፊ በካዝና ውስጥ የሚገኘውን ገንዘብ እና የባንክ ሂሣብን የሚጠብቅ እና የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚ/ር፣ በድሬደዋ ዩኒቨርስቲ፣ በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ እና በኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ቆጠራ የማይደረግና ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመዛዘን መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም በመመሪያው መሠረት የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ በሂሣብ ክፍሉ በኩል ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር መመሳከር እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 1.3 <u>ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ያልተፈቀደ የጥቃቅን ወጪ የገንዘብ መጠን</u>

የፌዴራል መንግስት ጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 24 (2) በመ/ቤቱ የስራ ባህሪይ ምክንያት የተፈቀደ የጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ ገንዘብ መጠን ከፍ እንዲል ካስፈለገ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጥያቄ በማቅረብ የተፈቀደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ማኔጅመንት ኮሚቴ ውሳኔ በመደበኛ በጀት ለሚሸፈኑ ጥቃቅን ወጪዎች (Petty Cash) ብር 50,000.00 እንዲሁም ከውስጥ ገቢ ለሚሸፈን ክፍያ ብር 10,000.00 በሳጥን ማደር እንዳለበት መመሪያ ያወጣ ቢሆንም፣ በመመሪያው መሰረት ጉዳዩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያልቀረበና ያልተፈቀደ መሆኑ ታውቋል፡፡

ይህም የጥሬ ገንዘብን ለመቆጣጠር የተዘረጋ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡

በመሆኑም ከዩኒቨርስቲው የስራ ባህሪይ አንጻር የጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ ገንዘብ መጠን ከፍ ለማድረግ አሳማኝ ሁኔታ ካለ ጉዳዩን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር  በማቅረብ ማስፈቀድ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

## 2.1 <u>የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ መሰብሰቡንና የተሰበሰበውም ገንዘብ በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የቴሌቪዥን ፈቃድ ገቢ እንዲሰበሰብለት በተዋዋለው መሰረት ከአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ብር 2,156,462.00 ከደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም ብር 114,236.64 እንዲሁም ከኦሞ ብድርና ቁጠባ ተቋም ብር 67,986.03 በድምሩ ብር 2,338,684.67 ባንክ ገቢ ለመደረጉ የባንክ ማስረጃ የቀረበ ቢሆንም፣ ገንዘቡ የተሰበሰበበት ደረሰኝ ለኦዲት ያልቀረበ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያለመቻሉን፤
- ከአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ድርጅትም በተመሳሳይ መልኩ በሂሣብ ሪፖርቱ ላይ የሚታየው ብር 157,541,223.90 ከአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያና የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና እንዲሁም ከተለያዩ የፈተና ጣቢያዎች ከተመዘገቡ ተፈታኞች የተሰበሰበው በኤጀንሲው የፈተናዎች ምዝገባና የገቢ አሰባሰብ አፈጻም መመሪያ ላይ በተገለጸው ታሪፍ መሠረት የተሰበሰበ መሆኑንና ከየክልል ጣቢዎች የተሰበሰበውም ገቢ በአግባቡ ተሰብስቦ ለኤጀንሲው ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የተፈታኞች ዝርዝር ከክሬዲት አድቫይሱና ከገቢ ደረሰኝ (RV) ጋር የማይያያዝ ወይም የማይጣቀስ በመሆኑ፤
- በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ባንክ ገቢ ለተደረገው ሂሳብ የባንክ አድቫይስ የሚቀርብ ቢሆንም፣ ባንክ ገቢ የተደረገው ገንዘብ መቼ እና በየትኛው ደረሰኝ የተሰበሰበው እንደሆነ ማረጋገጥ የሚቻልበት መንገድ የሌለና ባንክ ገቢ የተደረገውና ተሰበሰበ ተብሎ የሚያያዘው ማስረጃ የማይጣጣም ከመሆኑም በላይ ግንኙነት የሌላቸው ደረሰኞችም የሚያያዙ በመሆኑ በውስጥ ገቢ ሂሳብ አያያዝ አሰባበብ እና ክትትል ረገድ ያለው የቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ፤ ገቢ ለመሰብሰብ ውክልና በሌላቸው ሰራተኞች ገቢ የሚሰበሰብ ከመሆኑም በላይ ገንዘብ ለመሰብሰባቸው የሚፈርሙት ለከፋይ በሚሰጠው የመጀመሪያ ኮፒ ላይ ሲሆን፣ ሁለተኛውና ሶስተኛው ኮፒ ደግሞ በገንዘብ ያዥ እንዲፈረም

ይደረጋል፣ ይህ አሰራር የመንግስት ገንዘብ ቢጎድል ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስቸግር ከመሆኑም በላይ ለከፋይ የሚሰጠውንና ቀሪው ደረሰኝ በማበላለጥ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ እንዲመዘበር የሚያደርግ በመሆኑ፣ የገቢውን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ይህም የተሰበሰበው ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ላይገባ ከመቻሉ በተጨማሪ የተሰበሰበውን ገቢ ለመቆጣጠርና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያስቸግራል፡፡ አሰራሩ የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ኮፒ በማበላለጥ የመንግስት ገንዘብ እንዲባክን ሊያደርግ የሚችል በመሆኑ፤ በበጀት አመቱ ውስጥ ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ መሰብሰቡን ማረጋገጥ የማይቻልበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡

በመሆኑም ገቢ የተሰበሰበበት የገቢ ደረሰኝ በወቅቱ ከየተቋሞቹ ተሰብስቦ በመ/ቤቱ ሊያዝ የሚገባው ከመሆኑ በላይ ሂሳቡን ለማጣራት ሲጠየቅ ሊቀርብ በሚያስችል መልኩ ተደራጅቶ ሊቀመጥ እንደሚገባ፤ ለኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ያሳሰብን ሲሆን፣ ለአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲም የተፈታኞችን ዝርዝር፤ የክሬዲት አድቫይሱና የገቢ ቫውቸሩ፤ ከምዝገባው ጋር በማጠቃቀስ ለኦዲት በሚያመች መልኩ መቀመጥ እንደሚኖርበት፤ ባንክ ገቢ የተደረገው ገንዘብ እና በገቢ ደረሰኝ የተሰበሰበው የገንዘብ መጠን ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት አሰራሩም ተጠያቂነትን ሊያመጣ በሚችል መልኩ በማስተካከል የገቢ አሰባሰብ ስርዓቱ ትክክለኛውን መረጃ ሊሰጥ እና ብክነትን ሊከላከል በሚችል መልኩ መስተካከል እንደሚኖርበት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2.2 የገቢው ምንነት ያልታወቀ

በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የቴሌቪዥን ማስታወቂያ ገቢ ሂሳብ ውስጥ ከኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ወደ ድርጅቱ በባንክ በኩል የተላከ ሂሳብ ብር 133,903.20 በድርጅቱ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የተገኘው ሂሳብ የገቢው ምንነት የማይታወቅ በመሆኑ፤ የድርጅቱ የገቢ የሂሳብ ሪፖርት ከፍ ብሎ እንዲታይ ስለሚያደርገው ሪፖርቱ ትክክለኛ ገጽታ እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

ስለዚህ የሂሳቡ ምንነት ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.3 <u>በዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ</u>

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 29 ቁጥር 1 መሰረት በየቀኑ የተሰበሰበ ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ባንክ ገቢ ሳይሆን ከ 26 ቀን በላይ የሚቆይ መሆኑን፤ እንዲሁም በቤተ መንግስት አስተዳደር በስሩ ካሉት ቅርንጫፎች ውስጥ በአዋሽ መልካሳ ብር 53,685.87 እንዲሁም በቆቃ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር 4,194.00 በድምሩ ብር 57,879.87 ተሰብስቦ ገንዘቡ ባንክ ገቢ ሳይደረግ ከ1 ወር እስከ 6 ወር በግለሰቦች እጅ የሚቆይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የሚሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ ካልሆነ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት እንዲጋለጥ በር ከመክፈቱ በተጨማሪም ህግ እንዲጣስ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም በገንዘብ ያዥ እጅ ገንዘብ ከተጠራቀመ ላልተፈለገ ብክነት የሚገፋፋ በመሆኑ የተሰበሰበ የመንግሥት ገንዘብ በደንቡ መሠረት በወቅቱ ባንክ ገቢ መደረግ ያለበት ከመሆኑም በላይ ይህም ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ተገቢው የመከታተያ ስርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.4 <u>የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ያልቀረቡ ስለመሆኑ</u>

በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ ክፍል በበጀት ዓመቱ ከንብረት ክፍል ወጪ ካደረጋቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ውስጥ 11 ጥራዝ ደረሰኞች ለሆሩ ጉድሩ የእንሰሳት ማዕከል ተሰጥተው የነበረና አስራ አንዱም ደረሰኞች ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ከነዚሁ ውስጥ 9ኙ ብቻ ለኦዲቱ የቀረቡ በመሆኑ በ2ቱ (ከቁጥር 383051 - 383100 እና 382351-382400) የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡ በነዚህ ደረሰኞችም የተሰበሰበ ገቢ መኖር አለመኖሩም ስለአልታወቀ የተሰበሰበ ገቢ ካለ ወደ መንግስት ሳጥን ገቢ ላይሆን ይችላል፡፡

ደረሰኞች ገንዘብ የሚሰበሰብባቸውና በቀላሉም ለጥፋት ሊጋለጡ የሚችሉ በመሆኑ የደረሰኝ ስርጭት እንዲሁም ስራ ላይ የዋሉ ደረሰኞች ክትትል ሊጠናከር

ይገባል፡፡ ያልቀረቡትም ደረሰኞቹ እንዲቀርቡ በማድረግ በውስጥ ኦዲት በኩል የሂሳቡ ትክክለኛነት መረጋገጥ እንደሚኖርበት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በዚሁ መሰረት አልቀረቡም ከተባሉት ደረሰኞች ውስጥ 321551-321600 ከኦዲቱ በኋላ በተደረገ ማጣራት የተገኘ መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም፣ ይህ ደረሰኝ በኦዲቱ አልቀረቡም ከተባሉት ውስጥ ባለመሆኑ፣ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኦዲቱ ከተጠየቁት ደረሰኞች ውስጥ ከቁጥር 382351 - 382400 አንድ ጥራዝ ደረሰኝ ደግሞ ባልታወቀ ሁኔታ በመጥፋቱ ፖሊስ እንዲከታተለው የተደረገና ለመጥፋቱም ሰፊ ሽፋን ባለው ሚዲያ እንዲነገር ተደርጎ የሰረቀው ግለሰብ መያዙንና በህግ ጥላ ስር እንደሚገኝና ጉዳዩም በፍርድ ሂደት ላይ ያለ መሆኑን ዩኒቨርሲቲው በሰጠው ምላሽ የተገለፀ ቢሆንም በተሰጠው ምላሽ ላይ ተገኘ የተባለው ደረሰኝ ቁጥር 321551-321600 እና በኦዲቱ ወቅት አልቀረበም ተብሎ የተገለጸው ደረሰኝ አንድ አይነት ባለመሆናቸው ያልቀረበው ደረሰኝ ከቁጥር 383051- 383100 በመሆኑ ትክክለኛው ሁኔታ ሊጣራና ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ኦዲታችን ያተኮረው በ2003 በጀት ዓመት በተሰራጩት ደረሰኞች ላይ በመሆኑ ቀደም ባሉት አመታትም ተሰራጭተው ለግል መጠቀሚያነት የዋሉ ሊኖሩ ስለሚችሉ ዩኒቨርሲቲው በዚህ ረገድ ተገቢውን የማጣራት ስራ ሊያከናውን እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2.5 <u>የውስጥ ገቢ ከወጪ ቀሪ ፈሰስ ያለመደረጉ</u>

በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648 አንቀፅ 10(3) መሰረት የተሰበሰበው የመንግስት ገንዘብ ወደ ተጠቃለለው ፈንድ ገቢ ማድረጉንና ሂሳቡንም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በየወሩ ሪፖርት ማድረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ከሰበሰበው ከውስጥ ገቢ ብር 9,803,084.23 ውስጥ ብር 3,017,000.00 እንዲጠቀም የተፈቀደለት ሲሆን ቀሪው ብር 6,786,084.23 እና ቀደም ካሉት አመታት የዞረው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ በአዋጁ መሰረት ፈሰስ ያለመደረጉ፤ አሰራሩ በአዋጁ መሰረት እንዲስተካከል በ2002 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት ላይ የተገለፀ ቢሆንም ምንም አይነት እርምጃ አልተወሰደም፡፡

ዩኒቨርስቲው ከተፈቀደለት በጀት በላይ የውስጥ ገቢውን ስራ ላይ ሊያውል ይችላል፡፡ መንግስት ስራ ላይ ሊያውለው የሚገባው ገቢ እያለ በወለድ እንዲበደር

ሊያደረግ ከመቻሉ በተጨማሪ የመንግስት ትክክለኛው አመታዊ ገቢ እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ስራ ላይ እንዲያውል ከተፈቀደለት በላይ የሚሰበሰብ ገቢ በፋይናንስ አዋጁ መሰረት ፈሰስ መደረግ አለበት፡፡ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሪፖርት ያልተደረገውም ሂሳብ ሪፖርት መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

ባለፈው ዓመት ኦዲታችንም ተመሳሳይ የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አልተወሰደም፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት ሊሰራ የሚገባው መሆኑንና የተሰጠው ምላሽ አሳማኝ አለመሆኑን በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2.6 <u>በብልጫ የተመዘገበ የገቢ ሂሳብ</u>

የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በየክልሉ የገንዘብ ሰብሳቢ በመመደብ ከህብረተሰቡ የቴሌቪዥን ፈቃድ ገቢ የሚሰበስብ ሲሆን፣ ከደሴ ቅርንጫፍ ገንዘብ ሰብሳቢ በገቢ ደረሰኝ መሰረት ተሰብስቦ ደሴ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ የገባው ብር 210,510.00 ሲሆን ተጠቃሎ ወደ ዋናው መ/ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ ሲደረግ በተፈጠረው ስህተት ብር 214,330.80 ተደርጎ በመተላለፉና ምዝገባው በዚሁ መሰረት በመፈፀሙ ብር 3,820.85 በብልጫ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የድርጅቱ የገቢ ሂሳብ ሪፖርት ከፍ ብሎ እንዲታይ ሊያደርግ ስለሚችል የሂሳብ ሪፖርቱ በትክክለኛው ገቢ መስተካከል እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

## 2.7 <u>በገቢ አሰባሰብ የታዩ የአሰራር ድክመቶች</u>

የሚሰበሰበው ገቢ በአግባቡ ተመዝግቦ መያዙን፣ ሂሳቡም በወቅቱ መሰብሰቡንና እንዲሁም በተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርአት መሰረት መፈፀሙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በብሔራዊ ቤተመንግስት አስተዳደር በአዋሽ መልካሳ እና በቆቃ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

- በቤተ መንግስቱ ቅርንጫፎች ከልዩ ልዩ የአትክልትና የአዝዕርት ምርት ሽያጮች ገቢ የሚሰበሰብ ቢሆንም፣ የተመረቱት ምርቶች ከማሣ ወደ ንብረት (ሽያጭ) ክፍል ገቢ ከተደረጉ በኋላ በገቢም ሆነ በወጪ የማይመዘገቡ መሆኑን፣

- የምርቱ ዋጋ በኮሚቴ እየተተመነ ሽያጭ የሚከናወን መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም፣ ለኮሚቴነት የተመረጡ ሰዎችን ስም ዝርዝር የኮሚቴውን የዋጋ ትመና ውሳኔ የሚያሳይ ማስረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ የዋጋ ትመናው ሂደት ግልጽነት የጎደለው መሆኑ፣

- ምርቱን ለማግኘት የወጣ ወጪ እንዲሁም ከምርቱ ሽያጭ የተገኘ ገቢ እየተመዛዘነ ለበላይ ሃለፊዎች ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑ፤

- ከዋናው መ/ቤት የመጡ ደረሰኞች በሞዴል 19 ወይም በመዝገብ የማይመዘገቡ መሆኑ፣

- በአመቱ መጨረሻ የደረሰኞች ቆጠራ ተከናውኖ የማያውቅ መሆኑ፣

- በሁለቱም ቅርንጫፎች ቀድመው የነበሩት ሠራተኞች ከቦታቸው ሲነሱ የተሰራባቸውንም ሆነ ያልተሰራባቸውን የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ርክክብ የማይደረግ መሆኑ ታውቋል።

በመሆኑም አሰራሩ ላይ የሚታየው ክፍተት ለመንግስት ገንዘብ መባከን በር ሊከፍትና ተአማኒነትም ሊያሳጣ ስለሚችል ለታዩት የአሰራር ክፍተቶች የማስተካከያ ርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በላክነው የስር አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.8 <u>የውስጥ ገቢ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት የማይደረግ ስለመሆኑ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል አስራ አንድ አንቀጽ 62 (2) እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 መሰረት የዩኒቨርሲቲዎቹን የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ወርሀዊ ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መላኩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,355,773.83 በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,677,316.21 በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 2,762,216.69 በድምሩ ብር 26,795,306.73 በ2003 በጀት ዓመት ከውስጥ ገቢ የሰበሰበቡትን ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያቀርቡት የሂሳብ ሪፖርት ያላሳወቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

- በአዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10/2 መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባሳተመው ወይም እንዲታተም በፈቀደው ደረሰኝ ገቢ ሊሰበሰብ ሲገባው በድሬድዋ ዩኒቨርሲቲና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ሳያስፈቅዱ ራሳቸው ባሳተሙት የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ገቢ የሚሰበስቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

ዩኒቨርስቲዎቹ የሚያዘጋጁት የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የመንግስት ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን የመንግስት ገቢ ላያሳይ ይችላል፡፡ ባልተፈቀደና ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ መንገድ ገቢ ሊሰበሰብና ለግል ጥቅም ሊውል ይችላል፡፡

ይኸው አሰራር ባለፈው ዓመት ሪፖርታችንም እንዲስተካከል አስተያየት ስለተሰጠ በኦዲት በሚሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት የእርምት እርምጃ የማይወስድ ከሆነ ተጠያቂነትን ለማስፈን አይቻልም፡፡ በመሆኑም ገቢ የሚሰበሰብባቸውን ደረሰኞች ህትመት በማስፈቀድ ህጋዊ በሆኑ የገቢ ደረሰኞች የውስጥ ገቢን በመሰብሰብ ሂሳቡም በአዋጁ መሰረት ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 2.9 <u>የ2002 በጀት ዓመት ገቢ በ2003 በጀት ዓመት መመዝገቡ</u>

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የበጀት ዓመቱ ገቢ በበጀት ዓመቱ መመዝገቡ ሲጣራ የ2002 በጀት ዓመት ገቢ ሆኖ ሳለ በ2003 በጀት ዓመት የተመዘገበ ብር 895,902.12 ተገኝቷል፡፡

ይህም ፈሰስ ሊደረግ የሚገባው ገቢ በወቅቱ ፈሰስ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

ሂሳቡ በወቅቱ አለመመዝገቡ የበጀት ዓመቱን የገቢ ዕቅድ አፈፃፀም ያዛባል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመት መጨረሻ (ሰኔ/30) ከመዘጋቱ በፊት በበጀት ዓመቱ የተሰበሰቡ ገቢዎች በሙሉ መመዝገባቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

## 3. የወጪ ሂሳብ

### 3.1 ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበቂ ማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤

- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት ኮሚኒኬሽን ለድህረ ምረቃ ለሚማሩ ተማሪዎች የመመረቂያ ፅሑፋቸውን ለማዘጋጀት እንዲረዳቸው ተብሎ ለተለያዩ ዕቃዎች መግዣ የሚውል የግዢ መጠየቂያ ፎርም በመሙላት በጠየቁት መሰረት ብር 157,500.00 ወጪ ተደርጎ የተሰጠ ቢሆንም፣ ዕቃዎቹ መገዛታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱን፤
- በመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የዓለም ዜናዎችን በየዕለቱ ለመለዋወጥ በተገባው ስምምነት መሰረት ለቶምሶን ሮይተርስ በባንክ ለተላለፈው ብር 231,530.75 ድርጅቱ ገንዘቡን መቀበሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃና ከድርጅቱ ጋር የተፈፀመው የውል ስምምነት ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱን፤
- በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ከመጠባበቂያ ሂሳብ ተከፍሎ ማስረጃ ሳቀርብለት የተወራረደ የመስተንግዶ ሂሳብ ብር 8,865.96 የተገኘ መሆኑን፤
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በባንክ በኩል ለDulican Inc. ለሞያ አገልግሎት ክፍያ (በተለያዩ 7 ክፍያዎች) ብር 7,453,483.91፣ ለTCT ኩባንያ L/C ለመክፈት ብር 783,679.52 እና የሥራ ጊዜውን ላጠናቀቀ ተቋራጭ ብር 6,174,846.20፤
- የደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ ለአንድ የህትመት ድርጅት ለስልጠና አገልግሎት በባንክ የተላከ ብር 74,400.00፣ ለአዲስ አበባ ዩነቨርስቲ ለሶፍት ዌር ስልጠና በባንክ የተላከ ብር 18,900.00 እና ለባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ለተማሪ ስፖርተኞች ለምግብና ለሌሎች አገልግሎቶች በባንክ የተላከ ብር 91,520.00

  በድምሩ ብር 14,985,860.38 በባንክ በኩል ተልኮ ለባለጥቅሞች ለመድረሱ ማረጋገጫ ደረሰኝ ወይም ደብዳቤ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

በባንክ የተላከው ገንዘብ ለተጠቃሚዎቹ ላይደርስ ይችላል፡፡ ገንዘቡ ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ እና ለመከታተል አመቺ ባለመሆኑ የመንግስት ገንዘብ ያለአግብብ እንዲባክን ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም በቅድሚያ በሰነድ የተከፈለው ሂሳብ ሳይወራድ ሂሳቡን በወጪ መመዝገብ ተገቢ ባለመሆኑ በቅድሚያ የተከፈለው ሂሳብ ግኘው ተፈፅሞ በሚቀርበው የወጪ ማስረጃ መሰረት ሂሳቡ እንዲወራረድ ማድረግ ማስረጃው ሳይቀርብ በወጪ የተመዘበውም ሂሳብ ማስረጃ ሊቀርብለት እንደሚገባና ክፍያዎች በባንክ በኩል ሲፈፀሙ ገንዘቡ ለባለጥቅሙ መድረሱ ሳይረጋገጥ እና ባለጥቅሙም ገንዘቡ የደረሰው ስለመሆኑ በደብዳቤም ሆነ በደረሰኝ ማረጋገጫ ሳይሰጥ ሂሳቡ በወጪ መመዝገብ እንደሌለበትና አሰራሩም ሊታረም እንደሚገባና በመመሪያው መሰረት ደረሰኝ እየቀረበለት ሊወራረድ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 3.2 ደንብና መመሪያን ሳይከተል ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል

ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የጽ/ቤቱ ጋዜጠኞችና የውጪ ሚዲያ ወኪሎች የህዳሴውን ግድብ እንዲጎበኙ እና የወቅቱን አጠቃላይ ሁኔታ እንዲዘግቡ ለማድረግ 33 ጋዜጠኞች 7 ቀን በመስክ ላይ የቆዩ ቢሆንም የተከፈላቸው የ22 ቀን የውሎ አበል በመሆኑ ብር 34,650.00 በብልጫ መከፈሉ፣ እንዲሁም ለ19 ጋዜጠኞች ደግሞ 7 ቀን በመስክ ላይ የቆዩ ቢሆንም የተከፈላቸው የ26 ቀን የውሎ አበል በመሆኑ ብር 25,270.00 በብልጫ በመከፈሉ በድምሩ ብር 59,920.00 አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ሆኖም ይህ አሰራር ለመንግስት ገንዘብ መባከንና ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል፡፡

በመሆኑም ከመመሪያ ውጭ የተፈፀመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም በውሎ አበል መመሪያ መሰረት መፈፀም እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 3.3 <u>በብልጫ ተከፍሎ የተገኘ የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና ደንብ ቁጥር 190/2002 መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ እንዲሁም ክፍያው ዩኒቨርሲቲው ላገኘው አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡

የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል የአንድ ዳቦ ዋጋ በብር 0.90 ሂሳብ ለማቅረብ ውል ስምምነት የተፈፀመ ቢሆንም፣ ክፍያው የተፈፀመው ግን በውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ በብር 1.10 ሂሳብ በመሆኑ ምክንያት ብር 40,745.22 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ እንዲሁም ለተማሪዎች እንጀራ ለማቅረብ በተደረገው ውል መሰረት 375 ግራም እንጀራ በብር 2.10 ለማቅረብ የውል ስምምነት የተገባ ቢሆንም፣ ክፍያ የተፈጸመው በብር 2.25 ሂሳብ በመሆኑ ምክንያት ብር 14,904.56 በብልጫ የተከፈለ በመሆኑ በጠቅላላው ብር 55,649.78 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በገባው ውል መሰረት ክፍያ መፈጸም ያለበት ሲሆን፣ ውሉን ለመለወጥ አሳማኝ ምክንያትም ካለ የውል ማሻሻያ በማድረግ ክፍያ የሚፈጸምበትን አሰራር ሊዘረጋ እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በዚሁ መሰረት የሥራ አመራሩ የዱቄት ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት አቅራቢው ዋጋ እንዲሻሻልላቸው በጠየቁት መሰረት የአስተዳደር ካውንስሉ ጉዳዩን በጥልቀት ከመረመረ በኋላ ወሳኔ ያሳለፈ መሆኑን የሚገልጽ ቃለ ጉባኤ ከስራ አመራር ሪፖርት ጋር ተያይዞ ተልኳል፡፡ ይሁን እንጂ በስብሰባው ላይ ተገኙ የተባሉት ሰዎች ብዛት 15 ሲሆኑ በውሳኔው ላይ መስማማታቸውን በመግለጽ የፈረሙት ሰዎች ብዛት 4 ብቻ ከመሆናቸው በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት (ሰብሳቢው) ያልፈረሙበት ሰነድ በመሆኑ የተላከው ማስረጃ ትክክለኛነት አጠራጣሪ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የማስረጃው ትክክለኛነት ሊጣራ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.4 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቀረጠለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዙ እቃዎች ለመ/ቤቱ ገቢ የተደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ብር 56,666.27 ወጪ የተደረገባቸው 11 የDSTV መገልገያ ካርዶች፣ ብር 25,447.20 ወጪ የተደረገባቸው 24 የታተሙ መጽሔቶች እና ብር 51,233.65 ወጪ የተደረገባቸው 2400 የታተሙ የጥሪ ካርዶች በድምሩ ብር 133,347.12 የሚያወጡ ንብረቶች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸው ሳይረጋገጥ ሂሳቡ በወጪ መመዝገቡ ድርጅቱ ላልተረከበው ንብረት ክፍያ ሊፈጽም ይችላል፡፡

በመሆኑም ለእቃ ግዥ ወጪ የሆነ ሂሳብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው ንብረቶች ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.5 <u>የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ</u>

የተመዘገቡት የበጀት ዓመቱ ወጪዎች በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ (የሂሳብ መደብ 4201) መመዝገብ የሚገባው ብር 1,756,123.46 በረጅም ጊዜ የሠራተኞች ብድር (የሂሳብ መደብ 4203) ተመዝግቦ መገኘቱ፣ እንዲሁም በነዳጅ ወጪ (የሂሳብ መደብ 6217) መመዝገብ የሚገባው ብር 1,294.75 በመስተንግዶ (የሂሳብ መደብ 6233) መመዝገቡ፤ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለትራንስፖርት ወጪ ሆኖ የተከፈለው ሂሳብ ብር 934.91 በሂሳብ መደብ 6232 ሊመዘገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 6231 መመዝገቡ፤ ለካረቢያን ምንጣፍ ግዥ ለቅድመ ታክስ (Withholding tax) ወጪ ሆኖ የተከፈለው ሂሳብ ብር 1,905.70 በሂሳብ መደብ 6314 ሊመዘገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 6313 መመዝገቡ እና በደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ ለኩሽና (ማብሰያ ቤት) ማሰሪያ ለተለያዩ ቁሳቁሶች ግዥ ወጪ የተደረገው ብር 10,299.40 በወጪ ሂሳብ መደብ በ6323 መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 6244 በወጪ መመዝገቡ፤ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ብር 17,932.76 በሂሳብ መደብ 6251 መሆን ሲገባው በ6314 መመዝገቡ፤ እንዲሁም በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በሂሳብ መደብ 6313 መመዝገብ ሲገባው በ5054 የተመዘገበ ብር 11,030,800.46 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 6323 መያዝ ሲገባው በ6244 የተያዘ ብር 560,332.08 በድምሩ ብር 18,591,226.54 የሂሣብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ይህም የመ/ቤቱን ትክክለኛ የበጀት አፈጻጸም ለመለካት አያስችልም፡፡ በተጨማሪም የመንግስት አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ትክክለኛ የሂሣብ መደቡን ጠብቆ መመዝገብ ያለበት ሲሆን ሂሣቡም በትክክል ስለመመዝገቡ የሚረጋገጥበት ሥርዓትም መዘርጋት አለበት፡፡ በመሆኑም ከላይ የተመለከቱት የምዝገባ ስህተቶች የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የተስተካከለ የሂሳብ ሪፖርት ሊዘጋጅ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.6 ጨረታ ሣይወጣ የተፈፀመ ግዥ

በበጀት አመቱ የተፈጸሙ ግዢዎች በግዥ አዋጅና መመሪያዎች መሰረት መፈጸማቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 8,332,821.66 ደንብና መመሪያ ሳይከተል ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-18 ተመልክቷል/

ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸመው ግዥ በዝርዝር ሲታይ በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ለጽ/ቤቱ አገልግሎት የሚውሉ ሁለት ላፕቶፕ፤ አስር Dell ኮምፒውተሮችን፤ አምስት HP ኮምፒውተሮችን እንዲሁም አስራ ስምንት ዩፒ ኤስ ኮምፒውተሮች እና የኮምፒውተር እቃዎችን በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ በዋጋ ማቅረቢያ /proforma/ አማካኝነት ከ 20/10/03 እስከ 30/10/03 ባለው ጊዜ ውስጥ ግዥ ተፈጽሞ መገኘቱ፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ መቀሌ እና ሞያሌ የሚያስገነባውን ህንጻ ያለምንም የጨረታ ውድድር የግንባታ ስራውን የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት እንዲሰራው በማድረጉ፣ የደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ በለቀማ አተር መግዛቱ እና የኢ.ት. ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን ሌሎች ተጫራቾች ሣይሳተፉ በቀጥታ ለኮንስትራክሽን ዲዛይን አ.ማ ሥራውን እንዲሠራ መደረጉ ታውቋል፡፡

የፕሮፎርማ ግዥ ተመራጭ የሆነ የግዥ መንገድ ባለመሆኑ በግዥ እቅድ መሰረት በአንድ ጊዜ ግዥ እንዲፈፀም ሣይደረግ በበጀት ዓመት መጨረሻ በጥድፊያ በርካታ ግዥዎችን መፈፀም የመንግስት ገንዘብ ለብክነት እንዲጋለጥ ሊያደርግ ከመቻሉ በተጨማሪ መ/ቤቶቹ ሊያገኙ የሚችሉትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያሳጣው ይችላል፡፡ አሰራሩም መመሪያውን ያልተከተለ ከሆነ ለሙስና በር ሊከፍት ይችላል፡፡

በመሆኑም አሰራሩ ለከፍተኛ ወጪ የሚዳርግ በመሆኑ በግዥ በአዋጁ መሰረት የግዥ እቅድ ተዘጋጅቶ የዕቃዎች ግዢም ሆነ የግንባታና የምክር አገልግሎት በግዥ አዋጅ መሠረት በጨረታ መፈፀም እንደሚኖርበትና ግዥን በለቀማ መፈጸም ሲያስፈልግ ያስፈለገበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስታወሻ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ለዚህ ስራ በኃላፊው ውክልና ለተሰጠው አካል ቀርቦ መፈቀድ እንደሚኖርበት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳሳበናል፡፡

3.7 <u>የዋጋ ውድድር ሳይደረግ ከአንድ ድርጅት ብቻ የተፈፀመ ግዢ</u>

በበጀት አመቱ የተፈጸሙ ግዢዎች፣ በግዢ አዋጅና መመሪያው መሰረት የዋጋ ውድድር ተደርጎ የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ለጽ/ቤቱ አገልግሎት የሚውል ምንጣፍ በብር 24,200.00 ከሙናጃ አብዲ መሐመድ እንዲሁም የተለያዩ የድምፅ መቅጃ ዲቪካሞች በብር 93,300.65 ከግሎሪየስ ኃ/የተ/የግል ማህበር እንዲሁም በሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በተለያዩ ሆቴሎች ስልጠና ለተሰጠበት የተከፈለ ብር 227,565.92 በጠቅላላው ብር 3345,066.57 በአዋጁ መሰረት የዋጋ ውድድር ሳይደረግ ከአንድ አቅራቢ ብቻ የአገልግሎት ግዥው መፈጸሙ ታውቋል፡፡

አሰራሩ የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ እንዲጋለጥ ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ ሌሎች ተወዳዳሪ ድርጅቶች እንዳይሳተፉ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያውን ተከትሎ ግዥ መፈፀም እንደሚኖርበት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.8 <u>ጨረታውን ካላሸነፈ ድርጅት የተፈፀመ ግዢ</u>

በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት አነስተኛ የመወዳደሪያ ዋጋ ካቀረበው ተጫራች ግዢ መፈጸሙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት ብር 15,120.00 ያቀረበ ድርጅት እያለ ብር 16,590.00 ካቀረበ ድርጅት ግዥ በመፈፀሙ የብር 1,470.00 ብልጫ ተከፍሎ የኮምፒውተር ቫይረስ መከላከያ (antivirus) ግዢ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

አሰራሩ መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ እንዲሁም ለሙስናና ለብክነት በር የሚከፍት ሊሆን ይችላል፡፡

ስለሆነም ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ድርጅት እያለ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ግዥ መፈፀም ያስፈለገበትንና ጨረታው ውጤታማ ያልሆነበት ምክንያት ተገልፆ ለበላይ ኃላፊ ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች ውስጥ አነስተኛ የገንዘብ መጠን ያቀረበው ተወዳዳሪ ሊመረጥ እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.9 <u>የታደሰ የንግድ ፈቃድ ካላቀረበ ድርጅት የተፈፀመ የመጽሄት ሕትመት</u>

በንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 28 ንኡስ አንቀፅ 1/ረ መሰረት የአገልግት ግዥ የተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ለጽ/ቤቱ አገልግሎት የሚውል ብዛታቸው 2000 የሆኑ መጽሔቶች በብር 13,890.95 የታተሙ ሲሆን፣ አገልግሎቱን የሰጠው ድርጅት የታደሰ የንግድ ያላቀረበ እና ሁኔታውም ያልተጣራ መሆኑ ታውቋል፡፡

አሰራሩ የግብርና ታክስ ግዴታቸውን ያልተወጡ ነጋዴዎችን የሚያበረታታና ለሙስና ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

በአዋጁ መሰረት የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ ያለውና በኢትዮጵያ የግብር ህጎች በተደነገገው መሰረት የግብርና ታክስ ግዴታውን ከተወጣ አቅራቢ ግዥ ሊፈጸም እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.10 <u>ያለአግባብ የተከፈለ ክፍያ</u>

ክፍዎች በትክክል መፈጸማቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤

- የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት ብር 1004.25 ለውሎ አበል፤
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ብር 208,000.00 የማበረታቻ (Bouns) ክፍያ፤
- የኢ.ት. ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን ብር 11,451.68 የ2002 እና 2003 በጀት ዓመት የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ለ5 ሠራተኞች የተከፈለ ክፍያ፡
- የደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 መሰረት ዩኒቨርስቲው ለትምህርት የሚያስከፍላቸውን የክፍያ አይነቶች መጠን እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት በወሰነው መሰረት የተቋሙን ገቢ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ተከፋይ አበሎችን፣ የትርፍ ሰዓት

ክፍያዎችንና የመሳሰሉትን ለቦርድ በማቅረብና በማስወሰን ስራ ላይ ማዋል እንደሚችል የተደነገገ ቢሆንም፣ በአዋጁ ከተፈቀደው ውጭ ለዩኒቨርስቲው የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ብር 57,253.73 የትርፍ ሰአት ክፍያ፤

- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ የትርፍ ሰአት ክፍያ እንዲከፈል የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ሰኔ 29/2001 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ30/ጠ13/36/83 ፈቅዶ የነበረ ሲሆን፣ ጳጉሜ 5/2001 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ30/ጠ13/37/820 ደግሞ ክፍያው እንዲቆም የተደረገ ቢሆንም ባለአደራ ቦርዱ ብር 76,775.32 የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣ ለከባድ ስራ አበል ብር 3,948.00 እና ለአቧራ አበል ብር 210.00 በድምሩ ብር 80,933.32 በመከፈሉ፤ በድምሩ ብር 358,642.98 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

  የመንግስት ልማት ድርጅቶች ባለ አደራ ቦርድ በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት ተመሳሳይ ክፍያ ተፈጽሞ በመገኘቱ ያለአግባብ የተፈጸመው ክፍያ እንዲመለስ ወይንም የቦርዱን ስራ ለማከናወን የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚታመን ከሆነ ለሚመለከተው አካል ጉዳዩን አቅርቦ ማስፈቀድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም፣ በዚሁ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉ እና ድርጊቱ በ2003 በጀት ዓመትም መቀጠሉ ታውቋል፡፡

  ያልተፈቀዱ ክፍያዎችን መፈፀም መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል፡፡ የመ/ቤቶቹም አሰራር የፋይናንስ አዋጅና መመሪያዎችን ተከትሎ እንዳይሰራ የሚገፋፋ ነው፡፡

  በመሆኑም ከመመሪያ ውጭ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ እና ለወደፊቱም በመመሪያ መሠረት እንዲፈፀም ተገቢው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

### 3.11 ከውክልና ገደብ በላይ የተፈቀደ ክፍያ

በመንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 አንቀጽ 3 ከሀ-ሐ መሠረት የስልጣን ውክልና የተሰጣቸው ሀላፊዎች በተሰጣቸው ገደብ መሰረት የሚያከናውኑ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የስልጣን ውክልና ባልተሰጠው በበጀት ሂሳብ ዋና ክፍል ኃላፊ ፊርማ ብር 562,522.50 ጸድቆ መገኘቱ፣በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ

ማጥፊያ ብሔራዊ ጽ/ቤት ለፋይናስ ግዥና ንብረት ኃላፊ የተሰጣቸው ውክልና እስከ ብር 5000.00 ወጪ ላይ እንዲፈቅዱ ሆኖ ሳለ ብር 182,326.00 ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሌተር ኦፍ ክሬዲት መክፈቻ በክፍያ ማዘዣ ላይ ፈቅደው ተገኝተዋል፡፡

አሰራሩ ወጪዎች በስልጣን ገደብ መሰረት ተከፋፍለው እንዲፈቀዱ የሚደረጉት ሥራን ለማቀላጠፍ ቢሆንም የስልጣን ውክና የሌላቸው ሰራተኞች ገንዘብ እንዲፈቅዱ ማድረግ ተጠያቂ ለማድረግ አስቸጋሪ የሚሆን ከመሆኑም በላይ ለመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ መባከን መንስኤ ስለሚሆን የስልጣን ውክልና ሳይኖር በገንዘብ ላይ የማዘዝ ስልጣን ሊሰጥ አይገባም፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጸም ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.12 <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብ</u>

በወጭ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በ2002 በጀት ዓመት የህትመት አገልግሎት ሂሳብ ብር 38,754.04 ወጪው በ2003 በጀት ዓመት መመዝገቡ፣ የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ አየር መንገድ በ2002 በጀት ዓመት ያገኘውን ብር 8,779,302.00 የትራንስፖርት አገልግሎት ሂሳብ በ2003 በጀት ዓመት በወጪ መመዝገቡ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደግሞ በ2002 በጀት ዓመት ለመስተንግዶ የተከፈለ ሂሳብ ብር 20,882.80 እና ለነዳጅ የተከፈለ ሂሳብ ብር 82,317.33 ወጪው በ2003 በጀት ዓመት መመዝገቡ እና የኢትዮጵያ ስብሰባ ማዕከል በ2002 በጀት ዓመት ለተገኘ አገልግሎት ሊከፈልና ሊመዘገብ የሚገባው የውሎ አበል ክፍያ ብር 2000.20 በ2003 በጀት ዓመት መከፈሉና መመዝገቡ፤ በድምሩ ብር 8,921,256.17 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ በመሆኑ፤ የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የየመ/ቤቶቹ ስራ አመራር በሰጡት ምላሽ፤የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የህትመት አገልግሎት ብር 38,754.04 ወጪው በ2003 በጀት ዓመት የተመዘገበው አገልግሎቱን የሰጠው ድርጅት የክፍያ ጥያቄ ያቀረበው የበጀት ዓመቱ ካለፈ በኋላ በመሆኑ እንደሆነ እና ለወደፊቱ በበጀት ዓመቱ የተገኘ የአገልግሎት ክፍያ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ ተገቢውን ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን፣የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ከጽ/ቤቱ የሥራ ባህሪ የተነሳ ለቻርተር ጉዞ የትራንስፖርት አገልግሎት አስቀድሞ በጀት የማይያዝ በመሆኑና ጉዞው በተለይ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚደረግ ከሆነ በጀት የማስፈቀዱ ሂደት ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ምክንያት ሂሳቡን አገልግሎቱ በተገኘበት በጀት ዓመት ለመመዝገብ መቸገራቸውን ገልጸው፤ ለወደፊቱ ጉዳዩን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ጋር በመነጋገር የኦዲቱን አስተያየት ለመተግበር እንደሚሞክሩ ገልፀው፤ ለወደፊቱ ግን የተሰጣቸውን የማሻሻያ ሀሳብ እንደሚቀበሉ ገልፀዋል፡፡

3.13 <u>የጊዜ ገደቡን ጠብቆ ያልተወራረደ ሂሳብ</u>

በውጭ አገር ጉዞ የውሎ አበል መመሪያ አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ለመኝታና ለቁርስ እንዲሁም ለመጠባበቂያ የተወሰደ ገንዘብ በወቅቱ የሚወራረድ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ለውጭ አገር ጉዞ ለውሎ አበል ከተከፈለው ሂሳብ ውስጥ በጊዜ ገደቡ ውስጥ ያልተወራረደ ብር 397,983.33፤ እንዲሁም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በመመሪያው ላይ በተቀመጠው ቀነ ገደብ ውስጥ ያልተወራረደ ብር 19,169.50 ተገኝቷል፡፡

በቅድሚያ የተወሰደ ገንዘቡ ሳይወራረድ በቆየ ቁጥር ሊሰበሰብ የማይችልበት ዕድል ሊያጋጥም ይችላል፡፡

በመሆኑም ለውጭ አገር ጉዞ በቅድሚያ የተከፈለ ውሎ አበል በመመሪያው ላይ በተቀመጠው ቀነ ገደብ መሰረት እንዲወራረድ ተገቢው ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.14 <u>በድጋሚ የተከፈለ የውሎ አበል</u>

በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ክፍያ የፋይናንስ አዋጁን፣ ደንቡን እና መመሪያዎችን ተከትሎ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በድጋሚ የተከፈለ የአንድ ቀን የውሎ አበል ብር 9,590.00 (137 ሰልጣኞች x70) ተገኝቷል፡፡

የውሎ አበል ሂሳብ ሲከፈል ወይም ሲወራረድ ሊከፈል የሚገባው ቀን ብዛት ትክክል መሆኑ እየተረጋገጠ ሊሆን ይገባል፡፡ በድጋሚ የተከፈለውም የውሎ አበል ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ መደረግ እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.15 <u>በበጀት ዓመቱ ያልተሰበሰበ የወጪ መጋራት ሂሳብ</u>

የወጪ መጋራት አሰባሰብ መመሪያ ቁጥር 26/2001 ክፍል 5.2/ሀ መሰረት የተቀጣሪዎች የእፎይታ ጊዜ እንደተጠናቀቀ ከጥቅል የወር ደመወዝ ላይ 10% በአሰሪው እየተቀነሰ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈሰስ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የእፎይታ ጊዜያቸውን የጨረሱ 31 ሠራተኞች (ከጥቅምት 1/2002 እስከ መስከረም 30/2003) ሊሰበሰብ የሚገባው ብር 37,879.20 (ከጥቅምት/2003 እስከ ሰኔ 30/2003 ዓ.ም) መሰብስብ ያልተጀመረ መሆኑ ታውቋል፡፡

አሰራሩ መሰብሰብ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ሊዘገይ ከመቻሉም በላይ ሳይሰበሰብ ሊቀር የሚችልበትም አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡

በመሆኑም የወጪ መጋራት ሂሳብ በመመሪያው በተቀመጠው ቀነ ገደብ መሰረት እንዲሰበሰብ ተገቢውን ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና ያልተሰበሰበውም ሂሳብ እንዲሰበሰብ ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.16 <u>ባልታደሰ ውል የተከፈለ የቤት ኪራይ ሂሳብ</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለቤት ኪራይ ለሚከፍለው ሂሳብ ውል የገባ እና ክፍያውም በውሉ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በውሉ አንቀጽ 12 ከተራ ቁጥር 1-2 መሰረት ወሉ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት የፀና እንደሚሆንና የውሉ ዘመን ሲፈጸም ተከራይ ውሉን ለሌላ ዘመን የማሳደስ ግዴታ እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም በውሉ ላይ በተገለጸው መሰረት በ2003 በጀት ዓመት ለውሉ እድሳት ሳይደረግ (በ2000 በጀት ዓመት በተደረገ ውል አማካኝነት) ብር 17,146.60 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ውልን በወቅቱ አለማደስ አለመግባባትን ሊያስከትል ስለሚችል በውሉ ላይ በተቀመጠው ቀን መሰረት ውሎችን አድሶ አላስፈላጊ አለመግባባቶችን ቀድሞ

እንዳይደርሱ መከላከል ይገባል፡፡ በመሆኑም የውል ስምምነቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡

3.17 <u>የምዝገባ ስህተትን በተመለከተ</u>

በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ትክክል መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሔራዊ ጽ/ቤት በወጪ ሂሳብ መደብ 6311 የተመዘገበው ሂሳብ  በብር 58,948.30 (በዴቢት) ብልጫ የሚያሳይ መሆኑ እንዲሁም በሂሳብ መደብ 6256 የተመዘገበው ደግሞ በተመሳሳይ የገንዘብ መጠን ማለትም በብር 58,948.30 (በክሬዲት) የሚያንስ በመሆኑ ፤ የጽ/ቤቱ የበጀት አፈጻጸም ትክክለኛውን ሁኔታ ላያሳይ ይችላል፡፡

የሂሳብ ማስተካከያ ሊሰራለት እና የሂሳብ መግለጫውም በዚሁ መሰረት ተስተካክሎ ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

3.18 <u>ከተመደበው የውሎ አበል የክፍያ ተመን በላይ የተፈፀመ ክፍያ</u>

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በውጭ አገር ጉዞ የውሎ አበል መመሪያ በሠንጠረዥ ሁለት በፊደል ለ በምድብ ሁለት የተመደቡ አገሮች ዝርዝር መሠረት ለቱርክ የምሳና የእራት የውሎ አበል $50 ሆኖ ሳለ $80 ለልዑክ ቡድኑ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡በዚሁ ምክንያት በጠቅላላው በብልጫ $924 የተከፈለ ሲሆን፣ በዕለቱ በዋለው የባንክ ምንዛሬ መጠን ወደ ብር ሲመነዘር ብር 15,542.97 ($924*16.8214) በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

በየምድቡ ለሚገኙ አገሮች በተመደበው ተመን መሰረት የውሎ አበል ክፍያ የማይፈፀም ከሆነ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ወጪ ይሆናል፡፡

በመመሪያው መሠረት ለየአገሮቹ በተመደበው የምሳና የእራት የውሎ አበል ተመን ዝርዝር መሰረት ክፍያ ሊፈፀም የሚገባ ሲሆን ከተመን በላይ የተከፈለውን የውሎ አበል ሂሳብ በተመለከተ ከሚመለከታቸው ተጓዦች ላይ ገንዘቡ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.19 <u>ቅድመ ታክስ ሳይቀነስ ስለተፈጸመው ክፍያ</u>

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 መሰረት ከሚፈጽመው የግዥ/የአገልግሎት ክፍያ ላይ የቅድመ ክፍያ ታክስ እየተቀነሰ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ የሚያደርግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለጥገና አገልግሎት ከተፈጸመው ክፍያ

ብር 12,308.59 ላይ ቅድመ ታክስ ብር 246.17 ሳይቀነስ ክፍያ መፈጸሙ፣የኢትዮጵያ ስብሰባ ማዕከል ለኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከከፈለው ብር 6,994.15 የአገልግሎት ክፍያ ላይ 2% ብር 139.88፣ እንዲሁም በማዕከላዊ እስታስቲክስ የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት ለተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት ከፈጸመው ክፍያ ቀንሶ ያስቀረውን የቅድመ ታክስ ገቢ ብር 168.27 ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባው ታክሱን ሳይቀንስ ክፍያውን ለድርጅቱ መክፈሉ እና የደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ ለስልጠና አገልግሎት ከፈጸመው ክፍያ ብር 74,400.00 ላይ በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ተቀንሶ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ መደረግ የነበረበት የቅድመ ታክስ (withholding tax) ብር 1,488.00 ሳይቀነስ ክፍያ መፈጸሙ ታውቋል፡፡

መንግስት ሊሰበስብ የሚገባው ገቢ ሳይሰበሰብ ሊቀር ከመቻሉም በላይ የህግ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

በመሆኑም በአዋጁ መሰረት ከክፍያ ላይ ተቀንሶ መቅረት ያለበት ቅድመ ታክስ (withholding tax) መሰብሰብ እና ለሚመለከተው መ/ቤት ፈሰስ መደረግ የሚኖርበት ሲሆን ሳይሰበሰብ የቀረውም የቅድሚያ ታክስ ሊሰበሰብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 3.20 <u>በግዥ መጠየቂያ ላይ ከተፈቀደው በላይ የተገዛ</u>

ግዥ የተፈጸመው በቀረበው ጥያቄ እና በሀላፊ በተፈቀደው ልክ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ 10 የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ እንዲገዛ ተጠይቆና ተፈቅዶ ሳለ 30 የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ተገዝቶ ተገኝቷል፡፡

ተጠይቆ ከተፈቀደው በላይ ግዥ የሚፈፀም ከሆነ ንብረቱ ለብክነት ሊዳረግ ከመቻሉም በላይ ሳይፈቀድ ግዥ ሊፈጸም ይችላል፡፡

በመሆኑም መያዝ ያለበትን የስቶክ መጠንና የግዥ መጠን ለመወሰን ሊታዩ ከሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ ለመደበኛ ሥራ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉ የስቶክ ፍላጎቶችን፣ የታዘዙ ዕቃዎች መጋዘን ለመድረስ የሚፈጅባቸውን ጊዜ፣ የመጋዘኑ የመያዝ አቅም እና የግዥ ትዕዛዙን ለመፈፀም የሚያስፈልገውን ወጪ ሊታዩ የሚገባቸው በመሆናቸው የግዥ መጠን በዘፈቀደ የሚወሰንና ከሚሰራው ስራ ጋር ያልተገናዘበ እና ያልተጠየቀ መሆን እንደሌለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.21 <u>ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡ ተጫራች የተፈፀመ ግዥ</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሰኔ 2002 ባወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ 16.7.3.2 (ሀ) መሠረት መመዘኛውን ካሟሉ ተጨራቾች መካከል አነስተኛ ዋጋ ያቀረበው ተጫራች መመረጡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የጽህፈት ዕቃ ለመግዛት ከተሰበሰበው ፕሮፎርማ ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ግዥ መፈጸሙ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ስምዋ ሽለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሔራዊ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ደግሞ እስኪሪፕቶ ለመግዛት ከተሰበሰበው ፕሮፎርማ ውስጥ ብር 5195.50 ያቀረበ ተወዳዳሪ እያለ ብር 5,500.00 ካቀረበ ድርጅት ግዥ መፈፀሙ፣ በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት ብር 15,120.00 ያቀረበ ድርጅት እያለ ብር 16,590.00 ካቀረበ ድርጅት ግዥ በመፈፀሙ የብር 1,470.00 ብልጫ ተከፍሎ የኮምፒውተር ቫይረስ መከላከያ (antivirus) ግዢ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ ድርጅቶች እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡ ድርጅቶች ግዥ ሲፈፀም ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበው የተመረጡበት ምክንያት በመመሪያው መሰረት መገለፅ እና መፈቀድ አለበት፡፡ ማስረጃውም ለኦዲት ወይም ለማጣራት ስራ ሲፈለግ ሊቀርብ በሚችልበት ሁኔታ ወይም ከግዥ ሰነዶች ጋር ተያይዞ ሊቀመጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.22 <u>የግዥ ዕቅድ ያልተዘጋጀ ስለመሆኑ</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ክፍል 3 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ማእከሉ የስራ ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ግዥ በወቅቱ ለመፈጸም የሚያስችል በመርሀ-ግብር የተደገፈ በበጀት ዓመቱ የሚፈጸመውን ግዥ የሚያሣይ ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ያዘጋጀ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የኢትዮጵያ ስብሰባ ማዕከል የ2003 በጀት ዓመት የግዥ ዕቅድ ያለማዘጋጀቱ ሲታወቅ ፤ይህም የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን እና ቁጠባን መሰረት ያደረገ ግዥ ላይከናወን ይችላል፡፡

በመሆኑም ማእከሉ በግዥ አዋጁ መሠረት በበጀት ዓመቱ የሚፈጸመውን ግዥ በመርሐ-ግብር የተደገፈ የሥራ ፕሮግራም በማዘጋጀት ዓመታዊ የግዥ ዕቅድን አዘጋጅቶ በማጸደቅ ግዥን ሊፈጽም እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.23 የፕሮጀክት ሂሣቦች ገቢም ሆነ ወጪ በሂሣብ መደብ 5054 ተመዝግቦ መገኘቱ

በኢንፎርሽን መረብ ደህንነት የተለያዩ የሲስተም ዝርጋታ ፕሮጀክቶችን በማከናወን የውስጥ ገቢ የሚሰበስብ እና ለፕሮጀክቶቹም ማስፈጸሚያ ከሚያገኘው ገቢ በቀጥታ ወጪ የሚያደርግ ሲሆን በዚህም መሰረት የፕሮጀክቶቹን ገቢ ሆነ ወጪ ለገንዝብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ መደረጉን እንዲሁም የሂሳብ ምዝገባውም በመንግስት የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት መሰረት መከናወኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ኘሮጀክቶቹ የሚያስገኘው ገቢ እና የኘሮጀክቶች ግንባታ ወጪዎችን በተከፋይ የሂሣብ መደብ 5054 ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አልተወሰደበትም፡፡

ይህም የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛውን መረጃ አይሰጥም፡፡

በመንግሥት ሂሣብ አወቃቀር ሥርዓቱ ከተፈቀደው የሂሳብ ርዕስ ውጪ መጠቀሙ ኤጀንሲው በዓመቱ ውስጥ ላከናወናቸው ሥራዎች ፋይናንስ ሪፖርቶች በትክክል የዓመቱን እንቅስቃሴ ሊያሣይ አይችልም፡፡ በመሆኑም ኤጀንሲው የኘሮጀክቱን ሂሳብ በመንግስት የሂሣብ አወቃቀር /Chart of Account/መሰረት መዘጋጀት እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.24 በንብረትና በገንዘብ ያዥነት እና በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰሩ ሠራተኞች ዋስትና አለመቅረቡ

የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 አንቀጽ 6/01 መሰረት በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሠራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ ያቀረቡ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የንብረት ያዥሠራተኞች ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና እንዲያቀርቡ ያልተደረገ መሆኑ፤ የልማት ድርጅቶች ባለአራ ቦርድ አራት ሠራተኞች ዋስ ወይም ተያዥ የሌላቸው መሆኑ እንዲሁም ለአንድ ረዳት ንብረት ያዥ የቀረበው ዋስ/ተያዥ የወር ደመወዝ ከብር 2,000.00 በታች መሆኑ፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በገንዘብ ያዥነት የተመደቡ 1 (አንድ) ሠራተኛ፣ እና በንብረት ያዥነት የተመደቡ 3 (ሶስት) ሠራተኞች ዋስ ወይም ተያዥ የሌላቸው መሆኑ እና በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በገንዘብ ያዥነት

የተመደቡ 2 (ሁለት) ሠራተኞችና በንብረት ያዥነት የተመደቡ 1 (አንድ) ሠራተኛ ዋስ ወይም ተያዥ የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

ሰራተኞች በሀላፊነታቸው ስር ያሉ ንብረቶችን ቢያጠፉና ቢሰወሩ ተጠያቂ ሊደረግ የሚችል አካል ላይኖር ይችላል፡፡

በመመሪያ ቁጥር 11/2003 መሠረት ሠራተኞቹ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚመጥን ዋስትና እንዲያቀርቡ ማድረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.25 ለፋይናንስ ኃላፊ በፅሁፍ የተሰጠ የስልጣን ውክልና አለመኖሩ

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 በተራ ቁ.3 መሰረት የመ/ቤት ኃላፊዎች ዝርዝር የፋይናንስ ጉዳዮችን በተመለከተ የፋይናንስ ስራ ለሚያከናውን የሥራ ክፍል ኃላፊ ውክልና መስጠት ፤ ተወካዩም ለሌሎች በፋይናንስ የሥራ ሂደት ለተመደቡ ሠራተኞች መወከል የሚችልበት ኃላፊነት ሊሰጥ የሚችል መሆኑን እና እንዲህ ዓይነቱ ውክልናም የቁጥጥር፣ የሪፖርትና የተጠሪነት ግልፅ የሆነ መስመር መዘርጋት እንዳለበት የሚገልጽ ቢሆንም፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ፋይናንስ መምሪያ ጊዜያዊ ኃላፊ በገንዘብ ላይ የማዘዝ የስልጣን ውክልና እና እስከ ስንት ብር ድረስ ወጪ መፍቀድ እንደሚችሉ የሚገልጽ የፅሁፍ ውክልና ሳይሰጣቸው የክፍያ ትዕዛዝ ደብዳቤ የሚፅፉና በወጪ ማስመስከሪያ ላይ ወጪውን ያዘዘው ሀላፊ በሚለው ቦታ ላይ የሚፈርሙ በመሆኑ የአሰራር ችግር ቢከሰት የሚመለከተውን ሰራተኛ ተጠያቂ ለማድረግ ያስቸግራል፡፡

በመሆኑም ወጪውን የሚፈቅዱ የፋይናንስ ኃላፊዎች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ ቁጥር 6/2003 መሠረት የስልጣን ውክልና ገደብ በፅሑፍ እንዲሰጣቸው መደረግ እንደሚኖርበት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 3.26 ግብር ያልተቀነሰበት የቤት አበል ክፍያ

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 13 እንዲሁም በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀፅ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ (ጥቅማ ጥቅም) ለምሳሌ የቤት አበል ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንዲከፈልበት ቢያዝም በ2003 በጀት ዓመት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከአዋጁ እና ከደንቡ

ውጪ ለመምህራን እና ለኃላፊዎች ከሚከፈለው የቤት አበል ላይ ግብር እንደማይቀንስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በገቢ ግብር አዋጅና ደንቡ መሠረት የቤት አበል ላይ ግብር እንዲቀነስ ካልተደረገ የመንግሥት የግብር ገቢ አለአግባብ እንዳይሰበሰብ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ ዩኒቨርሲቲው በግብር አዋጅ እና ደንብ መሰረት እንዲፈፀም እና እስካሁንም ያልተቀነሰው ግብር ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተመላሽ መደረግ እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.27 በዩኒቨርሲቲው ውስጥ መመገብ ለማይፈልጉ ተማሪዎች የሚከፈለው

<u>ክፍያ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ ያልተቻለ ስለመሆኑ</u>

በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች መመገቢያ ካፌ የማይጠቀሙ ተማሪዎች ክፍያ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣ በፋይናንስ ንዑስ የስራ ሂደት እና በተማሪዎች ምግብ ቤት ክፍል በተማሪዎች ምግብ ቤት ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎች ብዛት ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ እና ይህንንም ለመቆጣጠር የሚያስችል የተዘረጋ የቁጥጥር ስርዓት የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች መመገቢያ ካፌ የማይጠቀሙ ተማሪዎች በተመለከተ የተፈጸሙ ክፍያዎች ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

በገንዘብ የተከፈላቸው ተማሪዎች መመገቢያ ካፌ እየተጠቀሙ አለአግባብ ሊከፈላቸውና ዩኒቨርስቲውም ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል ፡፡

በመሆኑም በዩኒቨርሲቲው መመገቢያ የማይጠቀሙ ተማሪዎች ብዛት በየጊዜው መመዝገብ ያለበት እና በትክክልም ሊታወቅ የሚችልበት የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.28 <u>በባለስልጣኑ ለተለያዩ ታሪካዊ ቅርሶች እንክብካቤ ሥራ ላይ የሚውል</u>

<u>የበጀት ድጋፍ አከፋፈል እና የቁጥጥር ስርዐት በተመለከተ</u>

ባለስልጣኑ ለክልሎች ለቅርስ ጥናትና እንክብካቤ የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ በትክክል ለተባለለት ዓላማና አገልግሎት ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከክልሎቹ ወጪ ለመሆኑ ማረጋገጫ እና በበቂ ማስረጃ ሳይደገፍ በስራ ላይ እንደዋለ ተቆጥሮ በ6412 ሂሳቡ በቀጥታ ወጪ ብር 5,962,482.58 እንዲሁም በሂሳብ

መደብ 6244 ብር 813,800.00 በድምሩ ብር 6,776,282.58 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ለክልሎች የሚላከው ገንዘብ በበቂ ማስረጃ ሳይደገፍ በስራ ላይ እንደዋለ ተቆጥሮ ሂሳቡ በቀጥታ እንደወጪ ተመዝግቦ መያዙ ገንዘቡ በትክክል ለተባለለት አላማና አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ አይቻልም ይህም የመንግስት ገንዘብ ያላግባብ እንዲባክን ያደርጋል ፡፡

በመሆኑም ክፍያዎች ለክልሎች ከተፈጸሙ በኋላ በትክክል ስራ ላይ ለመዋላቸው በቂ ማስረጃ ሊቀርብላቸው፣ በማስረጃ ሊደገፉ እና አስፈላጊው የቁጥጥር ስርአት ሊዘረጋላቸው እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.29 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ የወጪ ሂሳብ

ዩኒቨርሲቲዎች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ብር 1,942,149.92 እንዲሁም የደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ብር 8,959,340.44 በድምሩ ብር 10,901,490.36 ሪፖርት ያላደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

የዘመኑን የመንግስት ገቢ እቅድ አፈጻጸም እና የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል በተጨማሪም የዩኒቨርስቲዎቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

ስለዚህ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገው መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.30 ቋሚ ያልሆነን ሠራተኛ በቋሚነት ዝውውር መፈፀም

የመንግሥት መ/ቤቶች በመንግሥት ሠራተኞች ዝውውር አፈፃፀም በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 28 ድንጋጌ መሠረት አስቀድሞ ቋሚ የሆነ የመንግሥት ሠራተኛ ከአንድ የፌዴራል መንግሥት ወደ ሌላ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት በተመሳሳይ የሥራ ደረጃና ደመወዝ ማዛወር እንደሚቻል የሚደነግግ ቢሆንም በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት አንድ የኮንትራት ሠራተኛ (ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ) በቋሚ የመንግሥት ሠራተኛነት ወደ ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት እንዲዛወሩ ተደርጓል፡፡

አሰራሩ በውድድር ሊሟሉ የሚገባቸው የስራ መደቦች ግልጽ ባልሆነ መንገድ እንዲሞሉ ሊያደርግ ስለሚችል፤ የሠራተኞች ዝውውር በሠራተኞች የዝውውር አዋጅና መመሪያ መሰረት ሊፈፀም እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

4.1 <u>በወቅቱ ያልተወራረደ የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

በሰነድ ወጪ የተደረገ ሂሳብ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32(1) መሰረት በወቅቱ እንዲወራረድ ክትትል የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣በ13 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 58,770,372.28 ውዝፍ የተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ -9 ተመልክቷል/

ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ ላይሰበሰብ ይችላል፣ የመንግስት ገንዘብም ያለአግባብ ለብክነትና ለሙስና ይጋለጣል፡፡

ያልተወራረደው ሂሳብ አስፈላጊው ክትትል ተደርጎ መወራረድ ያለበት ሲሆን፣ ሊወራረድ የማይችለው ደግሞ ተጣርቶ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ መሰረት ከመዝገብ ላይ የሚሰረዝበት ሁኔታ መመቻቸት እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በተመለከተም የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲያሳይ ለማድረግ፡-

- በሂሳብ መደብ 4211 የተመለከተው ሂሳብ ብር 588,482.15፣ በሂሳብ መደብ 4210 የተመለከተው ሂሳብ ብር 10,952.15 እና ለግዥ ወጪ የሆነው ሂሳብ 152,030.00 በድምሩ ብር 751,464.30 በክትትል ማነስ ምክንያት በወቅቱ ያልተወራረደ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ሂሳቡ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት እንዲወራረድ መደረግ አለበት፡፡
- በ1994 ዓ.ም ለግብርና ናሙና ቆጠራ ከአውሮፖ ሕብረት በእርዳታ ከተገኘው ብር 14,400,000.00 ውስጥ ስራ ላይ ያልዋው ብር 10,450,567.81 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ እንዲደረግ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በ2004 በጀት ዓመት ፈሰስ የተደረገ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ቀሪው ሂሳብ ብር 3,949,456.19 ቀደም ባሉት ዓመታት ለአቅም ግንባታ ስራ የዋለ በመሆኑ በጀት በማስፈቀድ ሂሳቡ በወጪ የሚመዘገብበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡
- ለረጅም ጊዜ ሳይወራረድ የቆየውም የክልሎች እና የኤጀንሲውን የቆየ ሰነድ በተመለከተ እየተደረገ ያለውን ክትትል በማጠናከር በተሰብሳቢነት

የሚታየውን ሂሳብ የመጨረሻ እልባት መስጠት እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲ በተሰብሳቢነት ከሚታየው የሰነድ ሂሳብ ውስጥ ብር 35,162,049.66 በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የብሔራዊ ፈተና ለመፈተን ለተንቀሳቀሱ ባለሙያዎች ለሥራ ማስኬጃ የተፈፀመ ክፍያ መሆኑንና ከዚሁ ሂሳብ ውስጥ ብር 18,411,455.72 መወራረዱን፣ በላኩት የሥራ አመራር ሪፖርት ገልፀዋል፡፡

በወለጋ ዩኒቨርሲቲ በተሰብሳቢ ከተመለከተው ሂሳብ ውስጥ በጉድለት የሚታየው ሂሳብ ገዳዩ በህግ የተያዘ መሆኑን፣ እንዲሁም ለተለያዩ ጉዳዮች ማስፈፀሚያ ወጪ የተደረጉ ሂሳቦችን በተመለከተም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ የሚደረጉ መሆኑ፣ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ለውጭ ጉዞ አበል የተከፈላቸው የተወሰኑ ግለሰቦች ክስ ተመስርቶባቸው ውሳኔ የተሰጠና የፍርድ አፈፃፀሙ በክትትል ላይ የሚገኝ መሆኑን በላኩት ምላሽ ገልፀዋል። ሆኖም ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ (ከ1999-2003) የፍርድ ቤት ውሳኔ አፈፃፀሙን በተመለከተ የተወሰደ ርምጃ አለመኖሩ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ክትትሉ ቀጥሎ የመንግስት ገንዘብ በአስቸኳይ የሚመለስበት መንገድ ሊፈለግ እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡ የማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ከ1995 በጀት ዓመት ጀምሮ በተሰብሳቢነት ሲንከባለል የነበረውን ሂሳብ ኮሚቴ በማዋቀር የማጣራት ስራ በመከናወኑ ምክንያት የተሰብሳቢው ሂሳብ ምንነት ሊታወቅ በመቻሉ ምክንያት ቀጥሎ የተመለከቱትን እርምጃዎች መውሰድ መቻሉ ተገልጿል፡፡

- በሂሣብ መደብ 4201 የተመዘገበው ብር 3,787,728.82 አብዛኛው በ1995 ለተካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ለአፋር ክልል የተላከ ሲሆን በዚህ ሂሳብ ላይ እርምጃ ለመውሰድ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ውሳኔ እየተጠበቀ መሆኑን፣
- በሂሣብ መደብ 4210፣ 4210፣ 4211 እና 5028 የተመለከተውን ሂሳብ በተመለከተ በ2004 በጀት ዓመት ኮሚቴ ተቋቁሞ ዝርዝር ማጣራት ከተደረገ በኋላ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን፣
- በሂሣብ መደብ 4274 የተመዘገበው ብር 14,400,000.00 በ1994 ዓ.ም ለግብርና ናሙና ቆጠራ ከአውሮፖ ሕብረት በእርዳታ ከተሰጠው ሂሳብ ውስጥ የተረፈ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 10,450,567.81 በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በ2004 በጀት ዓመት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ የተደረገ መሆኑን፣ በተጨማሪም ብር 3,949,456.19 ኤጀንሲው አስፈቅዶ

ለአቅም ግንባታ ስራ የዋለ በመሆኑ በ2004 በጀት ዓመት ሂሳቡ በወጪ የሚመዘገብ መሆኑን፣ ብር 152,030.00 ደግሞ በቅ/ጽ/ቤቶች ለግዥ በቅድሚያ የተከፈለ እና በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ሂሳቡ የተወራረደ መሆኑን፣ ሌሎችም በተሰጠው አስተያየት መሠረት አሰራሩ የሚስተካከል እና ተገቢው ክትትል የሚደረግ መሆኑን በላኩት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

4.2 ማስረጃ የሌለው የተሰብሳቢ ሂሳብ

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የመ/ቤቱ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 11,004,054.87 ማስረጃ የሌለው የተሰብሳቢ ሂሳብ፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሔራዊ ጽ/ቤት ብር 2,482,145.92 ለቃሊቲ ማእከል ግንባታ ቅድሚያ ክፍያ ከተከፈለው ሂሳብ ማስረጃው ያልቀረበ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት ማስረጃዎቹ ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ይህም በተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ በማስረጃ ያልተደገፈ እና ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡

በመሆኑም በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከቱት የሂሳብ ሚዛኖች በማስረጃ የተደገፉ ሊሆን እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.3 በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ያልተገለጸ ሂሳብ

የኢትዮጵያ የሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የታየው የተሰብሳቢ ሂሳብ በትክክል በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ መያዙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ብር 84,878.90 በሂሳብ ሪፖርት ያልተገለጸ በመሆኑ፤ የሂሳብ ሪፖርቱ የመ/ቤቱን ትክክለኛ ገጽታ እዳያሳይ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም በተሰብሳቢነት ተመዝግቦ ያልተያዘው ሂሳብ በተሰብሳቢ የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ሊካተት እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.4 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሣብ

በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን የድርጅቱ ደንበኞች ከሆኑ የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በተገባው ውል መሰረት በወቅቱ ያልተሰበሰበና ለ16 ዓመታት የቆየ ውዝፍ የቴሌቪዥን ሂሳብ ብር 10,530,913.70 ፤ በኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን የሬድዮና የቴሌቪዥን

ፈቃድ አገልግሎት አመታዊ ክፍያ ሂሳብ ብር 102,789.95፣ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በዱቤ የተሰጠ የማስታወቂያ አገልግሎት ውዝፍ ሂሳብ ብር 3,564,840.80፣ በድምሩ ብር 14,198,544.45 ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዲሰበሰብ ጥረት እንዲደረግ በ2002 በጀት ዓመት ኦዲታችንም የማሻሻያ ሃሳብ የተሰጠ ቢሆንም ውዝፉ ሂሳብ በመጠን ጨምሮ መገኘቱ ሂሳቡን ለመሰብሰብ የሚደረገው ጥረት አናሳ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ይህም ጊዜው በረዘመ ቁጥር የመንግስት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

በመሆኑም ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ውዝፍ ሂሳቡ የሚሰበሰብበት ወይም በውሉ መሰረት ተገቢው ህጋዊ እርምጃ የሚወሰድበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባ እንዲሁም የዱቤ አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት የደንበኞች (የድርጅቶች) የመክፈል አቅም አስተማማኝነት የሚገመገምበት አሰራር ሊዘረጋና አገልግሎት የተሰጠበት ክፍያም በውሉ መሰረት በወቅቱ እንዲሰበሰብ የሚደረግበት አሰራር በመዘርጋት በውሉ መሰረት በማይከፍሉት ላይ ደግሞ ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ሂሳቡ የሚሰበሰብበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባና በውዝፍ የተመለከተው የዱቤ ሽያጭ ሂሳብ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት መሰብሰብ እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. <u>የተከፋይ ሂሳብ</u>

5.1 <u>ለሚመለከተው አካል ያልተከፈለ ሂሳብ</u>

በሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ ትክክል መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ8 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 4,479,137.81 በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-27 ተመልክቷል/

ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ካልተከፈለ ገንዘቡን ጥቅም ላይ ሊያውለው የሚችለውን ገንዘብ ማሰር ሊሆን ከመቻሉ በተጨማሪም ተከፋይ ሂሳቦችን በተገቢው ጊዜ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ አለማድረግ ቅጣትና የወለድ ክፍያ ሊያስከትል ይችላል፡፡

በመሆኑም የተሰበሰበ ገቢ ለሚመለከተው ክፍል በወቅቱ ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ፈሰስ ተደርጎ ምዝገባ ያልተከናወነውም ሂሳብ ሊስተካከል እና የሂሳብ መግለጫውም በዚሁ መልኩ መታረም ይኖርበታል፣፣እንዲሁም የቅድመ ታክስ የገቢ ሂሳብም በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት በወቅቱ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢ መሆን እንዳለበት ገቢ

ሳይደረግ የቆየውም ሂሳብ በአፋጣኝ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.2 <u>ማስረጃ የሌለው የተከፋይ ሂሳብ</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የመ/ቤቱ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ብር 7,150.81፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሔራዊ ጽ/ቤት ብር 4,403.65 (ሁለት የተለያዩ ሂሳቦች) መነሻ ሰነድ የሌላቸው መሆኑ፣ ኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን ብር 4,693.33፣ እንዲሁም በማዕከላዊ ስታስቲክስ ብር 700,860.51፣ በድምሩ ብር 717,108.30 ማስረጃው ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማጣራት አልተቻለም፡፡

በተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ በማስረጃ ያልተደገፈ እና ትክክል ላይሆን ይችላል፡

በመሆኑምለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ ማድረግ ወይም ሂሳቡን ወደ ገቢ መቀየር እንደሚኖርበት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. <u>የበጀት ሂሳብ</u>

6.1 <u>በስራ ላይ ላይ ያልዋለ በጀት</u>

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ የተጠቀሙበት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣በ18 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 169,346,266.43 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡መንግስት ለሌሎች ፕሮግራሞችና አስፈፃሚ መ/ቤቶች በሚመደበው በጀት ላይ ተፅእኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በመሆኑም ስራ ላይ ስላልዋለው በጀት የተለያየ ምክንያት ቢሰጥም መ/ቤቶቹ ማስፈቀድ ያለባቸው ሥራ ላይ ሊያውሉት የሚችሉትን በጀት ብቻ መሆን እንዳለበት ለመ/ቤቶቹ በተላከው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.2 <u>ከበጀት በላይ የወጣ</u>

መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና በጀት ድልድል መሰረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ከሰበሰበው ገቢ እንዲጠቀም በተፈቀደለት ልክ የተጠቀመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ ስራ ላይ እንዲውል የተፈቀደው በጀት ብር 3,017,000.00 ሆኖ ሳለ ስራ ላይ ውሎ የተገኘው ብር 8,389,351.05 በመሆኑ ከተፈቀደው በላይ ብር 5,558,063.79 ሥራ ላይ ውሎ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 5,372,351.05 በበጀት

ዓመቱ ከተሰበሰበው የውስጥ ገቢ ላይ ሲሆን፣ ቀሪው ብር 185,712.74 ደግሞ በፋይናንስ አዋጁ መሰረት ዝውውር ሳይፈጸም ለሌሎች የሂሳብ አርዕስቶች ከተፈቀደው ላይ ስራ ላይ የዋለ መሆኑ፤ የድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 530,357.59 ከበጀት በላይ የወጣ መሆኑ ታውቋል፡፡

ይህም የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ሊባክን ይችላል፡፡ በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

አሰራሩ የፋይናንስ አዋጅን ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ ባለፈው አመት ኦዲታችንም ተመሳሳይ ችግር የነበረና አሰራሩ ህግን የተከተለ እንዲሆን በሪፖርታችን የተገለጸ ቢሆንም መሻሻል አልተደረገም፡፡ በመሆኑም የዩኒቨርሲቲው የበጀት አጠቃቀም የፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648/2001 የተከተለ ሊሆን እንደሚገባ እንዲሁም ለስራው አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት ተገቢው የበጀት ዝውውር እንዲፈቀድ በማድረግ በተራፊነት ከሚታዩ የሂሳብ መደቦች መጠቀም የሚችል በመሆኑ ለወደፊቱ የፋይናንስ አዋጁን ተከትሎ በመስራት ረገድ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 6.3 ሳይፈቀድ ስራ ላይ ስለዋለው የውስጥ ገቢ ሂሳብ

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር190/2002 አንቀጽ 12 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከቀጥታ ገቢ ወይም ከውስጥ ገቢ በበጀት ተፈቅዶ ስራ ላይ መዋሉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,942,149.92፤ በደብራማርቆስ ዩኒቨርስቲ ብር 8,959,340.44 በድምሩ ብር 10,901,490.36 የውስጥ ገቢያቸውን በደንቡ መሰረት ሳያስፈቅዱ ስራ ላይ አውለው ተገኝቷል፡፡

ይህም የህግ ተጠያቂነትን ሊያስከትልና መንግስት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ጉዳዮች ገንዘቡ ስራ ላይ እንዳይውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ዩኒቨርሲቲዎቹ የሚሰበስቡትን የውስጥ ገቢ ለመጠቀም አሳማኝ ምክንያት ካላቸው በአዋጁ መሰረት እያስፈቀዱ ስራ ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም አሰራሩ በአዋጁ መስተካከል ይኖርበታል፡፡

## 6.4 የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር አለመዘጋጀቱ

የደቡብ ኢትዮጵያ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሄራዊ ጽ/ቤት በመንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ ሀ-መ መሰረት ጽ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ የተፈቀደውን በጀት በሚገባ ለመቆጣጠር እንዲቻል የበጀት መቆጣጠሪያ መዝገብ የተቋቋመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ጽ/ቤቱ በ2003 በጀት ዓመት

የተፈቀደለትን በጀት አጠቃቀም በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችል የበጀት መቆጣጠሪያ ቋት(ሌጀር) ያላዘጋጀ በመሆኑ ፤ከተፈቀደ በጀት በላይ ስራ ላይ ቢውል በወቅቱ ላይደረስበት ይችላል፡፡

በመሆኑም የበጀት አጠቃቀምን ውጤታማ ለማደረግና ለመቆጣጠር እንዲቻል በመመሪያው መሰረት ተገቢው የበጀት መቆጣጠሪያ ቋት (ሌጀር) ሊቋቋም ይገባል፡፡

### 6.5 የበጀት ዝውውር ስለመፈጸሙ የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበለት

ከሁለት የተለያዩ የሂሳብ መደቦች ማለትም ከሂሳብ መደብ 6212 ብር 25,000.00 እና ከሂሳብ መደብ 6313 ብር10,000.00 ወደ ሂሳብ መደብ 6259 ዝውውር የተከናወነ ስለመሆኑ በዘገባ መዝገብ ላይ ማየት የተቻለ ቢሆንም፣ በድምሩ ብር 35,000.00 የበጀት ዝውውሩ የተፈቀደበት ቅጽ በማ/1 ለኦዲት ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ይህም ያልተጠየቀና ያልተፈቀ የበጀት ዝውውር ሊመዘገብና ሥራ ላይ ሊውል ይችላል፡፡

በመሆኑም የበጀት ዝውውር ከመመዝገቡ በፊት የበጀት ዝውውር ጥያቄ ሊቀርብና ሊፈቀድ ይገባል፡፡ዝውውሩ የተፈጸመበት ማስረጃም በተገቢው ቦታ ሊቀመጥ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 7. ንብረት

### 7.1 የንብረት ከወጪ ቀሪ ያልተረጋገጠ ስለመሆኑ

የንብረት አጠባበቅና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ፣ በትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም በመዝገብ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ ፤ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚ/ር እና የኢትዮጵያ ሴቶች ልማት ፈንድ፤ የደብረ ብርሃን የኒቨርስቲ፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፤ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ፤ የማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የጠፋ ወይም የጎደለ ንብረት ካለ ማወቅ አይቻልም፡፡ ይህም ለንብረት ብክነት በር ከፋች ሊሆን የሚችል ከመሆኑም በላይ በወቅቱ እርምጃ ለመውሰድም አያስችልም፡፡

በመሆኑም ከጥፋት ለመጠበቅና ለመከላከል እንዲሁም ለክትትልና ቁጥጥር የተመቻቸ እንዲሆን ለማድረግ ይቻል ዘንድ መዝገብ ከሚያሳየው ከወጪ ቀሪ ጋር መመሳከር እንደሚኖርበት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 7.2 ለጥገና ጋራዥ የገቡ ተሽከርካሪዎች ከጋራዥ ሲወጡ በርካታ ኪ.ሜ የተነዱ ስለመሆኑ

የተሽከርካሪዎች የነዳጅ እና የኪሎ ሜትር ቁጥጥር ሁኔታ ሲጣራ በማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ተሽከርካሪዎች ጋራዥ ከገቡ በኋላ ተጠግነው ሲወጡ ለፍተሻ በሚል ምክንያት ከ100 ኪ.ሜ በላይ የሚነዱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም ውስጥ ከ300 ኪሎሜትር በላይ የተነዱትን አምስት ተሽከርካራዎች ብቻ በመለየት ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ታርጋ ቁጥር | ጋራዥ ሲገባ የተመዘገበ ኪ.ሜ | ከጋራዥ ሲወጣ የተመዘገበ ከ.ሜ | ጋራዥ በነበረበት ወቅት የተነዳው ኪ.ሜ |
|---|---|---|---|
| 4-11153 | 119576 | 119902 | 326 |
| 4-02613 | 177531 | 177856 | 325 |
| 4-1243 | 131254 | 131658 | 404 |
| 4-09579 | 235823 | 236276 | 453 |
| 4-09667 | 13106 | 13690 | 584 |

ይህም ተሽከርካሪዎቹ በጥገና ፍተሻ ምክንያት ከመንግሥት ሥራ ውጭ ለግል ጉዳይ መጠቀሚያ ሊውሉና ለአደጋ ሊጋለጡ እና የኤጀንሲውን ስራ ሊያስተጓጉሉ ይችላሉ፡፡

የኤጀንሲው የተሽከርካሪ እና የነዳጅ አጠቃቀም ስርዓት ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጥ መሆኑን የሚያመላክቱ በርካታ ችግሮች በኦዲቱ ወቅት መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ አሰራሩን በመፈተሽ የቁጥጥር ስርዓቱን ሊያጠናክር ይገባል።

መኪኖቹ ከተነዱት ኪሎሜትር ብዛት አንጻር ሲታይ የተሰጠውን ምክንያት ለመቀበል አዳጋች በመሆኑ ኤጀንሲው በተሽከርካሪ አጠቃቀሙ ላይ ተገቢውን የክትትል እና የቁጥርር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል።

## 7.3 ጋራዥ ገብተው ከሁለት ዓመት በላይ ስለቆዩት ሁለት ተሽከርካሪዎች

በማዕከላዊ ስታስቲክስ የሰሌዳ ቁጥር 4-03084 ቶዮታ ኮሮላ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-00637 ሱዙኪ መኪናዎች በብልሽት ምክንያት በእርሻ መሣሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት ጋራዥ ጥገና ሳይደረግላቸው ከሁለት ዓመት በላይ መቆየቱ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ይህም የመኪናዎቹ ዕቃ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡ በቀጣይም መኪኖቹ በዋጋ ልዩነት ምክንያት ሳይጠገኑ ተመላሽ እንዲሆኑ ሊደረግ ይችላል፡፡

ስለዚህ መኪናዎች ጋራዥ ሲገቡ በወቅቱ ተጠግነው ወደ ስራ ስለመግባታቸው ክትትል መደረግ ያለበት ሲሆን፣ በተገባው ውል መሰረት ደግሞ ጥገናውን አከናውኖ በማያስረክብ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ላይ በወቅቱ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በክትትል ማነስ ምክንያት በወቅቱ እርምጃ ካልተወሰደ ባለጋራዡ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ዘዴ እንዲቀይስ መንገድ ይከፍታል፡፡ በመሆኑም ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ተሽከርካሪዎቹ ከጋራዥ ወጥተው ስራ ላይ የሚሰማሩበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

## 7.4 ለቋሚ ዕቃዎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ

የመ/ቤቱ ቋሚ ዕቃዎች የመለያ ቁጥር የተሰጣቸው መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ለቋሚ ዕቃዎች አልፎ አልፎ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣ በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ፣ በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሐፍት ኤጀንሲ፣ በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ለቋሚ ዕቃዎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ በመሆኑ ፣ለቁጥጥርና ክትትል አመቺ ካለመሆኑም በላይ ንብረቶቹ ለብክነት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

በመሆኑም መ/ቤቱ በንብረት አያያዝ መመሪያ  መሠረት የመለያ ቁጥር መሰጠት እንደሚኖርበት በተላከው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 7.5 የንብረት ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ያልተቻለ ስለመሆኑ

በጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ት/ቤት የንብረት አጠባበቅና አያያዝ ሁኔታ ለማጣራት ሙከራ ተደርጎ የንብረት ክፍል ኃላፊዋ በመታመማቸው ምክንያት እሳቸውን ተክቶ ሊሰራ የሚችል ሰው በቦታው ባለመመደቡ፣ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ተሠርቶባቸው ያለቁ የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች በቢሮዋቸው ውስጥ የተቆለፈበት በመሆኑ ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የትምህርት ቤቱን ንብረት ኦዲት ለማድረግ አልተቻለም፡፡ ለሁኔታው መፍትሔ በመፈለግ የሚያሳውቁ መሆኑ ቢገለጽም  የትምህርት ቤቱ ንብረት አያያዝና አጠባበቅ ስርዓት ደካማ  ሊሆን ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ ተመሳሳይ ችግር ሲያጋጥም የትምህርት ቤቱም ስራ እንዳይስተጓጎል ለማድረግ አፈጣኝ መፍትሂ መፈለግ ወይም ሌላ ሰው ሊወከል የሚችልበትን አሰራር መዘርጋት እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

7.6 <u>ለበርካታ አመታት ተከማችተው የተገኙ ንብረቶች</u>

በመንግሥት ንብረት መመሪያ ቁጥር 6/91 መሰረት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች እንዲወገዱ መደረጉን እንዲሁም ሊያገለግሉ የሚችሉት ደግሞ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤በመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት

- በተደራራቢ ግዥ በመፈፀሙ ምክንያት በመጋዘን ውስጥ ዕቃዎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በመጋዘን ውስጥ ያለአገልግሎት ለብዙ አመታት የተቀመጡ የተለያዩ ዕቃዎች መገኘታቸው፤

ከፍተኛ ግጭት ደርሶባቸው ከአገልግሎት ውጪ የሆኑና ያልተወገዱ ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ እንዲሁም በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የቋሚ ዕቃ መጋዘን ውስጥ ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት ከ1999 ጀምሮ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ 10 ፕሮጀክተሮች ወደፊት ሊጠቅሙ ይችላሉ በሚል ለረዥም ጊዜ ያለስራ እንዲቀመጡ መደረጉ፤ ለብልሽት እንዲዳረጉ የሚዳርግ በመሆኑ በሽያጭ ወይም በስጦታ ሊወገዱ የሚችሉበት መንገድ መፈለግ እንደሚኖርበት እንዲሁም በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን፤ የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሐፍት ኤጀንሲ፤ በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ፤ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ኮምፒዩተሮች፣ ፕሪንተር፣ መደርደሪያ፣ በርካታ ዲቫይደርና ወንበሮች እና ሌሎች ዕቃዎች በንብረት ክፍል መገኘታቸው፣በኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሔራዊ ፕሮጀት ጽ/ቤት አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ መገኘታቸው እና በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ተገኝተዋል፡፡በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት ስለንብረት አወጋገድ አፈጻጸም የማሻሻያ ሃሳብ የተሰጠ ቢሆንም ጉዳዩ እልባት ያላገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቱ ከሚያስፈልገው በላይ ዕቃዎችን መግዛት በአቀማመጥ ላይ መጨናነቅን ከመፍጠሩ በተጨማሪ ጊዜው በረዘመ ቁጥር ለበለጠ ብልሽት ሊዳረጉ ስለሚችሉ

ሊወገዱ የሚገባቸው እንዲወገዱ፤ተጠግነው አገልግሎት የሚሰጡት ደግሞ እንዲጠገኑ በወቅቱ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገባ መሆኑን ያረጁና ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶች በመንግስት የንብረት አወጋገድ ስርአት መሰረት እንዲወገዱ ሊደረግ የሚገባ ሲሆን

ሳይዘገይ መከናወኑ ደግሞ ተጨማሪ ብልሽትንና ብክነትን ለመቀነስ የሚያስችል መሆኑን በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7.7 <u>የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች</u>

በመ/ቤቶች የሚገኙ ተሽከርካሪዎች አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ፣ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ዩኒቨርሲቲው ከሚገለገልባቸው ተሽከርካሪዎች መካከል አምስቱ ተሽከርካሪዎች፣ እንዲሁም በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 4 ተሽከርካሪዎች፣ በድሬደዋ ዩኒቨርስቲ 3 ተሽከርካሪዎች ሊብሬያቸው ለኦዲት አለመቅረቡ ታውቋል፡፡

ይህም የተሽከርካሪዎቹ ሊብሬ ከሌለ መኪናዎቹ የዩኒቨርሲቲው ለመሆናቸው ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

በመሆኑም የተሽከርካዎቹም የባለቤትነት መታወቂያ ካለበት ቦታ ተጠይቆ ሊሟላ እነደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7.8 <u>ለአላቂ ዕቃዎች መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ መዝገብ ወይም ስቶክ ካርድ</u>

<u>ያልተቋቋመ መሆኑ፣</u>

በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባዘጋጀው ቅጾች መሰረት ለአላቂ ዕቃዎች መዝገብ አቋቁሞ ምዝገባ የሚያከናውን መሆኑን እና በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የስቶክ (የአላቂ ዕቃዎች) ምዝገባ እና ስቶክ የመጠበቅ ተግባራት በተለያዩ ሰራተኞች መሰራታቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ ለአላቂ ዕቃዎች መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ መዝገብ ወይም ስቶክ ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፣ እንዲሁም የንብረት ምዝገባና የመረከብ /የመጠበቅ/ ሥራ በአንድ ሠራተኛ ተደርቦ የሚከናወን መሆኑ ታውቋል፡፡

አሰራሩ የመንግስት ንብረት ቢጠፋ ወይም ቢጎድል ሊደረስበት እንዳይቻል ለያደርግ ስለሚችል የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባዘጋጃቸው ቅጾች መሰረት የአላቂ ንብረቶች ምዝገባ መከናወን የሚገባው ሲሆን ንብረት የመጠበቅና የንብረት ሂሳብ ምዝገባ ሥራዎች በተለያዩ ሠራተኞች እንዲሠሩ ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 7.9 <u>በ2001 በጀት ዓመት የተሸጠ መኪና በ2003 በጀት ዓመት የቆጠራ ሪፖርት ውስጥ የተካተተ ስለመሆኑ</u>

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ተሽከርካሪ መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ (ሊብሬ) ያላቸው መሆኑንና በአካል የሚገኙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ሐምሌ 11/2003 በተደረገው የ2003 በጀት ዓመት የተሽከርካሪ ቆጠራ ወቅት ተገኝቷል ተብሎ ሪፖርት የተደረገ የታርጋ ቁጥር 4–01791 ኢ.ት ቶዮታ ጃፓን የሆነ ተሽከርካሪ መኪና በ2001 በጀት ዓመት በሽያጭ የተወገደ እና በባለአደራ ቦርድ ባለቤትነት የማይታወቅ መሆኑ ታውቋል፡፡

የቆጠራ ዋነኛ ዓላማው በአካል የተገኙትን የመ/ቤቱ ንብረቶች እና በመዝገብ ላይ የተመለከተው የንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክል መሆኑን በማረጋገጥ ልዩነት ካለ በወቅቱ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ በመሆኑ፣ ቆጠራ በአግባቡ ሊከናወን ይገባል፡፡ በመ/ቤቱ ቁጥጥር ስር የሌሉ ንብረቶችም በቆጠራ ሪፖርት ውስጥ እየተካተቱ ሪፖርት የሚደረግ ከሆነ፣ በግለሰቦችም የተመዘበረ ንብረት በተመሳሳይ መልኩ አለ ተብሎ ሪፖርት ሊቀርብበት የሚችል በመሆኑ መ/ቤቱ በቆጠራ አፈጻጸሙ ላይ ተገቢውን ትኩረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## 7.10 <u>ለረዥም አመት ያለ አገልግሎት የቆሙ መኪናዎች</u>

በመ/ቤቶች የሚገኙ ተሽከርካሪዎች አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ፤ በሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚ/ር 3 ተሽከርካሪዎች ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን 4 ተሽከርካሪዎች ከአንድ ዓመት በላይ የቆሙ፤ መሆኑ ታውቋል፡፡

ተሽከርካሪዎች በአግባቡ እንዲጠበቁ ካልተደረገ መስጠት የሚገባቸውን አገልግሎት ላይሰጡና ለስርቆት ሊዳረጉ በተጨማሪም መ/ቤቱን ላላስፈላጊ ወጪ ሊዳርጉት ይችላል፡፡

በመሆኑም የመንግስት ንብረት ውጤታማ ሳይሆን ሲቀር በመመሪያው መሰረት ማስወገድ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም ሊብሬ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች በትክክል የመ/ቤቱ ለመሆናቸው ማረጋገጫ የሌላቸውና በጉዞው ላይ እያሉ አደጋ ቢደርስባቸውና በህግ ለመጠየቅ ጉዳዩን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም የሚወገዱትን ተሽከርካሪዎች ማስወገድ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸውን ደግሞ የባለቤትነት መታወቂያ ማውጣት እንደሚያስፈልግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 7.11 <u>ከአየርላንድ ኤምባሲ በዕርዳታ ስለተሰጠው ቋሚ ዕቃ</u>

በማእከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2003 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት መሰረት ከአየርላንድ ኢምባሲ በእርዳታ ከተሰጡት እቃዎች ውስጥ

ብዛታቸው 15 የሆኑ ያገለገሉ ቋሚ ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ አለመደረጋቸው እና እቃዎቹንም የተረከበው ግለሰብ ስራው የማይመለከተው መሆኑ ታውቋል፡፡

ይህም አሰራር ለኤጀንሲው በእርዳታ መልክ የተሰጡት እቃዎች ለግለሰብ መጠቀሚያ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ከኢምባሲው የተሰጡት ቋሚ ዕቃዎች በእርዳታ ስምምነቱ መሰረት በኤጀንሲው ውክልና የተሰጠው ሰራተኛ ተረክቦ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረግ ነበረበት፡፡ በስምምነቱ መሰረት ያልመጡ እቃዎችም ካሉ ወዲያውኑ ከኢምባሲው ጋር ግንኙነት በመፍጠር መፍትሄ ሊፈለግለት ይችል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ በውስጥ ኦዲት ሪፖርት ከመደረጉ በፊት ምንም ዓይነት እርምጃ አለመወሰዱ ለጉዳዩ የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑንና ሁኔታው ብልሹ አሰራርን የሚያበረታታ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም በጉድለት የታዩት ዕቃዎች ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት በአሳሰብነው መሰረት ንብረቱ በማይመለከተው ሰራተኛ ርክክብ መፈጸሙ አግባብ ባለመሆኑ ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ መመራቱ ተገልጿል፡፡

8. <u>ልዩ ልዩ</u>

8.1 <u>የስጋት አስተዳደር ፖሊሲ ያልተዘጋጀ ስለመሆኑ</u>

በፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሰረት በጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን፤ በትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲ፤ ፤ በቤተመንግስት አስተዳደር፤ በፌዴሬሽን ምክር ቤት፤ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ፤ በቱሪዝም ሚኒስቴር፤ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚ/ር፤ በኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ፤ በድሬደዋ ዩኒቨርስቲ፤ በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ፤ በኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን፤ በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ፤ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን፤ በኢትዮጵያ ሴቶች ልማት ፈንድ፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሔራዊ ጽ/ቤት፤ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ፣ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና በኢትዮጵያ ስብሰባ ማዕከል የስጋት ምንጮች ዳሰሳ አለማድረጋቸው ታውቋል፡፡

ይህም መ/ቤቶች የተቋቋመበትን አላማ ለማስፈፀም እቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት ለሚከሰቱ ችግሮች ተጋላጭነታቸው የሰፋ ሊያደርገው ይችላል፡፡

ስለዚህ መ/ቤቶቹ የስጋት ምንጮች በሆኑበት አካባቢዎች የሚከሰቱ ችግሮችና የተጋላጭነት ደረጃ በመለየት ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እና የመከታተያ ስልት በመዘርጋት ስጋቶችን ለመቀነስ እንዲቻል ስጋቶችን ለይቶ ማወቅ እና ስጋቶችንም ለመቀነስ ተገቢው የስጋት አስተዳደር ፖሊሲ ሊዘጋጅ እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 8.2 ገቢ ስለሚደረጉ የተለያዩ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥርን በተመለከተ

የድሬደዋ ዩኒቨርስቲ ከተለያዩ ድርጅቶች የተለያዩ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች እንዲሁም የምግብ አቅርቦት ያሉት ሲሆን ዕቃዎቹ ለዩኒቨርስቲው ገቢ ሲደረጉ መስፈርታቸውን ጠብቀው ስለመቅረባቸው እንዲገመግሙ በተለያዩ አቃዎች ዓይነት መሰረት ኮሚቴ የመደበ ሲሆን ነገር ግን በጥራት ደረጃው መሰረት ገቢ መሆናቸውን የሚያረጋግጡት በአብዛኛው በኮሚቴ ያልተመደቡ አባላት እንዲያዩ መደረጉና በተወሰኑ አቅርቦቶች ላይ ደግሞ በቁጥር ከተመደቡት ባነሰ መታየቱ እቃዎቹ በመስፈርቱ መሰረት ለመግባታቸው ኮሚቴው የማያረጋግጥ መሆኑ ታውቋል፡፡

## 8.3 <u>የ2003 በጀት ዓመት የውስጥ ኦዲት አለመከናወኑ</u>

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 11 አንቀፅ 61(3) እንዲሁም በፌደራል መንግስት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁ.7/2003 በክፍል አምስት አንቀፅ 20 (2) የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍሉ ባዘጋጀው ዕቅድ መሠረት በየሩብ ዓመቱ ባከናወነው ኦዲት የደረሰበትን ውጤት በዚሁ አንቀፅ (3) በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በውስጥ ኦዲት ኃላፊው ፊርማ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እና በግልባጭ ደግሞ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንደሚላክ ይገላጻል ስራውም በዚሁ መሰረት መሰራቱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚ/ር፣ የድሬደዋ ዩኒቨርስቲ፣ የደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ፤ የብሔራዊ ቤተመንግስት አስተዳደር፤ እንዲሁም የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የውስጥ ኦዲት ክፍላቸው ባዘጋጀው ዕቅድ መሰረት ያልሰራ መሆኑ እንዲሁም የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን የኦዲት ሥራ ወረቀቶቹ የውስጥ ኦዲት ማንዋል በሚያዘው መሠረት ያልተሠራና በበቂ ማስረጃ የተደገፉ አለመሆኑ ታይቷል፡፡

ይህም ሊከሰቱ በሚችሉ ግድፈቶች ላይ በወቅቱ የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ የማይቻልበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡

በመሆኑም የውስጥ ኦዲት ክፍሉ ዕቅድ ባወጣው መሠረት የተቋሙን ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ለበላይ አካል ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

# የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
# የ2003/4 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

## ሀ. መግቢያ

ይህ ሪፖርት ከጥር 2004 ዓ.ም. እስከ ከታህሳስ 2004 ዓ.ም.ድረስ ያለውን የአንድ ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ለማመላከት የተዘጋጀ ሪፖርት ነው፡፡ ሪፖርቱም ከተዘጋጀው ዕቅድ አንፃር የተከናወኑትን የኦዲት ሥራዎች ከማመላከቱም ባሻገር፣ የተገኙትን ዋና ዋና ግኝቶች አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

## ለ. የተከናወኑ የኦዲት ሥራዎች

በ2003 በጀት ዓመት የኦዲት ጊዜያት የ31 መ/ቤቶችን ኦዲት ለማከናወን ታቅዶ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን፣ ቀደም ባለው በጀት ዓመትና በዚሁ በጀት ዓመት የተወሡ ኦዲተሮች ሥራው ከተጀመረ በኋላ ሥራ በመልቀቃቸው ከፍተኛ ጫና ተፈጥሮ ነበር፡፡ ሆኖም ያሉትን ችግሮች ሁሉ በተቻለ መጠን በመቋቋምና አንድ መ/ቤት ተጨምሮ የሠላሣ ሁለት መ/ቤቶች የኦዲት ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤቶች ተልኳል፡፡

## ሐ. በኦዲት ሥራ ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

### 1. የሳጥንና የባንክ ሂሳብ

#### 1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

በበጀት ዓመቱ የሂሣብ መግለጫዎች ላይ ሪፖርት የተደረገውና በመ/ቤቱ በተደረገው ቆጠራ ከተገኘው ጥሬ ገንዘብ ጋር ሲመዛዘን በጅማ የኒቨርስቲ ብር 591,605.11፤በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 392,544.73 በድምሩ ብር 984,149.84 ጉድለት መገኘቱ ታውቋል፡፡

#### 1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶች

የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ፣ እንዲሁም የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉ /የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አድርገናል ቢሉም ማስረጃ ያላቀረቡ/ እና የጥሬ ገንዘብ ቆጠራውን ከሂሣብ ቋት (ሌጀር) ጋር የማያመዛዝኑ መ/ቤቶች 19

መ/ቤቶች(ዝርዝራቸው በአባሪ-8 የተመለከቱ )ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሪፖርት የተደረገው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት ሲጣራ፣ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብና ሠነድ ፣

| | | |
|---|---|---|
| -የወሎ ዩኒቨርስቲ | ብር | 789,647.53 |
| -የሠመራ ዩኒቨርስቲ | | 181,729.49 |
| በድምሩ | | 971,377.02 |

ልዩነት ያላቸው ለመሆኑ ተረጋግጧል ።

- በመዳወላቡ የኒቨርስቲ ባንክ ገቢ ሆኖ በገቢ ያልተመዘገበ ብር 17,270,301.78 ፤እንዲሁም ከባንክ ወጪ ሆኖ በወጪ ያልተመዘገበ ብር 1,192,668.91 መገኘቱ፤
- በአርባ ምንጭ የኒቨርስቲ ባንክ ገቢ ሆኖ በገቢ ያልተመዘገበ ብር 59,923.38 እንዲሁም ከባንክ ወጪ ሆኖ በወጪ ያልተመዘገበ ብር 898,556.04 የተገኘ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰኔ 30/2003 በተዘጋጀው (የውስጥ ገቢ ባንክ ሂሣብ ቁጥር Gov-166) የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ ላይ ከባንክ ወጪ ሆኖ በባንክ ሌጀር ላይ ያልተመዘገበ ተብሎ ብር 8,681,833.13 የተያዘ ቢሆንም ገንዘቡ ከባንክ ወጪ ለመደረጉ ደጋፊ የሠነድ ማስረጃ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡
- የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ 3 የባንክ ሂሳብ እንዲሁም የጅማ ዩኒቨርስቲ የውስጥ ገቢ የባንክ ሂሣብ ያላቸው ቢሆንም የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በሃዋሳ ዩኒቨርስቲ የወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ እየተዘጋጀ ባንክ በየወሩ ከሚልከው የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ጋር የማይመሣከር በመሆኑ የባንክ ሂሳብ ቁጥር GOV 12 ትክክለኛ ከወጪ ቀሪ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ኮሌጁ ባቀረበው የ2003 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫዎች መሠረት በ30/10/2003 ዓ.ም በውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ቁጥር GOV-12 ብር 4,327,349.49 የተገኘ መሆኑ ቢገለጽም በሰኔ 30 2003 ዓ.ም በባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ከተመለከተው ብር 4,286,566.50 ጋር ሲመሣከር የሂሣብ መግለጫው በብር 40,782.99 ብልጫ የሚያሣይ መሆኑ ታውቋል፡፡

- የጅማ ዩኒቨርስቲ የተለያዩ የገቢ ማመንጫዎች ያሉት ሲሆን ስለባንክ ሂሣብ አከፋፈት የተላለፈውን መመሪያ(የፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003) በመጣስ የጅማ ዩኒቨርስቲ ሞዴል ፋርማሲ ቁጥር 1 እና የጅማ ዩኒቨርስቲ ሞዴል ፋርማሲ ቁጥር 2 አቢሲኒያ ባንክ ጅማ ቅርንጫፍ፤ የጅማ ዩኒቨርስቲ ኮሚኒቲ ትምህርት ቤት ደግሞ በዳሽን ባንክ ፤የጅማ ዩኒቨርስቲ መጻህፍትና ሸቀጣሸቀጥ መደብር እና የጅማ ዩኒቨርስቲ የሠራተኞች መዝናኛ ክበብ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባንክ ሂሳብ የተከፈተላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

- የወሎ ዩኒቨርስቲ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ፣ ለልዩ ልዩ ጥቃቅን ወጪዎች በሳጥን ሊያዝ ከሚገባው ጥሬ ገንዘብ (ፔቲ ካሽ ) መጠን በላይ ብር 303,676.45 በገንዘብ ያዦች ካዝና፣ በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ በውስጥ ኦዲት በተደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በዋና ገንዘብ ያዥ ካዝና ውስጥ ብር 225,826.45 ፤በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ በአንድ የግዢ ሠራተኛ እጅ ብቻ ብር 1,621,880.00 እና በሁለት ሠራተኞች እጅ ደግሞ ብር 138,284.99 በድምሩ ብር 1,760,164.99 ጥሬ ገንዘብ ተቀምጦ ተገኝቷል።

የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያና የጥሬ ገንዘብ ሂሣብን በተመለከተ ያሉትን ሥጋቶች በመዘርዘርና መወሠድ ያለበትን ዕርምጃ በገለፅነው መሠረት ለማስተካከል እየተንቀሣቀሡ መሆኑን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ገልፀዋል፡፡

## 2 ተሰብሣቢ ሂሣብ

2.1 ለዕቃ ግዥና ለተለያዩ ሥራዎች ወጪ ተደርገው (ከተሰጠው አገልግሎት ያልተሰበሰበ ገቢ) በፋይናንስ ደንቡ መሠረት ያልተወራረዱ ወይም ያልተሰበሰቡ ሂሣቦች በ15 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 770,261,856.19 (ዝርዝራቸው በአባሪ-9 የተመለከተ) ተገኝቷል፡፡

መሰብሰብ የሚችለው ሂሣብ ሣይዘገይ እንዲሰበሰብ ማድረግ፣ ከአቅም በላይ የሆኑትን ደግሞ የፋይናንስ ደንቡን ተከትሎ እንዲሠረዝ ማድረግ እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት፣ ትምህርት ሚኒስቴር ለየዩኒቨርስቲዎች ግንባታ የተሰጠውን በርካታ ገንዘብ እንዲወራረድ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑንና ሎሎች ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችም ክትትል በማድረግ ዕርምጃ እንደሚወስዱ

በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡ የትምህርት ሚኒስቴር ሂሣቡን ዘግቶ ለኦዲት ካቀረበ በኋላ ዩኒቨርስቲዎች እየቀረቡ ሂሣባቸውን ሲያወራርዱ እንደነበረ ተገንዝበናል፡፡

## 2.2. በተሰብሣቢ ሂሣብ ላይ የአሠራር ችግሮች

- የወሎ ዩኒቨርስቲ የተሰብሳቢውን ሂሳብ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ ብር 1,953,500.00 በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድመ ክፍያዎች ፣ ብር 21,205.30 በልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ እና ብር 20,849.64 በአቅራቢዎች ቅድመ ክፍያ መያዝ ሲገባው ፣ በጥቅሉ ብር 1,995,554.94 በግኘ ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መደብ ተይዞ ተገኝቷል ፡፡ በተጨማሪ የዚሁ ዩኒቨርስቲ የተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ፣ ብር 66,145.03 በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች የሂሳብ መደብ የተያዘ ቢሆንም ሂሳቡ ከማን እንደሚፈለግና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ የማይታወቅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 448,095.38 ተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ የተያዘ ቢሆንም ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ የሠነድ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፡-
- በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 74,313.27 በተቋሙ ሠራተኞች ላይ የሚፈለግ ዕዳ እንደሆነ ቢገለጽም በእያንዳንዱ በለዕዳ ስም ተቀጽላ የሂሳብ ሌጀር በመክፈት የሚፈለግበት ሂሣብ ፤የተከፈለው ገንዘብና ቀሪ ዕዳ እየተቀናነሰ የማይመዘገብ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከሁለት የተቋሙ ሠራተኞች ደመወዝ ላይ በየወሩ 1/3 እየተቀነሰ ለጉራፈርዳ ወረዳ የገንዘብና ኢ/ል/ጽ/ቤት ገቢ እንዲደረግ የተወሰነው ገንዘብ ብር 37,814.66 አላግባብ በተቋሙ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱ፣
- በባህርዳር ዩኒቨርስቲ በበበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለሥራ አመራሩ በተዘጋጀው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት መሠረት ብር 20,105,034.19 ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ የተገለጸ ቢሆንም በዝርዝር ለማየት ተሞክሮ ትክክለኛ ገጽታውን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- በመዳወላቡ ዩኒቨርስቲ ለእቃ ግዥ ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በተደጋጋሚ የሚሰጥ ቢሆንም በእያንዳንዱ የእቃ ግዥ ሰራተኛ ተቀጽላ ሌጀር ባለመኖሩ ማስረጃ ቀርቦለት ያልተወራረደና በሰራተኛው ላይ የሚፈለግ ቀሪ እዳ ለይቶ ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ ታውቋል፡፡

- በትምህርት ሚኒስቴር ከተመለከተው ተሰብሣቢ ሂሣብ ውስጥ የካፒታል ሂሳብ (የሂሳብ መደብ 4274) ብር 37,883,977.02 ከሰኔ 1994 ዓ.ም ጀምሮ ያለና በ1999 በጀት ዓመት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በቀረበው ሪፖርት ላይ የተመለከተ/ያልተወራረደ/ ሲሆን፣ የመደበኛ ሂሳብ (የሂሳብ መደብ 4201፣ 4202 እና 4253) ብር 5,478,706.92 ከ1995 ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ የተሰብሳቢ ሂሣብ ነው፡፡

## 3 ተከፋይ ሂሣብ

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሣብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከተው(ረጅም ዘመን ያስቆጠሩ ይገኙበታል) ተከፋይ ሂሣብ በ8 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 18,279,511.19 ተገኝተል፡፡/ዝርሩም በአባሪ -27 ተመልክቷል/ በተጨማሪም የሚከተሉት የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፣

- በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 79,416.94 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን /Abnormal Debit balance/ በመያዙ የ2003 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሣብ ሚዛን በብር 79,416.94 አላግባብ ዝቅ ተደርጎ ተይዟል፡፡
- በሃዋሳ ዩኒቨርስቲ-የወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮለጅ የተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች በድምሩ ብር 55,713.75 ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን / Abnormal Debit balance/ የሚያሣዩ በመሆኑ የ2003 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሣብ ሚዛን  በብር 55,713.75 ዝቅ እንዲል አድርጓል ፡፡
- የጅማ ዩኒቨርስቲ ግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ ብር 4,648.52 ተከፋይ ዕዳ መኖሩ የተመለከተ ቢሆንም ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ ባለመኖሩ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ የ2003 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሳብ መግለጫ መሰረት ለዩኒቨርስቲው ሠራተኞች ያልተከፈለ ደመወዝ ብር 342,021.17 መኖሩ የተመለከተ ቢሆንም ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ ሂሣብ ውስጥ ብር 191,810.66 ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ ሂሣብ እንደሆነና በጉዳዩ ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በተደጋጋሚ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር እርምጃ ያልተወሰደበት ሲሆን' ቀሪው ብር 150,210.51 በበጀት ዓመቱ የተከሰተ ሂሳብ እንደሆነ ቢገለጽም ደመወዝ ያልተከፈላቸው ሠራተኞች የስም ዝርዝርና

ያልተከፈላቸው ደመወዝ እንዲሁም ክፍያው ያልተፈጸመበት ምክንያት በዝርዝር የሚገልጽ መረጃ ለኦዲት ሊቀርብ አልቻለም፡፡ በተጨማሪም የሠራተኞች የጡረታ መዋጮ ብር 543,285.30 ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ያልተላለፈ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- በሃዋሳ ዩኒቨርስቲ-የወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮለጅ ከሥራ ግብር፣withholing tax እና ከተጨማሪ እሴት ታክስ በድምሩ ብር 182,543.83 የተሰበሰበ ቢሆንም ገንዘቡ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ሣይተላላፍ ተገኝቷል፡፡
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለሥራ አመራሩ በተዘጋጀው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት መሠረት በባህርዳር ዩኒቨርስቲ ብር 5,758,577.00 እና በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ብር 7,546,129.63 በድምሩ ብር 13,304,706.63 ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ የተገለጸ ቢሆንም በዝርዝር ለማየት ተሞክሮ ትክክለኛ ገጽታውን የሚያሳይ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

የተከፋይ ሂሣቦቹን ዓይነት በመዘርዘር መወሥድ ስላለበት ዕርምጃ የሰጠነውን አስተያየት አብዛኛዎቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የተቀበሉት መሆኑን በሰጡት ምላሽ አስታውቀዋል፡፡

# 4 የገቢ ሂሣብ

## 4.1 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

የውስጥ ገቢ የሰበሰቡ መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ማካተታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ10 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 110,123,572.53 የሰበሰቡትን በገቢ ሂሳብ ሪፖርት አላካተቱም፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-13 ተመልክቷል/

ከዚህም በተጨማሪ፣

- የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ደግሞ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ብር 7,423,800.00 የሰበሰበ መሆኑን ቢገልፅም የውስጥ ገቢ ሂሣቡን አልመዘገበም፣ ከወጪ ቀሪም የሚያሣይ መዝገብ የለም፡፡
- የወሎ ፣የመቀሌ ጤና ሳይንስና አይደር ሪፈራል ሆስፒታል፣የጎንደር ዩኒቨርስቲና የሠመራ ዩኒቨርስቲን የውስጥ ገቢ ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ ተሞክሮ ፣ የውስጥ ገቢ ሂሳብና ከገቢው ወጪ የሚደረገው ሂሳብ

የማይመዘገብና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት የማይደረግ በመሆኑ ኦዲት ለማድረግ አልተቻለም።

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚዘጋጁት ሂሣብ መግለጫዎች ከተለያዩ ምንጮች የተገኙትን ገቢዎች አካቶ መያዝ እንዳለበት ለሰጠነው አስተያየት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የተቀበሉት መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

4.2 <u>በወቅቱ ያልተሰበሰበ ገቢ</u>

መ/ቤቱ በተፈቀደለት የሥራ ዘርፍ አገልግሎቱን በሚሰጥበት ወቅት መሰብሰብ የነበረበትና በወቅቱ ያልተሰበሰበው የገቢ ሂሣብ ቀጥሎ የተመለከተው ነው፡፡

የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 424,483.83በወቅቱ ያልሰበሰበ ሲሆን ገቢውን እንዲሰበስብ አሳስበናል፡፡

**4.3** <u>ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያልተደረገ ገቢ</u>

የወሎ ዩኒቨርስቲ ለተለያዩ የኮንትራትና የጉልበት ሠራተኞች ክፍያ ሲፈጽም ተቀናሽ የሆነው የሥራ ግብር ፈሰስ መሆኑን ሲጣራ ፣ በጥቅሉ ብር 589,186.21 የተሰበሰበው የሥራ ግብር ለሚመለከተው አካል ፈሰስ አመደረጉ ተረጋግጧል ።

4.4 <u>በገቢ ግብርና ተጨማሪ እሴት ታክስ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ</u>

ግዥ ሲፈጸም በደንቡና መመሪያው መሠረት ታክስና የታክስ ቅድሚያ ክፍያ ለመቀነሱ ሲጣራ ፣

- የወሎ ዩኒቨርስቲ-የተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተቀነሰ ብር 393,452.00
- የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ የጤና ሳይ. ኮሌጅ ተጨማሪ እ.ታክስ 1,858.04
- የዲላ ዩኒቨርስቲ-ከተከፋይ የሚቀነስ ግብር ያልተቀነሰ 208.60

በድምሩ <u>395,518.64</u>

የተጨማሪ እሴት ታክስና የገቢ ግብር አለመቀነሱ ተረጋግጧል ።

4.5 <u>በገቢ አሠባሰብ ላይ የታዩ የአሠራር ድክመቶች</u>

- የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የውስጥ ገቢ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ለማጣራት ሲሞከር ከፕሮጀክት ሂሳብ ጋር ተጣምረው በተመሳሳይ ቋት (ሌጀር) የተያዙ በመሆናቸው ኦዲት ለማድረግ አልተቻለም።
- -የጅማ ዩኒቨርስቲ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት የገቢ ማመንጫዎች፤-
    1. የጅማ ዩኒቨርስቲ ሞዴል ፋርማሲ ቁጥር 1፤

2. የጅማ ዩኒቨርስቲ ሞዴል ፋርማሲ ቁጥር 2፣

3. የጅማ ዩኒቨርስቲ ኮሚኒቲ ትምህርት ቤት፣

4. የጅማ ዩኒቨርስቲ መጻህፍትና ሸቀጣሸቀጥ መደብር፣

5. የጅማ ዩኒቨርስቲ የሠራተኞች መዝናኛ ክበብ፣

6. የውስጥ ገቢና ፕሮጀክት ሂሳብ

7. የጅማ ዩኒቨርስቲ የቁሳቁስ ማምረቻና ጥገና ኢንተርፕራይዝ

8. የጅማ ዩኒቨርስቲ ኪቶ ፉርዲሣ ግብርና ልማት ኢንተርፕራይዝ

እንዳሉት ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የገቢ ማመንጫዎቹን የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚገልጹና አግባብነት ያላቸው የሂሳብ ዶክመንቶች፣ ሪፖርቶችና ደጋፊ ማስረጃዎች ዩኒቨርስቲው ለማቅረብም ሆነ ኦዲት ለማስደረግ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት የገቢ ማመንጫዎች ሂሣብ ኦዲት ማድረግ አልተቻለም፡፡

ማንኛውም የመንግስት ገንዘብ ሊሰበሰብ የሚችለው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባሳተመው የገቢ ደረሰኝ ወይም በሚኒስቴሩ ፈቃድ በሚዘጋጀው የገቢ ደረሰኝ ወይም ኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ እንደሆነ በፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቀጥር 3/2003 የታዘዘ ቢሆንም የጅማ ዩኒቨርስቲ፣ የመቀሌ ጤና ሳይንስና አይደር ሪፈራል ሆስፒታል፣የጎንደር ዩኒቨርስቲ፣የአክሱም ዩኒቨርስቲ፣የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ እና የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ የሚኒስቴሩን ፈቃድ ሳያገኙ ለከፋዩ የሚሰጥ የጥሬ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በስማቸው በማሳተም ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ገንዘብ የሚሰበስቡ ሲሆን በሃዋሳ ዩኒቨርስቲ-የወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ ደግሞ የውስጥ ገቢ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ፣ ጆርናል ቫውቸር፣ የፔቲ ካሽ ቫውቸር እና እንዲሁም የዕቃ ገቢ ደረሰኝ በኮሌጁ ስም በማሣተም ለውስጥ ገቢ ሂሳብ የሚገለገል መሆኑ ታውቋል፡፡

- በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ብር 98,277.62 የያዙ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለተቀነሰ ገንዘብ የሚሰጥ ደረሰኝ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡
- በአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ ከትምህርት አገልግሎት የሚሰበሰበው ገቢ በገቢ ደረሰኞች ላይ የገቢው ዓይነትና የተከፈለበት ምክንያት ተለይቶ የማይጠቀስ በመሆኑ የተከፈለው ገንዘብ ተቋሙ ባወጣው የማስከፈያ ታሪፍ/ተመን ጋር በማመሣከር ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አለመቻሉና ከንብረት ክፍሉ ወጪ

የሆኑት ደረሰኞች ተሰርቶባቸው ሲጠናቀቁ አስቀድሞ ደረሰኞቹን ወጪ ያደረገው ሠራተኛ ወደ ንብረት/ሰነድ ክፍል ተመላሽ ለማድረጉ ቀጥጥር አይደረግም፡፡ በመሆኑም አስቀድሞ ወጪ የሆኑት ደረሰኞች የተሰራባቸው ለመሆኑ፤ ቀሪ ጥራዞቹ በሙሉ ተጠቃለው ወደ ንብረት/ሰነድ ክፍል ለመመለሳቸው ሳይጣራ ሠራተኞቹ ተጨማሪ ደረሰኞችን ወጪ ያደርጋሉ፡፡

- በጎንደር ዩኒቨርስቲ፣በባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣በመቀሌ ዩኒቨርስቲና በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ የውስጥ ገቢና ልዩ ልዩ የፕሮጀክት ሂሳቦች በአንድ የሂሳብ ቋት የሚመዘገቡ በመሆኑ በየሂሣቡ ዓይነት ተቀጽላ የሂሣብ ሌጀር በመክፈት ሂሳቡ ተለይቶ የማይያዝ መሆኑና ከንብረት ክፍሉ ወጪ የሆኑት የውስጥ ገቢ ገንዘብ መቀበያ  ደረሰኞች የተሰራባቸው ለመሆኑ የተሰበሰበውም ገንዘብ ባንክ ገቢ ለመደረጉ  ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- ጎንደር ዩኒቨርስቲ በውስጥ ገቢ ደረሰኝ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ተገኝቷል፡፡
- በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቁጥር አው-ግ-54/ በቀን 9 ነሐሴ 2000 በተላለፈ መመሪያ መሰረት ለቤት አበል የሚፈጸም ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት የተመለከተ ቢሆንም የጅማ ዩኒቨርስቲ ግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ፣የጅማ ዩኒቨርስቲ፣የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ፣ የመዳወላቡ ዩኒቨርስቲ፣የጎንደር ዩኒቨርስቲና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ በተላለፈው መመሪያ መሰረት ለቤት አበል የተፈጸመው ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ የሥራ ግብር እንደማይቀነስ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ጎንደር ዩኒቨርስቲ ለትምህርት ወደ ውጭ አገርና ወደ ተለያዩ የትምህርት ተቋማት ለሄዱ መምህራን የመኖሪያ ቤት አበል እንደሚከፍልና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ለአስተዳደር ሰራተኞች የመኖሪያ ቤት አበል ክፍያ የሚፈፀም መሆኑ ታውቋል፡፡

ተቋማቱ በመንግሥት የሚወጡ አዋጆችንና ደንቦችን በመከተል ደረሠኝ ከማሣተም በፊት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማስፈቀድ እንዳለባቸው በተጨማሪም ክፍያዎች ደንቡንና መመሪያውን ተከትሎ መፈፀም እንዳለበት በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

# 5 የወጪ ሂሣብ

## 5.1 በወጪ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ

በበጀት ዓመቱ የተከፈሉት ወጪዎች በሂሳብ ሪፖርት በትክክል ለመካተታቸው ኦዲት ሲደረግ በ4 መ/ቤቶች ብር **12,031,574.35** የወጪ ሂሳብ ፣ በ2003 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አለማካተታቸውና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት አለማድረጋቸውን ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-23 ተመልክቷል/

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ከውስጥ የተገኘውን ገቢ መዝግበው ሪፖርት እንዲያደርጉ፣ ወጪ የተደረገውም ሂሣብ በሪፖርት ውስጥ መካተት እንዳለበት አስተያየት የሰጠን ሲሆን፣ በአስተያየቱ መሠረት ጉዳዩን በማጣራት የእርምት ዕርምጃ እንደሚወስዱ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

## 5.2 የሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ የተከናወኑ ምዝገባዎች

ለተለያዩ ወጪዎች የዋሉ ሂሳቦች በየሂሳብ መደባቸው መመዝገባቸው ኦዲት ሲደረግ የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ በ8 መ/ቤቶች ብር 6,636,263.97 ተመዝግበው ተገኝተል፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-26 ተመልክተዋል፡፡/

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ አለመመዝገብ ከበጀት አጠቃቀም አንፃር ተፅዕኖ ሊፈጥር ስለሚችል (ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀም) ተገቢው ጥንቃቄ እንዲወሰድ አስተያየት ሰጥተናል፡፡

## 5.3 ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ

ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡና ወደሂሣብ መግለጫ ከመተላለፉ በፊት በቂ የሆነ ደጋፊ ማስረጃ ሊቀርብለት እንደሚገባ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም በተለያዩ 5 መ/ቤቶች ማስረጃ ሣይቀርብላቸው በድምሩ በብር 34,650,635.60 በወጪ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-17 ተመልክቷል/

## 5.4 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች ለመ/ቤቱ አገልግሎት የዋሉና የተሟላ መረጃ ቀርቦላቸው በወጪ ለመመዝገባቸው ሲጣራ፣ በ11 መ/ቤቶች በድምሩ ብር **31,890,494.49** የተሟላ ማስረጃዎች ሣያቀርቡ ወጪውን መዝግበዋል፡፡/ዝርራቸው በአባሪ-16 ተመልክቷል/

የየመ/ቤቱ ሥራ አመራር የሰጠነውን ማሻሻያ ተቀብሎ ችግሩ እንዳይደገም ክትትል እንደሚያደርግና ለሚመለከተውም ክፍል መመሪያ እንደሚያስተላልፍ ገልጿል፡፡

5.5 <u>የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሣይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች</u>

መ/ቤቶች በውል የሚፈጽሟቸውን ክፍያዎች ደንብና መመሪያን እየጠበቁ መከፈሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣

| | | |
|---|---|---|
| • የወሎ ዩኒቨርስቲ -የጨረታ ሠነድ ያልቀረበ | ብር | 627,700.92 |
| -የውል ስምምነት የሌለው | | 59,565.50 |
| -ውሉ የዩኒቨርስቲውን ስም ያልጠቀሰ | | 14,057.50 |
| • የከፍተኛ ትም. ስተራቴጂ-ያልታደሰ ውል ስምምነት | | 625,922.76 |
| • የዲላ ዩኒቨርስቲ-የጨረታ ሠነድና የውል ስምምንነት የሌለው | | 59,619.28 |
| በድምሩ | | 1,386,865.96 |

የጨረታ ሠነድና የውል ስምምነት ያልቀረበለት ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

-የወሎ ዩኒቨርስቲ በብር 454,994.78 የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎት ግዥ ሲፈጽም ከሦስት የተለያዩ ድርጅቶች የዋጋ ማወዳደሪያ ያልቀረበ ሲሆን ፣ በብር 74,839.65 ደግሞ የስፖርት ትጥቅ በአቅራቢነት ካልተመዘገበ ግዥ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

-የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ደንብና መመሪያን ተከትሎ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣ ለተማሪዎች መኝታ ክፍልና መደርደሪያ የጸረ ተባይ መድሐኒት ለማስረጨት በወጣው ዋጋ ማወዳደሪያ መሠረት ዝቅተኛ ዋጋ የቀረበ ድርጅት እያለ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት ግዥ በመፈጸሙ ያለአግባብ ብር 17,778.05 በብልጫ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

-የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ አነስተኛ ዋጋ ካቀረቡ ተወዳዳሪዎች ላይ ግዥው መፈጸም ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡት ተወዳዳሪዎች እቃው በመገዛቱ ብር 195,418.30 አላግባብ በብልጫ ከፍሏል፡፡

-በመዳወላቡ ዩኒቨርስቲ በጨረታ ውድድር ከተሳተፉት ተጫራቾች መካከል አነስተኛ የዕቃ ዋጋ ካቀረቡት ተጫራቾች መገዛት ሲገባው ከፍተኛ የዕቃ ዋጋ ካቀረቡት ተጫራቾች ዕቃው በመገዛቱ በድምሩ ብር 120,765.00 አላግባብ በብልጫ የተከፈለ ሲሆን ብር 9,000.00 ከውል ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

-ያለግልፅ ጨረታ ከአንድ አቅራቢ፣ በዋጋ ማቅረቢያና በውስን ጨረታ የተከናወነ ግዥ፣

| | |
|---|---|
| የመቀሌ ጤና ሳይንስና አይደር ሪፈራል ሆስፒታል | ብር 3,063,572.81 |
| ጎንደር ዩኒቨርስቲ | 506,684.55 |
| ባህርዳር ዩኒቨርስቲ | 41,388,521.78 |
| መቀሌ ዩኒቨርስቲ | 224,219,092.76 |
| አክሱም ዩኒቨርስቲ | 1,339,445.04 |
| አክሱም ዩኒቨርስቲ | 235,595.00 |
| ጎንደር ዩኒቨርስቲ | 999,970.00 |
| ጅማ ዩኒቨርስቲ ግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ | 398,000.78 |
| መዳወላቡ ዩኒቨርስቲ | 270,509.58 |
| ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ | 539,997.12 |
| ድምር | 272,961,389.42 |

ለወደፊቱ ግዥዎች ሲፈፀሙ የመንግሥትን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መከተል እንዳለባቸው በሰጠነው አስተያየት ገልፀናል፡፡

## 6.6. በኃላፊ ሣይፈቀድ የተፈፀመ ክፍያ

ክፍያዎች በሚመለከተው ኃላፊ በትክክል መጽደቃቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የዲላ ዩኒቨርስቲ በሚመለከተው ኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 256,188.23 እና ብር 812,317.97 ደግሞ ከሥልጣን ገደብ ውጪ ውክልና ሳይኖር ወጪው ለመጽደቁ ተረጋግጧል ፡፡ በተጨማሪም በባህርዳር ዩኒቨርስቲ በሚመለከተው ኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 2,622,754.80 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም ማንኛውም ክፍያ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ መፅደቅ እንዳለበት አሣስበናል፡፡

## 6.7. ቅድሚያ ክፍያን በወጪ መመዝገብ

-በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ለትምህርት መሣሪያዎች መግዣ Letter of Credit መክፈቻ Construction&Business Bank P.L.C. ገቢ የተደረገው ብር 68,160,410.85 በተሰብሳቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባው አላግባብ በወጪ የተያዘ፣

-በጅማ ዩኒቨርስቲ ለሥራ ተቋራጮች በቅድሚያ የተከፈለው ገንዘብ ብር 109,053,192.63 እና ለህክምና መገልገያዎች መሳሪያዎችና መፃህፍት ግዢ /Letter of Credit/ መክፈቻ ኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ አክሲዮን ማህበር ገቢ የተደረገ ብር 59,380,129.12 በድምሩ ብር 168,433,321.75 በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ሲገባው አላግባብ በወጪ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

-የትምህርት ሚኒስቴር የሌተር ኦፍ ክሬዲት ክፍያ ብር 539,693,122.65 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ክፍያው ተስተካክሎ እንዲያዝ በሰጠነው ማሣሰቢያ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወስዱ መ/ቤቶቹ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

6.8. <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበበት የወጪ ሂሣብ</u>

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተገዙት ዕቃዎች በሙሉ ለየመ/ቤቶቹ ገቢ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሲሞከር ቀጥሎ የተመለከተው የገንዘብ መጠን የንብረት ገቢ ደረሰኝ አልተቆረጠለትም፡-

| | |
|---|---|
| ❖ የኢትዮጵያ ስቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ | ብር 3,901,500.00 |
| ❖ የጎንደር ዩኒቨርስቲ | 4,025,832.76 |
| ❖ የትምህርት ሚኒስቴር | 75,264,593.77 |

በመሆኑም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉት ዕቃዎች ዝርዝር ሁኔታ ተጣርቶ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሊቆረጥለት እንደሚገባ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

6.9. <u>ሁለት ጊዜ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

የገቢ ሂሳቦች በትክክል ለመመዝገቡ ኦዲት ሲደረግ ፣

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 95,432.91

በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ግብርና ኮሌጅ ብር 74,078.00 ሁለት ጊዜ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ተገኝተል፡፡

ይህም የሂሳብ ሪፖርቱን ስለሚያዛባ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

6.10. <u>በብልጫ/በድጋሜ የተከፈለ</u>

ክፍያዎች በደንቡና በውሉ መሠረት መከናወኑን ሲጣራ ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የንግድ ስራ ት/ቤት ብር 2,293.10 በድጋሜ እና ሠመራ ዩኒቨርስቲ ለተማሪዎች

የምግብ አገልግሎት ለሚሰጠው ድርጅት ያለአግባብ ብር 214,706.78 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል።

6.11. <u>ከበጀት ዓመቱ ውጭ ተመዝግቦ የተገኘ</u>

| | | |
|---|---|---|
| የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ | ብር | 48,352.00 |
| የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲት | | 5,008.68 |
| የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | | 1,332,206 .95 |
| የአ. አ ዩኒቨርስቲ የስነትምህርትና የባህርይ ጥናት ኮሌጅ | | 757,501.60 |
| ድምር | | 2,143,069.23 |

በመሆኑም ሂሣቡ አገልግሎቱ በተገኘበት በጀት ዓመት ተስተካክሎ መመዝገብ እንዳለበት ያሣሰብን ሲሆን፣ ሥራ አመራሩም የማሻሻያ ሃሣቡን ተቀብሎታል፡፡ በተጨማሪም ያለፈውን ዓመት ወጪ ወደ 2003 በጀት ዓመት ማምጣት ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀምን ሊያስከትል ስለሚችል የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በሰጠነው ማሻሻያ ሃሣብ ላይ ገልፀናል፡፡

6.12. <u>ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያላግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ስለትርፍ ሠዓትና ልዩ ልዩ አበሎች አከፋፈል ከወጣው ከደንብና መመሪያ ውጭ ብር 192,871.00 የተከፈለ ሲሆን ብር 4,000.00 ለዳቦ አቅርቦት በብልጫ የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

በተጨማሪም ደንብና መመሪያ ሣይጠብቁ በወጪ ተመዝግበው የተገኙት ሂሣቦች በ6 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 235,619,304.87 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-19 ተመልክቷል/

ከውስጥ ገቢ ወጪ ለማድረግ ከተፈቀደው በጀት በላይ ጥቅም ላይ የዋለ፤

- ጎንደር ዩኒቨርስቲ - ብር 2419084.20
- ባህርዳር ዩኒቨርስቲ - ብር 66247352.36
- ከትምህርት ሚኒስቴር ለቋሚ ዕቃ ግዥ በሚል የመጣን ብር ከዩኒቨርስቲው (አክሱም ዩኒቨርስቲ) የውስጥ ገቢ እንደተከፈለ ተቆጥሮ በውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት ብር 201670.95 በወጪ ተመዝግቧል፡፡

6.13. ለኦዲት ያልቀረቡ የወጪ ሠነዶች

የወጪን ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣

| | |
|---|---|
| አክሱም ዩኒቨርስቲ | ብር 1,313,459.79 |
| የወሎ ዩኒቨርስቲ | 794,117.11 |
| የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ | 12,482,013.83 |
| በድምሩ | 14,589,590.73 |

የያዙ የወጪ ማስረጃዎች (ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ሠነዶች) ለኦዲት ያልቀረቡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

# 7. የዕቃና ንብረት አስተዳደር

ቋሚም ሆኑ አላቂ ዕቃዎች በተቀመጠለት ሥርዓት ተመዝግቦ መያዙን ለማረጋገጥ ሲሞከር፣ በ19 መ/ቤቶች/ዝርዝራቸው በአባሪ-29 ተመልክቷል/ የቋሚ ንብረት መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ መዝገብ አቋቁመው (ያቋቋሙትም ቢሆን ምዝገባውን አጠናቀው፣ ለቋሚ ዕቃም መለያ ቁጥር ሰጥተውና ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ አድርገው) ከወጪ ቀሪያቸውን ወይም ያሉትን ዕቃዎች የሚያውቁበት መንገድ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ፤

በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ

- የምግብ ጥሬ እቃዎች ገቢና ወጪ ደረሰኞች የማዘጋጀት ንብረት የመጠበቅ ስራ በአንድ ሰው የሚከናወን መሆኑ፣
- እንዲሁም የንብረት ወጪ ደረሰኝ ላይ ወጪ የሚያደርጉ ሰዎች የማይፈርሙ መሆኑ፣
- ክፍያ በሚፈጸምበት ወቅት የጥራት አጣሪ ኮሚቴዎች፣ የጨረታ ኮሚቴ ውሳኔና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 የማይገናዘብ መሆኑ ታውቋል፡፡

በሚዛን ዩኒቨርስቲ፤-ሚዛን ካምፓስ፤

- በንብረት መጠበቂያ መጋዘን የሚገኙት እቃዎች በዓይነት፤በባህሪይና በሚሰጡት አገልግሎት ተለይተው በሥርዓት ያልተቀመጡ በመሆኑ ከፍተኛ ዋጋና ብዛት ያላቸው እቃዎች ለብልሽትና ለጉዳት የተዳረጉ መሆኑን፡
- ብዛት ያላቸው ያገለገሉ ዕቃዎች በዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ተበታትነው የሚገኙ መሆኑን፡
- ለቋሚ ንብረቶች የመለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑን፤
- በቤተ መጻህፍት ግምጃ ቤት የሚገኙት መጽሐፎች መቆጣጠሪያና መከተታተያ ስቶክ ካርድ ወይም መዝገብ የሌለ በመሆኑ የመፅሐፍት ገቢና ወጪ የማይመዘገብ መሆኑን፤

- በተቋሙ ውስጥ የሚባዙ ወይም ኮፒ የሚደረጉ የመማሪያ መጽሐፍቶች/ Text Book/ ተባዝተው ከተጠረዙ በኋላ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የማይዘጋጅላቸው መሆኑን፣ በተጨማሪም በተቋሙ የተባዙና ኮፒ የተደረጉ በርካታ መጽሐፍቶች በመጠረዣ ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ መጽሐፍቶቹን በኃላፊነት የተረከባቸው ሠራተኛ አለመኖሩን፣
- በተለያዩ ምክንያቶች ለሚጠፉ መጽሐፎች የማስከፈያ የዋጋ ተመን ያልተዘጋጀ መሆኑን፣

- በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ በብር 123,280.00 ከተገዙት 400 /Flash Disk 4 GB/ ውስጥ ብር 121,122.00 ዋጋ ያላቸው በቁጥር 393 ፍላሾች የተበላሹና አገልግሎት ላይ ሊውሉ የማይችሉ ሲሆን፣በአቅራቢው ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡
- የኢትዮጵያ ስቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የመድኃኒት መጋዘን ክፍል የመጠበቅ ኃላፊነት፣ ገቢና ወጪ ማድረግ፣ የመመዝገብና መድኃኒት ለተጠቃሚ የማሰራጨት ተግባር በአንድ ሰው ይከናወናል፡፡
- በጅማ ዩኒቨርስቲ *ለሣትኮን ኮንስትራክሽን ድርጅት በብድር የተሰጠ ብዛት 100 እና ለኮሚኒቲ ት/ቤት ብዛት 200 ኩንታል ሲሚንቶ እንዲሁም ለጅማ ግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ በብድር የተሠጠ ቱራዞ የመሬት ምንጣፍ በቁጥር 1550 ተመላሽ አልተደረገም፡፡በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው ለሚከናወኑ ጅምር ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚሆን ብዛት 64,400 ኩንታል ሲሚንቶ በተቋሙ መገዛቱንና ለስራ ተቋራጮች በዱቤ የተከፋፈለ መሆኑን ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ የወሰደው ሲሚንቶ ብዛትና ዋጋ እንዲሁም ተቋራጩ ተመላሽ ያደረገው ወይም የከፈለው ገንዘብና የሲሚንቶው ብዛት መከታተያና መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርድ/መዝገብ በማቋቋም ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡*

በመሆኑም በቋሚ ዕቃነት መመዝገብ ያለባቸው እንዲመዘገቡ፣ ሥራ ላይ ሊውሉ የማችሉት ከማይችሉት እንዲለዩ፣ ዕቃዎች እንዳይበላሹ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሠድ፣ አላቂና ቋሚ ዕቃዎች የንብረት ገቢና ወጪ ደረሠኝ ተዘጋጅቶለት /ለቋሚ ዕቃ ወጪ ማድረጊያ ማዋሻ ቅፅም ሊሆን ይችላል/ ተመዝግበው ከወጪ ቀሪያቸው በትክክል መታየት እንዳለበትና ተደራራቢ ሥራዎችም ተለያይተው እንዲሠሩ በሰጠነው አስተያየት አሣስበናል፡፡

7.1 <u>የነዳጅ ኩፖኖችን በተመለከተ</u>

<u>በአዳማ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ</u>

- ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ነዳጅ መሙለት ኩፖኖችን ወደ ፋክቱር መቀየር ቀሪ ኩፖኖችንና ነዳጅ የተቀዳባቸውን ፋክቱሮች የመጠበቅ ስራ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፣
- ለወጪና ለገቢ ኩፖኖች መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑና ከወጪ ቀሪው የማይገናዘብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

7.2 <u>የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም</u>

<u>የቆሙ ተሽከርካሪዎች</u>

- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አንድ አምቡላንስ በውስጡ ከመኪናው ጋር የተያያዘ 793,910.00 የአሜሪካን ዶላር የህክምና መሳሪያ ይዞ የቆመ መሆኑ፣
- የጅማ ዩኒቨርስቲ ግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ የተሽከርካሪዎች አጠቃቀምና አካላዊ ጥበቃ ሲገመገም የሠሌዳ ቁጥር 4-08136 ላንድሮቨር ለአንድ ዓመት፣ የሠሌዳ ቁጥር 4-00704 ሚትስቡሽ ደግሞ ከ 5 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑን፣
- በጅማ ዩኒቨርስቲ *የሠሌዳ ቁጥር 4-02555 FJ40 ቶዮታ ሃርድ ቶፕ እና የሠሌዳ ቁጥር 4-02570 ቶዮታ በብልሽት ምክንያት ለበርካታ ዓመታት የቆሙ መሆኑን፤ የሠሌዳ ቁጥር 4-02472 አይሱዙ GCR 450፤ የሠሌዳ ቁጥር 4-02512 አይቪኮ M29 እና የሠሌዳ ቁጥር 4-02513 አይቪኮ በመለዋወጫ ምክንያት ከ1ዓመት በላይ የቆሙ መሆኑን፤*
- በሚዛን - ቴፒ ዩኒቨርስቲ የሠሌዳ ቁጥር ኮድ 4-12473 ማርቼዲስ አውቶቡስ በመለዋወጫ ምክንያት ከ8 ወራት በላይ ያለአገልግሎት የቆመ መሆኑ፤

*በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡*

ሊብሬ ያልቀረበላቸው

- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል 9 መኪናዎች የሌላ መ/ቤት ሊብሬ የቀረበ መሆኑ፣

- የአዲስ አበበባ ዩኒቨርስቲ የስነትምህርትና የባህርይ ጥናት ኮሌጅ በባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩ (በሊብሬው) ላይ የተገለጸው የሞተር ቁጥርና በመኪናው አካል ላይ የተጻፈው የተለያየ መሆኑ፣
- በጅማ ዩኒቨርስቲ ግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ 2 ትራክተሮች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፣
- በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ የሰሌዳ ቁጥር 4-14964 ሚኒባስ መኪና እና የሰሌዳ ቁጥር የሌለው ያማሃ ሞተር ብስክሌት የባለቤት ደብተር የሌላቸው መሆኑ፣
- በጅማ ዩኒቨርስቲ *ከካናዳ የህክምና ድርጅት በዕርዳታ የተገኘ የሠሌዳ ቁጥር 12-069AA ሚትስቡሽ L042Gv4100 በተቋሙ ስም ወደ ኮድ 4 ያልተለወጠ መሆኑ፣*
- በጎንደር ዩኒቨርስቲ ለዘጠኝ የዩኒቨርስቲው ተሽከርካሪዎች ሊብሬ ያልቀረበላቸው መሆኑ፣

## 7.4 <u>አገልግሎት ላይ ያልዋሉ ንብረቶች፣</u>

- በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ 15 የውኃ ማሞቂያዎች ከ 20 ዓመት በላይ፣67 የገላ መታጠቢያ ሳህኖች (ገንዳዎች) ከ20 ዓመት በላይ፣ በከፍተኛ ገንዘብ የተገዙ 2 ጄኔሬተሮች ያለአገልግሎት በንብረት ክፍል ተከማችተው ተገኝቷል፡፡
- በሚዛን - ቴፒ ዩኒቨርስቲ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የመጡ 7 የማተሚያ ማሽኖች ከ2 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት በሚዛን ካምፓስ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በሃዋሳ ዩኒቨርስቲ የወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ የንብረት መጋዘኖች ውስጥ ያገለገሉ፣ በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ እንዲሁም በሽያጭ ሊወገዱ የሚገባቸው በርካታ ንብረቶች በአንድ ላይ ተከማችተውና ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡
- በባህርዳር ዩኒቨርስቲ በርካታ አገልግሎት የማይሰጡ ቋሚ ዕቃዎች በመጋዘን ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡
- የአክሱም ዩኒቨርሲቲው በ28/12/2000 ዓ.ም መፅሀፍ ኮፒ አድርጎ የሚጠርዝ ማሽን ከትምህርት ሚኒስቴር በንብረት ገቢ ደረሰኝ ቁጥር 34854 የተቀበለ ሲሆን፣ ይህ ማሽን ለሶስት አመት ያህል ለዩኒቨርሲቲው አገልግሎት አልሰጠም፡፡ በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው የጨፍ መጋዘን ውስጥ ከትምህርት ሚኒስቴር የመጡና ከሁለት አመት በላይ የሆናቸው በእንጨት የታሸጉ ብዛት ያላቸው የወጥ

ቤት እቃዎች (Kitchen utensils) መኖራቸው ታውቋል፤ ሆኖም እነዚህን እቃዎች ዩኒቨርሲቲው በንብረት ገቢ ደረሰኝ አልተረከባቸውም፡፡

## 8. የበጀት አጠቃቀም

ለየመ/ቤቶቹ የተመደበው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ሂሣብ ጋር ሲነፃፀር፤ በ13መ/ቤቶች ብር 206,646,896.66 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የተደረገና በ25 መ/ቤቶች ብር 1,774,583,553.58 ሥራ ላይ ያልዋለ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-28 ተመልክቷል/

ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም የበጀት ሕግን ከመጣስ ባሻገር መንግሥት ያለውን ውስን ሃብት ለብክነት እንደሚያጋለጥና የታወጀን በጀት አለመጠቀሙ መ/ቤቱ ሊደርስበት ካቀደው ግብ እንዳይደርስ ከማድረጉም ባሻገር ሀገሪቱ ያላትን ውስን ሃብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዳይውል ስለሚያደርግ ዕቅድን ከክንውን ማጣጣም እንደሚገባ አስተያየት የሰጠን ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አስፈላጊውን ክትትልና ማሻሻያ እንደሚያደርጉ በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡

## 9. የአካባቢ ጥበቃ

- ከጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ክፍሎች የሚወጣው ፈሳሽ ቆሻሻ በቀጥታ ወደ ውጪ የሚለቀቅ በመሆኑና ለደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ስፍራ የሚሆን ጉድጓድ ባለመዘጋጀቱ አካባቢውን በመበከል ላይ እንደሚገኝ፣
- ጎንደር ዩኒቨርስቲ - ከማራኪ እና አፄ ቴዎድሮስ ካምፓስ ከተማሪዎች ካፍቴሪያ የሚወጣ ተረፈ ምግብ የሽንኩርት ልጣጭ፣የድንች ልጣጭ፣አመድ፣ አጥንት እና የመሳሰሉት በመመገቢያ አዳራሽ አቅራቢያ በአግባቡ ባልተሰራ የቆሻሻ ማስወገጃ እየተደፋ በመሆኑ በአካባቢው ላይ መጥፎ ጠረን እየተፈጠረና ለጤና አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱ፤
- አክሱም ዩኒቨርስቲ - ከተማሪዎች ካፌቴርያ የሚወጣው ፈሳሽ ቆሻሻ ቀጥታ ካፌቴርያው አካባቢ የሚፈስ በመሆኑ አካባቢው ላይ መጥፎ ጠረን ያስከተለና ለጤና አስጊ ደረጃ ላይ የደረሠ መሆኑ፤
- ጎንደር ጤና ሳይንስ ኮሌጅ - በሆስፒታሉ የህሙማን ማንቂያ ክፍል አቅራቢያ በአግባቡ ባልተሰራ የቆሻሻ ማስወገጃ የተለያዩ ቆሻሻዎች የሚደፉ መሆኑ እና የፕላሴንታ ማቃጠያውና የህመምተኞች ሽንት ቤቶች ሞልተው መጥፎ ጠረን እየፈጠሩ መሆኑ ታውቋል፡፡

የየመ/ቤቱ ሥራ አመራሩ የኦዲት ግኝቱንና የማሻሻያ ሃሣቡን ተቀብሎ ለተግባራዊነቱ እየተንቀሣቀሠ መሆኑን ገልጿል፡፡

10. <u>ልዩ ልዩ ጉዳዮች</u>

- የወሎ ዩኒቨርስቲ የወጪ ማስመስከሪያ (ፒ.ቪ.) እና የሠነዶችን አያያዝና አጠቃቀም በሚመለከት ማጣራት ሲደረግ ፣ ዩኒቨርስቲው የሚጠቀምባቸው የወጪ ማስመስከሪያ (መሂ/7) ፣ የሂሳብ ቋት (መሂ/17) ፣ የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (መሂ/12) እና ሌሎች ሞዴሎች በፌዴራል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በታተመ መጠቀም ሲገባው የክልሉ ቢሮ ባሳተመው የሚጠቀም ሲሆን ፣ የተለያዩ ሠነዶች በአግባቡ ያልተያዙ በመሆኑ ለኦዲት የሚፈለጉ ሠነዶች ሊቀርቡ አለመቻሉ ተረጋግጧል ፡፡
- ባህርዳር ዩኒቨርስቲ -
  - ✓ የዩኒቨርስቲው መምህራን ከተሰማሩበት ስራ በተደራቢነት በአስተዳደራዊ ስራ ላይ ተመድበው የሚሰሩ መሆኑ፣
  - ✓ የዩኒቨርስቲው ውስጥ ኦዲት ነፃና ገለልተኛ መሆን ሲገባው የዩኒቨርስቲው የውስጥ ኦዲት ዳይሬክተር ከኦዲት ስራ በተጨማሪ በመምህርነት እና በሌሎች የአስተዳደር ስራዎች የሚሰሩ መሆኑ፣
- መቀሌ ዩኒቨርስቲ - በዩኒቨርስቲው ወጪ ሃያ አንድ አስተማሪዎች በውጭ አገር ትምህርታቸውን ለተከታተሉት በውሉ መሰረት ተመጣጣኝ አገልግሎት ወይም ክፍያ ሳይፈፅሙ የለቀቁ፣
- አክሱም ዩኒቨርስቲ - የተማሪዎች ካፍቴሪያ በተለያየ ጊዜ ተማሪዎች ለመስክ ስልጠና ሲወጡ ስለ ካፌ ተጠቃሚ ተማሪዎች ብዛት ከመሰረታዊ አገልግሎት ማዕከል ዳይሬክተር ማስረጃ የማይደርሰው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

# የልማትና ማኅበራዊ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
# የ2003 በጀት ዓመት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን፣ እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ፣በዳይሬክቶሬቱ የታቀዱ የ31 መ/ቤቶችን የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብን ኦዲት አድርገናል፡፡

ለመሥሪያ ቤቶቹ በሙሉ ለሥራ አመራር የተዘጋጀውን ሪፖርት የላክን ሲሆን፣ መ/ቤቶቹ በሙሉ ለሪፖርቱ በሰጡት መልስ ውስጥ ስለማሻሻያ ሃሣቦቹ ያላቸውን አስተያየት በገለጹት መሰረት ለሁሉም መ/ቤቶች ኦዲት በተደረገው ሂሣባቸው ላይ ያለንን አስተያየት የያዘ ሪፖርት ተልኳል፡፡

በዚሁ መሠረት 20 መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት፣ 9 መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ግድፈቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆኖ ስለተገኘ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት፣እና 2 መሥሪያ ቤቶች አሠራር ብዙ ጉድለት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ የሂሣብ መግለጫው አጥጋቢ እንዳልሆነ የሚያንፀባርቅ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

በኦዲቱ የተገኙ ዋናዋና ግኝቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

## 1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሒሳብ

### 1.1 የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመት

የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ታኅሳሥ 2003 ዓ.ም ባወጣው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የሚከናወን መሆኑ ኦዲት ሲደረግ :

- በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በየወሩ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተደረገ እና ከመዝገብ (ከሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋርም ያልተመዛዘነ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ የምግብ ፣መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ በሪፖርት ከተመለከተው በብር 12,118.83 አንሶ የተገኘ መሆኑ፣

- በኢትዮጵያ ስጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በሪፖርት የተመለከተው ብር 763.50 በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ወቀት ያልተገኘ መሆኑ፣
- በብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ በሪፖርት ከተመለከተው በብር 227.61 አንሶ የተገኘ መሆኑ፣
- በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተደረገና ማመዛዘኛም ያልተሰራ መሆኑ ፣
- በአላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ፡
  - የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በየዕለቱ ያልተከናወነ መሆኑ ፣
  - የዋና ገንዘብ ያዥ የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠሪያ መዝገብ (ሌጀር) ያልተቋቋመ መሆኑ፣
  - ከተለያዩ የገቢ አርዕስቶች የተሰበሰበዉ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማይደረግ መሆኑ ፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም አስተማማኝ የሆነ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር በመመሪያዉ መሰረት የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠሪያ መዝገብ (ሌጀር) እንዲቋቋም፣ ዕለታዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እንዲካሄድና የሚሰበሰበውም ገቢ በወቅቱ ባንክ ገቢ እንዲደረግ እንዲሁም በልዩነት በታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ላይ ተገቢው ማጣራት ተደረጎ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

### 1.2 ለረጅም ጊዜ በባንክ ሂሳብ ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ

በፌደራል ስፖርት ኮሚሽን ለመኪና መግዣ ተብሎ በብሔራዊ ባንክ በተከፈተ ልዩ አካውንት ሂሳብ ውስጥ ከ1999 በጀት ዓመት ጀምሮ የተቀመጠ ብር 686,237.50 ተገኝቷል:: ገንዘቡ ያለሥራ ለረጅም ዓመታት በመቀመጡ በግሽበት ምክንያት ዋጋው ሊቀንስ ይችላል ። በመሆኑም ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ በአስቸኳይ እንዲውል በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ::

## 2. ተሰብሳቢ ሂሳብ

### 2.1 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌደራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች በወቅቱ የሚወራረዱ ለመሆኑ

ማጣራት ሲደረግ፤ በ14 መ/ቤቶችመሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 206,836,496.13

በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል።/ዝርዝራቸው በአባሪ-9 ተመልክቷል/

ተሰብሳቢ ሒሳቦቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ ባለመወራረዳቸው ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አልተቻለም ።

በመሆኑም ለቅድሚያ ክፍያ የተሰጡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2.2 መመሪያዉ ከሚፈቅደው በላይ የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ

በፋይናንስ ግዥ መመሪያው መሰረት ለቅድመ ክፍያ መከፈል ያለበት ከዉሉ ጠቅላላ ገንዘብ ውስጥ 30% መሆን ይኖርበታል ። ይሁን እንጂ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ለአጋርፋ ኮሌጅ የመስኖ ግንባታ የማማከር አገልግሎት የሚሆን የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ለኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማኅበር ሲከፈል ከጠቅላላው ክፍያ ብር 926,117.82 ውስጥ 30% ብር 277,835.34 መከፈል ሲገባው 50% ብር 463,082.00 በመከፈሉ ምክንያት መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ በብልጫ ብር 185,246.66 መከፈሉ ታውቋል::

በመሆኑም የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በመመሪያዉ መሰረት እንዲከፈሉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ ለመሥሪያ ቤቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

## 2.3 በክሬዲት ባላንስ የታየ ተሰብሳቢ ሂሳብ

በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በተቀጽላ የሂሳብ ሌጀሮች በድምሩ ብር 420,850.71 በክሬዲት አቅጣጫ ተመዝግቦ ተገኝቷል::

በመሆኑም ሁኔታው ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

## 3. ተከፋይ ሒሳብ

### 3.1 ማስረጃ ሳይቀርብ በተከፋይ ሂሣብ ሪፖርት የተካተተ ሂሳብ

መሥሪያ ቤቶች ያዘጋጁት የሂሣብ መግለጫዎች በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት መሆኑን እና በሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በግብርና ሚኒስቴር :
    - በወቅቱ መወራረድ የነበረበት ያልተወራረደ የደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ ብር 831,146.42 ፣
    - በበጀት ዓመቱ ሳይከፈል የታለፈ የጡረታ መዋጮ ተከፋይ ሂሳብ ብር 41,747.56 ፣
- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ:
    - የጡረታ መዋጮ ብር 125,146.77 ፣
    - የደመወዝ የተጣራ ተከፋይ ሂሣብ ብር 23,000,357.47 ፣

በድምሩ ብር 23,998,398.22 ተከፋይ ሒሳቦች ሰኔ 30/2003 በተከፋይ ሂሣብ መግለጫ ውስጥ ተካተው ሪፖርት ተደርገው ተገኝተዋል ፡፡ በተለይም በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ሪፖርት ለተደረገው ሂሣብ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም ፡፡

በመሆኑም የተከፋይ ሒሳቡ ሁኔታ ተረጋግጦ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለመሥሪያ ቤቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ።

### 3.2 ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ

የተከፋይ ሒሳቦች በወቅቱ የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :

በ11 መ/ቤቶች ለተለያዩ ድርጅቶች ሊከፈል የሚገባው በጠቅላላው ብር

ብር 3,853,116.16 ሳይከፈል ተገኝቷል::/ዝርዝራቸው በአባሪ-27ተመልክቷል/

በመሆኑም ሁኔታው ተጣርቶ ሒሳቡ በወቅቱ ሊከፈል እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ::

### 3.3 በገቢ መያዝ ሲገባው በተከፋይ ተይዞ የተገኘ ሂሳብ

በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ተከላ እና ሽያጭ የተሰበሰበው ብር 1,403,036.37 በገቢ መያዝ ሲገባው በተከፋይ ሒሳብ ተይዞ ተገኝቷል :: በመሆኑም ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ::

### 3.4 በዴቢት ባላንስ የታየ የተከፋይ ሂሳብ

በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 283,295.29 ተከፋይ ሂሳብ በዴቢት አቅጣጫ ተመዝግቦ ተገኝቷል :: በመሆኑም ሁኔታው ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ::

### 3.5 በስህተት የተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ

በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በሌሎች የመያዣ ሂሳቦች ( 5054 ) የሂሳብ መደብ በመነሻነት (Opening Balance) የተመዘገበው በDአካውንት ባንክ ስቴትመንት ላይ ከታየው በብር 748,767.88 አንሶ ተገኝቷል :: በመሆኑም ሁኔታው ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ::

## 4. የገቢ ሒሳብ

### 4.1 ከሽያጭ ለሚሰበሰበው ገቢ ተመን አለመኖሩ

ገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በጥናት ላይ የተመሰረተ የገቢ ተመን የወጣለት መሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :

- የብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ከአባላዘርና ፈሳሽ ናይትሮጅን ሽያጭ ለሚሰበስበው ገቢ በጥናት ላይ የተመሰረተ የገቢ ተመን እንዲወጣለት ያላደረገ መሆኑ ፣
- የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በበጀት ዓመቱ ለሰበሰበው ብር 1,273,606.00 በሚመለከተው አካል የጸደቀ የዋጋ ተመን እንዲወጣለት ያላደረገ መሆኑ ፣ ታውቋል፡፡

  በመሆኑም መሥሪያ ቤቶቹ ለሚሰበስቡት ገቢ ተገቢው ተመን በመመሪያ ደረጃ እንዲወጣለትና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ የበኩላቸውን ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 4.2 በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት በሂሳብ ሌጀሮች ላይ በፋይናንስ ምንጫቸው የተመዘገቡ ሂሰቦች ሚዛን ተወስዶ ወርሃዊና ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶች መዘጋጀት አለባቸው፡፡ በዚሁ መሰረት በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት በማስተባበሪያው ሥር የሚገኙ ኮሌጆች በበጀት ዓመቱ የሰበሰቡትን የገቢ ሂሳብ በፋይናንስ ምንጫቸው መሰረት በመለየት የሚመዘግቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚያካትቱ መሆኑ ሲጣራ ፡

- የአላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች ከኮንትራት ሠራተኞች የደመወዝ ክፍያ ላይ የሰበሰበው ብር የገቢ ግብር 103,940.21 ፣
- የአጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ የሰበሰበው የሳር ሽያጭ ገቢ ብር 74,850.96 ፣

በጠቅላላው ብር 178,791.17 የገቢ ሂሳብ በየኮሌጆቹ የገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ እንዲካተት ያልተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በወቅቱ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ መካተት እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 4.3 በዕቅድ መሰረት ያልተሰበሰበ ገቢ

በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ የአጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ የገቢ አርዕስቶች ለመሰብሰብ ካቀደው ብር 16,940,970.00 ዉስጥ በበጀት ዓመቱ የሰበሰበው ብር 3,539,312.19 ብቻ እንደሆነ ታውቋል፡፡ ኮሌጁ የገቢ ዕቅድ በሚያዘጋጅበት ወቅት በትክክለኛ መረጃ ላይ ተደገፎ ሊሰበስብ የሚችለውን ማቀድ እንዳለበት እንዲሁም በመጀመሪያ በታቀደው ዕቅድ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ዕቅዱን መከለስ እንደሚያስፈልግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

### 4.4 የገቢ ዕቅድ ያልተዘጋጀ ስለመሆኑ

የፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 የመንግሥት መ/ቤቶች የዓመቱን የገቢ ዕቅድ በወር ከፋፍለው ማዘጋጀት እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ሲጣራ ፡

- የኢትዮጵያ የምግብ ፣ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

የገቢ ዕቅድ ያላዘጋጁ መሆኑ ታውቋል:: በመመሪያው መሰረት የገቢ ዕቅድ ሊያዘጋጁ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ::

### 4.5 <u>የዋጋ ማስተካከያ ሳይደረግለት ለረጅም ዓመታት የቆየ የቤት ኪራይ ገቢ</u>

የፌደራል ስፖርት ኮሚሽን በስታዲዮም ዙሪያ ከሚያከራያቸው የንግድ ቤቶች የሚሰበስበው የኪራይ ገቢ ከ15 ዓመታት በፊት በተተመነ ዋጋ መሰረት መሆኑ ታውቋል :: በመሆኑም ኮሚሽኑ ወቅቱን ያገናዘበ የቤት ኪራይ ገቢ ተመን ሊያዘጋጅ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ::

## 5. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

### 5.1 <u>የወጪ ( ደጋፊ ) ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሒሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶች ለፈጸሟቸው የአገልግሎት ግዥዎች በተገቢው ውል የተደገፉ መሆኑን እንዲሁም የተፈጸሙት ክፍያዎች መሥሪያ ቤቶቹ አገልግሎት ላገኙባቸው ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :

- የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ለመ/ቤቱ የበላይ ሀላፊ ለውጭ ጉዞ ለመኝታና ቁርስ ለከፈለው የአሜሪካን ዶላር 3,450.00 እና ለእጅ ኳስ ፌደሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ ለመጠባበቂያ ለከፈለው ዩሮ 70.00 ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ ፣
- የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለውጭ ጉዞ ለተከፈለው የአሜሪካን ዶላር 621.39 ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣
- ሰራተኞች በሥልጠና ላይ ለመካፈላቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ፎርማ ሳይቀርብ በኢትዮጵያ የምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ብር 33,520.00 ፣ በብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ብር 41,986.00፣ በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 218,240.00፣ በድምሩ ብር 293,746.00 ለሰራተኞች ስልጠና ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ ታውቋል ።

በመሆኑም ለክፍያው ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብለት ለመሥሪያ ቤቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ።

## 5.2 ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በመስክ ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ሠራተኞች የሚከፍለው የውሎ አበል የካቲት 17/1985 በቁጥር መ30/ጠ/13/223 ከጠቅላይ ሚኒስቴር በወጣው የአፈፃፀም እና ጥቅምት 22/1993 በቁጥር መ30/ጠ/13/11/95 በተሻሻለው የመንግሥት ሠራተኞች የቀን የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ እንዲሁም ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የተላለፈው የትርፍ ሰዓት አከፋፈል መመሪያ ተግባራዊ መሆኑ ሲጣራ:

- የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል :
    - ሁለት የማዕከሉ ሰራተኞች በሰዓት መቆጣጠሪያ ደብተር ላይ ፈርመው እያለ የመሥክ ሥራ ላይ እንደነበሩ ተደርጎ ብር 1,554.00 የውሎ አበል የተከፈላቸው መሆኑ፣
    - የማዕከሉ ሰራተኞች ለመሆናቸው ወይም ከሌላ መሥሪያ ቤት በትብብር ለመምጣታቸው ማስረጃ (ደብዳቤ) ሳይቀርብ ወይም ሳይያያዝ ለሁለት ግለሰቦች ብር 1,127.00 የውሎ አበል የተከፈላቸው መሆኑ ፣
    - አዲስ አበባ ላይ የኮምፒዩተር ሥልጠና ለተካፈሉት የማዕከሉ ሰራተኞች በሥልጠናው ላይ ከተካፈሉበት ቀናቶች በላይ ብር 14,826.00 የውሎ አበል የተከፈላቸው መሆኑ ፣
- በፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ከውሎ አበል ተመን በላይ ብር 2,520.00 የተከፈለ መሆኑ ፣
- በኢትዮጵያ ስጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለውሎ አበል ከተከፈለው በተጨማሪ ለአልጋ ብር 2,912.00 የተከፈለ መሆኑ ፣
- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከመንግሥት የውሎ አበል ተመን በላይ በቀን ብር 150.00 ሂሣብ በድምሩ ብር 10,200.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ ፣
- የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዳይከፈል ከሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ (ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር) መመሪያ የተላለፈ ቢሆንም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሰራተኞች በትርፍ ጊዜያቸው ለሰሩበት በሚል ብር 11,571.35 የተከፈለ መሆኑ ፣

በጠቅላላው ብር 44,710.35 ደንብና መመሪያን ሳይከተል ክፍያ መፈጸሙ ታውቋል፡፡ በመሆኑም በብልጫ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ ፣

ለወደፊቱም የውሎ አበል ክፍያ በደንቡ መሰረት ብቻ እንዲፈጸም መሥሪያ ቤቶቹ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 5.3 የግዥ አዋጅ ፣ ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዥዎች

በግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንዲሁም ሰኔ 2002 በወጣው የመንግሥት የእቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት መሥሪያ ቤቶች ግዥዎችን መፈጸማቸውን ፣ በግዥ መመሪያዉ አንቀጽ 16.25 መሰረት በጨረታ ለሚፈጸሙ ግዥዎች ከአሸናፊዉ ድርጅት ጋር ዉል መግባታቸውን፣ በተጨማሪም በአንቀጽ 16.16.1 መሰረት የጨረታ አሸናፊዎች የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዛቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :

- የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል:
    - ለሚያስገነባውን የዲያግኖስቲክ ላቦራቶር ቤት ግንባታ የቁጥጥር ሥራውን የኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት በወር ብር 32,340.00 ለአንድ ዓመት ብር 389,160.00 እየተከፈለው እንዲያከናውን ያለምንም ጨረታ የተሰጠው መሆኑን ፤
    - ማዕከሉ ፋርማቴክ ከተባለ ድርጅት የላብ ፕሪንተር ግዥ በብር 16,341.00 ብቸኛ አቅራቢ ነው በሚል የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበስብ ግዥውን የፈጸመ ቢሆንም ድርጅቱ ብቸኛ አቅራቢ ለመሆኑ መረጃ ያልቀረበ መሆኑን፤
- የቡና ጥራት መቆጣጠሪያ ማዕከል ለመኪና መለዋወጫ ግዥ ብር 10,223.50 ፤ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ለመኪና ጎማ ግዥ ብር 6,200.00 ፤ የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ለተለያዩ እቃዎችና አገልግሎት ግዥ ብር 181,148.00 እንዲሁም ብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ለሆቴል መስተንግዶ ግዥ ብር 41,986.00 በጠቅላላው ብር 239,557.50 ወጪ ያደረጉ ሲሆን፣ ለግዥው በቂ የዋጋ ማወዳደሪያ ያልተሰበሰበ መሆኑን ፣
- በፌደራል ስፖርት ኮሚሽን ጨረታ ሳይወጣ በብር 374,990.50 የአትሌቲክስ ማንዋል ግዥ የተፈጸመ መሆኑን ፣
- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የግዥ መጠየቂያ ሳይቀርብና በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈቀድ የነዳጅ ኩፖን ግዥ በብር 50,000.00 ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የሞኤንኮ ድርጅት ተሸከርካሪ ለመጠገን ተወዳድሮ ካሸነፈበት ዋጋ በተጨማሪ በኮሚቴ ውሳኔ ሳይጸድቅ ብር 37,834.44 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ፣
- የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በብር 863,738.67 የአቃና አገልግሎት ግዥ በጨረታ የፈጸመ በሆንም ፣ ተጫራቾች ያቀረቡት የዋጋ ዝርዝር ለኦዲቱ ሥራ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑን ፣
- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ :
  - በበጀት ዓመቱ በብር 2,969,247.83 የተፈጸሙት የግንባታ ዲዛይን ክለሣ፣ ቁጥጥር ሥራና የማማከር አገልግሎት ግዥዎች ያለጨረታ የተፈጸሙ መሆኑን ፤
  - በአጋርፋ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የሚሰራውን የውሃ መስመር ዝርጋታ ሥራ የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ድርጅት በብር 16,000,000.00 እንዲያከናውን የመንግሥትን የግዥ መመሪያ ሳይከተልና ጨረታ ሳይወጣ ኮንትራክት የተሰጠው መሆኑን ፤
  - የአርዳይታ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ የጸረተባይ መከላከያ በብር 252,000.00 ሲገዛ ግዥዉ የተፈጸመዉ ያለ ዉል እና የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ሳይቀርብ መሆኑን ፤
  - የአሰሳ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለተማሪዎች የምግብ ጥሬ እቃ ለመግዛት ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት ደሳለኝ ነጋሳ አሸናፊ በመሆኑ በብር 465,120.00 ግዥዎቹ ተፈጽመዋል፡፡ ይሁን እንጂ :
    - አሸናፊው ግለሰብ የንግድ ሥራ ፍቃድ ያላቀረቡ መሆኑ፣
    - በአሸናፊው ግለሰብ የቀረበው የታክስ ከፋይ ምዝገባ የምስክር ወረቀት (Tax Payables Registration Certificate) የግንባታ (Construction) እንጂ የእህል ንግድ ሻጭ አለመሆኑ፣
    - ግለሰቡ ለተቀበሉት ገንዘብ የሰጡት ደረሰኝ (Payment Invoice) የጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ መሆኑን፣
- አማኑኤል ሆስፒታል ለህንፃ ጥገና ያለ ውል ብር 1,717,613.36 ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣

ለማረጋገጥ ተችሏል ።

በመሆኑም ግዥዎች የግዥ አዋጅና መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት እንዲፈፀሙ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 5.4 ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ያልተቀነሰ የቅድሚያ ክፍያ ግብር

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ግንባታ ከፈጸማቸው ክፍያዎች ላይ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 ክፍል ሁለት አንቀጽ 53 ò2ñ እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/2002 አንቀጽ 24 " 1 እና 2 " መሰረት ( 2% ) የቅድሚያ ገቢ ግብር ታክስ መቀነሱ ሲጣራ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በተለያየ ጊዜያት ለተገጣጣሚ ህንጻ አካላት ድርጅት ከፈጸመው ክፍያ ብር 5,490,539.93 ላይ ብር 109,810.78 የቅድሚያ ግብር ታክስ ያልተቀነሰ መሆኑ ታውቋል። ሁኔታው ሊከሰት የቻለው ሰኔ 15/1996 ዓ.ም በቁጥር LTO/2899/96 ከፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ከከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቢሮ ለሚመለከተው ሁሉ ተብሎ በተጻፈው ደብዳቤ መሰረት የተገጣጣሚ ህንጻ አካላት ድርጅት የ1995 በጀት ዓመት የተመረመረና የ1996 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ዘጠኝ ወራት ረቂቅ ሪፖርት የሂሳብ መግለጫን አባሪ በማድረግ ለቢሮው ያቀረበ መሆኑን በመግለጽ ድርጅቱ አትራፊ ሆኖ ግዴታውን መወጣት እስኪችል ድረስ ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ 2% እንዲሁም ከገቢ እቃዎች ላይ 3% የቅድሚያ ግብር ታክስ ተቀናሽ የማድረጉ ሥርዓት በድርጅቱ ላይ ተፈጻሚ እንዳይደረግ በሚል ከሰባት ዓመት በፊት በተላለፈው ደብዳቤ መሰረት የቅድሚያ ግብር ታክሱ አለመቀነሱ ታውቋል። ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፣ ድርጅቱ በአሁን ወቅት ያለውን የፋይናንስ አቋም ሳያረጋግጥና ማጣራት ሳያደርግ ከሰባት ዓመት በፊት የተላለፈን ደብዳቤ መሰረት በማድረግ የቅድሚያ ግብሩን አለመሰብሰቡ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም ሁኔታ ተጣርቶ ከድርጅቱ ላይ የቅድሚያ ግብሩ እንዲሰበሰብ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 5.5 የግዥ መመሪያን ተከትሎ ያልታቀደ ግዥ

መሥሪያ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 3 አንቀጽ 22 እንዲሁም ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል ሶስት አንቀጽ 8 መሰረት የግዥ እቅድ ያዘጋጁ እና ለተዘጋጀው የግዥ እቅድ የተመረጡት የግዥ ዘዴዎችም በአዋጁና በመመሪያው መሰረት መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች ባሟላ መልኩ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በግዥ መመሪያው ክፍል አምስት አንቀጽ

24.1 መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አስቀድመው ማቀድ እስከቻሉ ድረስ በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም አለባቸው ። ሆኖም ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ግዥዎች ብቻ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ሊፈጸሙ እንደሚችሉ ተመልክቷል። ይሁን እንጂ፡

- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በብር 839,908.00 በተለያየ ጊዜያት የጽሕፈት መሣሪያዎች ፣ የጽዳት እቃዎች ፣ የተለያዩ መሣሪያዎች እና የማስታወቂያ ግዥዎች በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መታቀድ ሲገባቸው በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ እንዲፈጸሙ ታቅደው አብዛኛዎቹ ግዥዎች በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተፈጸሙ መሆኑ ታውቋል።

- የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል የ2003 በጀት ዓመት የግዥ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል ።

በመሆኑም መሥሪያ ቤቶቹ በግዥ አ□ጻጸም ረገድ ቁጠባን የአ□ጻጸም ብቃትንና ዉጤታማነትን ለማረጋገጥ ዓመታዊ የግዥ □ቅድ በግዥ መመሪክዉ መሰረት በማ□ጋጀት ግዥ□ች በእቅድ መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ።

## 5.6 ሥራው ለመጠናቀቁ በባለሙያ ሳይረጋገጥ እና ተገቢው ርክክብ ሣይፈጸም የተፈጸመ ክፍያ

የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በ2002 በጀት ዓመት በናዝሬት መልካሳ ላይ ባለ 2 ክፍል ቢሮና ባለ 3 ክፍል ማሰልጠኛ የፋይበር ተንቀሳቃሽ ቤት ለማሰራት ከደጀን አቬሽን ኢንጅነሪንግ ኮምፕሌክስ ጋር በብር 1,109,380.00 ዉል ገብቶ የውሉን 50% ክፍያ ብር 554,690.22 መፈጸሙ ይታወቃል።
በዚህ ኦዲት ወቅትም የግንባታውን ቀጣይ ሂደት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተከስተዋል። ይኸውም ፡

- ኤጀንሲው ሚያዚያ 8,2002 ዓ.ም ግንባታውን ከሚያከናውነው ከደጀን አቬሽን ኢንጅነሪንግ ኮምፕሌክስ ጋር በፈጸመው ውል ላይ ቀሪው 50% ብር 554,690.22 ርክክቡ እንደተፈጸመ በሶስት ቀናት ውስጥ የሚከፈል ለመሆኑ የተመለከተ ቢሆንም፡ ኤጀንሲው ግንባታው በተገቢው መንገድ ለመጠናቀቁ በቅድሚያ ባባለሙያ ሳያረጋገጥና ርክክቡ ሳይፈጸም የችሮታ ጊዜ ክፍያ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጠይቆ ቀሪውን ክፍያ በሙሉ ለደጀን አቬሽን ኢንጅነሪንግ ኮምፕሌክስ ፈጽሞ ተገኝቷል።

- በዉሉ አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 6.1 መሰረት ዉሉ በተፈረመ በስድስት ሳምንት ግዜ ዉስጥ ድርጅቱ ስራዉን አጠናቆ እንደሚያስረክብ ሥምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም ስራዉ ከተጀመረ ከአስራ ሰባት ወራት በላይ በኋላም ርክክብ ያልተፈጸመ መሆኑ ታውቋል ።

- ሐምሌ 1997 በወጣው የግዥ መመሪያ አንቀጽ 11 ተራ ቁጥር 11.14 መሰረት ደጀን አቬሽን ኢንጂነሪንግ 10% የውል ማስከበሪያ ብር 110,938.00 እንዲያሲዝ ያልተደረገ መሆኑ ተገልጾ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በ2002 በጀት አመት ሂሳብ ሪፖርት ላይ የተገለጸ ቢሆንም ይህ ሳይፈጸም ሙሉ ክፍያው እንዲፈጸም ተደርጓል። አሰራሩ የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ኤጀንሲው በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም ግዥ□ች የግዥ አዋጁና መመሪክው በሚ□ቅ□ዉ መሰረት እንዲ□ጸሙ ተገቢዉ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

## 5.7 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተያዙ ሒሳቦች

የገቢ፣ የወጪ ፣የተሰብሳቢ፣ የተከፋይና የመሳሰሉት ሒሳቦች የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በተገቢው የሂሳብ መደቦች የሚያዙና የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡ በ8 መ/ ቤቶች በድምሩ 616,704.59 ብር በተገቢው የሒሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

በመሆኑም መስተካከል የሚገባቸው ሂሳቦች ሁሉ እንዲስተካከሉ ፤ ለወደፊቱም ሂሳቦች በሙሉ በፋይናንስ መመሪያው መሰረት በተገቢው የሂሳብ መደብ እንዲመዘገቡ ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 5.8 ያለበጀት ዓመቱ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ

በየመሥሪያ ቤቶቹ የተመዘገቡት የወጪ ሂሣቦች በ2003 በጀት ዓመት በተፈቀደው የበጀት ድልድል መሠረት መሆኑን እና የበጀት ዓመቱ ሂሣብ በበጀት ዓመቱ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣በ4 መ/ቤቶች ብር 9,904,590.31 የሌላ በጀት ዓመት ወጪ እንደ 2003 በጀት ዓመት ወጪ ተደርገው ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም በየሒሳብ ማመዛዘኛዎቹ ላይ የተመለከተው ሂሳብ የበጀት ዓመቱን ወጪ እንዳያሳይ ምክንያት ሊሆን ችሏል። በመሆኑም የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ እና በወጪ ሂሣብ

ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

## 5.9 በግዥ ውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረጉ የላቦራቶሪ ቋሚና አላቂ እቃዎች

የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል በበጀት ዓመቱ የላቦራቶሪ ቋሚና አላቂ እቃዎች ግዥ ለመፈጸም ውል የገባላቸው ግዥዎች በውሉ መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ውል ከተገባላቸው ግዥዎች ውስጥ ከኢትዩ ፎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የብር 314,481.91 ከፋርማቴክ ኢንተርናሽናል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የብር 164,321.01 በድምሩ የብር 478,802.92 ቀሪ እቃዎች በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ ታውቋል ፡፡ ውል ተቀባዩች ውሉ በተፈረመ በ120 ቀናቶች ውስጥ የተገዙትን ንብረቶች ማስረከብ እንዳለባቸው በውሉ ላይ የተመለከተ ቢሆንም ማዕከሉ በውሉ መሰረት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ድርጅቶቹ ገቢ ያልተደረጉትን እቃዎች በአስቸኳይ ገቢ እንዲያደረጉ፣ ይህ ካልሆነ ግን ማዕከሉ በውሉ መሰረት ተገቢ የሆነ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

## 5.10 ለሰራተኞች ላልተከፈሉ ደሞዝዎች ማስተካከያ ያልተሰራላቸው መሆኑ

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በተለያዩ ምክንያቶች ለሰራተኞች ላልተከፈሉ ደሞዝዎች ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ የሚሰራለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡

- በብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል ለብር 23,327.40 ለደሞዝና የጡረታ ተከፋይ ሒሳብ በዴቢትና በክሬዲት በየሂሳብ መደቦቹ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ ፣
- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ በዴቢት ለብር 136,353.81 ለደሞዝና ለመዘዋወሪያ አበል ሒሳብ በዴቢትና በክሬዲት በየሂሳብ መደቦቹ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ ፣
- በምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ለሠራተኞች ደመወዝ ለመክፈል በተዘጋጀው እና መዘጋጀት በሚገባው ልዩነት ከማሳየቱም በላይ የተዘጋጀው የሂሣብ ማስተካከያ ተገቢ ባለመሆኑ የወጪ ሂሣብ መግለጫው በብር 94,498.16 የተዛባ መሆኑ ፣

ታወቋል። በመሆኑም ሂሳቦቹ እንዲስተካከሉ ካልተደረጉ በሂሳብ ማመዛዘኛው ላይ የተመለከተው የደመወዝ ክፍያ ትክክለኛውን ሂሳብ አያሳይም። በመሆኑም ላልተከፈሉት ደሞዝዎች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ መደረግ እንዳለበት፤ ለወደፊቱም በወጪ ተመዝግበው ያልተከፈሉ ደሞዝዎች ሲያጋጥሙ ወዲያው ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ።

## 5.11 <u>በደንቡ መሰረት ያልተቀነሱ እና ያልተመዘገቡ ሂሳቦችን በተመለከተ</u>

ለኮንስትራክሽን ሥራ ወጪ የተደረጉ ሒሳቦች ምዝገባ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት የሚከናወን መሆኑን እንዲሁም ተቀናሽ ሊደረጉ የሚገባቸው ሂሳቦች በህጉና በደንቡ መሰረት የተቀነሱ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና የተመረጡት ሒሳቦች ኦዲት ሲደረጉ፤

- በውሃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት ፣
  - በርሄ ሐጎስ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ የተባለው ድርጅት ክብረ መንግሥት የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ላይ ለሚያከናውነው ሥራ የክፍያ የምስክር ወረቀት በየደረጃው ሲቀርብ ሊከፈል ከሚገባው የቅድሚያ ግብር ታክስ ውስጥ ብር 64,954.75 ያልተቀነሰ መሆኑ ፣
  - በሒሳብ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ እና የመያዣ ሒሳብ እንዲመዘገብ ባለመደረጉ እንዲሁም ያልተቀነሰ የቅድሚያ ግብር ታክስ በመኖሩ ምክንያት የወጪውን ሒሳብ በብር 2,798,267.17 ዝቅ ሊያደረገው የቻለ መሆኑ ፣
  - መከፈል የሌለበት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ደግሞ በብር 64,954.75 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ ፣
- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ፣
  - ከአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን ብር 3,024,760.99 ፤ ከከሰም ግድብና መስኖ ፕሮጀክት ብር 1,874,863.33 ፤ ከውኃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን 20,738,321.72 በድምሩ ብር 25,637,946.04 የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተቀናሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

- ከአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን ብር 403,301.46፤ ከአፋር ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ብር 348,633.70 በድምሩ ብር 751,935.16 የቅድሚያ ግብር ታክስ ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- ከውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ የቅድመ ክፍያ ብር 45,226,370.13 የቅድሚያ ግብር ታክስ ያልተቀነሰ መሆኑ ፣
- ከውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ የመያዣ ሂሳብ ብር 49,014,371.83 ያልተቀነሰ መሆኑ ፣

➢ ግብርና ሚኒስቴር ለሚያስገነባው የጥራት መቆጣጠሪያ (Quality Control) ላባራቶሪ በስፍር ክፍያ ምስክር ወረቀት መሰረት :

- ሁለተኛ ክፍያ ሲፈጽም የመያዣ ሂሳብ ብር 99,577.52 እና የቅድሚያ ሂሳብ መተኪያ ብር 458,057.82 ባለመመዝገቡ የወጪ ሂሳብ በብር 557,635.34 ዝቅ ሊያደረገው የቻለ መሆኑ ፣
- አራተኛ ክፍያ ሲፈጽም ከመያዣ ሂሳብ ብር 249,255.23 መቀነስ ሲገባው ብር 188,134.20 ብቻ በመቀነሱ የመያዣ ሂሳቡ በብር 61,121.00 ያነሰ ሲሆን ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ደግሞ ብር 598,212.54 ብቻ ሆኖ ሳለ በስህተት በብር 619,333.57 ተብሎ ስለተመዘገበ ሂሣቡ በብር 61,121.00 ከፍ ሊያደረገው የቻለ መሆኑ ፣

ታውቋል።የአሰራር ግድፈቱ ካልታረመ በሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከተውን ሒሳብ ያዛባዋል፡፡ በመሆኑም ጽህፈት ቤቱ በፋይናንስ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት መቀነስ ያለባቸው ሒሳቦች በአግባቡ እንዲቀነሱ እንዲሁም መመዝገብ ያለባቸው ሒሳቦች ደግሞ እንዲመዘገብ መደረጋቸውን መከታተልና መቆጣጠር እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ።

**5.12 <u>በወጪ የተመዘገበ የቅድመ ክፍያ ሂሳብ</u>**

ነሐሴ 1999 በወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የቅድመ ክፍያ በተሰብሳቢ መያዝ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ፡

- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የላቦራቶሪ እቃዎች ግዥ ለመፈጸም ሌተር ኦፍ ክሬዲት (LC) የተከፈተለት ሂሳብ ብር 17,814,150.81 ፣
- ማዕድን ሚኒስቴር ለወርቅ ማጣሪያ መግዣ በሌተር ኦፍ ክሬዲት ለገባው ዋስትና የተላለፈ ብር 817,782.65 እና ለዳታ ቤዝ ግንባታ ቅድመ ክፍያ የከፈለው ብር 23,459,891.00 ፣

- የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ለስቴራላይዘር ግዥ በቅድሚያ የከፈለው ብር 1,141,675.20፣
- የአማኑኤል ሆስፒታል ለህንፃ ግንባታ በቅድሚያ የከፈለው ብር 6,503,000.00፣
- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን ብር 28,932,382.41 ፣ ለአፋር ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ብር 18,918,803.05፣ ለኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ብር 19,642,808.43፣ ለርብ ግድብ ፕሮጀክት ብር 64,835,302.90፣ ለአልናይል ቢዝነስ ግሩፕ ፒ.ኤል.ሲ ( AL Nilo Business Group PLC ) ብር 23,511,819.00 በድምሩ ብር 155,841,115.79 በቅድሚያ የከፈለው ሂሳብ ፣

በድምሩ ብር 49,736,499.66 በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል። ሁኔታው የሂሳብ መግለጫዎቹ ትክክለኛውን የፋይናንስ እንቅስቃሴ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሆኗል ፡፡

በመሆኑም መሥሪያ ቤቶቹ አስፈላጊውን ማስተካከያ ሊያደርጉ እንደሚገባና ለወደፊቱም የቅድመ ክፍያ ሂሳቦች መንግሥት ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የወጪ ማስረጃ ሲቀርብላቸው ብቻ በወጪ ሊመዘገቡ እንደሚገባ ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

## 5.13 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ( ሞ19 ) ያልቀረበለት ሂሳብ

በኢትዮጵያ የምግብ፣ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን በብር 26,730.00 ለተገዛው የጠረጴዛ መታወቂያ ማስቀመጫ የንብረት ገቢ ደረሰኝ አልቀረበለትም :: በመሆኑም የተገዛው እቃ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

## 5.14 ያለሙያተኛ እገዛ የተፈጸመ ግዥ

በብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል የሙያተኞችን እገዛ የሚጠይቁ ግዥዎች ሲፈጸሙ የግዥውን ጥያቄ ካቀረበው የሥራ ክፍል አስፈላጊው ባለሙያ ተመድቦ እንዲገዛ የሚደረግ መሆኑ ታውቋል ። ይሁንና በብር 7,820.00 የተገዛው አንቲ ቫይረስ ግዥ የተፈጸመው ያለሙያተኛ እገዛ በመሆኑ ምክንያት የሚፈለገው ዓይነት አንቲ ቫይረስ ስላልተገዛ ንብረቱ ያለጥቅም በንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጦ ይገኛል። በመሆኑም ማዕከሉ በግዥ አፈፃፀም ረገድ ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ይችል ዘንድ የሙያተኞችን

እገዛ የሚጠይቁ ግዥዎች ሲፈጸሙ የግዥውን ጥያቄ ካቀረበው የሥራ ክፍል አስፈላጊው ባለሙያ ተመድቦ እንዲገዛ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 5.15 ገንዘቡን በተቀበለው ሰው ፊርማ ያልተረጋገጠ የውሎ አበል ክፍያ

የኢትዮጵያ የምግብ ፣መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን ቅርንጫፍ መ/ቤት በሆኑት በድሬዳዋ ብር 8,625.00፣ በአዋሳ ብር 27,603.00 በድምሩ ብር 36,228.00 ለሰራተኞች የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጸም፣ የወጪ ማስረጃዎቹ ገንዘቡን በተቀበለው ሰራተኛ ሳይፈረሙ ተገኝተዋል:: እንዲሁም የቅርንጫፍ መ/ቤት ሰራተኞች በስልጠና ላይ ለቆዩበት ለተከፈለው የውሎ አበል ብር 33,520.00 የውሎ አበል መፍቀጃና ማረጋገጫ ቅጽ አልቀረበለትም። በመሆኑም የወጪ ማስረጃዎቹ ገንዘቡን በተቀበለው ሰው ፊርማ ሊረጋግጡ እንደሚገባ እንዲሁም ለወደፊቱ በደንቡ መሰረት የውሎ አበል መፍቀጃና ማረጋገጫ ቅጽ እንዲሞላ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

## 5.16 በሂሳብ አያያዝ ላይ የታዩ የአሰራር ድክመቶች

በኢትዮጵያ የክብደት ማንሳትና የሰውነት መገንባት ፌዴሬሽን :

- የተሟላ የገቢና የወጪ ሂሣብ መመዝገቢያ መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ ፣
- በየእለቱ ወጪ ለሆኑት ሂሣቦች የወጪ ማስመስከሪያ ቫውቸር ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፣
- የውሎ አበል መጠየቂየና መፍቀጃ ቅጽ በስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ፣

ታውቋል ።

በመሆኑ በፋይናንስ ደንብና ሥርዓት መሰረት አሰራሩ እንዲስተካከል በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

# 6. ለሚመለከተው አካል ገቢ (ፈሰስ) ያልተደረገ ሂሳብ

በየመሥሪያ ቤቱ በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ የገቢ አርዕስቶች የተሰበሰበዉ የገቢ ሂሳብ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በባንክ፣ በጥሬ ገንዘብ ፣ በተሰብሳቢ ሂሳብና በአላቂ ዕቃ የተገኙት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ የተደረጉ መሆኑ ሲጣራ :

- በቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የተቀነሰው ተጨማሪ ዕሴት ታክስ ብር 6,864.00 እንዲሁም በኢትዮጵያ ስጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተቀነሰው ተጨማሪ ዕሴት ታክስ ብር 95,936.34 እና የቅድሚያ ግብር ታክስ

ብር 12,791.51 በድምሩ ብር 115,591.85 በደንቡ መሰረት ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣

- በአላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በባንክ፣ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲሁም በአላቂ ዕቃ ቆጠራ የተገኘው ብር 1,489,946.95 ፣
- በአጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ከቀን ሰራተኞች የተሰበሰበዉ የሥራ ግብር ገቢ ብር 8,114.90 ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ መደረግ ሲኖርበት ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፈሰስ የተደረገ መሆኑ ፣
- በአርጳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በኮሌጁ የውስጥ ገቢ ማድረጊያ የባንክ ሂሳብ ከተገኘው 7,846,901.96 ውስጥ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ብር 3,846,901.96 ፈሰስ ያልተደረገ ሲሆን፣ ከቀን ሰራተኞች የተሰበሰበዉ የስራ ግብር ገቢ ብር 6,214.20 ደግሞ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ መደረግ ሲኖርበት ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፈሰስ የተደረገ መሆኑ ፣

ታውቋል።

አሠራሩ ለመንግሥት ገቢ መሆን ያለበት ገንዘብ ሳይገባ እንዲቀር የሚያደርግ በመሆኑ ሂሳቡ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ገቢ መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 7. <u>የሒሳብ ሪፖርትን በተመለከተ</u>

### 7.1 <u>በሒሳብ ሪፖርት ላይ ያልተጠቃለለ እና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ያልተደረገ ሂሳብ</u>

በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያና በሥሩ ላሉት ኮሌጆች ለሥራ ማስኬጃና ለደመወዝ እንዲሆን ከማዕከላዊ ግምጃ ቤትና ከውስጥ ገቢ የተፈቀደውን በጀት ተጠቅመው በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት በሂሳብ ሌጀሮች ላይ በፋይናንስ ምንጫቸው መሰረት የሚመዘገቡና በዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሚካተቱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በአላጌ፣ አጋርፋና አርጳይታ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጆች ውስጥ የተሰበሰበው ገቢና እንዲሁም ከገቢው ሂሳብ ላይ ወጪ የተደረገው ሒሳብ ብር **31,779,357.45** በዴቢት እንዲሁም ይሄው ገንዘብ

በክሬዲት በየሒሳብ ዓይነቱ ተለይቶ ከፕሮጀክት ማስተባበሪያው ሂሳብ ጋር ተጠቃሎ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል። አሰራሩ የሂሳብ መግለጫዎቹ ትክክለኛውን የፋይናንስ እንቅስቃሴ እንዳያሳዩ አድርጓል ፡፡

በመሆኑም የኮሌጆች የውስጥ ገቢና ከውስጥ ገቢ ላይ የተጠቀሙት የወጪ ሒሳብ አጠቃቀም ሁኔታ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት እንዲደረግ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለፕሮጀክት ማስተባበሪያው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 8. የንብረት ሒሳብ

### 8.1 ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያላደረጉ መ/ቤቶች

በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 17/1997 አንቀፅ 61 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ እየተቆጠረ ከዕቃ ዝርዝር መዝገብ ጋር በመመሳከር መረጋገጥ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ :

- በምግብ ክምችት አስተዳደር በናዝሬትና በሽንሌ መጋዘን እህል ክምችት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በበጀት አመቱ አመታዊ የእህል ክምችት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ ፣
- በኢትዮጵያ የምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣንና በብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት የቋሚ እቃ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመሳከረ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በማዕድን ሚኒስቴር፣ በአማኑኤል ሆስፒታል እና በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በአለርት ሆስፒታል እና በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የንብረት ምዝገባ በተሟላ መልኩ ያልተከናወነ መሆኑ ፣
- በአላጌ በአጋርፋና በአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች በ2003 በበጀት ዓመት መጨረሻ ዓመታዊ የቋሚ ንብረት ቆጠራ ቢከናወንም በአብዛኛው ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ ፣
- በአርዳይታ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ በ2003 የንብረት ቆጠራ በወቅቱ ያልተጠናቀቀ መሆኑ ፣

ታውቋል።

መሥሪያ ቤቶቹ በንብረት አስተዳደር መመሪያው መሰረት ዓመታዊ ቆጠራ ማድረግ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

## 8.2 የአላቂ ዕቃዎች ምዝገባ ያላከናወኑ መ/ቤቶች

በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 65.5 መሠረት ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መቆጠር እንዳለበት ተመልክቷል ፡፡ ይሁንና ፡

- በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በበጀት አመቱ መጨረሻ አመታዊ የአላቂ እቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ ፣
- በኢትዮጵያ የምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣንና በብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት አላቂ እቃ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ማመዛዘኛ ያልተሰራ መሆኑ ፣

ታውቋል፡፡

መሥሪያ ቤቶቹ በንብረት አስተዳደር መመሪያው መሰረት ዓመታዊ ቆጠራ በማድረግ የቆጠራው ውጤት ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር መመዛዘን እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

## 8.3 እንዲወገዱ ያልተደረጉ ንብረቶችን በተመለከተ

በመንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ከአገልግሎት ወጪ የሆኑ ንብረቶች አስፈላጊው ማስወገድ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑ ሲጣራ :በ8 መ/ቤቶች የተለያዩ ያገለገሉ ንብረቶች ፤ኬሚካሎች፤ የተለያዩ ማሽኖች፤ ብዛት ያላቸው የተለያዩ እቃዎች፣ ጀነሬተሮች፣ ግራይንደር፣ ኮምፒዩተሮች፣ ፕሪንተሮችና ሌሎች ፣ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ በርካታ አላቂ እና ቋሚ ዕቃዎችበንብረት ክፍሉና በየቦተው ተገኝቷል፡፡/የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ-29 ተመልክቷል/
በመንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ንብረቶች እንዲጠገኑ አገልግሎት መሰጠት የማይችሉት ንብረቶች ደግሞ እንዲወገዱ መደረግ እንዳለበት ለመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

## 8.4 የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀም

የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተሽከርካሪ መኪናዎች የመንግሥት የንብረት አስተዳደር ሥርዓት በሚያዘው መሠረት ተመዝግበው መያዛቸውን እና በተገቢው ሁኔታ አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ስምንት ተሽከርካሪ መኪናዎች ከሶስት ዓመት በላይ የቆሙ ሲሆን፣ መጠገን የሚችሉት እንዲጠገኑ መጠገን የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፣
- በብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል:
  - ስድስት ተሽከርካርዎች በግብርና ሚኒስቴር፣ 14 ተሽከርካርዎች በግብርና ምርምር ድርጅት እና 1 ተሽከርካሪ ደግሞ በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ስም የተመዘገቡ መሆኑ፣
  - ሁሉም ተሽከርካሪዎች በነፍስ ወከፍ ቋሚ ንብረቶች መዝገብ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
  - የሰሌዳ ቁጥራቸው ኢት 15258 ፣ ኢት 15259 ፣ ኢት 152581 የሆኑ ሶስት ተሽከርካርዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር በማዕከሉ ያልተገኘ መሆኑ ፣
- በኢትዮጵያ የምግብ፣ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን 1 ተሽከርካሪ መኪና በብልሽት የቆመ መሆኑ ፣
- በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር 18 ተሽከርካሪ መኪናዎች በብልሽት የቆሙ መሆኑ ፣
- በኢትዮጵያ ስጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት 3 ተሽከርካሪ መኪናዎችና 3 ትራክተሮች በብልሽት የቆሙ መሆኑ ፣
- በመድን ፈንድ ጽ/ቤት የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ሊብሬ ያልቀረበላቸው መሆኑ፣
- በብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር 4 ክሪዝ ክሬን እና ዚል ዎርክ ሾፕ ተሽከርካሪ መኪናዎች በብልሽት የቆሙ መሆኑ ፣
- በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ 10 ተሽከርካሪ መኪናዎች በብልሽት የቆሙ መሆኑ ፣
- በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አርባ አምስት መኪናዎች ከአንድ ዓመት በላይ የቆሙ መሆኑ ፣

- በአጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ:
  - አገልግሎት በመስጠት ላይ ከሚገኙ 15 ተሽከርካሪዎች ዉስጥ የ11 ተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር መቆጣጠሪያ (ጌጅ) የማይሰራ በመሆኑ የነዳጅ ቁጥጥር ሥርዓቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ፣
  - የኮሌጁ ንብረት የሆኑ 14 የእርሻ ትራክተሮች የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸዉ ሲሆን፣ ከእነዚህ ዉስጥ 12 ትራክተሮች ደግሞ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ ፣
- በአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ:
  - የሰሌዳ ቁጥር 4-19651 ኢ.አ ቶዮታ ስቴሽን ዋገን እና የሰሌዳ ቁጥር 4-16331 ኢ.አ ሃርድ ቶፕ መኪናዎች ወደ ግብርና ሚኒስቴር ጋራዥ ለጥገና በ1993 ዓ.ም የተላኩ ቢሆንም መኪናዎቹ ያሉበት ሁኔታ የማይታወቅ መሆኑ ፣
  - የሰሌዳ ቁጥር 4-24818 ኢ.አ ፊያት የሕዝብ ማመላለሻ መኪና በኮሌጁ ውስጥ ያልተገኘ መሆኑ፣ ታዉቋል፡፡

ተሽከርካሪዎቹ ያለጥቅም እንዲቀመጡ መደረጋቸው አግባብ ባለመሆኑ መሥሪያቤቶቹ በመንግሥት ተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ።

## 8.5 <u>በንብረት አስተዳደር ላይ የታዩ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች</u>

- በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ :
  - ከግብርና ሚኒስቴር የመጡ የተለክዩ አሮጌ ንብረቶችን የንብረት ክፍል ሰራተኛው ያልተረከቧቸው መሆኑ፣
  - በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሰራተኛ መሰጠት እንደሌለባቸው እንዲሁም ለንብረት ሥራ የሚመደቡ ሰራተኞች ቢቻል በሙያው ወይም ተዛማጅነት ባለው የትምህርት ዘርፍ የሰለጠኑ መሆናቸው መረጋገጥ እንዳለበት ተመልክቷል። ይሁንና የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ ከመከናወኑም በላይ ሥራው የሚከናወነው በኤጀንሲው የመልዕክት ሰራተኛ በተደራቢነት መሆኑ፣

- በብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል :
  - በአብዛኛው በእንስሳት እና በአንዳንድ ቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ሪፖርት ላይ የንብረቶቹ ዋጋ ያልተጠቀሰ መሆኑ ፣
  - ታኅሳስ 2000 ዓ.ም በወጣው የመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል መሰረት ለማዕከሉ እና ለሆለታ ጣቢያ ቋሚ እቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸዉ መሆኑ ፣
- በምግብ ክምችት አስተዳደር :
  - በዋናው መሥሪያ ቤት፣ በናዝሬትና በሽንሌ መጋዘን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በእቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ በማዘጋጀት እቃዎችን የመረከብና የመጠበቅ እንዲሁም የንብረት ወጪ ደረሰኝ በማዘጋጀት እቃዎችን ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰው የሚሰራ መሆኑ ፣
  - በናዝሬት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በእቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ እቃዎች ከሚወገዱ እቃዎች ጋር ሳይለዩ ተቀላቅለው ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ ፣
  - በናዝሬት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በእቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ኬሚካሎች በወለል ላይ ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ ፣
  - በናዝሬትና በሽንሌ መጋዘን በእህል ክምችት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እህልና እህል ነክ ያልሆኑ እቃዎች ክምችት አስተዳደር በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር ሥርዓትና በመሥሪያ ቤቱ የምግብ ክምችትና ሥርጭት መመሪያ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤
    - በሁለቱም መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስቶክ የመረከብና ወጪ የማድረግ እንዲሁም መዛግብቶችን የመመዝገብና የመያዝ ኃላፊነቶች በአንድ ሰው የሚከናወን መሆኑ፣
    - በናዝሬት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወደ መጋዘን የሚገቡ እህሎች በከፊል እንጂ በሙሉ የማይመዘኑ ሲሆን፤ በሽንሌ መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ደግሞ በጊቢው ውስጥ የሚገኙ የምድር ውስጥ ሚዛንና ሌሎች ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች የተበላሹና

ጥቅም የማይሰጡ በመሆኑ ወደ መጋዘኖቹ የሚገቡና የሚወጡ እህሎች የማይመዘኑ መሆኑ ፣

- በናዝሬት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የተለያየ መጠንና አገልግሎት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ምግብ ነክ ያልሆኑ እቃዎች በየአይነታቸው ተለይተው ቢን ካርድ ላይ መመዝገብ ሲገባቸው በአንድነት እንዲመዘገቡ የተደደገ መሆኑ ፣
- በናዝሬት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የሚገኙ ምግብ ነክ ያልሆኑ እቃዎች ለቆጠራ አመቺ በሆነ መልኩ በሥርዓቱ ያልተደረደሩ መሆኑ ፣
- የሸንሌ መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የእሳት አደጋ መከላከያ የሌለው መሆኑ ፣
- የሸንሌ መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት መጋዘኖች ውስጥ እህሎች የታሸጉበት ማዳበሪያ በመቀደዱ በመጋዘኖቹ ወለል ላይ ስንዴ በብዛት ፈሶ የተገኘ መሆኑ ፣

➢ በብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል :
   - ለምርምር የተገዙት የቀንድ ከብቶች ማለትም ፍየሎችና በጎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጣቸዉ መሆኑ ፣
   - ቋሚ እቃዎች በተሟላ መልኩ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸዉ መሆኑ፣

➢ በኢትዮጵያ የምግብ ፣ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን መ/ቤቱ ነዳጅ ለመቅዳት የሚጠቀምበት አቢሲንያ ካርድ በሾፌሮች እጅ የሚቀመጥ መሆኑ ፣

➢ በኢትዮጵያ የምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን በብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ለቋሚ እቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸዉ መሆኑ ፣

➢ በብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ንብረቶች እንዲሁም በስፖርት ኮሚሽን በዕርዳታ የሚገቡ የስፖርት ትጥቆች ፣ ቱታዎች ፣ ማልያዎች በመዝገብ ተመዝግበው ያልተያዙ መሆኑ ፣

- በቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል አንድ የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ የተረከቡትን የቡና መቁያ ማሽኖች፣ የቡና ሳንፕል ሚዛን፣ የኤሌክትሪክ ምድጃዎች ኮምፒዩተር ከነፕሪንተሩ እና የተለያዩ ቋሚ አቃዎች ያላስረከቡ መሆኑ ፣
- በኢትዮጵያ የክብደት ማንሳትና የሰውነት መገንባት ፌዴሬሽን ንብረት የሆኑት 2 የብረት ዲስኮች የት እንደሚገኙ የማይታወቅ መሆኑ ፣
- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ 173 ሰራተኞች ብር 1,594,818.71 የሚገመት ንብረት እና የገንዘብ እዳ ኖሮባቸው መ/ቤቱን የለቀቁ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ መካኒሳ በሚገኘው መጋዘን ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸው በርካታ ኬሚካሎች ሳይወገዱ በሰራተኞቹ ላይ የጤና ጉዳት እያደረሱ መሆኑ፣
- በግብርና ሚኒስቴር :
  - ለረጅም ዓመታት ግምጃ ቤት ገቢ የተደረጉ፣ እና በተለይም በ1996 የተለያዩ መ/ቤቶች ሲዋሐዱ ተመላሽ የተደረጉ ንብረቶች በዓይነትና አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡት ሳይለዩ ለቁጥጥር በሚያስቸግር ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ ፣
  - መሥሪያ ቤቱ ለተመላሽ ንብረቶች ማከማቻ እንዲሆን የሚጠቀምበት 9 መጋዘኖች ሲኖረው ንብረቱን የሚረከበው እና ወጪ የሚያደርገው አንድ የግምጃ ቤት ሰራተኛ ብቻ ከመሆኑም በተጨማሪ ንብረቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል ቢን ካርድ ወይም ሌላ የመቆጣጠሪያ ስልት የሌለ መሆኑ ፣
  - በመሥሪያ ቤቱ የተከማቹት ተመላሽ ንብረቶች ዋጋቸው የማይታወቅ መሆኑ፣
  - የመሥሪያ ቤቱ የተመላሽ ንብረት ምዝገባ ለቁጥጥር የማያመች ከመሆኑም በላይ የተሟላ መረጃ ያልያዘ መሆኑ፣
  - በመሥሪያ ቤቱ ለረጅም ጊዜ የንብረት ማስወገድ ስራ ባለመስራቱ ምክንያት ብዛት ያለው ንብረት ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣
  - ተመላሽ ንብረት በውስጥ ኦዲተርም ይሁን በሌላ አካል ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ መሆኑ፣
  - በመሥሪያ ቤቱ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች፣ የእንስሳት መድሃኒቶች እና ሰብሎች የሚገኙ መሆኑ ፣

- የተመላሽ ንብረት ቆጠራ እና የመዝገብ ማስታረቂያ ተሰርቶ ለመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣
- በቃሊቲ በሚገኘው የመሥሪያ ቤቱ መጋዘን በክልሎች ስም የመጡ የተለያዩ ብዛት ያላቸው የግብርና መሳሪያዎች እንዲሁም በዕርዳታ የተገኙ ዘመናዊ ለግብርና ሥራ የሚያገለግሉ፣ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ ፣

➢ በአላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ፡

- የሰኔ 30/2003 በጀት ዓመት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም በኮሌጁ ውስጥ የሚገኙትን ንብረቶች ሙሉ ለሙሉ በቆጠራው ያልተካተተ መሆኑ፣
- በበጀት አመቱ የንብረት ቆጠራ ቢከናወንም በቆጠራ ሪፖርት ላይ በአብዛኛው የንብረቶች ዋጋ የማይጠቀስ መሆኑ ፣
- በቆጠራ ሪፖርት መሰረት 10934 ሊትር ነዳጅ ጉድለት የሚያሳይ መሆኑ ፣

➢ በአጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ፡

- በንብረት ቆጠራ ሪፖርት ውስጥ የዕቃዎች ዋጋ የማይሞላ (የማይገለፅ) መሆኑ፣
- የነዳጅ መጠን መቆጣጠሪያ (Dip stick) በትክክል ለመሰራቱ ተገዝቶ በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን ያልተረጋገጠ መሆኑ ፣

➢ በአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ፡

- የመንግሥትን ንብረት ሳያስረክቡ ከኮሌጁ የለቀቁ ሰራተኞች እንዳሉ ፣
- የመንግሥትን ንብረት አጥፍተው በስራ ላይ በሚገኙ ሰራተኞች ላይም እርምጃ ልተወሰደ መሆኑ ፣
- አሳሳ እንዲሁም አርዳይታ ኮሌጅ ግቢ ውስጥ የሚገኙት የነዳጅ ማደያ ቆጣሪዎች የተበላሹ ቢሆንም አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ፣

➢ በአላጌ በአጋርፋና በአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ለቋሚ ንብረቶች በመንግሥት የቋሚ ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸዉ መሆኑ ፣

ታውቋል::

በመሆኑም የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል እና እንዲፈፀም መሥሪያ ቤቶቹ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

## 9.የበጀት አጠቃቀም

### 9.1 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሒሳብ

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በበጀት ደንብ መሰረት ከተመደበላቸው በጀት በላይ የማይጠቀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ10 መ/ቤቶች /ዝርዝራቸው በአባሪ-28 ተመልክቷል/ በድምሩ ብር 7,663,228.96 ከበጀት በላይ ወጪ ማድረጋቸው ታውቋል ።

መሥሪያ ቤቶቹ የበጀት ዝውውር ሳያስፈቀዱ ከበጀት በላይ መጠቀማቸው አግባብ አይደለም ።

በመሆኑም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 9.2 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

የመሥሪያ ቤቶች የ2003 በጀት ዓመት የወጪ በጀት አጠቃቀም ሁኔታ ሲገመገም ከመደበኛና ከካፒታል በጀት ከ10% በላይ በየሂሳብ ኮዶቹ ሥራ ላይ ያልዋለው በጀት በ26 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,018,356,356.15 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ታውቋል፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-28 ተመልክቷል።/

መሥሪያ ቤቶች ሥራ ላይ የማይውል በጀት ካስፈቀዱ መንግሥት ለሌላ ሥራ ሊያውለው የሚችለው ገንዘብ አለአግባብ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ለወደፊቱ በበጀት እቅድ ዝግጅት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

# 10 ልዩ ልዩ

## 10.1 የቅጥር ደንብን ተከትሎ ያልተፈጸመ የሠራተኞች ቅጥር

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሰራተኛ ቅጥር የሚፈፅመው በፌዴራል ስቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የሰራተኛ ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :

➢ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ :

በሕግ ጉዳዩች ላይ የሙያ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት እንዲሰጡ የቀጠራቸው የሕግ ባለሙያ የኮንትራት ቅጥር አፈጻጸም ሁኔታ ሲገመገም :

- የኮንትራት ቅጥር የተፈጸመው በሙያው ብቃት ያላቸው ሌሎች ተወዳዳሪዎች እንዲወዳደሩ ሳይደረግ መሆኑን፣
- ግለሰቡ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀጥረው የሚሰሩ መሆኑን ካቀረቡት የሥራ ልምድ ማስረጃ ለመገንዘብ ተችሏል። በመሆኑም በታክስ አዋጁና ደንቡ መሰረት የሥራ ግብሩ ተቀናሽ መደረግ ያለበት በሌላ መንግሥት መሥሪያ ቤት ከሚያገኙት ደመወዝ ጋር ተዳምሮ በትርፍ ጊዜያቸው ካገኙት ገቢ ላይ መክፈል ያለባቸው ሥራ ግብር እንዲሰላ መደረግ ሲገባው ግብሩ የተቀነሰው በኤጀንሲው ከሚከፈላቸው ደመወዝ ላይ ብቻ መሆኑን፣

➢ የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ነሐሴ 4 ቀን 2003 እና ጥቅምት 28 ቀን 2003 ዓ.ም የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ከፍተኛ ኦፊሰር I በቋሚነት ለመቅጠር ባወጣው ማስታወቂያ መሰረት ክፍት የሥራ መደቡ በፕሣ 6 ደረጃ ሰባት ዓመት የሥራ ልምድ ይጠይቃል ። ይሁን እንጂ ለወጣው ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ አግባብነት ያለው አንድ ዓመት የሥራ ልምድ ብቻ ያላቸው ግለሰብ እንዲመዘገቡ ተደረጎ በዜሮ የስራ ልምድ በሚጠይቅ ቦታ ላይ ማስታወቂያ ሳይወጣ እንዲቀጠሩ የተደረገ መሆኑን፣

➢ በአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ አንድ የህግ ባለሙያ በኮንትራት እንደቀጠረ ታዉቋል፡፡ ይሁን እንጂ ቅጥሩ ማስታወቂያ ሳይወጣ እና ያለውድድር የተፈጸመ መሆኑን ፣

ለመገንዘብ ተችሏል ።

ከላይ በየመሥሪያ ቤቶቹ የተፈጸሙት የቅጥር አፈጻጸሞች ለጥፋት መንገድ የሚከፍቱ ከመሆኑም በላይ የሌሎች ዜጎችን ተወዳድሮ የመቀጠር መብት

የሚገድቡ በመሆኑ መሥሪያ ቤቶቹ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር (የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ)ያወጣውን የቅጥር አፈጻጸም መመሪያ ተከትለው ቅጥር መፈጸም እንዳለባቸው ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

## 10.2 የቅጥር መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመ የውጭ አገር ዜጎች ቅጥር

በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 22/2/ መሰረት አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከፍተኛ ባለሙያ ለሚጠይቅ ማናቸውም ክፍት የሥራ መደብ በደረጃ፣ በዕድገት፣ በዝውውር ወይም በቅጥር ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ለማግኘት አለመቻሉን በማረጋገጥ፣ የውጭ አገር ዜጎችን በአገር ውስጥ በኮንትራት መቅጠር አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ፣

- በመንግሥት የተፈቀደ በጀት መኖሩ፡
- ተቀጣሪዎቹ በኮንትራት የሚቀጠሩበትን የሥራ መደብ የሚገልፅ የሥራ ዝርዝር መኖሩ ፡
- የትምህርት ማስረጃው በሚመለከተው አካል አቻ ግምት የተሰጠው መሆኑ፣
- የሙያና የሥራ ልምድ ማስረጃው በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ መሆኑ፣
- ከሥራ ዝርዝሩና ከስምምነቱ አንጻ እንዲከፈላቸው የታሰበው ደመወዝ ልክ የሚያሣይ መግለጫ መኖሩ፣
- የኮንትራት ውል መኖሩ ፣

መረጋገጥ ይኖርበታል። በዚሁ መሰረት የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ በ2002 እና በ2003 በጀት ዓመት ለ15 የቻይና እና ለ2 የኬንያ ዜጎች ለሁሉም በጠቅላላው በየወሩ 17,900.00 የአሜሪካን ዶላር በመክፈል ቅጥሩን የፈጸመው ከላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች ከተሟሉ በኋላ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ቅጥሩ እንዲፈጸም በባለሥልጣን የተፈቀደ ለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም።
- ቅጥሩ የተፈጸመው ያለውድድር መሆኑ ታውቋል።
- በቻይና ቋንቋ የተጻፈ የትምህርት ማስረጃ ቢቀርብም፣ የትምህርት ማስረጃው እንዲተረጎም እንዲሁም በሚመለከተው አካል አቻ ግምት እንዲሰጠው አልተደረገም።
- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 ክፍል አንድ አንቀጽ 5 በዋሪስርተራ ቁጥር 1

እና 2 መሰረት ተቀጣሪዎቹ ታክስ እንዲከፍሉ አልተደረገም።

በመሆኑም ቅጥሩ የቅጥር አፈጻጸም መመሪያን ተከትሎ አለመፈጸሙ፤እንዲሁም በግብር አዋጁ መሰረትም ተገቢው ግብር እንዲከፍሉ አለመደረጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም ።እንዲህ ዓይነቱ ከደንብ ውጪ የሆነ አሰራር የሌሎች ዜጎችን ተወዳድሮ የመቀጠር መብት ከመገደቡም በላይ የቅጥሩን አካሄድና አፈጻጸም ተዓማኒነት ያሳጣዋል ። መሥሪያ ቤቱም ከአገልግሎቱ ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ወጪ ሊያወጣ ይችላል። በመሆኑም ማንኛውም ቅጥር የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ያወጣውን የቅጥር መመሪያ ተከትሎ እንዲፈጸም እንዲሁም በግብር አዋጁ መሰረት ተገቢው ታክስ እንዲቀነስ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል ።

## 10.3 ዋስትና እንዲያቀርቡ ያልተደረጉ ሰራተኞችን በተመለከተ

በፌደራል መንግሥት ሰራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 አንቀጽ 6 ቁጥር 1 መሠረት በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር እና የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጆች እና እነዚህን አዋጆች ለማስፈፀም በወጡ፣ ደንቦች እንዲሁም መመሪያዎች ስለመንግሥት ገንዘብና ንብረት አጠባበቅ፣ አመዘጋገብና አያያዝ፣ ስለወጪ አከፋፈልና ጥቃቅን ወጪዎች የተወሰነ ገንዘብ እንዲሁም በግዥ ላይ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሠራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን በቂ ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲሰጡ መደረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ የአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጁ በተለያዩ የሥራ መደቦች በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት፣ ንብረት ያዥነት እና በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሠራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ ሳያቀርቡ ሥራቸውን እንደሚያከናውኑ ታውቋል፡፡ ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት መመሪያን ያልተከተለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ኮሌጁ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው መመሪያ መሠረት መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች በማሟላት ሰራተኞቹ ዋስትና እንዲያሲዙ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

# 11 የውስጥ ኦዲት ክፍል

## 11.1 የውስጥ ኦዲት ክፍልን አፈጻጸም በተመለከተ

በየመንግሥት የመሥሪያ ቤቱ የተዋቀሩት የውስጥ ኦዲት ክፍሎች ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም በወጣው የፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648/2001 ፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 3 እንዲሁም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 መሠረት ሥራቸውን የሚያከናውኑ መሆኑ እና የውስጥ ኦዲት ክፍሎቹ በየሩብ ዓመቱ የመሥሪያ ቤቱ ሥራ አመራርና ሠራተኞች ኃላፊነታቸውን በብቃት መወጣት እንዲችሉ በተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትና በስራ ላይ ባሉት ሕጎችና የአሠራር ሥርዓቶች መሠረት ሥራዎች መከናወናቸውን ኦዲት እያደረጉ በመመሪያው ላይ በተቀመጡት ጊዜ ውስጥ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ማድረጋቸው ሲጣራ፣

- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ :
  - ኦዲት ክፍሉ ዓመታዊ ዕቅዱን በየበጀት ዓመቱ አዘጋጅቶ ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ እስከ ሰኔ 20 ድረስ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረብ እንዳለበት በወጣው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያው ላይ የተመለከተ ቢሆንም የ2003 በጀት ዓመት የኦዲት እቅድ ያልጸደቀና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያልተላከ መሆኑ፣
  - የኤጀንሲው ኦዲት ክፍል የ/ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው መመሪያ መሰረት በየሩብ ዓመቱ ኦዲት ያላደረገ መሆኑ ፣
- የብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል :
  - ኦዲት ክፍል በአመቱ መጨረሻ ካደረገው የፈሰስ ሪፖርት በስተቀር በየሩብ ዓመቱ ኦዲት ያላደረገ መሆኑ ፣
  - የውስጥ ኦዲት ክፍል የቅድመ ኦዲት (Pre Audit) እንዳያከናውን ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተላለፈው መመሪያ ቁጥር 7 ክፍል 2 አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 3 ላይ የተገለጸ ቢሆንም የማዕከሉ የውስጥ ኦዲት ክፍል ቅድመ ኦዲት (Pre Audit) የሚያከናውን መሆኑ ፣
  - ለዉስጥ ኦዲት ክፍል ኃላፊ ያልተመደበለት መሆኑ ፣

- የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል :
    - ኦዲት ክፍል የሶስተኛውና የአራተኛው ሩብ አመት ሂሳብ ኦዲት ያላደረገ መሆኑ ፣
    - የፈሰስ ሒሳብ ሪፖርቱ የተሰብሳቢ ሒሳብን ያላካተተ መሆኑ ፣
- በብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በሰው ሀይል ያልተሟላ መሆኑ፣
- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ :

  የግብርና ሚኒስቴር የውስጥ ኦዲት ዳይሪክቶሬት እና የየኮሌጆቹ የውስጥ ኦዲት ክፍሎች በተቀመጠው መመሪያ መሰረት የሚፈጽሙ መሆኑ ሲጣራ፡

    - የግብርና ሚኒስቴር የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የማስተባበሪያውን የሶስተኛውንና የአራተኛውን ሩብ ዓመት ሂሳብ ኦዲት ያላደረገ መሆኑ፣
    - የአላጌ፣ የአጋርፋና የአርዳይታ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች የውስጥ ኦዲት ክፍሎች በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ካደረጉት የፈሰስ ሪፖርት በስተቀር በዕቅዳቸው መሠረት ዝርዝር የኦዲት ሥራ ያላከናወኑ መሆኑ፣

  ታውቋል፡፡

  የየመሥሪያ ቤቶቹ የውስጥ ኦዲት ክፍሎች ካልተጠናከሩና በመመሪያው መሰረት የኦዲት ሥራቸውን ካላከናወኑ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ከፍተኛ አስተዋፆኦ ያደርጋል ። በመሆኑም የየመሥሪያ ቤቶቹ የውስጥ ኦዲት ክፍሎች በፋይናንስ አዋጅ ፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እና በገ/ኢ/ል/ሚ/ር በወጣው መመሪያ መሠረት ይበልጥ አሠራራቸውን በማስተካከል የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ የተጠናከረ እንዲሆን የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ እንዳለባቸው ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 12 በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልወሰዱ

በ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ወቅት አስተያየት በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ እርምጃ የተወሰደባቸው መሆኑ ሲጣራ፣

- በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሁለት ሠራተኞች ወደ ውጪ ሀገር ሲሄዱ ያለ አግባብ በብልጫ 320 የአሜሪካን ዶላር የተከፈላቸው መሆኑ፣

- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በአንድ ትልቅ መጋዘን፣ ጊዜ ያለፈባቸው ብዛት ያላቸው ፀረ ተባይ ኬሚካልና ዲዲቲ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ በዕቃ ግምጃ ቤት ባለበት አካባቢ መጥፎ ሽታ የፈጠረ ከመሆኑም በተጨማሪ ግምጃ ቤቱ በእርጅና ምክንያት በመፍረስ ላይ የሚገኝ መሆኑ ፣

- በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር:
  - በግንባታ የሥራ ክፍያ ወቅት ብር 23,440,193.83 የተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ ፣
  - የቅድመ ክፍያንና የመያዣ ሂሣብ ሳይቀነስ ለተቋራጩ ብር 132,710,589.58 የተከፈለ መሆኑ ፣
  - በወጪ ተመዝግቦ ለተገኘው የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ ብር 113,692,327.25 ማስተካከያ ሳይሠራለት የተገኘ መሆኑ ፣

- በምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ለብር 310,240.46 የተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች የተሰሩበት ምክንያት አይታወቅም። በተጨማሪም ማስተካካያ ሊሰራላቸው ለሚገቡ ሂሳቦችም የተሰራው ማስተካከያም ቢሆን በትክክለኛው የገንዘብ መጠን ካለመሆኑም በላይ ሂሳቡ እንዲገጥም ለማድረግ ብቻ የተሰራ መሆኑ ፣

ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ተገልጾ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራላቸው ለየመሥሪያ ቤቶቹ በተላከላቸው ሪፖርት የተገለጸላቸው ቢሆንም በዚህ ኦዲት ወቅት በተደረገው ማጣራት ለሂሳቦቹ ማስተካከያ ያልተሠራላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራላቸው ለመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት በድጋሚ አሳስበናል ።

# የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች
# ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2003/2004 ዋና ዋና
# የኦዲት ግኝቶችና ዕቅድ ክንውን ሪፖርት

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ

የጥሬ ገንዘብ የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶች

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር

- በሀገር መከላከያ ሚ/ር የጤና ዋና ዳይሬክቶሬት
  በቆጠራ ከተገኘው በላይ ሪፖርት የተደረገ ብር 42,125.66
- በበጀት ዓመቱ በባንክ የተገኘ ገንዘብ
  ለገ/ኢ./ል/ሚ/ር ፈሰስ ማድረግ ሲገባ ከመመሪያ
  ውጭ በባንክ ያለ ገንዘብ ተብሎ ሪፖርት የተደረገ ብር 22,139,481.63
- የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ለዓመታት ያልተተካ ብር 291,928.19

በውጭመልዕክተኞች /የውጭ ጉዳይ ሚ/ር/

- በውጭ ምንዛሪ ባንክ ያለ ገንዘብ /4102/
  ሪፖርት የተደረገውን ትክክለኛነት
  ለማረጋገጥያልተቻለ ብር 309,975,177.68
- በ4103 የሂሣብ መደብ በባንክ ያለ ሂሣብ
  ለማረጋገጥያልተቻለ ብር 1,109,319.73
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ማስርጃ ያልቀረበለት ብር 2,388,707.89

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን

- በሰኔ 30/2003 በቆጠራ ከተገኘው በላይ
  ሪፖርት የተደረገ ብር 21,023,.37

ከላይለተገለጹት 3 መ/ቤቶች ለውጭ ጉዳይ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ በውስጥ ኦዲተር ተቆጥሮ ማረጋገጫ ሊቀርብለት እንደሚገባ፡ በባንክ ያለገንዘብተብሎ ሪፖርት ላይ ለተመለከተው የባንክ ሂሣብ መግለጫዎቹ ተሟልተው ለኦዲት በማስረጃነት መቅረብ እንደሚባቸው ጠቅሰን ይህም ባለመደረጉ የሂሣቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ ገልጸልናል፡፡ እንዲሁም በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በባንክ ያለ ገንዘብ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ /Block/ መደረገ ሲገባው ከመመሪያ ውጭ ገንዘቡ ብሎክ ሳይደረግ ሪፖርት መደረጉ አግባብ አለመሆኑን፣ ለወደፊቱም አሰራሩ እንዲስተካከል፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቆጠራ ከተገኘው በላይ በሀገር መከላከያ ሚ/ር እና በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሂሣብ ማስተካከያ እንዲወስድ በጉድለት የታየው ሃሣብም ክትትል ተደርቦ ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት በላከው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ የውጭ መልዕክተኞች በኦዲቱ ወቅት የባንክ እስቴትመንቶችን ማቅረቡን የቀሪዎቹን ማስረጃዎች ማለት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ማስረጃዎች ከሚስዮኖች ምላሽ

እንዳገኘ እንደሚያቀርብበሰጠው ምላሽ ተገልጿል፡፡ ከኦዲት የመውጫ ስብሰባ በኋላ የተጠቀሱት ኤምባሲዎች የባንክ እስቴትመንቶች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ተሟልቶ የሁሉም አልቀረበም፡፡ በዚህም ምክንያት የሂሣቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ ገልጸናል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ፌሰስ ስለአልተደረገው ሂሣብ የገንዘብና ኢኮኖሚ ል/ሚ/ር ሂሣቡ ፌሰስ እንዲደረግ ለባንኮቹ ትዕዛዝ መስጠት እንደነበረበት ይህ ባለመደረጉ ፌሰስ አለመሆኑን፣ እንዲሁም ከፍተኛው የማዕከላዊ ዕዝ መሆኑንና ሂሣቡም የደመወዝ፣ የሠራዊት ቀለብ እንደሆነ ይህ ገንዘብ ፌሰስ ቢሆን የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ተጠይቆ እንደሚከፈል፤ የጥሬ ገንዘብ ጉድለቱንና ከተቆጠረው በላይ ሪፖርት ስለተደረገው ክትትል እንደሚያደርግና በጉድለት ከታየው ከፍተኛው በፍ/ቤት ክስ እንደተመሰረተበት፣ በላከው መልስ ገልጿል፡፡ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በብልጫ ሪፖርት ስለተደረገው ሂሣብ የኮሚሽኑ የፋይናንስ ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከውስጥ ኦዲት ጋር በመሆን አጣርቶ ለኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊ እና ለመ/ቤታችን እንደሚያሳውቅ በላከው መልስ ገልጿል፡፡

2. <u>ተሰብሳቢ ሂሣቦች</u>

2.1 <u>ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

ለተለያዩ ስራ ማስኬጃ የተሰጠው ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱን ለማረጋጥ ኦዲት ሲደረግ በ20 መ/ቤቶች ብር ያልተወራረደ ሂሳብ ተገኝተል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 9 ተመልክቷል/ ከዚህም ዋናዋናዎቹ፤-

- በሀገር መከላያ ማኒስቴር ከ5-19 ዓመታት በተሰብሳቢ የተያዘ ሂሣብ ከ1984 ጀምሮ ከ19 ዓመታት በላይ የቆየ ብር 18,500,490.05፤በዕዞች መምሪያዎች ወዘተ የተመለከተ ብር 17,830,739.30፤ለሥራ ተቋራጮች በቅድሚያ ተከፍሎ ሥራ ተጠናቆ ለረጅም ጊዜ በተሰብሳቢ የተያዘ ብር12,788,201.40፤በሚ/ር መ/ቤቱ ሥር ለሚገኙ ሶስት ድርጅቶች አላግባብ ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ /ያልተከፈለ ደመወዝ /በብድር ተሰጥቶ ያልተሰበሰበ፣ብር 55,000,000.00፤ለዕቃ አቅራቢዎች ለኢንዱስትሪ ዘርፉከተከፈለው/ብረታ ብረት ኢንጁነሪንግ/ ተከፍሎ ለዓመታትያልተወራረደ /ያልተሰበሰበ፣ ብር 29,670,133.95፤
- የውጭ መልዕክተኞች ማስረጃ የሌለው ብር 23 767 620.87፤በውጭ መልዕክተኞች በሀገር መከላከያ ሚ/ር ስም በተሰብሳቢ የያዘው ሂሣብ በሚ/ር መ/ቤቱ የማይታወቅ ብር 3,321,728.46፣በውጭ መልዕክተኞችበኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ስም የተያዘ ዋና መምሪያው የማያውቀው፤
 ብር 2,889,523.25
- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከ1995-2003 ለምርጫ ሥራ በሰነድ ተሰጥቶ ያልተወራረደ ብር 31,789,234.76 እና

- በፌደራል ፖሊስ   ብር 23,992,363.36

  ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡

ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፣ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ፣ የውጭ መልዕክተኞች በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እና በኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ስም የያዘው ተሰብሳቢ ሂሣብ በሚ/ር መ/ቤቱ እና በዋናው መምሪያው ሂሣብ የማይታወቅ መሆኑ፣ በተለይ ሂሣቡ ለረጅም ዓመታት የቆየ በመሆኑ መ/ቤቶቹ እንዲያውቁት አለመደረጉ የሚሲዮኖች ተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት ትክክለኛውን ሁኔታ እንደማያሳይ፣ ማስረጃ የሌላቸው ተሰብሳቢ ሂሣቦች ሁኔታ እንዲጣራ ማስረጃ ሳይኖረው በተያዘው የተሰብባቢ ሂሣብ የገንዘብ መጠን ያህል በሂሣብ አሠራር ማዛባት የመንግሥት ገንዘብ ለግል ጥቅም ሊውል እንደሚችል ጠቅሰን ሁኔታው ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወስድ አሳስበናል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር ለሥራ አመራር ሪፖርት በሰጠው መልስ ብር 18,500,490.05 በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ማለት በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ብር 11,593,098.46 በሌሎች 8 ክፍሎች ብር 6,907,391.59 የወደመ፣ የጠፋና የተሰረቀ መሆኑን እና በፋይናንስ ሕግ መሠረት ከመዝገብ ለማስረዣ ኮሚቴ መቋቋሙን፣ ለብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽንና ለብራና ማተሚያ ቤት አላግባብ ከሠራዊት ደመወዝ በብድር ከተሰጠው ብር 55,000,000.00 ብር 4,000,000.00 ከብራና ማተሚያ ቤት የሚፈለግ የሚቀር መሆኑንና ሌላው በር 51,000,000.00 በዚህ ዓመት ተመላሽ መደረጉን፣ ብር 17,830,739.30 ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ በሰነድ ወጪ መደረጉን ጠቅሶ እየተወራረደ መሆኑን በአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ በተሰብሳቢ ከሚታየው ብር 5,896,729.22 ውስጥ ብር 4,213,093.82 በተመለከተ የአስተደደር መምሪያው ምን ያህል እንደሰበሰበ ቀሪው ምን ያህል እንደሆነ ከወጪ ቀሪው እንዲሁም እስካሁን እርምጃ ያልተወሰደባቸው ካሉ በማጣራት እንዲሰበሰብ እርምጃ እንደሚወሰድ ሌሎቹ በተለያየ ምክንያት ሊሰበሰቡ ያልቻሉትን በማጣራት ለውሣኔ እንደሚያቀርብ እንደሚደረግ፣ ከተቋራጮች ስለሚፈለገው ብር 12,788,201.40 ከመከላከያ መሠረተ ልማትና ግንባታ ዘርፍ በተሰጠው ምላሽ መሠረት የመከላከያ ፋይናንስ

ዳይሬክቶሬቱ ክትትል እንደሚያደርግ፣ ብር 29,670,133.95 ለብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን /ኢንዱስትሪ ዘርፍ/ የተከፈለው በተደጋጋሚ ማስረጃ ለማሰባሰብ ጥረት መደረጉን ሆኖም እስካሁን ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉን ጠቅሶ ለወደፊት በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ክትትል እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

የውጭ መልዕክተኞች /የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ በሰጠው መልስ ያልተሟሉትን ለማሰባሰብና ከሌሎች መ/ቤቶች የሚፈለጉ ሂሣቦችን በማጣራት ቀጣይ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥራ በመሥራት ላይ የሚገኝ መሆኑን፣

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በላከው መልስ እስከ 2004 በጀት ዓመት አጋማሽ በርካታ ሂሣብ እንዲወራረድ መደረጉን፤

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣የፌደራል ወንጀል መከላከል ዘርፍ እና የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተሰጠውን አስተያየት የተቀበሉት መሆኑንና የተጠቀሰውን ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን እርምጃ እንደሚወሰዱ በላኩት መልስ ገልጸዋል፡፡ የንግድ ሚኒስቴር በላከው ምላሽ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲቋቋም በጀት እስኪፈቀድለት ከመ/ቤቱ በተለያየ ጊዜ መከፈሉንና በክፍፍሉ ወቅት ኢንዱስትሪ ሚ/ር ያልወሰደኩት ገንዘብ ስለአለ አልከፍልም ማለቱን ጠቅሶ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጋር በጉዳዩ ላይ እንደሚወያይ በላከው መልስ ገልጿል፡፡ በፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት አጀንሲ ከአሥራ አንድ የተለያዩ ድርጅቶች ብር 2,930,414.61 ሳይሰበሰብ መገኘቱን በመግለጽ ሂሣቡ እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡ ኤጀንሲው ጉዳዩ ከነሐሴ 2003 ጀምሮ ወደ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መዛወሩን በመግለጽ ኃላፊነት እንደሌለበት አስታውቋል፡፡

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንዱስትሪ መንደር ውዝፍ የቤት ኪራይ ሂሣብ በሰኔ 30 2003 ብር 1,338,319.16 ሳይሰበሰብ መገኘቱን በመግለጽ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.2. <u>በተሰብሳቢ ሂሣብ የታዩ የአሠራር ችግሮች</u>

- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሂሣብ መደብ 4203 በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት የተደረገው ሂሣብ በተቀጽላ ሌጀሮች ድምር ከታየው በብር 1,289,269.38 አንሶ መገኘቱንና ይህ ባለፉት ኦዲቶችም የታየ ልዩነት መሆኑን በመግለጽ ሁኔታው እንዲጣራ በድጋሚ አሳስበናል፡፡በኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ብር 141,686.45 የተሰብሳቢ ሂሣብ ከማን እንደሚፈለግ እና የየትኛው በጀት ዓመት ሂሣብ እንደሆነ ማስረጃ የሌለው ተገኝቷል፡፡በልዩነት ሪፖርት የተደረገው እንዲጣራ

ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አስተያየት የሰጠን ሲሆን፣ የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያም ያለማስረጃ በተሰብሳቢ የተያዘው ሂሣብ በውስጥ ኦዲት እንዲጣራ አሳስበናል፡፡የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሰጠው መልስ የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ልዩነቱን ማግኘት ባለመቻላቸው የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የባለሙያ ድጋፍ እንዲያደርግለት ጠይቆ እንዳልተሳካ አሁንም ለማጣራት አስፈላጊውን ጥረት እያደረገ መሆኑን ገልጿል፡፡

- የውጭ መልዕክተኞች በሂሣብ መደብ 4274 ብር 8,968,986.06 ያልተለመደ የሂሣብ ሚዛን ክሬዲት ማሳየቱን በመግለጽ ሁኔታው እንዲጣራ አሳስበናል፡፡ ይህ ሁኔታ የታወቀው የሥራ አመራር ሪፖርቱ ከተላከ በኋላ ሂሣቡ ሲጣራ ሲሆን፣ በመውጫ ውይይት ወቅት እና ከመውጫ ውይይት በኋላ በቆየንባቸው 3 ቀናት ሁኔታውን አንስተን የኦዲት ማስታወሻ ሰጥተናቸው የፋይናንስ ዳይሬክተሯ አሁን ጊዜ የለኝም በዚህ ላይ መልስ ለመስጠት በማለት ለጥያቄአችን መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡ ኦዲት ሪፖርቱ ወጪ እስከተደረገ ድረስ የሚያጋጥሙ የአሠራር ችግሮች ወይም መስተካከል ያላባቸው ሁኔታዎች ካሉ በኦዲት አሠራር የሚቻል በመሆኑ ዳይሬክተሯ መልስ አለመስጠታቸው አግባብ አለመሆኑን በመጥቀስ የሂሣቡ ሁኔታ እንዲጣራ አሳስበናል፡፡

3. ተከፋይ ሂሣቦች

3.1. <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2003 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 144,432,745.54 የሠራዊቱ አባላት ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና ሂሣቡም በወጪ የተመዘገበ መሆኑን በመጥቀስ አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ከገ/ኢ/ል/ማ/ር እየተጠየቀ እንዲከፈል አሳስበናል፡፡ እንዲሁም ከዚህ ሂሣብ ውስጥ ከላይ በ2.1. እንደተጠቀሰው በሥሩ ለሚገኙት 3 ድርጅቶች ብር 55,000,000.00 ብድር መሰጠቱ አግባብ አለመሆኑን ገልጸናል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በሰጠው መልስ ገንዘቡ በመከላከያ ሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ የባንክ ሂሣብ እንደሚገኝ ገንዘቡን ሙሉ በሙሉ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመለስ እንደማይቻል ሆኖም ገንዘቡ እንዳይከማች ደረጃ በደረጃ ወደ

ገ/ኢ./ል/ሚ/ር ፌሰስ የሚደረግበት አሠራር መቀየሱንና በዕቅድ መያዙን በላከው መልስ ገልጿል፡፡

በውጭ መልዕክተኞች ብር19,336,114.33 ማስረጃ የሌለው የተከፋይ ሂሣብ መገኘቱን በመግለጽ ሂሣቦቹ ተጣርተው መረጃዎቹ እንዲሟሉ አሳስበናል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በላከው መልስ የተከፋይ ሂሣብ እንደተሰብሳቢ ሂሣብ ለረጅም ዓመታት ሲንከባለል የቆየ መሆኑንና የተከፋይ ሂሣብ ዝርዝር መግለጫ ከሞላ ጐደል መዘጋጀቱን ጠቅሶ ቀሪ ማስረጃዎችን የማሰባሰብና ለሌሎች መ/ቤቶች የሚከፈሉ ሂሣቦችን በማጣራት ላይ መሆኑን በላከው መልስ ገልጿል፡፡

- በወቅቱ ያልተከፈለ፡-

| | |
|---|---|
| - ንግድ ሚኒስቴር /ከ1996 ጀምሮ/ | 690,130.29 |
| - ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት /1998-9003/ | 21,648.98 |
| - ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | 47,262.03 |
| - የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ | 33,650.05 |

ለረጅም ጊዜ በተከፋይ የተያዘው ሂሣብ እንዲጣራ፤ በፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ማስረጃ ሳይኖረው በተከፋይ የተያዘው አጣርቶ እርምጃ እንዲወስድ አሳስበናል፡፡

3.2. <u>በተከፋይ ሂሣብ የታዩ የአሠራር ችግሮች</u>

የውጭ መልዕክተኞች በተለያዩ የተከፋይ የሂሣብ መደቦች ባልተለመደ የሂሣብ መደብ (Abnormal Balance) የዴቢት ሚዛን ብር 112,770.06 መገኘቱን በመግለጽ ሁኔታው እንዲጣራ አሳስበናል፡፡ ይህ ሁኔታ የታወቀው የሥራ አመራር ሪፖርቱ ከተላከ በኋላ ሂሣቡ ሲጣራ ሲሆን፣ በመውጫ ውይይት ወቅት እና ከመውጫ ውይይት በኋላ በቆየንባቸው 3 ቀናት ሁኔታውን አንስተን የኦዲት ማስታወሻ ሰጥተናቸው የፋይናንስ ዳይሬክተሯ አሁን ጊዜ የለኝም በዚህ ላይ መልስ ለመስጠት በማለት ለጥያቄአችን መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡ ኦዲት ሪፖርቱ ወጪ እስከተደረገ ድረስ የሚያጋጥሙ የአሠራር ችግሮች ወይም መስተካከል ያላባቸው ሁኔታዎች ካሉ በኦዲት አሠራር የሚቻል

በመሆኑ ዳይሬክተሯ መልስ አለመስጠታቸው አግባብ አለመሆኑን በመጥቀስ የሂሣቡ ሁኔታ እንዲጣራ አሳስበናል፡፡

4.<u>የገቢ ሂሣብ</u>

4.1. <u>በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ያልተደረገ</u>

- የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ብር 306,693.61
- የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1,138,705.14

- የኢትዮጵያ አእምሯል ን/ጽ/ቤት ደረሰኝ ያልቆረጡለት 51,920.00

ተገኝቷል፡፡ ሁለቱ ፍ/ቤቶች በስማቸው አንጻር የተገለጸውን ገንዘብ ድሬደዋ የሚገኙት የፌደራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች የሰበሰቡት ገቢ አዲስ አበባ በሚገኙት ሁለቱፍ/ቤቶች በኩል የወጪ በጀት የሚላከላቸው ሲሆን፣ የወጪ ሂሣብ ሪፖርት እየተደረገ ገቢው ግን ለድሬደዋ ገቢዎች ቢሮ እንደሚገባ መታወቁን በመግለጽ አሠራሩ እንዲስተካከል፤ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከተሰብሳቢ ሂሣብ ተመላሽ ለተደረገው ሂሣብ የገቢ ደረሰኝ መቁረጥ ሲገባው በጀቪ መመዝገቡ አግባብ ባለመሆኑ እንዲስተካከል አስተያየት ሰጥተናል፡፡ፍ/ቤቶቹ በላኩት መልስ ገቢው ወደ ፌደራል መንግሥት ገቢ እንዲሆን በፍ/ቤቶቹ እየተሰበሰበ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት አስተያየቱን መቀበሉን በላው መልስ ገልጿል፡፡

4.2. <u>የገቢውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ</u>

- የውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ

  - ከወጪ መጋራት ብር 353,921.36
  - ልዩ ልዩ ገቢ ብር 9,221.32

ከማን እንደሚሰበሰብ ሳይገለጽ በኮድ በመሰብሰቡ የተሰበሰበው ገቢ መሰብሰብ በሚገባው ልክ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ፣ አሠራሩ ተስተካክሎ ማስረጃ በማቅረብ ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ ለዋና መምሪያው አሳስበናል፡፡ ዋና መምሪያው ለተላከለት የሥራ አመራር ሪፖርት መልስ አልሰጠም፡፡

4.3. <u>የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ገንዘብ የማይሰበስቡ መ/ቤቶች</u>

- የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም
- የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና
- የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን

በከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት አዋጅ እና የዕዳውን አሰባሰብ አስመልክቶ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በወጣው የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከሕዳር 2004 ጀምሮ ከሠራተኞቹ የወር ደመወዝ ላይ ተቀናሽ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን፣ የፌደራል ፖሊስ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ለወደፊቱ እርምጃ እንደሚወስድ በላኩት መልስ ተገልጿል፡፡

4.4. <u>ስለ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ እና የሂሣብ ምዝገባ</u>

የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሚሰበስበው የውስጥ ገቢ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባሳተመው ደረሰኝ አለመሆኑ ገቢው የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የፋይናንስ መመሪያ መሠረት ያልተመዘገበና ሌጀር ያልተቋቋመለት መሆኑን ገቢው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት እንደማይደረግ በመግለጽ አሠራሩ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

4.5. <u>በገቢ ሂሣብ የታዩ የአሠራር ችግሮች</u>

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ከፍትህና የህግ ስርዓት ምርምር ኢንስቲቲዩት ጋር ባለው ስምምነት መሰረት በበጀት ዓመቱ ብር 2,343,492.60፣ በ2001 እና በ2002 በጀት ዓመት በድምሩ ብር 10,537,950.00 የሰበሰበውን በግላዊ ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ ገቢ ማድረጉ፣ ገንዘቡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፍቃድ ባልተገኘበት የባንክ ሂሳብ ከግላዊ ሂሳብ ወይም ከውስጥ ገቢ ጋር በባንክ የሚቀመጥ መሆኑ፣ የዚህ ሂሳብ ገቢም ሆነ ወጪ ከግላዊ ሂሳብ ጋር የሚመዘገብና ከዩኒቨርስቲ ኮሌጁ የበጀት ሂሳብ ጋር ተካቶ በየወሩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት የማይደረግ መሆኑና በዚህ ምክንያት በመ/ቤታችን ሂሳቡ ኦዲት የማይደረግ መሆኑ ታውቆ አሰራሩእ ንዲስተካከል አሳስበናል፡፡የገ/ኢ/ል/ሚ/ርን ጠይቀው ወደፊት በተሰጠው አስያየት መሰረት ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

5. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

5.1. <u>ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑ ኦዲት ሲደረግ በ8 መ/ቤቶች ብር 25,423,906.59 ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ- 17 ተመልክቷል/

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የፌደራል ፖሊስና የወንጀል መከላከል ዘርፍ ለመረጃ አገልግሎት በሂሣብ መደብ 6251 ወጪ የተደረገው በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን፣ የውጭ መልዕክተኞች ሁለት ሠራተኞች በፔሮል ላይ ሳይፈርሙ በወጪ መመዝገቡን፣ ለሁለት ሾፌሮች የትርፍ ሰዓት ተከፍሏል ተብሎ ብር 39,060.00 ወጪ ሲሆን ሾፌሮቹ ገንዘቡን ስለመቀበላቸው የፈረሙበት ማስረጃ አለመቅረቡን፣ እንዲሁም ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 511581.91 በብራስልስ ኤምሳቢ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑን በመጥቀስ ለሂሣቡ ማስረጃ እንዲቀርብ በፔሮል ላይ ሳይፈርሙ ወጪ ለሆነው ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ኦዲቱ ለወታደራዊ መረጃ አገልግሎት ወጪ መደረጉንና ለማን እንደተከፈለ ከሚስጥራዊነት አኳያ ማስረጃ ሊቀርብእንደማይችል በደብዳቤ አሳውቋል፡፡ የፌደራል ፖሊስና የወንጀል መከላከል በተመሳሳይ ሁኔታ ለመረጃ ሥራ ወጪ መደረጉን ማስረጃ ማቅረብ እንደማይቻል ወጪው በሚመለከተው ኃላፊ ትክክለኛነቱ እየተጣራ እንደሚከፈል፣ የውጭ መልዕክተኞች በሰጠው መልስ ደመወዝ ሳይፈርሙ በኒውዮርክና በለንደን ለተከፈለው ሂሣብ የኒውዮርኩን በተመለከተ ሠራተኛዋ የወሩን ደመወዝ በመውሰዳቸው በፊርማቸው ተረጋግጦ እንዲላክለት ዋናው መ/ቤት ሚሲዮኑን መጠየቁን፣ የለንደንን በተመለከተ ሠራተኛዋ ደመወዝ ስለመውሰዳቸው የፈረሙበት ማስረጃ ከሚሲዮኑ እንደተላከ ተገልጿል፡፡ በሌላ በኩል በብራስልስ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 366,005.98 የገ/ኢ/ል/ሚ/ር በዚያ ላካሄደው ሚስጥራዊ ሥራ ወጪ መደረጉንና ሚ/ር መ/ቤቱ የሚተካ መሆኑ ከመግለጽ ውጪ በመልሱም ሆነ በመውጫ ውይይት ወቅት ስለወጪው መ/ቤቱ ለመግለጽ ፈቃደኛ ሆኖ አልተገኙም፡፡ ፡ በለንደኑ ለሾፎሮች የትርፍ ሰዓት ክፍያ በሚል ወጪ የተደረገው ያለማስረጃ በመሆኑ እንዲጣራ ወይም ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ሾፌሮቹ ስለመቀበላቸው ማስረጃ አልቀረበም ለሚለው መልስ ያልሰጠ ሲሆን ከመውጫ ውይይት በኋላ ማስረጃ እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡

የንግድ ሚኒስቴር በላከው መልስ ድርጅቱ ጄኔቭ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ማስረጃው እንዲላክለት በፋክስ ጠይቆ በመጠባበቅ ላይ መሆኑ፣ ተገልጿል፡፡

5.2. <u>ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

ለተለያዩ አገልገሎቶች የተከፈሉ ወጪዎች በመንግስት የወጡ ህግ ፤ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው የተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ7 መ/ቤቶች ብር ደነብና መመሪያ ሣይከተሉ ያለአግባብ ክፍያ ተፈጽም ተገኝተል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ ተመልክተል/

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በልደታ ፍ/ቤት ቅጥር ግቢ ለሚያሰራው ሕንጻ ክፍያ ብር 341,790.08 እና ብር 3,000.00 በድምሩ ብር 343,790.08 ኮንትራክተሩ ከሠራው ሥራ በላይ ተከፍሎት መገኘቱን፣ የውጭ መልዕክተኞች በኒውዩርክ ቆንስላ ጽ/ቤት አንዲት ሠራተኛ በሚ/ር መ/ቤቱ ሳይፈቀድ ቅጥር በመፈጸሙ ለአንድ ዓመት ብር 329,312.36፣ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በሰው ሃብት ሥራ አመራር ግምገማ ውጤት መሠረት የቅጥር ማስተካከያ ተደረገላቸው ለተባሉት ሠራተኞች የማስተካከያ እርምጃው አግባብነት ማረጋገጫ አለመቅረቡን ፤ ፍ/ቤቱ አላግባብ ለተቋራጩ የተከፈለውን ገንዘብ ተመላሽ እንዲያስደርግ ባለፈውም ዓመት ተመሳሳይ ሁኔታ በመፈጠሩ በሕግ መጠየቅ እንደሚገባ/ የውጭ መልዕክተኞች በ2002 በጀት ዓመትም ብር 458,400.00 ለሁለት ሠራተኞች አላግባብ መከፈሉንና ውሉ እንዲቋረጥ ቅጥሩን ካካሂደው ኃላፊ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡ ሆኖም በ2003 በጀት ዓመት ቅጥሩ ባለመቋረጡ ብር 329,312.00 አላግባብ ለተፈጸመ ቀጥር ክፍያ ተፈጽሞ በመገኘቱ መ/ቤቱ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወስድ፣ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ጽ/ቤት አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ መ/ቤቶቹ በሰጡት መልስ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የባለፈው ዓመትን እና በድጋሚ በ2003 በጀት ዓመት አላግባብ የተፈጸሙትን ክፍያዎች አስመልክቶ ለአማካሪው መሐንዲሰ ማስጠንቀቂያ መጻፈን፤ይህንንም ለመ/ቤታችን በግልባጭ ማሳወቁን፣ ገነዘቡም ከቀጣዩ ክፍያ እንደተቀነሰ ተገልጿል፡፡ የውጭ መልዕክተኞች በላከው መልስ ሚሲዮኑን ጠይቆ ቅጥሩ ከ4 ዓመት በላይ የቆየ መሆኑንና አሁን ያሉት ኃላፊዎች ጉዳዩን የማያውቁት መሆኑን ቅጥሩ ሲፈጸም የተከተሉትን ሂደት የሚያሳይ መረጃ ማግኘት እንዳልቻሉ፣ የሂሣብና አስተዳደር ሠራተኛው የጠፋ

በመሆኑ አሁን በሚሲዩኑ የሚወሰድ እርምጃ እንደማይኖር ጉዳዩ በዋናው መ/ቤት እልባት እንዲያገኝ መልስ መስጠቱን ጠቅሶ ችግሩ በሁለቱም ወገን ማለት በሚሲዩኑና በዋናው መ/ቤት እንዳለ መመልከቱን ጉዳዩን በቅርቡ መርምሮ ውሣኔ እንደሚሰጥበት ሚ/ር መ/ቤቱ በላከው መልስ ገልጿል፡፡ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በጻፈው ደብዳቤ ከተከፈላቸው ሠራተኞች ገንዘቡን ተመላሽ ለማድግ አስቸጋሪ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

5.3. <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸመ ግዥ</u>

በበጀት አመቱ የተፈጸሙ ግዢዎች፣ በግዢ አዋጅና መመሪያው መሰረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ8 መ/ቤቶች በብር 5,478,289.66 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ተገኝተል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ ተመልክተል/

በተለይም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባለ 8 ፎቅ ሕንጻ ቢሮ ሲከራይ ለ5 ወር ብር 2,643,907.50 የግዥ መመሪያው የሚፈቅደውን የግዥ ዘዴ ባለመጠቀሙ፤ ሌሎቹ በፕሮፎርማ ግዥ መፈጸም ሲገባ ወይም ሌሎች የግዥ ዘዴዎችን አልተጠቀሙም፡፡ በመሆኑም የፌደራል መንግሥት የግዥ ሕግና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

መ/ቤቶቹ በላኩት መልስ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሰጠው የግብርና ሚኒስቴር የነበረበት ቢሮ መሆኑን ቢሮው ያረጀ፤ የተሟላ አገልግሎት ለሠራተኞችም ለደንበኛም ባለመሰጠቱ መ/ቤቱ ኮሚቴ አቋቁሞ ኮሚቴው አመቺ ቢሮ ናቸው ያላቸውን በመጐብኘትና ዋጋ በመጠየቅ የውሣኔ ሃሣብ አቅርቦ ሕንጻውን እንደተከራዩት፣ ይህም በአዋጁ አንቀጽ 51/2/ በውስን ጨረታ የተቀመጠውን እንደተከተሉ መልስ ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ አንቀጽ 51/2/ ስለውስን ጨረታ የሚደነግገው አንቀጽ የተወሰኑ ተጫራቾችን በደብዳቤ በመጋበዝ መስፈርት በማውጣት እና ዋጋ እንዲያቀርቡ በማድረግ አወዳድሮ መግዛት እንደሚባ እንጂ ኮሚቴ እየዞረ ቢሮ በማየት ዋጋ በመጠየቅ ሃሣብ እንዲያቀርብ ማድረጉ አግባብንት እንደሌለው ገልጸናል፡፡ የሆቴሎችና ቱሪዝም ሥራ ማስልጠኛ የ6 ወር ቤት ኪራይ ብር 244,127.40 ያለ ውድድር መሆኑ፣  ብር 688,776.45 በገነት ሆቴል ግቢ የማስተማሪያ ክፍሎች እድሳት ለማካሄድ የተመረጠው አሸናፊ ድርጅት የቫት ተመዝጋቢ መሆኑ፣ የታደሰ የንግድ ፈቃድ እንዳለው፣ ለኦዲት

እንዲቀርብ ተጠይቆ ባለማቅረባቸው የግዥ ሕጉ የሚጠይቀውን ሳያሟሉ የአገልግሎት ግዥውን ፈጽመው መገኘታቸውን፡፡

ተቋሙ በሰጠው መልስ የ6 ወር ብር 244,127.40 ኪራይ በነበረው የማስተማሪያ ችግር የተነሳ ችግሩን ለመቅረፍ ያለዋጋ ማወዳደሪያ በማዕከሉ የማኔጅመንት ኮሚቴ መወሰኑን ይህም ጉዳይ በሥነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን የተያዘ መሆኑ ተገልጿል፡፡

5.4 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ /መ/19/ ያልቀረበ</u>

| | |
|---|---|
| - የውጭ መልዕክተኞች | 168,503.65 |
| - የሀገር መከላከያ ሚ/ር | 25,992.20 |
| - የፌደራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል | 5,909.29 |

በውጭ መልዕክተኞች በብራሰልስ፣ ቶሮንቶና በዋሰህንግተን የተለያዩ ዕቃዎች ተገዝተው ንብረቶቹ ገቢ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሞ/19 ሳይቀርብ፣ በቀሩትም ሁለቱ መ/ቤቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ሞ/19 ሳይቀርብ ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ የመንግስትን መመሪያ ያልተከተለ አግባብ ባለመሆኑ አሠራሩ እንዲስተካከል፣ ሞዴል 19 ያልተቀረጠላቸው ንብረቶች እንዲቀረጥላቸው ወይም ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር በላከው መልስ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ሞ/19 ያልቀረጡት ኤምባሲዎች ዋሽንግተን፣ቶሮንቶና ብራሰልስ መላካቸውን ቢገልጽም ከመውጫ ስብሰባ በኋላ የተላኩት ሞ/19 ኮፒ ከመሆናቸውም በላይ ቀን የሌላቸው፣ አንዳንዶቹ የገንዘብ መጠኑ ያልተጠቀሰና አስረካቢና ተረካቢ ያልፈረሙባቸው በመሆኑ፣የቀረቡትን ሞ/19 ለመቀበል አልተቻለም፡፡ በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የጤና ዳይሬክቶሬት መድሃኒት ግዥ ፈጽሞ የኢትዮጵያ አየር ኃይል የተለያዩ ሸቀጦች ግዥ ፈጽሞ ሞ/19 ሳይቀርብ ሂሣቡ መወራረዱን አስመልክቶ፣ ሚ/ር መ/ቤቱ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ በሰጠው መልስ በጤና ዋና ዳይሬክቶሬት ያለውን የግዥ ሁኔታ በሚመለከት አሰራሩን ፈትሾ የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ ተጠየቂ በሚሆኑ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላይ እርምጃ ለመውሰድ በዝግጅት ላይ መሆኑ ተገልጿል፡፡

5.5.<u>በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት ያልተሰበሰበ</u>

- በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር
  - የሥራ ግብር 31,802.75
  - የተጨማሪ እሴት ታስክ 37,634.45
  - የተከፋይ ሂሣብ <u>5,017.97</u> 74,455.17
- በኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ በወቅቱ ለባለሥልጣኑ ፈሰስ ያልሆነ፣ 58,654.65
- የፌዴራልጉዳዮች ሚኒስቴር 2,006.91

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የጤና ዳይሬክቶሬት በግል ሕክምና ዘርፍ (Private wing) የሕክምና አገልግሎት በትርፍ ሰዓታቸው አገልግሎት ለሰጡ የሆስፒታሉ የሕክምና ባለሙያዎችና የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ወጪ ሆኖ ሲከፈል ከዳይሬክቶሬቱ ኃላፊዎች የሥራ ግብር ሳይቀነስ እንዲከፈል በተላለፈ ትዕዛዝ መሠረት የሥራ ግብሩ አለመቀነሱ የገቢ ግብር አዋጁን የሚቃረንና ኃላፊዎቹ በሕጉ ከተቀመጠው ውጭ ማንንም ከግብር ነጻ የማድረግ ሥልጣን እንደሌላቸው በመጥቀስ የሥራ ግብሩ ከሚመከታቸው ሠራተኞች ወይም ትዕዛዙን ከሰጡት ኃላፊዎች ተሰብስቦ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ፈሰስ እንዲደረግ፣ የተጨማሪ እስት ታክሱ አለመቀነሱም አግባብ ባለመሆኑ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ ለወደፊቱም ጥንቃቄ እንዲደረግ፣ የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስና የተከፋይ ሂሣብ (WHT) በመመሪያው መሠረት ከወሩ መጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባው ጊዜውን ማሳለፉ አግባብ እንዳልሆነ በላከነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒሰቴር በላከው መልስ የሰጠነውን አስተያየት ተቀብሎ ያልተቀነሰው የሥራ ግብር ከሚመለከተው ሠራተኛ ወይም ትዕዛዝ ከሰጠው ኃላፊ ደመወዝ ላይ ተቀናሽ ተደርጎ ለሚመለከተው የግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ እንዲደረግ በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በኩል ክትትል እንደሚደረግ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ያልሰበሰቡት የጤና ዋና ዳይሬክቶሬትና የኢትዮትያ አየር ኃይል እንዲሰበሰቡና ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲያደርጉ የመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ክትትል እንደሚያደርግ

በላከው መልስ ተገልጿል፡፡ የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ መልስ አልሰጡም፡፡

5.6.<u>የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

| | |
|---|---|
| - በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር | 1,877,834,619.00 |
| - በኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ | 49,994,569.11 |
| - ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት | 54,255,300.60 |
| - የውስጥ ደህንነት ዋና መመሪያ | 33,344,141.60 |

የደህንነት መ/ቤቶቹ ለደመወዝ ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ፔሮሉ በኮድ በመቅረቡ ኮዱን የሚገልጽ ማስረጃ ለመሰጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሌሎቹ የወጪ ሂሣቦች ለምሳሌ የመኪና ጥገና፣ የነዳጅ ለማጣራት የመኪኖች ታርጋ የስልክ ቁጥሮችና የመሳሰሉት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የሶስቱንም መ/ቤቶች ሂሣብ ኦዲት በማድረግ የወጪውን ወይም የሂሣባቸውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ መ/ቤቶቹ ከሚስጥራዊነት አንጻር ማቅረብ እንደማይቻል በኦዲት ወቅት ገልጸዋል፡፡ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የደመወዝ ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የተቀጠሩ፣ በዝውውር የመጡ፣ በጡረታ የተገለሉ እና በተለያየ ምክንያት የተሰናበቱ የሠራዊት አባላት ስም ዝርዝር እና የተወሰኑ ዓመታተ በማገልገላቸው ማበረታቻ የተሰጣቸው አባላት ስም ዝርዝር ለኦዲት ተጠይቆ መ/ቤቱ ለማቅረብ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሠራዊት ደመወዝ ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ፣ ይህም ወጪ ለሚ/ር መ/ቤቱ ከተመደበው በጀት በመቶኛ 41% መሆኑና ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰነ ማስረጃዎቹ ለኦዲት የሚቀርቡበት ሁኔታ እንዲመቻች አሳስበናል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በላከው መልስና ቀደም ብሎም በኦዲቱ ወቅት በደብዳቤ ለመ/ቤታችን እንደገለጸው ከወታደራዊ ሚስጥራዊነት አንጻር በሀገር ደህንነት ላይ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ መረጃዎችንና ዶክመንቶችን ለኦዲት ለማቅረብ እንደሚያስቸግር ጠቅሶ ከላይ የተገለጹትን ለማቅረብ እንደሚቸገር ተገልጿል፡፡

5.7. <u>ውል ያልቀረበለት ክፍያ</u>

የውጭ መልዕክተኞች በኒውዮርክ የኢትዮጵያ ኮንስላ ጽ/ቤት ለፎቶ ኮፒ ማሽን ኪራይ ብር 232,264.66፣ ለጋራ ሕንጻ ኪራይ ብር 1,828,038.44፣ ለሚሲዮኑ

ሕንጻ ኪራይ ብር 343,487.93 በድምሩ ብር 2,404,791.03 ለሁለት ድርጅቶች Cannon Fine Serin እና Brown Hwis Stavens ወጪ የተደረገው በውሉ መሠረት መሆኑንና የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ውል እንዲቀርብ ተጠይቆ ባለመቀረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ፡፡ እንዲሁም በዚሁ ኤምባሲ ለአንድ ግለሰብ ለአውሮፕላን ትኪት USD1,651.19 እና በአሜሪካን ጥሬ ገንዘብ USD 10,000.00 በድምሩ USD11,651.19 ወይም ብር 160,203.86 ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ መመዝገቡን በመጥቀስ ውል እነዲቀርብ ማስረጃውም እንደዚሁ እንዲቀርብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ መ/ቤቱ ለሥራ አመራሩ በሰጠው መልስ የቤቱ ኪራይና የፎቶ ኮፒ ማሽን ኪራይ ውል ከሚሲዮኑ መላኩን ቢገለጽም፣ ከመውጫ ውይይት በኋላ የቀረቡት ውሎች ሲታዩ በ2004 በጀት ዓመት ማለት በነሀሴ 2003 የተደረጉ ውሎች በመሆናቸው ይህ ወጪ ደግሞ በ2003 January እስከ June 2003 በመሆኑ አግባብነት ያላቸው ሆኖ አልተገኙም፡፡ በሌላ በኩል ለግለሰቡ የተከፈለው በተመለከተ የአውሮፕላን ትኬተና ግለሰቡ USD 10,000.00 ፈረመው የተቀበሉበት ማስረጃ የቀረበ ቢሆንም USD 10,000.00 ለምነ አገልግሎት ወጪ እንደተደረገ የሚገልጽ ማስረጃ ባለመቅረቡ ግለሰቡ የሚ/ር መ/ቤቱ ሠራተኛም ባለመሆናቸው በአጠቃላይ ብር 160,203.86 ወጪ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

5.8. <u>ትክክለኛ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ</u>

የሀገር መከላከያሚኒስቴር ለደብረዘይት የጋራ መኖሪያ ሕንጻ ግንባታ የተከፈለ ብር 3,278,843.86 ለጐፋ ካምፕ ፌዝ 2 የጋራ መኖሪያ ሕንጻ ግንባታ የተከፈለ ብር 5,194,661.92 በድምሩ ብር 8,473,505.78 በመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ስም ክፍያ መፈጸም ሲገባው በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 185/2010 በፈረሰው የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በማስረጃነት በመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉን እና የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት ፈረሶ የመከላከያ ኮንስትራክሽ ኢንተርፕራይዝ በሐምሌ 21/2002 በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ሲቋቋም መብትና ግዴታው ለዚሁ ኢንተርፕራይ የተላለፈ፣ ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ ድርጅቱ መፍረሱ የተገለጸ በመሆኑ፣ በፈረሰው ድርጅት ስም ክፍያ መፈጸሙ አግባብ እንዳልሆነና ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ አሳስበናል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በላከው መልስ የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና

የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የሚ/ሮች ም/ቤት ደንብ መፈረሱንና የድርጅቱ መብትና ግዴታዎች በሙሉ ወደ መከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ መተላለፍን መደንገጉን ጠቅሶ የገቢው ሁኔታ በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በኩል ተጣርቶ ሪፖርት እንዲቀርብ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

5.9. <u>ከቀረበው የወጪ ማስረጃ በላይ የተመዘገበና የተወራረደ ሂሣብ</u>

| | |
|---|---|
| - የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ | ብር 497,232.20 |
| - የውጭ መልዕክተኞች | 4,251.01 |

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በ2002 ሀገር አቀፍ ምርጫ ሲኬሄድ በሠነድ ወጪ የተደረገው ሂሣብ ሲወራረድ በበርካታ ቫውቸሮች ከቀረበው ማስረጃ በላይ በድምሩ ብር 497,232.20 አላግባብ በብልጫ ተወራርዶና ተመዝግቦ መገኘቱን በመግለጽ፣ አላግባብ ወጪ የተመዘገበው ሂሣብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡ ጽ/ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ ለሥራ አመራረ ሪፖርቱ መልስ ያልሰጠ ሲሆን በመውጫ ውይይት ወቅት ሂሣቡ ብዛት ስለነበረው ቶሎ እንዲወራረድ በመደረጉ መከሰቱን ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተደጋጋሚ በበርካታ ቫውቸሮች ላይ የተፈጸመ በመሆኑ በምክንያትነት የቀረበውን ለመቀበል እንደሚያስቸግር በሪፖርታችን ገልጸናል፡፡

5.10. <u>የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የክፍያ</u>
መመሪያ መሠረት ያልተፈጸሙ

| | ብር |
|---|---|
| የውጭ መልዕክተኞች | 4129,735.31 |
| የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር | 121,775.00 |

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው የክፍያ መመሪያ ቁጥር 4 ከብር 50,000.00 በላይ መ/ቤቶች የሚፈጽሙት ክፍያ በቀጥታ አቅራቢው ወይም ተጠቃሚው የባንክ ሂሣብ እንዲገባ የሚያዘውን በመተላለፉ የውጭ መልዕክተኞ ለሰነአ የትብብር ፎረም በቼክ የሀገር መከላያ ሚ/ር የኢትዮጵያ አየር ኃይል በጥሬ ገንዘብ ከፍለው መገኘታቸውን በመግለጽ በመመሪያው መሠረት

ክፍያዎች አለመፈጸሙ በርካታ ገንዘብ ግለሰቦች እጅ ሊገባና ለብክነት ሊጋለጥ እንደሚችል በመግለጽ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

መ/ቤቶቹ በላኩት መልስ ለወደፊቱ በመመሪያው መሠረት እንደሚፈጽሙ ተገልጿል፡፡

5.11. <u>በተመሳሳይ ፊርማዎች ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት በቅድሚያ ለምርጫ በሰነድ ተሰጥቶ የተወራረዱ ተሰብሳቢ ሂሣቦችኦዲት ሲደረግ ብር 183,950.00 ከ32-772 ሰዎች ክፍያ በተመሳሳይ ፊርማ ተፈጽሞ ሠነድ የወሰዱት ሰዎች አወራርደው ካቀረቡት ማስረጃ መረዳት መቻሉን በመግለጽ፣ ወጪዎች ሲወራረድ የማስረጃዎች አግባብነት መጣራት እንደሚገባ በናሙና ታይቶ ከላይ የተገለጸው ሁኔታ እንዲጣራ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. <u>ንብረት</u>

6.1. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ኦዲት መምሪያ በሰኔ 2 ቀን 2002 በተጻፈ ደብዳቤ ብር 1,574,134.88 በሁለት ክፍሎች ጉድለት መገኘቱን እንደተገለጸ በመጥቀስ አስፈላጊው ማጣራት ተደርጐ እርምጃ እንዲወሰድ በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ያሳሰብን ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመት እርምጃ አለመወሰዱን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ አሳስበናል፡፡

6.2. <u>የዕቃና ንብረት አስተዳደር</u>

<u>በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት</u>

መጋዘን ኬሚካሎች የጐማ የውስጥ ላስቲኮች /ከመነዳሪያ/ሌሎችም ለረጅም ዓመታት እንውገዱ እርምጃ ሳይወሰድ መገኘቱን፣

<u>በፌደሪል ፖሊስ</u>

የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከመዝገብ ወይም ከስቶክ ካርድ ከወጪ ቀሪ ጋር አለመገናዘቡን እና እርምጃ ያልተወሰደባቸው ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ዕቃዎች መገኘታቸውን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

- ታህሳስ 2000 የተዘጋጀው የመንግስት kሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል (ጎፋም) በየቢሮው ያሉ ቋሚ ዕቃዎችን ለመቆጣጠር እንዲያስችል የቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ በንብረት ክፍል እና በተጠቃሚዎች እጅ መያዝ እንዳለበት እንደሚያዝ፤ሆኖም

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት
- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት
- የወንጀል ምርመራ ዘርፍ
- የኢት. ፖሊስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ

- ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ተሟልቶ አለመስጠታቸውን፤
- በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ አለመስጠታቸውን፤፣

በመግለጽ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ከ/ፍርድ ቤት ቀደም ብሎ የተቋቋመውን ኮሚቴ በአዲስ በማደራጀት ሥራውን በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑን፤መጀመሪያ ፍ/ቤት ሁኔታውን ለማሻሻል አስፈላጊው እርምጃ እየተወሰደ መሆኑንአሳስበናል፡፡የወንጀል ምርመራ ዘርፍ በቀረበው የመፍትሔ ሃሣብ መሠረት እንዲስተካከል የሚያደርግለኦዲቱ በሰጡት ምላሽገልጸዋል፡፡

<u>የፍትህ ሚ/ር</u>

- ዕቃ ግምጃ ቤቱን የሚጠበቀው እና የዕቃዎች ገቢና ወጪ ምዝገባ የሚከናወነው በአንድ ሰው ብቻ መሆኑ፣
- በሞ/19 እና በሞ/22 ገቢና ወጪ የሆኑት ዕቃዎች በአብዛኛው ወደ ስቶክ ካርድ ያልተመዘገቡ መሆኑን፣

በመግለጽ የስራ ክፍፍል እንዲኖር አሳስበናል፡፡ የተሰጠው አስተያየት ተገቢና መስተካከል እንዳለበት በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅት ገልጸዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚ/ር

- በመሥሪያቤቱውስጥካሉትተሽከርካሪዎችውስጥ 11 ተሽከርካሪዎች ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ በብልሽት የቆሙ እንደሚገኙ ፤እንዲሁም ከነዚህ ውስጥ አንድ ተሽከርካሪ የሠሌዳ ቁጥር ኮድ 2-24351 ሞዴል BMW (አውቶሞቢል) የባለቤትነት ደብተር /ሊብሬ/ የሌለው መሆኑን፤

በመግለጽ በመንግስት መመሪያ መሠረት ተሽከርካሪዎቹ ለተጨማሪ ብልሽት ከመዳረጋቸው በፊት እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ቢኤም ደብሊው መኪና ከብሄራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት ጽ/ቤት ለደህንነት ሲባል ተሰጥቶ የነበረ መሆኑን፤ተሽከርካሪው ለመ/ቤታቸው ለብዙ ጊዜ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠት ማቆሙንና የባቤትነት

ደብተር ሳይወጣለት የቆየ እንደሆነና ሌሎች አገልግሎት የማይሰጡ መኪናዎችን በተመለከተ የ/ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ለብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጥያቄ ቀርቦ የድርጅቱ ባለሙያዎች መጥተው የመኪናዎቹን ሁኔታ ያዩ መሆኑን፣ በቀጣዩ ድርጅቱ የሚወስደው እርምጃ እየተጠበቀ እንደሚገኝ በሰጡት ምላሽና በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅት ገልጸዋል፡፡

<u>የፌዴራል ልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት</u>

የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 65 (2) መሰረትማናቸውንም ንብረት የንብረቱን አይነት እና ብዛት በዝርዝርመዝግቦ መያዝ እንዳለበት እንደሚያዝ፣ ይሁን እንጂ በጽ/ቤቱ የቋሚ ዕቃመመዝገቢያ መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፤

<u>በብረታ ብረት ልማት ኢንስቲተዩት</u>

- የወርክ ሾፑ የንብረት ክፍል ኃላፊ እና የንብረት አስተዳደር ሠራተኛ የሆኑት አንድ ሰው የንበረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ የማዘጋጀት፣ ንብረት የመመዝገብ እና የዕቃ ግምጃ ቤት ጠበቂ በመሆን ሁሉንም ሥራዎች በአንድ ሰው መከናወኑ ቁጥጥሩ የላላ ከመሆኑም በላይ የሥራ ክፍፍል ባለመኖሩ የንብረት መባከን ሊያስከትል እንደሚችል፣
- የሚያገለገሉና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በአንድ ላይ ተከማችተው እንደሚገኙና ሌሎች ተመሳሳይ የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ድክመት ያለባቸው መ/ቤቶች በአባሪ-29 ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በየመ/ቤቶቹ የቋሚና አላቂ ንብረት ገቢ እና ወጪ መዝገብ እንዲሁም ቢን ካርድ ሊቋቋም እንደሚገባ ፣ የንብረት ቆጠራ ከመዝገብ ወይም ከስቶክ ካርድ ከወጪ ቀሪ ተገናዝቦ በልዩነቱ ላይ እርምጃ መውስድ እንዳለበት፣ የንብረት መዝጋቢ፣ የዕቃ ግምጃ ቤት ጠባቂና የንብረት ክፍል ኃላፊ ሠራተኞች የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚገባ፣ እንዲሁም በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙት ከአገልግሎት ውጭ በሆኑት ዕቃዎች ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው በአጠቃላይ የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.3. <u>የተሽከርካሪ መኪኖች አያያዝና አጠባበቅ</u>

➢ በፌደራል ፖሊስ ባለቤትነት ሥር ካሉት ተሽከርካሪዎች ውስጥ ፤

- የባሌቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው 156
- ጊዜያዊ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ያላቸው 43
- ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ 87

የተገኙ መኖኑን እና እርምጃ ሳይወሰድመገኘቱን፤በመግለጽ

መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች ደብተርእንዲወጣላቸው፣ በጊዜያዊነት ሊብሬ ያላቸውም ቋሚ ደብተር ሊወጣላቸው እንደሚገባ፣ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑት ተጠግነው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉት እንዲጠገኑ፣ ሊጠገኑ የማይችሉትን ደግሞ በመንግስት መመሪያ መሠረት የሚወገዱበት ሁኔታ መመቻች ያለበት መሆኑን በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡::

<u>የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር</u>

የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት አስተዳደር የነዳጅ አጠቃቀም የቁጥጥር ስርዓት ኦዲት ሲደረግ፣

- የማረሚያ ቤቱ ተሽከርካሪዎች ለስራ በሚሰማሩበት ወቅት የተሽከርካሪ መውጫ ፎርም የማይሞላ በመሆኑ የተጓዙትን ኪ/ሜትርማረጋገጥ የሚቻልበት አሰራር አለመኖሩ፤
- ተሽከርካሪዎቹ በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚጓዙ በባለሙያ ያልተጠና በመሆኑ የተሽከርካሪዎቹ የነዳጅ ፍጆታን መቆጣጠር የሚቻልበት አሰራር አለመኖሩ

<u>የኢት.ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት</u>

- በጽ/ቤቱ ውስጥ ካሉት ተሽከርካሪ መኪናዎች ውስጥ 5 ተሽከርካሪዎች ለረጅም ዓመት በብልሽት የቆሙ መሆናቸው ፣2 ተሽከርካዎች የሠሌዳ ቁጥር 4-14454 እና የሠሌዳ ቁጥር UN-0078 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ)የሌላቸው መሆኑ እና የሠሌዳ ቁጥር 4-10696 በንብረት መዝገብ ላይ ያልተመዘገበና የባለቤትነት ደብተር የሌለው መገኘቱን፡

ንግድ ሚኒስቴር

- በሚኒስቴርመ/ቤቱስር ከሚገኙት ተሽከርካሪዎች ውስጥ የታርጋ ቁጥር 4-07742 ላንድሮበር፤ 00145 ማዝዳ፤ 00294 ኒሳን ፤ 03767

ላንድሮበር ተሽከርካሪዎች ለረዥም ጊዜ ያለአገልግሎት የቆሙ እና በሚ/ር መ/ቤቱ ለተሽከርካሪዎቹ ትኩረት ሳይሰጣቸው ማለትም አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ከሆነ ተጠግነው እንዲሰጡ ካልሆነም በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ አለመደረጉ፤

- በኢንዱስትሪመንደርለረዥምጊዜያለአገልግሎት የቆመ ተሽከርካሪ (ማርቸዲስ) በቀድሞው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር ስር እንደነበር ነገር ግን አሁን በንግድ ሚ/ር የተሽከርካሪዎች ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ እንዲሁምየኢንዱስትሪ ሚ/ር የንብረት ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፣ በሚ/ር መ/ቤቱ ተሽከርካራዎች ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ የተሽከርካሪው ንብረትነት የየትኛው መ/ቤት እንደሆነ ለማወቅ ያልተቻለና ባለቤት በማጣት ለጥፋት የተጋለጠ መሆኑን በመግለጽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎት የሚሰጡትን አስጠግኖ አገልግሎት እንዲሰጡ እንዲደረግ ካልሆነም በወጣው መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚኖርበትና እንዲሁም በኢንዱስትሪ መንደር ለረዥም ጊዜ ያለአገልግሎት የቆመው ተሽከርካሪ ማርቼዲስ ሁለቱ ሚ/ር መ/ቤቶች ተነጋግረው ተሽከርካሪው በአንደኛው ሚ/ር መ/ቤት ባለቤትነት እንዲጠበቅ መደረግ እንዳለበት እአሳስበናል፡፡ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሚ/ር የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት የመውጫ ስብሰባ ላይጉዳዩን አንስተን ክቡር ሚኒስትሩ ሁኔታውን ክትትል እንደሚያደርጉበት ገልጸዋል፡፡

  ለሥራ አመራሩ ሪፖርት በተሰጠው ምላሽየሠሌዳ ቁጥር 4-07742፣4-00145፣4-00294 እና 4-0367 ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ በአዲሱ መመሪያ መሠረት ለማስወገድ ለመከላከያ ኢንጂነሪንግ ጥያቄ አቅርበው ሥራውን ለመጀመር በዝግጅት ላይ እንደሆኑ እና አሁን ጉዳዩን የሚከታተለው አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ኤጀንሲ ውክልና የተሰጠው መሆኑ ተገልጿል፡፡

የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት

ኢንስቲትዩቱ ከታህሣስ 1/2003 እስከ ሰኔ 30/2003 በወር በብር 172,327.50 ለ7 ወር ጠቅላላ ብር 1,206,292.50 የሕንጻ ኪራይ አካሂዶ ኢንስቲትዩቱ በተከራየው ሕንጻ ተሽከርካሪዎቹን ለማሳደር ባለመቻሉ

ተሽከርካሪዎቹን ለማሳደር በአካባቢው የሚገኙትን የመንግሥት ተቋማት ትብብር እየጠየቀ በትምህርት ቤትና በወረዳ ጽ/ቤቶች የሚያሳድርና የተሽከርካሪዎቹ አጠባበቅ ሥጋት ላይ መሆኑን በመግለጽ ኢንስቲትዩቱ በመኪኖቹ ጥበቃና ደህንነት ላይ ችግር ከመፈጠሩ እና በሾፌሮች መኖሪያ አካባቢ እንዲያድሩ በመደረጉ ለተጨማሪ የነዳጅ ወጪ የሚያስከትል መሆኑን ጠቅሰን ከህንፃው አከራይ ጋር በውሉ በተጠቀሰው መሰረት ለተሽከርካሪዎቹ ማሳደሪያ ቦታ እንዲኖር በመነጋገር መፍታት ወይንም የማሰደሪያ ቦታ ያካተተ አዲስ ህንፃ መከራየት እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡ የተሽከርካሪ ማሰደሪያ ቦታ እንዲኖር ኢንስቲትዩቱ ከአከራዩ ጋር እየተነጋገረበት መሆኑን ለሥራ አመራሩ በሰጠው ምላሽ ተገልጿል፡፡

ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር

- መ/ቤቱ በሥሩ ለሚገኙት ተሽከርካሪ መኪናዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ መኖሩ ሲጣራ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-00936 ተሽከርካሪ መኪና ሊብሬ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑንበመግለጽለተሽከርካሪው ሊብሬ ለማውጣት ትኩረት ተሰጥቶ ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

ለሥራ አመራር ሪፖርቱ በሸጠው ምላሽ በመ/ቤቱ ሥር የሚገኙት ተሽከርካሪዎች ራሱን የቻለ ፕሮፋይል እንዲኖራቸው ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑንና በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ሊቃርብ ያለቻለው የሠሌዳ ቁጥር 4-00936ተሽከርካሪ መኪና ሊብሬውን በተመለከተ የዓመቱን ተሽከርካሪ ብቃት መረጋገጫ ቦሎ ለማውጣት ለምርመራ መንገድ ትራንስፖርት ቀርቦ በነበረበት ወቅት በተከሰተ የአሠራር ችግር ምክንያት ያልተገኘ ስለሆነ መ/ ቤቱ ጊዜ እንዲሰጠው በመጠየቁ ለጊዜው ባይቀርብም በአሁኑ ጊዜ ክትትል እየተደረገበት እንደሚገኝ ተገልጿል ፡፡

7. <u>በጀት</u>

7.1 <u>ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት</u>

በ2003 በጀት ዓመት የተመደበው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲገናዘብ ከ10% በላይ ያለውን ብቻ በመውሰድ ያልተሠራበት በጀት በ22 መ/ቤቶች ብር 73,007,404.39 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-28 ተመልክቷል/

7.2. <u>ከበጀት በላይ የወጣ</u>

- የንግድ ሚኒስቴር 657,624.44
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮምሽን 98,524.98
- የጨርቃጨርቅኢንዱስትሪልማትኢንስቲትዩት 20,403.00

የበጀት ዝግጅት በበቂ ጥናት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን፣ የበጀት እጥረት ሲያጋጥም የበጀት ዝውውር በመጠየቅ እንዲፈጸም በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ካፒታል በጀትን በተመለከተ ማሽኖች ለመግዛት ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ወጥቶ ተጫራቾች ቀርበው የቀረበው ዋጋና በበጀት የተያዘው ሊጣጣም ባለመቻሉ፣ ገንዘቡ ተመላሽ መደረጉን መደበኛ በጀትን በተመለከተ ገበያ ላይ ባለው የአቅርቦት ችግር በመሠረታዊ የሠራተኞች ድልድል ወደ ሌላ የሥራ ክፍል መመደቡ ሠራተኞች የደንብ ልብስ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ በጀቱን መጠቀም እንዳልተቻለ ኢንስቲትዩቱ ገልጿል፡፡

የሆቴሎችና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል የካፒታል በጀትን በተመለከተ በማዕከሉ እና በሕንጻ ተቋራጩ መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት በሚኒስትሮች በኩል ሌላ ቦርድ ተቋቁሞ ሥራውን በአዲስ መልክ ለማሰራት መወሰኑን በላው መልስ ገልጿል፡፡

8. <u>የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን በተመለከተ</u>

የውስጥ ቁጥጥር ድክማቶች፤

- የንግድ ሚኒስቴር እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአብዛኛው በሣጥን የወጪ ማስመስከሪያ እና በባንክ የወጪ ማስመሰከሪያ ቫውቸሮች ላይ በጀቱ ስለመፈቀዱ ያረጋገጠው በሚለው ላይ በጀቱ ስለመፈቀዱና ሂሣቡን ያረጋገጠው ኃላፊ ወይም ሠራተኛ እንደማይፈርሙ፤
- በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን አንድ ወጪ ብር 15,420.42 ወጪውን ያዘዘውና ተቀባዩ አንድ ሰው ሆኖ በመገኘቱ ቁጥጥሩ የላላ መሆኑን በመግለጽ እንዲታረም አሳስበናል፡፡

9. <u>ያለፉት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ክትትል</u>

<u>የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር</u>

በ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ውጤት ብር 1,275,750.00 ለአሰልጣኝ፣ ለቱቶር እና ለወታደራዊ አሠልጣኞች ከውል ውጭ በብልጫ የተከፈለው ያልተተካ መሆኑን በመግለጽ እንዲተካ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

<u>የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት</u>

በ2002 በጀት ዓመት በኦዲት ሪፖርት በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት እርምጃ የተወሰደ ለመሆኑ ሲጣራ፡-

- በ1994 ዓ.ም ለትምህርት መሣሪያዎች አቅራቢ ድርጅት ለተከፈለው ብር 279,101.07 ንብረቱ ለጽ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ /ሞዴል/19/ ያልቀረበለት መሆኑ፣
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ከወጪ ቀሪው የማይመዛዘን መሆኑ፣
- በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት እና በተቀጽላ ሌጀር ልዩነት መኖሩ፣
- ከጽ/ቤቱ ሠራተኞች ለረጅም ዓመት ያልተወራረደ ብር 183,482.74 መኖሩ፣

ከላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች በ2003 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም የማስተካከያ እርምጃ ሣይወሰድባቸው ተገኝተዋል፡፡ጽ/ቤቱ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት በወቅቱ የእርምት እርምጃ ያለመውሰድ ለሥራው በቂ ትኩረት አለመስጠትን ስለሚያመለክት፣ አሁንም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ ባሳሰብነው መሠረት በኦዲት አስተያየቱ መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ በእንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን እና ለትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ ድርጅት የተከፈለው ክፍያ በተመለከተ በ1984 ዓ.ም ድርጅቱ ለምርጫ ኮሚሽን በወቅቱ ለተካሄደው ክልላዊ እና የወረዳ ምርጫ ማስፈጸሚያ የሰነድ ሕትመት በውሰት የተሰጠው እንደሆነና ድርጅቱ ከዓመታት በኋላ በውሰት የሰጠውን ወረቀት ዋጋ በመተመን የቦርዱ ጽ/ቤት በሕግ ለመጠየቅ በመንቀሳቀሱ እዳው በየጊዜው ከሚካሄዱ ምርጫዎች በጀት ጋር እየተያዘ እንዲከፈል መደረጉና የሕትመት ወረቀቱ ከፍተኛ መጠን የነበረው በመሆኑ እና የሕትመቱ ሥራ አጣዳፊ በመሆኑ በቀጥታ በቦርዱ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ከድርጅቱ ርክክብ ተደርጎና ማተሚያ ድርጅቶቹ እንዲረከቡ ተደርጎ ሕትመቱ እንደተከናወነ ተገልጿል፡፡